ነከተን

# የፖለቲካል ኢኮኖሚ መሠረተ-ሃሳቦች

ቅጽ ፩

# FUNDAMENTALS OF Political Economy

Proudly Brought to You
By
www.binyamhk.wordpress.com

# የፖለቲካዊ ኤኮኖሚ መሠረተ-ሀሳቦች

# Fundamentals of Political Economy

## ቅጽ ፩

## Vol. 1

ካፒታሊዝም

**CAPITALIST MODE OF PRODUCTION**

ከፒ. ኒኪቲን

ትርጉምና ዝግጅት

በስለሽ አንዳርጌ

ጥቅምት 1971 ዓ. ም.

## ማ ው ጫ ፡


ገጽ

መቅድም ........................................4

## የፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ምንነት ........................................7

ምዕራፍ ፩. ቅድመ — ካፒታሊስት ሥልተ — ምርቶች ........................................15

1. የጥንታዊ ጋርዮሽ ሥልተ — ምርት ........................................15
2. የባሪያ አሳዳሪ ሥልተ — ምርት ........................................17
3. የመልከኛው ሥልተ — ምርት ........................................20
4. የመልከኝነት መሰባበርና መጨማተር ........................................21

— የካፒታሊስት ግንኙነቶች በመልከኛው ሥርዓትውስጥመወለድ..21

## የካፒታሊስት ሥልተ—ምርት

### ሀ - ቅድመ - ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም

ምዕራፍ ፪. የሸቀጥ ምርት — ሸቀጥና ገንዘብ ........................................22

1. የሸቀጥ ምርት አጠቃላይ መግለጫ ........................................22
2. ሸቀጦችና ሸቀጥን የሚፈጥረው ጉልበት (ሥራ) ........................................25
3. የልውውጥ ማደግና የዕሴት መልኮች (ቅርጾች) ........................................30
4. ገንዘብ ........................................31
5. የዕሴት ሕግ — የሸቀጥ ምርት ምጣኔ—ሀብታዊ ሕግ........................................35

ምዕራፍ ፫. ካፒታል(ወረት)እና ትርፍ ዕሴት—ምንዳዕ በካፒታሊዝምውስጥ..38

1. የካፒታል (ወረት) ጥንታዊ ክምችት ........................................38
2. የገንዘብ ወደ ካፒታል (ወረት) መለወጥ ........................................40
3. የትርፍ ዕሴት ምርት—የካፒታሊስት ብዝበዛ ........................................42
4. ካፒታልና (ወረት) ሌሎች አካሎቹ ........................................46
5. የሠራተኛውን መደብ የመበዝበዝ ደረጃ ለመጨመር ሁለት መንገዶች........................................49
6. ምንዳዕ በካፒታሊዝም ውስጥ ........................................53

ገጽ

ምዕራፍ ፬. የወረት መከማቸትና የወዝአደሩ ኑሮ እያሽቆለቆለ መሄድ ....58

1. የወረት መከማቸትና የሥራ—አጡ ሠራዊት ........................................58
2. የካፒታሊስታዊ ክምችት አጠቃላይ ሕግ........................................65

ምዕራፍ ፭. የትርፍ ዕሴት ወደ ትርፍ አለዋወጥና በተለያዩ የበዝባዥ ቡድኖች መካከል መሠራጨት (መከፋፈል)........................................70

1. የወረት (የካፒታል) ልዩ መልኮች ........................................70
2. አማካይ ትርፍና የምርት ተመን ........................................72
3. የንግድ ትርፍ ........................................76
4. የብድር ወረት (ካፒታል)የተዋሃዱ—(ጥቅል)ግዙፍ ኩባንያዎች..78
5. በካፒታሊዝም ውስጥ የመሬት ኪራይና እርሻ ነክ ግንኙነቶች..81

ምዕራፍ ፮. የሕብረተሰብ ወረት ዕርባታና የምጣኔ — ሀብት ቀውስ ....87

1. የሕብረተሰብ ወረት ዕርባታ........................................87
2. ብሔራዊ ገቢ ........................................92
3. ምጣኔ—ሀብታዊ ቀውሶች ........................................94

### ለ. ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም - ኤምፔሪያሊዝም ........................................98

ምዕራፍ ፯. የኢምፔሪያሊዝም መሠረታዊ የምጣኔ—ሀብት ገጽታዎች ....100

1. የምርት መድለብና ሞኖፖሊዎች ........................................100
2. ገንዘባዊ ወረትና ገንዘባዊ ሥልጣን (Financial Oligarchy) ....104
3. የወረት ወደውጭ መላክ—የዓለም ምጣኔ—ሀብታዊና ግዛታዊ ክፍፍል ........................................107
4. የሞኖፖሊ ትርፎች — ለሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መገፋፊያው ኃይል ........................................112

ምዕራፍ ፰. ኢምፔሪያሊዝም በታሪክ ውስጥ ያለው ቦታ—የዓለም ካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ........................................114

1. ኢምፔሪያሊዝም በታሪክ ውስጥ ያለው ቦታ ........................................114
2. የዓለም ካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ........................................121

# መቅድም ።

አብዮት ፡ በጸረ—አብዮትና በአብዮት ኃይላት መካከል የሚካሄድ የሕብረተ
ሰብ ትግል ነው ። የነበረውን አሮጌውን ሥርዓት አፈራርሶ በይዘትና በቅርጽ አዲስ
በሆነ ሥርዓት በፍራሹ (በመቃብሩ) ላይ መተካትና መገንባት ነው ። ይህ ደግሞ
ሕብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ ደረጃዎች ተካሂዷል ።
አብዮት በሕብረተሰቡ መካከል የሚካሄድ የመደብ ትግል ነጸብራቅ ነው ። የመደብ
ትግልም በገዥና በተገዥ ፡ በበዝባዥና በተበዝባዥ መካከል የሚካሄድ ያልገዛም፣
ያልበዘበዘም፣ የነጻ ልውጣ ግብ ግብ እንደሆነ ማንም ይረዳዋል ። ያስ ሆነ ፡ ታዲ
ያ ወይም ይህ ትግል እንዴት ይካሄዳል ? በየመስመሩ (በየሥፈሩ) ያሉት የሕብረተ
ሰብ አባላት (በተመሳሳይ መደብ ውስጥ ያሉት) እንዴት ይሰባሰቡና ፡ ይተባበሩና
የየመደብ ዝንባሌአቸውን ለማስጠበቅ ይታገላሉ ? ይህ ቀላል ነው ። የገዥና የበዝ
ባዥ መደብ የራሱ የሆነ ፖለቲካ ፡ ርዕዮተ—ዓለም (ፍልስፍና) አለው ። ይህ ገዥ
ነትን ፡ በዝባዥነትን ፡ ጨቋኝነትን የሚአጠናክር ፍልስፍና በዚህ መደብ ሥር የተ
ጠለሉትን አባላት ዝንባሌ በመመሥረት ስለሆነ የተመሠረተው ምንጊዜም የገ
ዥው መደብ አባላት ይደግፉታል ፡ ይታገሉለታል ። የተገዥውና የተበዝባዡ መደ
ብም እንዲሁ የራሱ የሆነ ፖለቲካ ፡ የራሱ የሆነ ርዕዮተ — ዓለም (ፍልስፍና)
አለው ። ይህን የምንለው በተለይ ካፒታሊዝም በሕብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ከተ
ከሠተ ጊዜ ጀምሮ በቡርዧው መደብ መምጣት ምክንያት የተገኘውን የወዛደር
መደብን ርዕዮተ—ዓለም ማለት እንጂ ሌላ አይደለም ። እንግዲያማ በባሪያ አሳዳ
ሪው ሥርዓት ጊዜ የነበረው ባሪያማ ! የራሱ የሆነ ርዕዮተ—ዓለም አልነበረውም፣
ወይም ደግሞ በመልከኛነት ሥርዓት ውስጥ ከመልከኛው አንጻር የነበሩት ገባሮች
(አርሶ—አደሮች) የራሳቸው የሆነ ርዕዮተ — ዓለም አልነበራቸውም ። እንዲያውም
ርዕዮተ — ዓለማቸው የመልከኛው (የፊውዳሉ) ነበር ። ስለሆነም እነኚህ የሁለቱ
ሥርዓተ—ማኅበሮች ተበዝባዥ መደቦች በራሳቸው የተቀናበረ ርዕዮተ — ዓለም
የሚመራ ፖለቲካ ስላልነበራቸው የሌላው ገዥ መደብ ርዕዮተ — ዓለም ጥገኛ
በመሆን ትግላቸውን ስለሚአካሂዱ ፡ የትግል ውጤታቸውን ከአንዱ ገዥ ወደ
ሌላው ገዥ በማሸጋገር እነሱም ካንድ ጨቋኝና በዝባዥ ወደሌላ ጨቋኝና በዝባዥ
ተሸጋግረዋል ። የራሳቸውን የመደብ አሸናፊነት አላረጋገጡም ወይም ደግሞ የራ
ሳቸውን የበላይነት አላሠፈኑም ። ለዚህ ብቃት የደረሰው ከታሪክ ሂደት እንደተረ
ዳነው የወዛደሩ መደብ ብቻ ነው ። ስለዚህም በወዛደሩና በቡርዧው መደብ መካ
ከል የሚካሄደው ትግል በሁለቱ መደቦች ርዕዮተ—ዓለም መካከል የሚካሄደው ትግ
ል ነጸብራቅ ነው ። በአድሃሪውና (በሕሊናዊው) በተራማጁ (በቁስ—አካላዊው) ፍልስ
ፍና መካከል የሚካሄድ የትግል ውጤት ነው በሕብረተሰቡ መደቦች መካከል
ከሰላም ማለትም ከሀሳቦች እስከ መጣሪያ ትግል ድረስ ተንጸባርቆ የምናየው ።

እንዲህ ከሆነም ፡ ዛሬ በኢትዮጵያ የምናየው ይህን ክስተ ነው ። ክስቱ በከፊል
መልከኛውና — ከበርቴው ሥርዓት ውስጥ ባሉት መሠረታዊ መደቦች መካከል
(በመልከኛውና በገበሬው ፡ በቡርዥዋውና በወዛደሩ መካከል) መራራና ወሳኝ የሆነ
የመደብ ትግል ነው ። ይህ የመደብ ትግል ሁላችንም እንደምንለው በ1966
በየካቲት ወር በከመ—ቅፅበት ፈንድቶ የመጣ አይደለም ። የረዥምም ጊዜ የብልጭ
ድርግም ትግል ተካሂዶ ነው እዚህ የደረሰው ። ለረዥምም ጊዜ የመልከኛው ሥርዓት
በገባሮች ዓመፅ ይናጥ ነበር ። የሻማ መብራት የሆኑ ግለሰብ ተሟጋቾች ታይተው
ጠፍተውበታል ። መልኩ ምንም ይሁን ምን ብዙ የመፈንቅለ—አገዛዝ ሙከራዎች
ተካሂደዋል ፤ የምሁራንና የተማሪዎች እንቅስቃሴዎች ታይተዋል ፤ ሠርቶ —
አደሮች (ወዛደሮች) ለመደባቸው ትግል እንዲረዳቸው ማኅበራቸውን ለማቋቋም
ጥቂት ግለሰቦች መስዋዕት ሆነዋል ። የነአበራ ገሙ ፡ የነመንግሥቱ ንዋይ ፡ የነበ



ላይ ዘለቀ ፡ የነደጃዝማች ታከለ ወ/ሃዋርያት ፡ የደራሲ ብሔረ — ሰብ ፡ የባሌና የጎ
ጃም ገበሬዎች ፡ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና ያንዳንድ መምህራን ትግል ለዚህ ማረጋ
ገጫ ነው ። ግን ይህ ሁሉ ይዘቱ ሶሻሊስታዊ ነው ማለታችን አይደለም ። በዚህ
ደረጃ ለመገምገም ብዙ የሚአጠያይቁ ነገሮች አሉ ። ምናልባትም ፅንሰ — ሀሳቡ
እንኳ በጥቂት ግለ — ሰቦች ቢታወቅ ነው ። ሆኖም በአጠቃላይ የኢጣሊያን ፡
የእንግሊዝንና የፈረንሳይ ኢምፔሪያሊስቶች ወዘተ . . . የመሳሰሉትን ኃይሎች
መቋቋም የመሰሰለውን ስንመለከት ትግሉ ጸረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል እን
ደነበረ ነው የምናየው ። ስለሆነም ይህ ሁሉ የተበታተነ ትግል ይነስም ይብዛ
ባንድነት ኃይሉን አስተባብሮ በግብታዊ መልክ የታየው በ1966 የካቲት ላይ
ነበር ። ከዚያ ጀምሮ ከቀን ቀን ትግሉ መስመር እየያዘ ፡ የትግል ልምድ
እየሸመተ ፡ አብዮታዊ አመራር ለመያዝ እንዲችል አቅጣጫውን የሚጠቁሙ ፍን
ጮች ታዩ ። በተለይም 67 ዓ. ም. ጥሩ እመርታ ነበር ። በሕብረተሰቡም መካከል
ቢያንስ የፍልስፍናው (የሶሻሊዝም) ጽንሰ—ሀሳብ ከምሁራን ድንበር ወጣ አለ ።
እንዲያም ሲል በተከታዩ ዓመት የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መታወጅ
ይበልጥ ለፍልስፍናው መስፋፋት ሠፊ በር እየከፈተና ለብዙ ታጋዮች በሕቡዕና
በመድረክ ላይ ለመከሠት ሌላው ከፍተኛ ምክንያት ነበር ። የትግሉ መድረክ መስ
ፋቱን የሚአረጋግጠው በዚሁ ዓመት በ68 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ፍልስፍናውን
የሚአስፋፉ መጻሕፍት በአማርኛ እየተመለሱ መታተም ነበር ። እርግጥም ባሳለፍ
ናቸው አራት የአብዮት ዓመታት ውስጥ በታሪክ ጐታችና በታሪክ አራማጅ መደ
ቦች መካከል በተካሄደው ትግል ሚናን ባለመለየትና በውዥንብር ውስጥ በመግባት
አግባብ ላልሆነ መስዋዕትነት ሕይወታቸውን ያሳለፉና አካለ—ጎደሎ ሆነው የቀሩ
ብዙ ዜጐች መኖራቸው ዕውቅ ነው ። የትግል መስመራቸውን ለይተው ለአድ
ሃሪ አቋምም ሆነ ለተራማጅ የሞቱት ዓላማቸው ስለሆነ በተለይ በተራማጆች በኩል
የትግል ሞታቸው ሕብረተሰቡን አስተምሮ ሌላ ታጋይ አፍርቶ እስከሆነ ድረስ የጠ
ፋው ሕይወት መጥፋት አይደለም ፡ መለምለም እንጂ ። በተለይ የኢትዮጵያን የአ
ብዮት ሂደት ስንመለከት እጅግ ፈጣን ከመሆኑ የተነሣ (ወዶ አይደለም የፈጠነው
በሁኔታዎች መባባስ ምክንያት ነው !) ሰዎች ጭራውን እንኳ ለመያዝ እየተሳናቸው
ጊዜ በማይሰጥ ምክንያት እየተንጠባጠቡ ነው ያሉት ። ስለዚህ አሁን ያለንበት
ደረጃ ለመድረስ የቻሉት ነገሮችን ያለማቋረጥ የተከታተሉ በእርግጥ ስለአብዮቱ
የቆሙ ፡ አጉል ጀብደኝነት ያላጠቃቸው፤በጥቂት ድሎች ያልሰከሩ ወዘተ . . . .
ናቸው ። ሌሎቹማ ፤ ማለትም አስመሳይ ተራማጆች በየአደባባዩ መፈክር በማው
ጣትና በማለት በሕብረተሰቡ ዘንድ የተራማጅነትን ስም ለመሸመት የተሯሯጡት ፡
ባቋራጭ የሥልጣን ጥማቸውን ለማርካት ጥድፍ ጥድፍ ያሉት ፤ ውስጣዊ ባሕሪ
ያቸው ባለው የአብዮት ፍጥነት ምክንያት እየተከሰተባቸው ታይተው ጠፍተዋል ።
ውዥንብር የተሞላበትን ንድፈ — ሀሳባቸውን ለማስፋፋትና የጥገና መንግሥ
ትን ለማቋቋም ፤ እንዲሁም በተዘዋዋሪ መንገድ ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሰፊ
ውን ሕዝብ ሲአስማሙት ከነሴራቸው አፈር ተበትኖባቸዋል ። አሁንም ይቀጥላል !!

እላይ ያለውን ሁኔታ ከተመለከትን ዘንድ የሕብረተሰቡ ጭቁን ክፍል በብዙ
አወቅሁ ባይና ተብለጥላጮች እንዳይምታታና የትግል አቅጣጫውን እንዳይስት
ማድረግ የኮሚኒስቶች ፡ የተራማጆችና የዲሞክራቶች ፋንታ ነው ። በተለይም በአ
ሁኑ ወቅትና ወደፊትም አብዮታችን ጥራት እየያዘና ያመራሩንም ሁኔታ ወደ ከሚኒ
ስቶቹ እያሸጋገረ በሚሄድበት ጊዜ ካለው የአብዮት ስፋትና ጥልቅት ማደም
ሀሳዊ—አብዮታውያን (Pseudo—revolutionaries) የሴራ ድራቸውን የሚአውጠነጥ
ኑት የዚያኑ ያህል ጥልቀትና ስፋት በመስጠት ነው ። ስለሆነም ፊት እናደርገው
ከነበረው ትግል ይበልጥ ለማካሄድ በየጊዜው ታክቲክና ስትራቴጂያችን ወቅታዊ
ግምገማ ልናካሄድበት ይገባል ።

ይህን ለማድረግ ደግሞ ወደድንም ጠላን የግድ ማርክሲዝም — ሌኒኒዝምን ጠንቅቆ ማወቅና ካለው የትግል ሁኔታም መረዳት ብሎም ለሰፊው ሕዝብ ማስተማርና ማስራጨት በዚህም የትግሉን ሠፈር በማስፋት የአብዮቱን ኃይላትና ወዳጆች ማጠናከር አግባብ ያለው ነው።ዛሬ የሕዝቡ ንቃተ—ሕሊና መዳበር ብቃት ያለው ነው ብለን አናቆምም ። ሊቆምም አይችልም ። ትግላችን አንዳንድ እርከን በተወጣ ቁጥር ቀድሞ የነበረ ንቃተ—ሕሊናችንን ስንመለከተው ኋላ—ቀር ሆኖ ነው የምናገኘው ። ፊት የነበረን የትግል ታክቲክና ስትራቴጅ ከደረስንበት የአብዮት እርከን ላይ ሊአገለግል አይችልም ። ሌላ ሻል ያለ መቀየስ ይኖርብናል ። ይህንም የምናደርገው የማርክሲዝም—ሌኒኒዝምን መሠረተ—ሀሳቦች በማጥናት ካለው የጊዜ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ነው ።

ስለሆንም በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ከሩሲያ ታላላቅ የሶሻሊስት ጸሐፊዎች አንዱ ፒ. ኒኪቲን ያቀናበረውን የማርክሲዝም—ሌኒኒዝምን አንዱን ዓይነተኛ ክፍል «የፖለቲካዊ ኤኮኖሚ መሠረተ— ሀሳቦችን» ተርጉሜ አቅርቤአለሁ ። መጽሐፉ ተደናቂነትን ካገኙት ጽሑፎች አንዱ ነው ። ተደናቂነቱ እንዲሁ ዓይደለም ፤ ግሩም የሆነ ማርክሳዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አተናተን ስለሚሰጥ ነው ። ይህን መጽሐፍ ስተረጉም በውስጡ ያሉት ፅንሰ—ሀሳብ ገላጭ የሆኑ ቃላት አማርኛ አልገኝላቸው እያሉ እጅግ አስቸግረውኛል።ይሁን እንጂ አስከተቻለ ድረስ እጅግ እደናጋሪ ለሆኑት ከግርጌም ማስታወሻ በመስጠት ጭምር ግልፅ እንዲሆኑ ሞክሬአለሁ ። ብዙዎቹ ቃላት ደግሞ ከዚህ በፊት በተረጎምኳቸው መጻሕፍት ውስጥ የተለመዱ በመሆናቸው እምብዛም አያደናግሩም ።

መጽሐፉን ሙሉ በሙሉ ባንድ ቅጽ ለማውጣት አልተቻለም ። ምክንያቱ ሌላ አይደለም ፤የህትመት ችግር ነው። ስለዚህ በሁለት ክፍል ከፍያዋለሁ ። ቅጽ 1 የካፒታሊስት ሥልተ—ምርት ቅጽ 2 የኮሚኒስት ሥልተ — ምርት በማለት ። ስለዚህ አሁን የወጣው የካፒታሊስት ሥልተ — ምርቱ ነው ። ሁለተኛው ደግሞ ይህን ተከትሎ በቅርብ ጊዜ ይወጣል ። ዋናው ቁም ነገር የመከፋፈሉ ሳይሆን በሀገር ቋንቋ ተመልሶ ለትግል መሣሪያ እንድንጠቀምበትና በሁላችንም ዘንድ እንዲነበብ መሆኑ ላይ ነው ።

ስለሺ አንዳርጌ

Proudly Brought to You
By
www.binyamhk.wordpress.com



# የፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ትምህርት ምንነት

የማርክሲስት — ሌኒኒስት ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ የማርክሲዝም — ሌኒኒዝም ሳይንስን ከሚያስገኙት ነገሮች ሊነጠል የማይችል አንዱ ክፍል ነው ።

ማርክሲዝም — ሌኒኒዝም ስለሕብረተሰብ ዕድገት ሕጐች ፣ ስለሕብረሱታፊ (ሕብረሰባዊ) አብዮትና ስለወዛደሩ አምባገነንነት ፤ የሶሻሊስትና የኮሚኒስት ሕብረተሰብን ፣ ስለመገንባት የሚናገርና የሚሠራ ነው ። አንድ የሆነ ፤ የተያያዘ ትምህርት (የተዋሃደ) ፣ ከሶስት የማይነጣጠሉ ክፍሎች የተሠራ ነው — ክፍልስፍና ፣ ከፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ፣ እና ከሳይንሳዊ ኮሚኒዝም ንድፈ—ሀሳብ ። ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ በሰብአዊ ሕብረተሰብ መሠረታዊ ኑሮ (ሕይወት) ላይ ስለሚሠራ ፣ የማርክሲዝም —ሌኒኒዝም ዓይነተኛ ክፍልን ይመሠርታል ።

**የቁሳዊ ሀብት ምርት የሕብረተሰብ መሠረት**

ለዘመናት ሰዎች በሰብአዊ ሕብረተሰብ ዕድገት ምክንያቶች ላይ አተኩረዋል።የተለያዩ የአመለካከት ነጥቦች ተብራርተው ነበር።ሃይማኖታዊ አቀንቃኞች ለምሳሌ ፣ ሁሉም ዕድገት የሚካሄደው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ሁሉም ለፍፈዋል ። ይሁንና ሳይንስና ተግባር ከሁሉ በላይ የሆነ ኃይል እንደሌለ አረጋግጠዋል ። የሕብረተሰብ ዕድገት ጥገኛ የሚሆነው በመልክዐ—ምድራዊ አካባቢ የወሳኝነት ስሩት ፣ ማለትም ፣ የተወሰነ ተፈጥሮአዊ ሁኔታ (የአየር ንብረት ፣ አፈር ፣ ማዕድን ፣ ወዘተ . . .) ነው የሚል ፣ በዛሬው ጊዜ ብዙ የቡርዧ ምሁራን የሚናገሩት ፣ አመለካከትም ነበር ። ግን ምልከዓ—ምድራዊ አካባቢ ለሕብረተሰብ ዕድገት ከአስፈላጊ ሁኔታዎች አንዱ እንጂ ፣ ወሳኝ ግን አይደለም ። በሶስት ሺ ዓመታት ርቀት ውስጥ በአውሮጳ ሶስት የሕብረተሰብ ሥርዓቶች ተወራርሰዋል ፣ በመካከለኛውና በምሥራቅ አውሮጳ ግን አራትም አልፏል ፤ ሆኖም በዚያ ወቅት መልከዓ—ምድራዊ ሁኔታዎች በአውሮጳ እንዲአውም አልተለወጡም ፣ ወይም ለመልከዓ—ምድር ምሁራን አሳሳቢ ያልሆነ እጅግ ጥቂት ለውጥ ነበር ያለው ። አንዳንድ ሰዎች የታሪክ አቅጣጫ የሚንተራሰው (ጥገኛ የሚሆነው) በንቁ ግለ—ሰቦች ብቻ እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ — በመሪዎች ፣ በጄኔራሎች እና በሌሎችም ። ይሁንና ፣ የሚታየው እውነት ፣ እነዚህ ግለሰቦች የከዊኑ ነገሮችን አካሄድ ያፋጥናሉ ወይም ይጐትታሉ እንጂ ፣ የታሪክን ሂደት አይለውጡትም ።

ታዲያ ፣ የሕብረተሰብን ዕድገት የሚወስነው ምንድነው ? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማቅረብ የመጀመሪያው ሰው ማርክስ ነበር ።

ለመኖር ሲባል ፣ ሰዎች ምግብና ልብስ ፣ ቤትና ሌላም ለኑሮ ቁሳዊ ዘዴዎች እንዲኖሯቸው ያሻል ፣ እናም እነኝህን ለማግኘት ሰዎች ሊአመርቷቸው ይገባል ፣ መሥራት አለባቸው ። ማንኛውም ሕብረተሰብ ቁሳዊ — ሀብትን ማምረት ካቆመ ይሰባበራል ። «ስለዚህ» ፣ ይላል ማርክስ ፡— « የቁሳዊ ሀብት ምርት ለማንኛውም ሕብረተሰብ ሕይወትና ዕድገት መሠረት ነው ። »

ቁሳዊ — ሀብት ሲባል ምን ማለት ነው ? ቁሳዊ — ሀብትን የማምረት ሂደት ሰብዓዊ ጉልበትን ፣ የተግባር መገልገያዎችን ፣ እና የምርት መመንጫዎችን ይጨምራል ።

« ሥራ » በቁሳዊ — ሀብት ምርት ላይ የሚውል የሰዎች የክንዋኔ ተግባር ነው ። በሥራ ሂደት ውስጥ ፣ በተፈጥሮ ውስጥ ያሉ ነገሮችን ከራሱ ፍላጐት ጋር ለማስኬድ ሰው በተፈጥሮ ላይ ድርጊቱን ያውላል ። ሥራ ነዋሪ አስፈላጊነት ያለው ለሰዎች ሕይወት ተቀዳሚ የሆነ ፣ ዓይነተኛ ራሱን የቻለ የሰዎች ጸባይ ነው ። እን ግልስ እንዳስቀመጠው ሥራ ራሱን ሰውን ፈጠረው ።

የምርት ሂደት ያለተግባር መገልገያዎች ሊታለም የማይችል ነው ። ይህ ቃል ነው ሰዎች በምርት መመንጫዎች ላይ ድርጊታቸውን ለማዋል የሚረዷቸውን ነገሮች የሚወክልና እነሱንም ለመለወጥ የሚአስችለው። የተግባር መገልገያዎች ፣ ማሺኖችን ፣ ማሙያ ዕቃዎችን ፣ መሣሪያዎችንና ቁልፎችን ፣ ገመዶችን ወዘተ . . . ለምርት ተግባር የሚውሉ ሕንጻዎችን ፣ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ፣ መስኖዎችን የኃይል ማመንጫዎችን ወዘተ . . . ይይዛሉ ። የምርት ማከናዎኛዎች በተግባር መገልገያዎች ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ። የሰው ኃይል በተፈጥሮ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር በሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ላይ ጥገኛ ነው ። ማርክስ ሲጠቁም ፡— ምጣኔ ሀብታዊ ወቅቶች አንዱ ካንደኛው የሚለዩበት በሚመረተው ነገር ሳይሆን ግን ቁሳዊ ሀብት ለማምረት በጥቅም ላይ በዋሉት መሣሪያዎች ነው ።

ከምርት መሣሪያዎቻቸው ጋር ሰዎች በምርት መመንጫዎች ላይ ድርጊታቸውን ያውላሉ ፣ ማለትም ፣ የሰው ጉልበት በሚውልበት ሁሉ ። እናም ይህ ጉልበት በአካባቢው በሚገኘው ተፈጥሮ ላይ ስለሚውል ፣ ተፈጥሮ ራሱ (መሬትና የመሬት ውስጥ) ሁለንታዊ የሆነ የምርት መመንጫ ነው ። ሁሉም ተቀዳሚ የምርት መመንጫዎች በተፈጥሮ ውስጥ እንደልብ ናቸው ። ሰው ከሚፈልጋቸው ነገሮች ጋር እነኝህን ማላመድ ፣ ማስማማት አለበት ።

የተግባር መገልገያዎችና የምርት መመንጫዎች ባንድነት የምርት መገልገያን ያስገኛሉ ። ግን በግልጽ እራሳቸው የምርት መገልገያዎች ቁሳዊ — ሀብት ሊአመርቱ አይችሉም ። ከሁሉ በላይና ይበልጥ የሆነው ቱክኒካዊ መሣሪያ ከሚጠቀሙበት ሰዎች ውጭ በድን ፣ ግዑዝ ነው ። ስለዚህ በማንኛውም ምርት ወሳኙ ምክንያት ራሱ ሰው ነው ፣ የጉልበት ኃይሉ ።

የምርት ኃይሎችና
የምርት ግንኙነቶች

የዕድገት ደረጃውን በመተው ፣ ምርት ሁልጊዜ ሁለት ክፍሎች አሉት ፡— የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች የሚባሉ ።

የምርት ኃይሎች በሕብረተሰቡ የሚፈጠሩትን የምርት መገልገያዎች ከሁሉም ቀደምና ይበልጥ የምርት መሣሪያዎችን ፣ እናም ቁሳዊ—ሀብትን የሚአመርቱትን ሰዎችም ይይዛል ። ሰዎች ናቸው ፣ ምክንያቱም በአገኙት ዕውቀት ፣ ባላቸው ገጠመኝና የሥራ ልምዶች ፣ የምርት መሣሪያዎች እንዲንቀሳቀሱ የሚአደርጓቸው የሚአሻሽሏቸው ፣ መኪናዎችን የሚሠሩ ፣ እናም ለዕውቀታቸው ሌላ ዕውቀት የሚጨምሩ ። በዚህ መልክ ፣ የምርት ኃይሎች ዕድገት ይረጋገጣል ፣ እናም ከዚህ በፊት ያልታዩ የቁሳዊ—ሀብት መጠን ጭማሪ ያገኛል ።

ግን ሰዎች ቁሳዊ — ሀብት የሚአመርቱት በተናጠል በመስራት ሳይሆን ፣ ባንድነት በቡድን በመሥራት ፣ ሕብረተሰባዊ በሆነ መንገድ ነው ። ለምሣሌ ፣ ዘመናዊ የጫማ ፋብሪካን እንውሰድ ። አንድ ሸቀጥ ብቻ የሚሠራ — ጫማን ፣ በዚያ ውስጥ ምን ያህል ሰዎች እናገኛለን ? በመቶ ፣ በሺም ፣ ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ሰዎች ፋብሪካውን በማሺን ፣ በቆዳ ፣ በክር ፣ በመርፌዎች ወዘተ . . . ለማገልገል ይሠራሉ ። ስለሆነም ፣ ቁሳዊ—ሀብትን በማምረት ሂደት ውስጥ ሰዎች በአንድነት ተያይዘዋል ፣ እርስ በእርሳቸው ጥገኛ ናቸው ። እናም እርስ በእርሳቸው በተወሰነ ግንኙነት ውስጥ ይገባሉ ።

በምርት ሂደት ፣ በቁሳዊ — ሀብት ማካፋፈልና ልውውጥ ጊዜ በሰዎች መካከል የሚታዩትን ግንኙነቶች ማርክስ የምርት ፣ ወይም የምጣኔ — ሀብት ግንኙነቶች ብሎ ጠርቷቸዋል ። የምርት ግንኙነቶች ከብዝበዛ ነጻ በሆኑ ሰዎች መካከል የሕብረትና እርስበእርሳቸው የመረዳዳት ፣ ወይም የሰውን በሰው መበዝበዝ ቅርፅ



ሊወስዱ ይችላሉ ። ይህ የሚንተራሰው የምርት መገልገያዎችን ማን ያዝባቸዋል ? በሚለው ነው — መሬትና የማዕድን ሀብትን ፣ ደኖችን ፣ ፋብሪካችንና የዕቃ መሥሪያ ሱቆችን ፣ የምርት መሣሪያዎችን ወዘተ . . . ። የምርት መገልገያዎች በግል ከተያዙ በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ ካልሆኑ ግን ለተለያዩ ግለሰቦች ፣ ለሕብረተሰብ ክፍሎች ወይም መደቦች ከሆኑ ፣ ግንኙነቶቹ የተመሠረቱት የሰውን በሰው ብዝበዛ ላይ ፣ በገዥነትና በተገዥነት ነው ። ይህ የሚሆነው ምክንያቱም በካፒታሊዝም ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ከምርት መገልገያዎች ስለተከለከሉና ለካፒታሊስቶቹ እንዲሠሩ ስለሚገደዱ ነው ። በሶሻሊዝም ውስጥ የምርት መገልገያዎች በሕብረተሰቡ የተያዙ ናቸው ። ስለሆነም ፣ የሰውን በሰው ብዝበዛ የለም ፣ እናም በሰዎች መካከል ያሉት ግንኙነቶች የጓዳዊ መተባበርና የሕብረ—ሱታፌአዊ መረዳዳት ነው ።

ከምርት መገልገያዎች ጋር ያለው የሰዎች ግንኙነት በሕብረተሰቡ ውስጥ ሰዎች የሚይዙትን ቦታ እና የጉልበት ውጤቶች የሚከፋፈሉባቸውን ዘዴዎች ይወስናል ። ለምሣሌ በካፒታሊዝም ውስጥ ቡርዧው ፣ የምርት መገልገያዎችን የያዘው ፣ የሠራተኞችን ጠቅላላ ውጤት ያጋብሣል ፣ ስሬው ሠራተኛ ግን በድህነት ይኖራል ። በሶሻሊዝም ውስጥ የምርት መገልገያዎች ለሕዝቡ በሆኑበት (የሕብረተሰቡ ንብረት ናቸው) ፣ የብሎት (የፍጆት) ዕቃዎች ሰዎች በአበረከቱት ሥራ መሠረት ይከፋፈላል ፣ እናም የማያቋርጥ የቁሳዊና የባሕላዊ ዕድገት ደረጃ ለሁሉም ሠራተኛ ሕዝብ ይረጋገጣል ። ይህ ነው በሰዎች መካከል የምርት (የምጣኔ—ሀብት) ግንኙነቶች ተብሎ የሚጠራው ።

በሰዎች ታሪክ ውስጥ አምስት ዓይነት መሠረታዊ የምርት ግንኙነቶች ታውቀዋል—እነሱም የጥንታዊ ጋርዮሽ ፣ የባሪያ አሳዳሪ ፣ የመልከኛ ፣ የካፒታሊዝምና የሶሻሊዝም (የኮሚኒዝም መጀመሪያ ደረጃ) ናቸው ። የእያንዳንዳቸው ዓይነተኛ ገጽ (ጸባይ) የምርት እና የተግባር መገልገያዎች የተወሰነ የንብረትነት ቅርፅ ነው ። ስለዚህ ፣ በባሪያ አሳዳሪ ፣ በመልከኝነትና በካፒታሊዝም ውስጥ የምርት ግንኙነቶች መሠረት የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ነው ። ይህ ባለቤትነት ለሕብረተሰብ መከፋፈልና ጨቋኝና ተጨቋኝ መደቦችን ለመፍጠር ምክንያት ሆኗል ፤ ወደፊትም ይሆናል — በዝባዦችና ተበዝባዦች ። ስለዚህ ኃይለኛ የመደብ ትግል ለባሪያ አሳዳሪው ፣ ለመልከኛውና ለካፒታሊስቱ ሥርዓት መሠረታዊ ጸባይ ነው ። በሶሻሊዝም ብቻ ነው ፣ የጋራ ፣ የምርት መገልገያዎች ሕብረተሰባዊ ባለቤትነት የምርት ግንኙነት የሚመሠረተውና የመደብ ትግል የማይኖርበት ። ሕብረተሰቡ በተባባሪ መደቦች ይሞላል — ሠራተኞችና ገበሬዎች ፣ እናም ምሁራን እንደሕብረተሰቡ ክፍል ።

የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ባንድነት ሥልተ—ምርትን ይቀርጻሉ።

የምርት ኃይሎች በሥልተ — ምርት ውስጥ ዋና አዳጊ ነገሮች ናቸው ፤ ሰዎች ሳያቋርጡ የተግባር መገልገያዎችን ስለሚአሻሽሉና የምርት ገጠመኝ ስለሚአጠራቅሙ ፣ በማከታተል ይለወጣሉ ። የምርት ግንኙነቶችም በምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ መሠረት ይለወጣሉ እናም በተራቸው ይህን ዕድገት ተፅዕኖ ያሳድሩበታል ።

የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ጋር ሲስማሙ ፣ የኋለኛው በማያቋርጥ ሁኔታ ያድጋል ። የሶሻሊስት አገሮች የምርት ግንኙነት ከምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ጋር የመስማማትን ምሣሌ ይሰጠናል ። እዚያ ፣ ምርት በአፋጣኝ ያድጋል ፣ ያለቀውስና ያለ ሥራ — አጥነት ፣ ምክንያቱም በምርት መገልገያዎች የጋራ ባለቤትነት የተመሰረተ ነውና ።

የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ጋር ካልተስማሙ ፤ እንደ ምርት አቋራጭ ሆነው ይሠራሉ ። የካፒታሊስት አገሮች የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ጋር ያለመስማማትን ምሣሌ ይሰጡናል ። በካፒታሊስት አገሮች ምርት በዝግታ ነው የሚአድገው ፤ እናም በምጣኔ — ሀብት ቀውስ ጊዜ ይበልጥ ወደኋላ ይንዳል ፤ ብዙሚሊዮን ሠራተኛ ሰዎች ስለማይፈለጉ ይትረፈረፋሉ ፤ ስለሆነም የሥራ—አጥነትን ደረጃ ያሳብጣሉ ። ይህ የሚሆነው ምክንያቱም በቡርዧ ሕብረተሰብ ውስጥ የምርት መገልገያዎች የግል ካፒታላዊ ባለቤትነት ስለሚገኝ ፤ እና ይህ የምርት ኃይሎችን የወደፊት ዕድገት ስለሚጐትት ነው ።

አንድ የተወሰነ የምርት ኃይሎች ደረጃ ከራሱ ጋር የሚስማሙ የምርት ግንኙነቶችን ደረጃ ይሻል ። ይህ ነው በማርክስ የተገኘው የምጣኔ — ሀብት ሕግ ፤ የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች ጸባይ ጋር ይጣማሉ ፤ ይስማማሉ የሚለው ። ይህ ሕግ የሕዝባዊ አብዮትን ምጣኔ — ሀብታዊ መሠረት ይገልጻል ። የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ በስተኋላ የሚጐተቱ ከሆነ ፤ አርጅተው ያፈጁና ዕድገታቸውን ይጐትታሉ ፤ በማይቀርም ሁኔታ በአዲሶች ይተካሉ ። በጨቋኝና በተጨቋኝ መደቦች በተከፋፈለ ሕብረተሰብ ውስጥ አሮጌዎቹ የምርት ግንኙነቶች በሕዝባዊ አብዮት ምክንያት በአዲሶቹ ይወረሳሉ ።

በሶሻሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ብቻ ነው ፤ ተጻራሪ መደቦች በሌሉበት ፤ የምርት ግንኙነቶች በሕዝባዊ አብዮት ሳይሆን ግን ከምርት ኃይሎች ዕድገት ጋር ለመስማማት በዕቅዳዊ መልክ (ገጽ) የሚአድጉት ።

ሥልተ — ምርት በአጠቃላይ መታየት ያለበት ከሕብረተሰብ « መሠረት » ነው ። « መሠረት » በአንድ በተወሰነ ሕብረተሰብ ውስጥ የሰፈኑ የምርት ግንኙነቶች ፤ ግንኙነቶችም ካለው የምርት ኃይል ደረጃ የሰመሩበት ፤ አጠቃላይ ድምር ነው ። የሕብረተሰብ መሠረት ወይ ተጻራሪ አለዚያም የማይጻረር ይሆናል ። የባሪያ አሳዳሪው ፤ የመልከኛውና የካፒታሊስቱ ሕብረተሰቦች በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት የተመሠረቱ በመሆናቸው ፤ በገዥና በተገዥነት ግንኙነቶች ፤ የሰው በሰው መበዝበዝ ላይ ፤ በተፈጥሮአቸው ከመሠረቱ ተጻራሪ ናቸው ። የሶሻሊስት ሕብረተሰብ ግን ብዝበዛ የሌለበት የምርት መገልገያዎች የሕዝብ ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ተጻራሪ አይደለም ።

መሠረት ከራሱ ጋር የሚስማማ ላዕላይ መዋቅር ይፈጥርና ዕድገቱንም ይወስናል ፤ ላዕላይ መዋቅር ማለት የፖለቲካዊ ፤ ፍልስፍናዊ ፤ ሕጋዊ ፤ ኪነታዊ ፤ ሃይማኖታዊና ሌላም የሕብረተሰብ አመለካከቶችና ከነዚህም የሚሰምሩት ተቋሞች በመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ ላዕላይ መዋቅሩ መደባዊ ጸባይ አለው ። የገዥው መደብ ከራሱ ሀሳቦች ጋር የሚስማሙ ተቋሞችን የመደብ ጥቅሙን ለመጠበቅ ይፈጥራቸዋል ።

ሁሉም መሠረትና ላዕላይ መዋቅር የሚኖሩት ለተወሰነ ጊዜ ነው ። መሠረቱ ሲለወጥ ላዕላይ መዋቅሩም ይለወጣል ። ስለዚህ ፤ የመልከኛው መሠረት መለወጥ ሲለወጥ ላዕላይ መዋቅሩም ይለወጣል ። ስለሆነም ፤ የመልከኛው መሠረት መለወጥ እናም በካፒታሊስቱ መተካት ፤ የመልከኛው ላዕላይ መዋቅር በካፒታሊስቱ መሠረትን አሳዩ ። የሶሻሊስት መሠረት መምጣት የሶሻሊስት ላዕላይ መዋቅርን በማስገኘት የካፒታሊስቱን ለመሰባበር ዳረገው ። በአጠቃላይ ላዕላይ መዋቅሩ በመሠረቱ የሚመጣ ቢሆንም ፤ በአሮጌው ሕብረተሰብ ውስጥ የአዲሱ ላዕላይ መዋቅር የተነጣጠሉ አካሎች ሊታዩ ይችላል ፤ ይህ የሚሆነው የተራማጁ መደብ ሀሳቦችና አመለካከቶች የሚከሠቱት በአሮጌው ሕብረተሰብ ውስጥ ስለሚሆን ነው ። ለም



ሣሌ ፤ በካፒታሊዝም ውስጥ ከአዲሱ አብዮታዊ መደብ ጋር የሚስማማ—ከወዝ አደሩ—የወዛደራዊ ርዕዮት — አለም ይታያል ።

የቁሳዊ — ሀብት ሥልተ — ምርት ፤ የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ጥምረት በመሆን ፤ ከሚስማማው ላዕላይ መዋቅር ጋር ባንድነት የሕብረተሰቡ ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረጾችን ይመሠረታሉ ።

በታሪክ ውስጥ አምስት ዓይነት የሕብረተሰብ ምጣኔ—ሀብታዊ — አቀራረጾች ይታወቃሉ — ጥንታዊ — ጋርዮሽ ፤ ባሪያ አሳዳሪ ፤ መልከኛ ፤ ካፒታሊስትና ኮሚኒስት (ሶሻሊዝም የኮሚኒዝም የመጀመሪያ ደረጃ በመሆን) ናቸው ። እያንዳንዳቸው እነኝህ አቀራረጾች ከራሳቸው የሚስማማ ምጣኔ — ሀብት ፤ አመለካከቶች ሀሳቦች ፤ ተቋሞች አሏቸው ። የሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረጾች ዕድገት ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛው ይወጣል ። ስለዚህ ፤ መልከኛነት ለካፒታሊዝም እርሱም ለሶሻሊዝም (ለኮሚኒዝም የመጀመሪያው ደረጃ) በተራ መንገድ ሰጡ ። የሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረጾች መወለድ ፤ ማደግና ፤ መሞት ለሕብረተሰብ የዕድገት ሕጎች ጥገኛ ናቸው ።

የሕብረተሰብ ዕድገት
ምጣኔ ሀብታዊ ሕጎች

ማርክሲዝም—ሌኒኒዝም ተፈጥሮና ሕብረተሰብ የተለያዩ የተገነጣጠሉ ክስቶች ድንገታዊ ጥርቃም ሆነው መቆጠር እንደሌለባቸው ያስተምራል ። ተፈጥሮአዊና ሕብረተሰባዊ ክስቶችሁሉ የተያያዙና እርስ በእርሳቸው የሚወሰኑ ናቸው ። ይህ ጥልቀታዊ መተሳሰር መግለጫ የሚአገኘው በተፈጥሮና በሕብረተሰብ ዕድገት ሕጎች ውስጥ ነው ። የሳይንስ ተግባር እነኝህን ሕጎች ማግኘት ነው ።

ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጎች የሕብረተሰብን የዕድገት መሠረት ያስገኛሉ ። እነኝህ ሕጎች በሰዎች መካከል በጣም የተለያዩ የሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ ግንኙነቶችን ይወስናሉ ፤ ማለትም ፤ በምርት አድማስ ፤ በማከፋፈል ፤ በልውውጥና በብሎት ግንኙነቶች መካከል ያለውን የሕብረተሰብ ዕድገት ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጎች መገኘት ለፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ሳይንስነት ዓይነተኛነት አላቸው ።

የሕብረተሰብና የተፈጥሮ ሕጎች የጋራ ገፅ አላቸው — የነባራዊነት ጸባይ ፤ ማለትም ፤ አወቅናቸውም ወይም ክንዋኔ እንዲአካሂዱ ፈለግናቸው አልፈለግናቸው ከኛ ውጭ በመሆን ይከሠታሉ ፤ ያከናውናሉ ። ይህም ማለት ሰዎች ሊለውጧቸው ፤ ሊአሻግሯቸው ወይም እነኝህን ሕጎች ሊአስቀሯቸው አይችሉም ማለት ነው ። ወይም አዲስ ሊፈጥሩም ቢሆን ። ግን ምንም እነዚህ ሕጎች ነባራዊ ቢሆኑ በእነሱ ፊት ሰዎች ኃይል የላቸውም ማለት አይደለም ። ሊአውቋቸው ይችላሉ ፤ እናም በሕብረተ — ሰቡ ዝንባሌም ሊአውሏቸው (ሊጠቀሙባቸው) ። ስለዚህ ፤ የሶሻሊስት አገሮች ወዛደሮችን የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች ጸባይ ጋር የመጣጣሙን ሕግ በመረዳት (በማወቅ) ከገበሬው ጋር ኪዳን በመፍጠርና በኮሚኒስትና በሠራተኛ ፓርቲዎች በመመራት ፤ የበዝባገሮችን ኃይል ወረወሩና አዲስ ሕብረተሰብን መገንባት ያዙ ።

ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጎችን ከተፈጥሮ ሕጎች ልዩ የሚአደርጓቸው ገፆች አሉ ። የመጀመሪያው ገፅ ከተፈጥሮ ሲነጻጸሩ አጭር ጊዜ ያላቸውና የሚከናወኑትም በተወሰነ ታሪካዊ ዘመን መሆኑ ነው ። የተወሰኑ ምጣኔ — ሀብታዊ ሁኔታዎች ፤ ማለትም ሕብረተሰቡ ያለፈባቸው የምርት ግንኙነቶች ፤ የምጣኔ — ሀብት ሕጎችን የአሠራር መሠረት ያስገኛሉ ። ከአንደኛው አቀራረፅ ወደሌላው በመሸጋገር ላይ ፤ አሮጌዎቹ የምርት ግንኙነቶች ተወግደው አዲሶቹ ቦታቸውን ይወስዳሉ ። ይህ ነው የአንድን ምጣኔ — ሀብታዊ ሕግ መጥፋትና የሌላውን መከሰት ምክንያት የሚአመጣው ።

ለምሣሌ ፣ በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ ፣ በምርት መገልገያዎች ካፒታላዊ የግል ባለቤትነት መወገድ ምክንያት ፣ አዲስ ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐች ወደሕልውና መጥተው ፣ አሮጌዎቹ ሕጐች ሥራቸውን አቋመዋል ።

ብዙ ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐች በእያንዳንዱ ሕብረተሰባዊ ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረፅ ውስጥ ይሠራሉ ። በአንድ ዓይነት አቀራረፅ ብቻ የተመለዱ ሕጐች ልዩ ሕጐች ተብለው ይጠራሉ ። ከነዚህ መካከል መሠረታዊ የምጣኔ — ሀብት ሕጐችን ሕብረተሰቡ ሊአገኝ የሚፈልጋቸውን ዓላማና ፣ እናም የማግኛው መንገድና ሥልቱን የሚወስኑትን መለየት ይቻላል ።

ከነኝህ ልዩ ምጣኔ ሀብታዊ — ሕጐች ሌላ ፣ ለማንኛውም የሕብረተሰብ ምጣኔ ሀብታዊ አቀራረፅ የሚውሉ አሉ ። ከነዚህ ውስጥ አንዱ የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች ጸባይ ጋር የመስማማታቸው ሕግ ነው ። በሁለቱ የሕብረተሰብ የምርት ክፍሎች ያለውን አስፈላጊ መተሳሰርና የእርስ በእርስ ጥገኝነት ይገልጸል — በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለውን ።

ሁለተኛው ገፅ የምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐችን የሚመለከተው በሕብረተሰብ ላይ በሚውሉበት ጊዜ ያላቸውን ጸባይ ነው ። እንደተፈሮ ሳይንስ ሕጐች ሳይሆን ይነስም ይብዛ አዲስ የተገኘ ሕግ በቀላሉ በተግባር እንደሚውልበት ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐች የሚገኙትና የሚውሉት ጠንካራ መቋቋም ባለው በአረጀው ኃይል ክፍል ጥርስ ውስጥ ነው ። በመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ የምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐች በተግባር መዋል መደባዊ ጸባይ አለው ።

እነኝህ ልዩ ገጾች ናቸው የምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐችን ከተፈጥሮ ሕጐች ልዩ የሚአደርጓቸው ።

በሁሉም ሥልተ — ምርት ውስጥ ተቀባይነት እንዳለው አስፈላጊነት በመሆን ፣ ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐች በግብታዊነት ሊሠሩ ይችሉ ይሆናል ወይም በንቃት በተግባር ይውላሉ ።

ሕጉ የምርት መገልገያዎችን የግል ባለቤትነት በሚፈቅድበት በተጻራሪ የሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ መቅረጾች ፣ ተቀባይነት አገኙ አላገኙ ፣ ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐች በእውር ጭፍን ነው የሚሠሩት ። ለምሣሌ ፣ በካፒታሊዝም ውስጥ የምርት ሂደት ሕብረተሰባዊ ጸባይ አለው ፣ ሁሉም ቅርንጫፎቹ የተያያዙት አንዱ ባንዱ ላይ ጥገኛ ናቸው ። ግን ይህ ሕብረሰባዊ ጸባይ የተመሠረተው በግል ንብረት ላይ ነው ፣ ማለትም እያንዳንዱ ካፒታሊስት በራሱ ድርጅት ውስጥ የሚአስገባው ለመበልጸግ ያለውን የስግብግብነት ዓላማና ከፍተኛ ትርፍ ለመበዝበዝ ያለውን ምኞት ነው ። በተለያዩ የምርት ቅርንጫፎች መካከል አስፈላጊዎቹ መያዣና ምጥነት የሚመረቱት በግብታዊ መልክ ነው — መጨረሻ በሌለውና በሚከታተል መለያየት ። አንድ ቀን ብዙ ዕቃዎች ይመረታሉ ፣ በሚቀጥለው ደግሞ ጥቂት ብቻ ፣ ወዘተ . . . ። ስለዚህም ፣ ለእያንዳንዱ ካፒታሊስት ፣ ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐችን ሊቆጣጠራቸው የማይችል ከራሱ በላይ እንደሆነ ኃይል ሆነው ይሠራሉ ። እርግጥ ፣ አንዳንድ ካፒታሊስቶች ስለካፒታሊዝም ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐች መገንዘብ ላይ ሊደርሱ ይችሉ ይሆናል ፣ ግን የግብታዊ ጸባይ አሠራራቸውን ለማቆም አይችሉም ።

በሶሻሊዝም ውስጥ ፣ ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐች ስለሚታወቁ በንቃትም ለሕብረተሰቡ ጥቅም ይውላሉ ፣ የምርት መገልገያዎች የሕዝብ ንብረትነት መኖር ምስጋና ይግባውና ! ።





ለሕብረተሰብ ዕድገትና ኑሮ መሠረት የቁሳዊ — ሀብት ነው ፣ ሥልተ — ምርቱ ። ግን ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ምርትን የሚአጠናው በምርት ሂደት ጊዜ በሰዎች መካከል ካሉት ግንኙነቶች አንጻር በመመልከት ነው ። የሕብረተሰብን መሠረት ይመረምራል ። « ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ » ፣ ይላል ሌኒን ፣ « ከምርት ጋር አይደለም ግንኙነቱ ፣ ግን በምርት ውስጥ በሰዎች መካከል ስላለው የሕብረተሰብ ግንኙነት ጋር ነው — በሕብረተሰብ የምርት ሥርዓት ። »[1] በዚያውም (እግረ መንገዱን) ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ በምርት ግንኙነቶችና በምርት ኃይሎች መካከል ያለውን ግንኙነት ሳያጤን አይሄድም ። ወይም ሙሉ በሙሉ ላዕላይ መዋቅሩን ንቆ አይተወውም ፣ የሚመጣው ከመሠረቱ ስለሚሆን በእርሱም ላይ ከባድ ተፅዕኖ ያሳድራልና ።

ስለዚህ የፖለቲካዊ — ኢኮኖሚ ትምህርት የሰዎች የምርት (የምጣኔ — ሀብት) ግንኙነቶች ነው ። ይህ የምርት መገልገያዎችን የባለቤትነት መልክ ፣ በምርት ውስጥ የተለያዩ የሕብረተሰብ ቡድኖች የያዙትን ቦታና በመካከላቸው ያሉትን ግንኙነቶች ፣ የቁሳዊ — ሀብት የሚከፋፈልበትን ቅርፅ ይይዛል ።

በሌላ አባባል ፣ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ የሕብረተሰባዊ አምራችነት ሳይንስ ነው ማለትም ፣ በሰዎች መካከል የምጣኔ — ሀብታዊ ግንኙነት ። በሰብዓዊ ሕብረተሰብ ውስጥ ባለው የተለያዩ የዕድገት ደረጃ ምርትን ሥርዓት የሚያሲዘውንና ቁሳዊ ሀብት የሚከፋፈልበትን ሕግ ይገልጻል ። ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ስለ ሕብረተሰብ ዕድገት መሠረት ጥናት ነው ።

ከዚህ የፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ትምህርት ምንነት በመነሳት ታሪካዊ ሳይንስ እንደሆነ ግልጽ ይሆንልናል ። ሕብረተሰብ ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛው ደረጃ እንዴት እንደሚአድግ ፣ እና የታሪካዊ ዕድገት ጠቅላላ ጉዞ እንዴት ለኮሚኒስት ሥልተ— ምርት ድል መንገዱን እንደሚጠርግ ያሳያል ።

ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ መደባዊ ፣ ቡድናዊ ሳይንስ ነው ፣ በሰዎችና በመደቦች መካከል ስላሉት ግንኙነቶች በእነዚህም ዐይነተኛ ዝንባሌ ውስጥ በሚነሱት ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል ።

የካፒታሊዝም መውደቅና የሶሻሊዝም ድል ማድረግ የማይቀር ነውን ? የቡርዧ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ በመሠረቱ ለዚህ ጥያቄ ጸር የሆነ መልስ ነው የሚሰጠው ፣ የሚወክለው የካፒታሊስቱን ዝንባሌ ነውና ።

የቡርዧ ኤኮኖሚስቶች ይነስም ይብዛ የቡርዧው መደብ አዳጊና የካፒታሊዝም ዕድገትም ከሕብረተሰቡ የዝንባሌ ርምጃ ጋር እስከነበረ ድረስ ዓለምን ተንትነዋት ነበር ። ይህ የተወሰነው አንድ ጊዜ የቡርዧው ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ታላላቅ ኤኮኖሚስቶችን እንደ አዳም ስሚዝና ዳዊት ሪካርድ ያሉትን ፣ በቡርዧ ሕብረተሰብ ውስጥ ያሉትን የምርት ግንኙነቶች በሳይንሳዊ መንገድ የተነተኑትን ፣ በማስገኘት ላይ ነው ። ግን ያ ጊዜ ካለፈ ረጅም ነው ። ወዲያውኑ ሠራተኛው መደብ ቡርዧዎቹን የሚጻረር ነጻ የሆነ መደብ ሆነ ፣ እናም የመደብ ትግሉ ዕድገት የካፒታሊዝምን መደርባት የሚአንገዐብበትን ደረጃ እንደደረሰ ፣ የቡርዧ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ሳይንሳዊ ጸባዩውን እንዳጣ አሳዬ ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ቡርዧዎቹ ባመቸው መንገድ ሁሉ ጊዜው ያለፈበትን የካፒታሊስት ሥርዓት መጠበቅ ፣ የሠራተኛውን መደብ ርዕዮተ — ዓለም መዋጋት ተግባሩ ሆነ ።

የሠራተኛው መደብ መሪዎች — ማርክስ ፣ ኤንግልስና ሌኒን — እውነተኛ በሆነ ሳይንሳዊ መሠረት ፖለቲካዊ ኤኮኖሚን አዳበሩ ።

1. ቪ. አይ. ሌኒን ፣ ጠቅላላ ሥራዎች ፣ ቅጽ 3 ሞስኮ ፣ ገጾች 62-63.

የማርክስ የዕድሜ ሙሉ ሥራው ፡ ካፒታል ፡ ከሌኒን በፊት በማርክሲዝም ለፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የተደረጉትን አስተዋፅዖዎች የያዘ ነው ። ይህ ሥራ የተመሠረተው የካፒታሊስትን ሥርዓት ጠልቆ በመተንተን ላይ ሆኖ በሳይንሳዊ መንገድ የካፒታሊዝምን መደርባትና የኮሚኒዝምን ድል ማድረግ ያረጋግጣል ።

በአዲስ ታሪካዊ ሁኔታዎች ሌኒን የማርክስንና የኤንግልስን ሥራ ቀጠለና ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ለከፍተኛ ደረጃ አደረሰው ። ሌኒን ያበረከተው ትልቁ ግል ጋሎት ለከፍተኛውና ለመጨረሻው የካፒታሊዝም ደረጃ ፡ ኢምፔሪያሊዝም ሳይን ሳዊ ትንተና ማቅረቡ ነው ። የእርሱ ስለ ኢምፔሪያሊዝም ትንተና እና ፡ ከሁሉም በፊት ፡ በኢምፔሪያሊዝም ዘመን የካፒታሊዝም ያልተሟላ (ያልተስተካከለ) ምጣኔ — ሀብታዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ሕግ ማግኘት ለአዲሱ የወዛደሩ አብዮት ንድፈ — ሀሳብ መሠረት ጣለ ።

ሌኒን ፡ በመጀመሪያ አብዮት በአንድ አገር ውስጥ ወይም በጥቂቶች ድል እንደሚአደርግ አሳዬ ። ለታላቁ የጥቅምት የሶሻሊስት አብዮት ዝግጅትና አብዮቱን የማካሄድ ጉዞ ፡ እናም በሶቪየት ሕብረት ለሶሻሊዝም ድል ለተደረጉት ተከታታይ ትግሎች ፡ ጠቅላላ ስትራቴጅውና ታክቲኩ የተመሠረተው በዚሁ ላይ ነበር ። የሶሻሊዝም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ « ሌኒን » ከሚለው ስም ጋር የተያያዘ ነው ።

የማርክሲስት — ሌኒኒስት ምጣኔ — ሀብታዊ ንድፈ — ሀሳብ እየተገነባ ያደገው በሶቪየት ሕብረት የኮሚኒስት ፓርቲና በሌሎች አገሮች የኮሚኒስትና ሠራተኛ ፓርቲዎች ውሣኔ ፡ እናም በሌኒን ሥራዎች ደቀ — መዝሙሮች ነው ። የማርክሲዝም — ሌኒኒዝም ጥበባዊ ዕድገት ምግሴ በአጠቃላይ ፡ እና የማርክሲስት ሌኒኒስት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በተለይ የሚገኘው ፡ የሶቪየት ሕብረት የኮሚኒስት ፓርቲ 22ኛ ስብሰባ ላይ በተካሄዱት እንዲህ ዓይነት በሆኑ አይነተኛ ጥያቂዎች፤እንደ ሁለቱ ደረጃዎች የኮሚኒስት ሕብረተሰብና የሶሻሊዝምን ወደ ኮሚኒዝም ማደግ ስለሚገዙት ሕጐች ፡ የኮሚኒዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት መፈጠር ፡ የዕድገት ጐዳናዎችና የሁለቱ ዓይነት የሶሻሊስት ንብረት ባንድነት መምጣት ፡ የመደብ ልዩነት መወገድና የሕብረተሰብ ዕኩልነት መቋቋም ፡ የኮሚኒስት ሕብረተሰብ ግንኙነቶች መመሥረት ፡ የኮሚኒዝምን መሠረታዊ መርኅ (ብሒል) በተግባር የማዋል ሁኔታ — « ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ፡ ለእያንዳንዱ እንደፍላጐቱ » ፤ የባሕላዊ አብዮት መጠናቀቅና የአዲሱ ሰው መቀረፅ አሠራር ላይ ነው ። ወደ ሶሻሊዝም በመሸጋገር ጊዜ ስላሉት የሕብረተሰብ ፖለቲካዊ ድርጅት ችግሮች እዚሁ በደንብ ተብራርተዋል ።

የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ዓይነተኛነት ታዲያ እምኑላይ ነው ?

ሠራተኛውን መደብና ሁሉንም ሠራተኛ ሕዝብ በሕብረተሰብ ምጣኔ-ሀብታዊ ዕድገት ሕጐች ያስታጥቃል ፡ እናም የሚገጥሟቸውን ችግሮች በትክክል ለመወጣት ያስችላቸዋል ። በካፒታሊስት አገሮች ላሉ ሠራተኛ ሕዝቦች የባርነታቸውን ፡ የድህነታቸውንና የእርዛታቸውን ምክንያት ይጠቁማቸዋል ። የሠራተኛው መደብና ባጠቃላይ የሠራተኛው ሕዝብ ጭቆናና ድህነት ድንገታዊ እንዳልሆኑ ፤ ከግለሰብ ካፒታሊስቶች አምባገነናዊ አገዛዝ ሳይሆን ፤ ግን ባጠቅላይ በካፒታሊስት ሥርዓት እንደሆን ያሳያል ።

በምጣኔ — ሀብት ባልዳበሩ አገሮች ያሉ ሰዎችን ማርክሲስት — ሌኒኒስት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ኋላ — ቀርና ድሀ የሆኑበትን እውነተኛ ምክንያት ይጠቁማል የጥገኛና የቅኝ ግዛት ሕዝቦች ጭቆናና ዝርፊያ የመ... ው በኢምፔሪያሊዝምና በ... ኛዊ ሥርዓት መሆኑን ያሳያል ። ለዘመናት እፍኝ ... ሙሉ የኢምፔሪያሊስት አገሮች በኃይልና በማታለል ፡ በቅኝት ውስጥ ያለው ... ፡ ሰፊ ሕዝብ በተገዥነት በማቆየት



ወደባርነት ሁኔታ ዝቅ አድርገውታል ። ከኢምፔሪያሊዝምና እሱን ከሚአንጸባርቁ ሁኔታዎች ሁሉ ጋር ወሳኝ የሆነ ትግል በማካሄድ ብቻ ነው ለእነዚህ ሕዝቦች ለብሔራዊ አርነታቸውና ርምጃቸው መንገድ የሚአስገኝላቸው ።

ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ከካፒታል (ወረት) ቀንበር ራሳቸውን ነጻ ያወጡ አገሮች ሶሻሊዝምንና ኮሚኒዝምን ለመገንባት የሚወሰደውን አቅጣጫ ያሳያል ፤ የሶሻሊስቱ በካፒታሊስቱ ምጣኔ—ሀብታዊ ሥርዓት ላይ ያለውን ጥቅም ግልፅ ያደርጋል ፤ እናም ኮሚኒዝም የማይቀር መሆኑንም ያረጋግጣል ። የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሕጐች ዕውቀት ከሚኒዝምን በመገንባት ላይ ሰፊው ሕዝብ በንቃት እንዲሳተፍ ሰፊ እና አመቺ ሁኔታዎችን ይከፍትለታል ።

ም ዕ ራ ፍ ፩

# ቅድመ - ካፒታሊስት ሥልተ - ምርቶች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለጥንታዊ — ጋርዮሽ ፡ ባሪያ — አሳዳሪውና መልከኛው ሥልተ — ምርቶች አመጣጥ ፡ ዕድገትና ውድመት ባጭሩ እንመለከታለን ።

## 1. የጥንታዊ ጋርዮሽ ሥልተ - ምርት

በመሬት ላይ ሕይወት መኖር የጀመረው በግምት ከ900 ሚሊዮን ዓመታት በፊት ነው ፡ ግን የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የታዩት ከአንድ ሚሊዮን ዓመታት ወዲህ ነው ።

የመጀመሪያው የሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ መቅረጽ ብዙ መቶ ሺ ዘመናት ያሳለፈው የጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት ነበር ። የሰብዓዊ ሕብረተሰብን መምጣት አስመዘገበ ። በመጀመሪያ ሰዎች ግማሽ አረማዊ ፡ የተፈጥሮ ኃይል ለመቋቋም ብቁ ያልሆኑ ነበሩ ። ተፈጥሮ አደግ ፍራፍሬዎችን ፡ ጠንካራ ፍሬዎችን (nut) ሥራሥሮችን ወዘተ . . በመሰብሰብ በመጀመሪያ በተክሎች ምግብነት ኖረዋል ።

የሰው የመጀመሪያ መሣሪያዎች ገርደፍዳፋ የደንጋይ ስባሪዎችና ዱላዎች ነበሩ ። በኋላ ፡ ቀስ በቀስ ገጠመኝ በማጠራቀም ፡ ሰዎች ለመምቻ ፡ ለመቁረጫና ለመቆፈሪያ የሚሆኑትን ቀላል መሣሪያዎች መሥራት ተማሩ ።

የእሳት መገኘት የጥንታዊ ሰዎች ካላቸው የተፈጥሮ ጋር ትግል ከፍተኛ ዓይነተኛነት ነበረው ። እሳት በምግባቸው ላይ የተለያየን ምግብ ለማቅረብ አስቻላቸው ። የቀስትና የፍላፃ መሠራት የተግባር መገልገያዎችን ለማሻሻል አዲስ ምዕራፍ ነበር ፤ ማለትም የጥንታዊ ሕብረተሰብን የምርት ኃይል ለማሳደግ ። እናም ሰዎች ፤ ሥጋቸው ለመጀመሪያው ምግባቸው ጠቃሚነትን የጨመረላቸውን እንስሳት (የዱር) ለማደን ችለው ነበር ። የአደን ዕድገት የጥንታዊ ከብት ርባታን አመለከተ ። አዳኞች እንስሳትን ማልመድ ጀመሩ ።

የእርሻ መምጣት በምርት ኃይሎች ዕድገት ውስጥ መጠቅ ያለ ታላቅ ዝላይ (ርምጃ) ነበር ። ለረጅም ጊዜ ፍጹም ኋላ — ቀር ሆኖ ቆይቷል ። በድርቅ ተግባር ከብቶችን መጠቀም የእርሻ ሥራን ይበልጥ ምርታማ ሲአደርገው እርሻም ጠንካራ መሠረት ጠየቀ ። ጥንታዊ ሰዎች በአንድ ቦታ የመስፈርን ኑሮ መጠቀም ጀመሩ ።
በጥንታዊ ሕብረተሰብ የምርት ግንኙነቶች የሚወሰኑት በምርት ኃይሎች

ሁኔታ ነበር ። የምርት ግንኙነቶች መሠረት የጥንታዊ የተግባር መገልገያዎች ፤ የም
ርት መገልገያዎች ሕዝባዊ ንብረትነት ነው ። የጋርዮሻዊ ባለቤትነት ከምርት ኃይ
ሎች የዕድገት ደረጃ ጋር ተጣማ ። የተግባር መገልገያዎች እንደነገሩ ስለነበሩ ጥን
ታዊውን ሰው በተናጠል ከተፈጥሮ ኃይሎችና ከዱር እንስሳት ጋር ለመታገል አላ
ስቻሉትም። ስዎች በቀበሌ በአንድነት መኖርና በጥምረት ኢኮኖሚያቸውን ማካሄድ
(አደን ፣ እሣ ማጥመድና ምግብ ማዘጋጀት) ነበረባቸው ።

ከምርት መገልገያዎች ጋርዮሻዊ ባለቤትነት ጐን ለጐን ግለሰባዊ ንብረት
ነበር ። ይህ የተግባር መገልገያዎችን ከተናካሽ አውሬዎች ለመከላከል በሚጠቀ
ሙባቸው ግለ — ሰብ የቀበሌ አባላት የመያዝ መልክ ሰጠ ።

በጥንታዊ ሕብረተሰብ የጉልበት አምራችነት በጣም ዝቅተኛ ነበርና ለሕይ
ወት ከሚአስፈልገው ውጭ ትርፍ ለማምረት አላስቻለም ። ሥራ የተመሠረተው
በቀላል ሕብረት ፤ ብዙ ሰዎች አንድ ዓይነት ሥራ በመሥራት ነው ። የሰዎች በሰው
ብዝበዛ አልነበረም ፣ ከእጅ ወደፍ የነበረው የምርት አከፋፈል (በቀበሌው አበላት
መከካል) በእኩልነት መሠረት ነው ።

ሆኖም አሁንም ሰው ከእንስሳት ዓለም ገና እየወጣ ነበር ፣ ሰዎችም በቡድን
ኖሩ ፣ ተከትሎም ከጋራ ምጣኔ — ሀብት መምጣት ጋር የሕብረተሰቡ የጐሣ ቅን
ጅት ቀስ በቀስ ወደ ሕልውና መጣ ፣ ዘመዳሞች ብቻ ለአንድ ዓይነት ሥራ የተባበ
ሩበት ማለት ነው ። በመጀመሪያ ጐሣው ከጥቂት ደርዘን ዘመዳሞች ያልበለጠ የያዘ
ነበር ፣ ግን ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ብዙ መቶዎች ደረሰ ። የተግባር መገልገያዎች እን
ደዳበሩ ፣ በጐሣው ውስጥ ተፈጥሮአዊ የሥራ ክፍፍል ታዩ — በወንዶችና በሴቶች
በጉልማሶች ፣ በሕጻናትና በመበለቶች እና ሽማግሌዎች ። ወንዶች ራሳቸውን ወደ
አደን አሰማሩ ፣ ሴቶች ግን በአትክልት ምግቦች ፣ እናም ይህ የተወሰነ የጉልበት
አምራችነትን አሳደገ ።

ከከብት ዕርባታና እርሻ ዕድገት ጋር የሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍል ታዩ ፣
አንድ የሕብረተሰብ ክፍል በእርሻ ላይ እና ሌላው ደግሞ በከብት እርባታ የተከማ
ቹበት ። የከብት ዕርባታ ከእርሻ መለየት በታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ዋና የሕ
ብረተሰብ የሥራ ክፍፍል ነበር ።

ይህ ወደ ከፍተኛ አምራችነት መራ ። ስለዚህ ጥንታዊ ቀበሌዎች አንዳንድ ምር
ቶች በብዛት ሲኖሯቸው የሌሎች ደግሞ እጥረት ነበር ። ከብት አርቢዎች ፤ ነጋዴ
ዎችና በእርሻ ሥራ ላይ የተሠማሩት ምርት መለዋወጥ ቀጠሉ ። ጊዜ እያለፈ ሲሄድ
ሰዎች ብረታ ብረትን ማቅለጥ ጀመሩ — መዳብና ቆርቆሮ (ብረት ማንጠር በኋላ
ነው የታወቀው) እናም የነሐስ ተግባር መገልገያዎችን ጦር መሣሪያዎችና ቁሳቁ
ሶች ፣ የእጅ ማጠንጠኛ ማለትም የጥጥና ልብስ ምርት ። ስለዚህ ፣ አንዳንድ የቀበ
ሌው አባላት በግላቸው ሥራ ላይና በሠራቸው ዕቃዎች ላይ ማተኮር ጀመሩና ይበ
ልጥ ልውውጥ እያደገላቸው ሄደ ።

ከምርት ኃይሎች ዕድገት ጋር ፣ የሰው ጉልበት አምራችነትና በተፈጥሮ ላይ
ያለው ኃይሉ በደንብ አደገና የሚፈልጋቸውን ነገሮች ይበልጥ ለማርካት ቻለ ። ግን
የሕብረተሰቡ አዲስ የምርት ኃይሎች ከእንግዲህ ወዲያ ባለው ጠባብ የምርት ግን
ኙነት ውስጥ ያለምንም እንከን አያድግም ። የጋርዮሻዊ ባለቤትነት ተፈጥሮአዊ
ክልልና የጉልበት ውጤት በእኩል መከፋፈል የምርት ኃይሎችን ዕድገት እየገታው
ሄደ ። ጥምር ጉልበት ከእንግዲህ አስፈላጊ አልሆነምና የግለሰብ ሥራ ፍላጎት ተነሳ
ምክንያቱም የኋለኛው የበለጠ ምርታማ ስለሆነ ፣ ጥምር ሥራ የምርት መገልገያ
ዎችን ጋርዮሻዊ ንብረትነት ሲጠይቅ ፣ ግለሰባዊ — ሥራ የግል ባለቤትነትን ጠራ ፣
የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ብቅ አለ ፤ ከእርሱም ጋር በሰዎች መካከል



የንብረት መበላለጥ ተከሰተ — በሁሉም በጐሣዎችና በጐሣዎችም ውስጥ ። አሁን
ሀብታሞችና ድሆች ሰዎች መጡ ።

ከምርት ኃይሎች ራቅ ያለ መስፋፋት ጋር ፣ ሰው ለራሱ አውሎ ከሚአሳድ
ረው በላይ ማምረት ጀመረ ። በእነዚህ ሁኔታዎች ለአንዳንድ ሰዎች በቤተሰ
ባቸው ውስጥ ሌሎችን ሰዎች ለማሠራት አስቻላቸው ፣ ይህ የሆነው የእነርሱም
ጉልበት ትርፍ ምርት የሚአስገኝ በመሆኑ ነው ። ይህ ምርት ሊከማችና በቤ
ተሰቡ ውስጥ ለማይመረት ምርት መለወጥ ችሏል ። እንዲህ ዓይነት ሠራተ
ኞች የተገኙት በጦርነት ነው—የተማረኩ እሥረኞች ባሮች ሆኑ ። በመጀመሪያ
ባርነት በቤተሰብ ደረጃ ነበር ፣ ግን በኋላ ለአዲሱ የሕብረተሰብ ሥርዓት መሠረት
ሆነ ። የባርነት ሥራ ወደከፍተኛ መበላለጥ መራ ፣ በባሮች የሚጠቀሙ ቤተሰቦች
በፍጥነት ሀብታም ሆኑ ። ከንብረት ያለመመጣጠን ዕድገት ግንኙነት ጋር ፣ ሀብታ
ሞች እሥረኞቹን ብቻ ሳይሆን ባሪያ ያደረጉት ፣ ግን በድህነት ወይም በዕዳ ውስጥ
የገቡ የራሳቸውንም የጐሣ አባላትንም ነው ። ከዚያ የመጀመሪያው የሕብረተሰብ
በመደብ መከፋፈል ተከተለ ፣ በባሪያ አሳዳሪና በባሪያው መከፋፈል ። ይህ ነው
የሰው በሰው ብዝበዛ መጀመሪያ ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ፣ ሶሻሊዝም እስከሚገነባ ፣
የሰዎች ጠቅላላ ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ ነበር ፣ በበዝባገዦችና በተበዝባገዦች
መካከል ያለትግል ።

በሰዎች መካከል የመበላለጥ ዕድገት የተበዝባገዦችን መደብ በበዝባገዦች እን
ደመጨቆኛ አካል የሆነውን የመንግሥትን መመሥረት አመለከተ ። ስለዚህ ባር
ነት በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥልተ — ምርት ፍራሺ ላይ አቆጠቆጠ ።

## 2 የባሪያ አሳዳሪ ሥልተ—ምርት

ባርነት የመጀመሪያው ፣ በታሪክ ውስጥ ጨካኝ ግልጽ የሆነ ብዝበዛ ነው ።
በአጠቃላይ በሁሉም ሕዝቦች መካከል ኖሯል ።

ከጥንታዊ — ሕብረተሰብ ወደ ባሪያ አሳዳሪው ሽግግሩ የተካሄደው በምርት
ኃይሎች ከፍተኛ ዕድገት ነው ፣ በሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍል ዕድገትና ልውውጥ
መሠረት ።

የብረት ማንጠርን ምስጢር በማወቅ ፣ የብረት የተግባር መገልገያዎች በባር
ነት ዘመን ጊዜ የበላይ መሆን ጀመሩ ። የብረታ ብረት መሣሪያዎች የሰዎችን ሥራ
ቢጋር (Frame work) አስፋት ። ለምሣሌ የብረት ምሣርን በመጠቀም ፣ ደንጣ
መሬትን በመመንጠርና ቁጥቋጦ በመቁረጥ ለእርሻ ለማዘጋጀት አስቻለ ፣ በእን
ጨት እርፍ ከብረት ማረሻ ጋር ሰፊ ማሳ ማረስ ተቻለ ። እርሻ ሰዎችን ያገለገለው
በአትክልትና በዳቦ ብቻ ሳይሆን ፣ ግን በወይን ፣ በአትክልት ዘይትም ጭምር ነው ።
የብረታ — ብረት ዕቃዎች መሠራት ልዩ የሠራተኛ ቡድኖችን መከሰት አስገኘ —
ሙያቸው ነጻ የሆነ የሥራ መስክ መሆኑን እየጨመረ የሄደው የእጅ ጥበበኞች ።
የእጅ ጥበበኞች ከእርሻ ተለዩ ። ይህ ነበር ሁለተኛው ዓይነተኛ የሥራ ክፍፍል ።

ከምርት በሁለት መሠረታዊ ቅርንጫፎች መከፋፈል ጋር ፣ የጉልበት ውጤት
ልውውጥ ዳበረ ። ልውውጥ ቀዋሚ የሆነ ክስተት ሲሆን ፣ ገንዘብ ተከሰተ ። ገንዘብ
የሌሎች ሁሉ ሸቀጦች እሴት የሚለካበትና በሸቀጥ ልውውጥ ጊዜ እንደአማካይ ሆኖ
የአገለገለ ሁለንታዊ ሸቀጥ ሆነ። የሥራ ክፍፍልና የልውውጥ ማደግ ሥራቸውን
ሸቀጥ መግዛትና መሸጥ ያደረጉ ሰዎችን አሳዩ — ነጋዴዎችን ። የነጋዴዎች መም
ጣት ሶስተኛው ዋና የሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍል ሆነ ። የአንዳንድ አምራቾች
ከገበያ ያላቸውን ርቀት በመጠቀም ፣ ነጋዴዎች ሸቀጦቻቸውን በዝቅተኛ ተመን
ገዝተው ለተጠቃሚው በከፍተኛ ተመን ይሸጣሉ ።

ከተሞችን ወደ መቆርቆሩ መራ ። በመጀ
የእጅ ሥራዎችና የልውውጥ ማደግ መሪያ ከተማን ከመንደር ለመለየት አስቸጋሪ ነበር ፣ ግን ቀስ በቀስ የእጅ ሥራዎችና ንግድ በተከማዎች ውስጥ ተበራከቱ ። ይህ ነበር የከተማና የገጠር መለያየት መጀመሪያ ።

የምርት ኃይሎችና ሰፋ ያለ የሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍልና ልውውጥ መስፋፋት የንብረት አለመመጣጠንን አጠናከረው ። የከብት መንጋ ፣ የተግባር መገልገያዎችና ገንዘብ በሀብታሞች እጅ ተጠራቀመ ። ስለሆነም ፣ ድሆች ፣ ይበልጥ ወደድህነት እያሽቆለቆሉና በማከታተል ለመበደር ሲሉ ወደ ሀብታሙ ፊታቸውን እንዲአዞሩ ተገደዱ ። ስለዚህ ከአበዳሪና ከተበዳሪ ጋር አራጣ ብቅ አለ ። « የጥንቱ ዓለም የመደብ ትግሎች በተለይ በአበዳሪና በተበዳሪ መካከል ያለ የይዘት ቅርፅ ለብቻው ይሁን ይህ በሮማ በፕሌብያን ተበዳሪዎች መደምሰስ አልቋል ። በባሮች ተተክተው ነበር ።»1 ግዙፍ የባሪያ አሣዳሪ ምጣኔ—ሀብት ተከሰተ ። ሀብታም ባሪያ አሳዳሪዎች በመቶና በሺ የሚቆጠር ባሪያ ፈለጉ ። ትላልቅ ኩዳድ በመሥራትና በእነዚህም ላይ ብዙ ባሮችን በማሠራት ሰፋፊ መሬቶች ያዙ ። በጥንታዊት ሮማ እነዚህ ላቲፋንዲያ ተብለው ይጠሩ ነበር ።

በባሪያ ሥርዓት ውስጥ የምርት ግንኙነቶች የተመሠረቱት በባሪያ አሣዳሪው ሁሉንም የምርት መገልገያዎች (መሬት ፣ የተግባር መገልገያ መሣሪያዎችን ወዘተ...) እና በምርት ሥራ ላይ የተሠማሩትን ሰዎች የንብረት ባለቤት በመያዝ ላይ ነው —ባሮችን ። ባሪያው እንደተንቀሳቃሽ ዕቃ ይቆጠራል ፣ ሙሉ በሙሉ የጌታውና በጌታው ቁጥጥር ሥር ብቻ ነበር ያለው ። ባሪያው « የሚናገር ዕቃ » ተብሎ ነበር የሚታወቀው ። በባሪያ አሣዳሪዎች ዓይን ፣ ባሪያው ከበሬ ወይም ከምሣር የሚለየው ለመናገር በመቻሉ ብቻ ነው ። በሌላው ሁኔታ እንደለማዳ እንስሳ ፣ ቤት ፣ መሬትና የተግባር መገልገያ ሁሉ ሙሉ በሙሉ የጌታው ንብረት ነው ።

የባሮች ብዝበዛ ፅንፋዊ የሆነ የጭካኔ መልክ ያዘ ። እንደከብቶች እንኳን አይታዩም ነበር ። እንዲሠሩ በጅራፍ እየተነዱና በትንሽ ጥፋት በጭካኔ እየተቀጡ ወይም እየተገደሉም ነበሩ ። ጌታው ባሪያውን በመግደሉ አይጠየቅም ። የጉልበት ውጤቱን በሙሉ ይወስድበታል ። ባሪያው ነፍሱን አውሎ ለማሳደር እንዳይሞት ብቻ እና ለጌታው መሥራቱን እንዲቀጥል የሚአስችለው ይሰጠዋል ።

የጥንቱ ዓለም በባሪያ ጉልበት ላይ በመመሥረት በባሕልና በምጣኔ — ሀብት ይህ ነው የማይባል መሻሻል አግኝቷል ። የተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች — ሂሣብ ፣ አስትሮኖሚ ፣ ሜካኒክስ ፣ ጥርብ — በከፍተኛ ደረጃ ዳብረዋል ። ይሁንና ፣ የባሪያ አሳዳሪው ሥልተ-ምርት ለሰዎች የዕድገት ጉዳና ደንቃራ ሆኖ ነበር ፣ ከጥንታዊ ጋር ዮሽ ጋር ሲወዳደር በፈጸማቸው ሁኔታዎች ምክንያት ማለት ነው ።

የባሪያ አሣዳሪው ሥልተ — ምርት ለጥፋቱ ባመራት ጥልቅና ሊወጣቸው በማይችላቸው ቅራኔዎች የተሞላ ነበር ። ከሁሉም የባሪያ አሳዳሪው የብዝበዛ መልክ « ባሮች » ተብለው የሚጠሩትን የሕብረተሰቡን መሠረታዊ የምርት ኃይል ሳያቋርጥ አጥፍቷል ። ባሮች በማከታተል ርህራኄ የሌለውን ብዝበዛ በመቃወም አምጸዋል ። ያልተቋረጠ የባሮች መጉረፍ ለባሪያ አሳዳሪ ምጣኔ — ሀብት የሕልውና መግለጫ ነው ። ባሮች ከሌላ መንግሥት ጋር በሚያረግ ግቡን የመታ ጦርነት ድል ያገኙ ነበር ። ገበሬዎች ፣ የእጅ ባለሙያዎች ፣ የጦርነቱ መሽከርከሪት የጀርባ አጥንት ነበሩ ፣ እነሱ ነበሩ እንደወታደር ሆነው የሚአገለግሉና ጦርነቱን ለማካሄድ ከባዱን የግብር ሸክም የሚከፍሉት ። ግን በርካሽ የባሪያ ጉልበት ላይ በተመሰረተ የከፍተኛ ምርት ውድድር ምክንያት ፣ ገበሬዎችና የእጅ ባለሙያዎች ጠፉ ። ይህ የባሪያ አሣዳሪውን መንግሥት የምጣኔ — ሀብቱን ፣ የፖለቲካውንና የወታደራዊውን ጥንካሬ ሕይወት አዳከመው ። ድል — ማድረግ ለድል መሆን ቦታ ሰጠ ። ያልተቋረጠ ርካሽ የባሪያ ጉልበት ይሰጥ የነበረው ምንጭ ደረቀ ። ይህ በጠቅላላ አጠቃላይ የምርት ውድቀት አመጣ ።

« ሁለንታዊ የሆነ ድህነት ፣ የንግድ ፣ የእጅ ሥራዎች ፣ የኪነት ፣ እና የሕዝቡ ማሽቆልቆል ፣ የከተሞች መውደቅ ፣ የእርሻ ወደዝቅተኛ ደረጃ መውረድ — ይህ ነበር የሮማውያን ዓለም የበላይነት የመጨረሻ ውጤት ። 1

በመጀመሪያ ሲጀምር ፣ የባሪያ አሣዳሪው ሥልተ — ምርት ለምርት ኃይሎች አስተዋፅኦ ነበረው ። ግን ከፍተኛ ዕድገቱ ፣ እንዳየነው ፣ ለምርት ኃይሎች መውደም ምክንያት ሆኗል ። በባሪያ ጉልበት ላይ የተመሠረቱ የምርት ግንኙነቶች በሕብረተሰቡ የምርት ኃይሎች ዕድገት ላይ እንደእንቅፋት ሆነው ሠርተዋል ። የባሮች ጉልበት በምንም መንገድ በምርት ውጤት ላይ ፍላጎት በሌላቸው ፣ ራሳቸውን ለብዙ ጊዜ አቆይቷል ። የባሪያ አሳዳሪ የምርት ግንኙነቶችን በሌሎች ለመተካት ታሪካዊ አስፈላጊነቱ ተነስቷል ፤ የሕብረተሰቡን ዋና የምርት ኃይል ሁኔታ የሚለውጥ መሆኑ ነው — ባሮችን ።

በባሪያ ጉልበት ላይ ከተመሠረተው ትላልቅ ላቲፋንዲያ መውደቅ ጋር ፣ ትናንሽ ቤተሰቦች ይበልጥ ጥቅም ያላቸው ሆኑ ። ስለዚህ ፣ ነጻ የወጡ ባሮች ቁጥር በረከተ ፣ እና ወዲያውም ትላልቅ ኩዳዶች በትናንሺ ማሳዎች ተከፋፍለው በገባሮች ታረሱ ። ገባር ከእንግዲህ ባሪያ አይደለም ፣ ማሳውን ለኑሮ እንዲጠቀምበት ዋስትና የተሰጠው መሬትን የሚአርስ ፣ ለዚሁ (ለመሬቱ) የተወሰነ ገንዘብ (እሕል) ለመክፈል የሚገደድ ነው ። ነጻ ጭሰኛ አይደለም ፤ ከመሬቱ ጋር የተሳሰረ ሊተወውም የማይችል ነው ፣ ግን ከማሳው ጋር አብሮ ሊሸጥ ይችላል ። ኮሎኒዎች የመካከለኛው ገባሮች አባቶች (ቀዳሚዎች) ናቸው ።

ስለዚህ ፣ በአሮጌው ሥርዓት ውስጥ ፣ አዲሱ የመልከኛ ሥልተ — ምርት ቅርፅ መያዝ ጀመረ ።

የባሪያ አሣዳሪ ምጣኔ — ሀብት እንዳደገ ፣ ብዙኃኑ ባሪያ የሆኑት ሕዝቦች ጨቋኞቻቸውን በመጻረር ላይ ያለው የመደብ ትግል ተጠናከረ ። ይህ ትግል ባሮች በጌቶቻቸው ላይ በሚአደርጉት አመፅ ተቀጣጠለ ። የባሮችን ትግል የነጻ ገበሬዎችና የእጅ ባለሙያዎች (በትላላቅ መሬት ከበሬዎችና በባሪያ አሳዳሪው መንግሥት ይበዘበዙ የነበሩቱ) ተቀላቀሉት ። ከብዙዎቹ የባሮች አመፆች ፣ በስፖርታኩስ(74—71 ክ. ል. በፊት) የተመራው ዓይነተኛ ነበር ። የውስጠኛው ጡጫ ከውጨኛው ጡጫ ጋር በመዋሃድ በመጨረሻ የባሪያን ሥርዓት መጨማተርና መደምሰስ አመጣ።

1 ካርል ማርክስ ካፒታል ፣ ቅፅ 1 ፣ ሞስኮ ፣ ገፅ 135

1. ፍ. ኤንግልስ «የቤተሰብ የግል ንብረትና የመንግሥት ሥርዎ—አመጣጥ ማርክስና ኤንግልስ ፤ ምርጥ ሥራዎች ቅፅ 2 ሞስኮ ገጽ 299»

## 3. የመልከኛው ሥልተ - ምርት

በአንድ ዓይነት ጸባይ ወይም በሌላ ፣ በአብዛኞቹ አገሮች ውስጥ የመልከኛው ሥልተ — ምርት ኖሮ ነበር ። የመልከኝነት ዘመን ብዙ ጊዜ የወሰደ ነው ። በቻይና የመልከኛው ሥርዓት ከሁለት ሺ ዓመታት በላይ ኖሯል ። በምዕራብ አውሮጳ አገሮች መልከኝነት ለብዙ መቶ ዓመታት ሰፍኗል ፣ ከሮማ ግዛት መውደቅ ጀምሮ (5ኛው ምዕተ — ዓመት ) እስከ እንግሊዝና ( 17ኛው ምዕተ — ዓመት) ፈረንሳይ ( በ18ኛው ምዕተ — ዓመት) የቡርዧ አብዮት ድረስ ማለት ነው ። በሩሲያ ከ9ኛው ምዕተ — ዓመት ጀምሮ ገባርነት እስከተወገደበት 1861 ዓ. ም. ድረስ ቆይቷል ።

የመልከኛ ሕብረተሰብ የምርት — ግንኙነቶች በመልከኛ መኳንንት የመሬት የግል ባለቤትነትና በገባሮች ላይ ባላቸው ግማሽ ባለቤትነት የተመሠረቱ ናቸው ። ባሪያ አልነበረም ፣ የራሱ የሆነ ይዞታ ነበረው ። ከመልከኛ መኳንንት ንብረት ጐን የገባሮችና የእጅ ባለሙያዎች ፣ የተግባር መገልገያ መሣሪያዎች ተብለው የሚጠሩበትና የግል ይዞታዎቻቸውም (መሬት) ንብረት ነበር ። የትናንሽ ገበሬዎች ምጣኔ— ሀብትና ነጻ የሆኑ የትናንሽ የዕጅ ባለሙያዎች ምርት የተመሠረቱት በግል ጉልበት ላይ ነው ። ሁሉም የዓይነት ነበር ፣ ማለትም ፡— ምርቶች በአጠቃላይ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ፍጆታ (ብሎት) እንጂ ፣ ለልውውጥ አልነበሩም ።

መሬት ነክ የሆነ የመልከኛው ከፍተኛ ንብረት ለገበሬዎች በመሬት መኳንንት መበዝበዝ መሠረቱ ነው ። የመልከኛው መኳንንት ጉልት የመሬቱን ከፊል ይይዛል ። ሌላውን ክፍል ገበሬዎች ከፍተኛ ኪራይ እየከፈሉ እንዲጠቀሙበት ይሰጣል ። የገበሬዎች ይዞታ የመሬት ከበርቴው የምርት ኃይሉን የሚአጠናክርበት መንገድ ነው ። በውርስ እየተዋረደ በሚሄደው ይዞታው ፣ ገበሬው ለመሬት ከበርቴው የራሱን መሣሪያዎችና ከብቶች በመጠቀም መሬቱን እንዲአርስለት (የጉልበት — ኪራይ ወይም የማይከፈልበት ቀን)* ወይም ለመልከኛው መኳንንት የምርቱን ከፊል በዓይነት (በምርት የሚከፈል ኪራይ ) ወይም ሁለቱንም ዓይነት ኪራይ እንዲከፍል ይገደዳል ። ይህ ዓይነት የምጣኔ — ሀብት ሥርዓት ጥርሱን ወደ አገጠጠ ብዝበዛ ብቻ አይደለም ያመራው ፣ ግን የገበሬውንም ሰብዓዊነት (አቋም) የመሬት ከበርቴው ጥገኛ እንዲሆንም ነው የአደረገው ። የመልከኛው መኳንንት ገበሬውን መግደል አይችሉም ፣ ግን መሸጥ አሌ አያሰኝም ።

የገባሮች የሥራ ጊዜ በአስፈላጊና በትርፍ ሰዓት ተከፍሏል ። በአስፈላጊው ሰዓት ፣ ገበሬው ለራሱ ሕልውና ለቤተሰቡ የሚሆነውን ያህል ያመርታል ። በትርፉ ሰዓት ለመልከኛው መኳንንት በኪራይ መልክ የሚከፍለውን (የጉልበት— ኪራይ ፣ የዓይነት ኪራይና የገንዘብ ኪራይ) ትርፍ ምርት ያስገኛል ። የገበሬዎች በመሬት ኪራይ መልክ በመልከኛው መበዝበዝ የመልከኝነት ዋና ገፅ ነበር ።

ከገጠሩ ሕዝብ ሌላ ፣ ከተማው የተመሠረተበት መሬት ባለቤት ለሆኑት መኳንንት ጥገኛ የሆኑት የእጅ ባለሙያዎችና ነጋዴዎች የሚገኙበት የከተማው ሕዝብ አለ ። ከተሜዎች ለነጻነታቸው ተዋግተው አሸንፈውም አግኝተዋል ።

የከተሞች ማደግና የንግድ መዳበር የገጠሬውን መልከኛ በሰፊው ተፅዕኖ አሳደረበት ። የመልከኛ መኳንንት ምጣኔ — ሀብት ወደገበያ ዝውውር ውስጥ መሳቡ እየጨመረ ሄዶ ነበር ። መኳንንቱ ድሎትን ለማግኘት ገንዘብ አስፈለጋቸው ። በዚህ ግንኙነት መሠረት ገበሬዎችን ከጉልበት — ኪራይና ከዓይነት ኪራይ ወደ ገንዘብ ኪራይ መለወጥ ጀመሩ ። የመልከኝነት ብዝበዛ ከገንዘብ ኪራይ መምጣት ጋር ይበልጥ እየተባባሰ ሄደ ፣ እኛም በመልከኛ መኳንንትና በገበሬዎች መካከል ያለውም ትግል የዚያኑ ያህል ጠፋ ።

---

* ገበሬዎች ለመሬት ከበርቴዎች በሳምንት በወር ወዘተ የተወሰነ ቀን ያለምንም ክፍያ የሚሠሩበት ነው ።



## 4. የመልከኝነት መሰባበርና መጨማተር ፣ የካፒታሊስት ግንኙነቶች በመልከኛው ሥርዓት ውስጥ መወለድ ።

በመልከኛው ሥርዓት ውስጥ የምርት ኃይሎች ከባሪያው ዘመን ይበልጥ ከፍተኛ ደረጃ ደርሰው ነበር ። የእርሻ የምርት ጥበብ ተሻሽሏል ፣ የብረት ማረሻና ሌሎችም የብረት የተግባር መገልገያ መሣሪያዎች ላቅ ባለ መልክ በጥቅም ላይ ውለዋል ። የተለያዩ የእርሻ ሥራዎች ብቅ ብለዋል ፣ የወይን ሥራ ፣ የወይን ተክልና ለገበያ የሚቀርቡ ተክሎች በከፍተኛ ደረጃ ዳበሩ ። የከብት ዕርባታና የእርሱ ጥገኛ ትርንጓሬች መሻሻሎች ተደርገዋል — የቅቤና የአይብ ምርት ። የድርቆሽና የግጦሽ አካባቢዎች ሰፍተዋል ፣ ተሻሽለዋል ።

ቀስ በቀስ የእጅ ባለሙያዎች የተግባር መገልገያዎችና ጥሬ ሀብቶችን የማምረት ዘዴ መሻሻል ተደርጎላቸዋል ። ዕደ — ጥበብ የተለዩ (ሙያ) ሆነ ። ጊዜ እየተጓዘ አዳዲስ ዕደ — ጥበቦች ተከሰቱ — የጦር መሣሪያ ሠራተኛው ፣ የምስማር ቀራጺው የቢላዋ ሰሪው ፣ የቁልፍ ጠበብቱ ፣ የጫማ ሰፊው ፣ የኮርቻ ሰፊው እና ሌሎችም ። ብረት የማቅለጥና የመሥራት ለውጥም ነበር ። የመጀመሪያው የብረት ማቅለጫ ምድጃ የተከሰተው በ15ኛው ምዕተ — ዓመት ነው ። ከፍተኛው የመልከዓ — ምድር አሰሳም ከዚህ ዘመን ላይ ነው የሚረከዘው ።

ግን የመልከኛው ሥርዓት ፣ ቀድሞውኑ አዲስ የምርት ኃይሎች በውስጡ የዳበሩበት ፣ ለከፍተኛ ዕድገታቸው መሰናከል ሆነ ፣ የምርት ኃይሎቹ ጠባብ ይዞት ቢጋራ) ካላቸው የመልከኛ የምርት ግንኙነቶች ጋር ተጋጩ ። ገበሬው ፣ በመልከኛው የብዝበዛ ቀምበር ሥር ያለው ፣ በምንም መንገድ የእርሻን ምርት በሚጨምርበት ደረጃ አልነበረም ፣ ምክንያቱም የገባር ጉልበት አምራችነት ዝቅ እያለ ሄዶ ነበርና ። በከተማ እየጨመረ የሄደው የእጅ ባለሙያዎች የጉልበት አምራችነት የሕብረት ድርጅቶች ( guild ) ሁኔታና ደንብ ድቅን ዕንቅፋቶች ገጠመው ። ይህ ሁሉ ተዳምሮ የአሮጌዎቹን ግንኙነቶች መወገድና ከመልከኝነት ሰንሰለት ነጻ የሆኑ የአዲስ ግንኙነቶችን መመሥረት ፍላጐት ጠቆመ በመልከኛው ሥርዓት ውስጥ የካፒታሊስት የምርት ግንኙነቶች መከሰት ጀመሩ ።

ከዚህም በላይ ፣ ቀላል የሸቀጥ ምርት ፣ ማለትም በግለ — ሰብ ጉልበትና በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረቱ ፣ ለልውውጥ የሚውሉ የሸቀጦች ምርት ቀስ በቀስ ተስፋፉ ። የሸቀጥ አምራቾች በከተማም ሆነ በገጠር በሀብታምና በድሃ መከፋፈል በአመራቸው በጠንካራ የውድድር ትግል ውስጥ ራሳቸውን አስገብተው አገኙት ። ከገበያ መስፋፋት ጋር ትልቁም ሆነ ትንሹ ሸቀጥ አምራች ከምንጊዜውም ይበልጥ ድህነት የገረፋቸውን ገበሬውች ወይም የእጅ ባለሙያዎች ለእርሱ እንዲሰሩለት ይቀጥራል ።

ካፒታሊዝምም በሌላ መንገድ አደገ ። የንግድ ካፒታል (ወረት) ነጋዴዎችን በመወከል ፣ በገበሬዎችና በእጅ ባለሙያዎች የተመሠረተውን ምርት በቀጥታ መቆጣጠር ጀመረ ። የንግድ ካፒታል (ወረት) በመጀመሪያ የተከሰተው በትናንሽ አምራቾች የሸቀጥ ልውውጥ ውስጥ እንደአማካይ (አዘዋዋሪ) ሆኖ ነበር ። በኋላ ነጋዴዎች ትናንሽ አምራቾችን ጥሬ ዕቃዎች በማቅረብና ገንዘብ አስቀድሞ በመስጠት ሥልታዊ የሸቀጥ ግዥአቸውን ጀመሩ ። እንዲህ ሆነና ትናንሽ አምራቾች የነጋዴዎች ምጣኔ—ሀብት ጥገኛ ሆኑ ። በንግድ ካፒታል (ወረት) የተወሰደው ሁለተኛ እርምጃ የተበታተኑትን የእጅ ባለሙያዎች በአንድ የሥራ ቦታ ባንድ ጣሪያ ሥር — የምንዳዕ

ሠራተኞች ሆነው በሚሠሩበት — ማምጣት ወይም መሰብሰብ ነበር ። ይህ የንግድ ካፒታል(ወረት) ወደ እንዱስትሪያዊ ካፒታልና (ወረት) ነጋዴውም ወደ ኢንዱስትሪያዊ ካፒታሊስት ተለወጡ ።

በገጠርም ካፒታሊዝም እያደገ ነበር ። ከሸቀጥ ምርት ዕድገት ጋር የገንዘብ ኃይል ጨመረ ። ገበሬዎች ለመልከኛ መኳንንቱ ከዓይነት ይልቅ በገንዘብ መክፈል ጀመሩ ። የገንዘብ ግንኙነቶች ዕድገት የገበሬዎችን በገጠሩ ቡርዧና በድህነት ማጥ ውስጥ ባለው ገበሬ ለመከፋፈል ኃይል ሰጡ ።

ስለዚህ ፤ የካፒታሊስቱ ምርት በከተማም ሆነ በገጠር በመልከኛው ሥርዓት ውስጥ ወደ ሕልውና መጣ ። የመልከኝነት መወገድ ታሪካዊ አስፈላጊነት ሆነ ።

የመልከኝነት አጠቃላይ ታሪክ በገበሬዎችና በመልከኛ መኳንንት መካከል የተካሄደ ከመራራ የመደብ ትግሎች አንዱ ነው ፤ ትግሉ በተለይ ትብ የሆነው የመልከኝነት ብዝበዛ ፍጹም በተጠናከረበት የመጨረሻ ዘመን ላይ ነው ። የገባር አመፆች የመልከኝነት ሥርዓትን መሠረቱን እናውጠው ወደ መጨረሻ ውድመቱ መሩት ። የጸረ—መልከኛውን ትግል ቡርዧዎች መሩትና የገባሮችን በመልከኞች ላይ አመፅ ሥልጣን ለመያዝና የገዥ መደብ ለመሆን ተጠቀሙበት ።

## የካፒታሊስት ሥልተ—ምርት

## ሀ ቅድመ ሞኖፖሊ — ካፒታሊዝም ።

### ም ዕ ራ ፍ ፩

### የሸቀጥ ምርት — ሸቀጥና ገንዘብ ፡

ማርክስ የካፒታሊዝም ትንታኔውን የጀመረው « በሸቀጥ » ነው ። በካፒታሊዝም ውስጥ ማንኛውም ነገር ፤ ከወረቀት መርፌ እስከ ግዙፉ ፋብሪካ ፤ የሰው የጉልበት ኃይልም እንኳን ፤ የሸቀጥ መልክ በመያዝ ይገዛል ፤ ይሸጣል ። በሕብረተሰብ ውስጥ በሰዎች መካከል ያሉ ግንኙነቶች የሚከሰቱት በሸቀጦች መካከል በሚደረጉ ግንኙነቶች ነው ። ሸቀጡ ፤ ማርክስ እንዳለው ፤ የቡርዧ ሕብረተሰብ የምጣኔ ሀብታዊ ሕዋስ ቅርፅ ነው ። አንድ የውሃ ጠብታ በአካባቢዋ ያለውን ዓለም እንደምታንፀባርቅ ሁሉ፤ሸቀጥ የካፒታሊዝምን ሁሉንም መሠረታዊ ቅራኔዎች ያንፀባርቃል

የማርክስ የሸቀጦችና የሸቀጥ ምርቶች ፍልፈላ የካፒታሊስትን የምርት ግንኙነቶች ባሕሪ እንዲአብራራ አስችሎታል ።

### 1 የሸቀጥ ምርት አጠቃላይ መግለጫ

የሸቀጥ ምርት ፅንሰ-ሀሳብ

የሸቀጥ ምርት ማለት ለግል መገልገያ ሳይሆን ፤ ለሽያጭ ፤ ለገበያ ልውውጥ የዕቃዎች መሠራት ነው ። « የሸቀጥ ምርት ሲባል » ፤ ይላል ሌኒን ፤ « በተለያዩ ፤ ለየብቻ በሆኑ ፤ እያንዳንዳቸው የተለዩ ምርትን በማምረት ጠበብት በሆኑ ሰዎች ዕቃዎች የሚመረቱበት ሕብረተሰብዊ (ሶሻላዊ) የምጣኔ ሀብት ድርጅት ሆኖ ፤ ስለዚህም የሕብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት በገበያ ውስጥ ምርቶችን መግዛትና መሸጥ (ስለዚህም በዚህ ምክንያት ሸቀጥ የሚሆኑበት) አስፈላጊ የሆነበት ነው ። » 1

የሸቀጥ ምርት አመጣጡ የጥንታዊ ጋርዮሻዊ ሥርዓት ከተበታተነበት ዘመን ጀምሮ ነው ፤ ምንም እንኳ ተራጥሮአዊ ምጣኔ — ሀብት በማንኛውም መልክ ገዥ

1. ቪ. አይ. ሌኒን፤ [illegible] ሥራዎች ቅጽ 1 [illegible] ገጽ 93



(የበላይ) ቢሆን ፤ በባሪያ አሳዳሪውና በመልከኛ ሥልተ — ምርቶች ውስጥ ነበር ። በዚህ ምጣኔ — ሀብት ውስጥ ሕብረተሰቡ አንድ ዓይነት የሆኑ ምጣኔ — ሀብታዊ ክፍሎችን የያዘ ነው ፤ እያንዳንዱ ሁሉንም ዓይነት ሥራ የሚአካሂዱበት ፤ የተለያዩ የጥሬ — ሀብቶችን ከማምረትና ከማግኘት ጀምሮ እነሱንም ከራሱ ብሎት (ፍጆት) እስከ መሥራት ጭምር ማለት ነው ። ይህ ዓይነት ምጣኔ — ሀብት ፤ በተለይ ትርፍ ምርት ለልውውጥ ይውል የነበረበት ፤ ካፒታሊዝም እስከገባ ድረስ ሰፍኖ ነበር ።

የካፒታሊዝም ማደግ (መምጣት) ለተፈጥሮዓዊ ምጣኔ — ሀብት ደምሳሺ ጡጫ ሰጠው ። በካፒታሊዝም ውስጥ ማንኛውም ነገር ፤ የሰውን ጉልበት ኃይል ጨምሮ ፤ የሸቀጥ መልክ ያዘ ። ከጉልበት ኃይል ወደ ሸቀጥ መለወጥ ጋር ፤ የሸቀጥ ምርት ገዥና ሁለንታዊ ሆነ ።

የሸቀጥ ምርት በካፒታሊዝም ውስጥ አንዱ የሰፈነ ዓይነት ምርት ከሆነ ፤ በምርት ሂደት ጊዜ በሰዎች መካከል ያሉት ግንኙነቶች ፤ ማለትም ፤ የምርት ግንኙነታቸው ፤ የሸቀጥ ግንኙነቶችን መልክ ነው የሚይዙት ። ይህን ለማብራራት ፤ በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ያለውን መሠረታዊ የምርት ግንኙነት እንውሰድ — የወዝ አደሩ በቡርገዮዋው መበዝበዝን ። ሠራተኛውን ለመበዝበዝ ፤ ካፒታሊስቱ እርሱን መቅጠር አለበት ፤ ሠራተኛው ግን አሁን ሸቀጥ የሆነውን የጉልበት ኃይሉን መሸጥ ይኖርበታል ። ካፒታሊስቱ ለሠራተኛው ምንዳስ ይከፍለዋል ፤ የኋለኛው ራሱን ለማኖር የሚአስችሉትን ዕቃዎች የሚገዛበትን — ሸቀጦችን ። ስለዚህ በሠራተኛውና በካፒታሊስቱ መካከል ያሉት የምርት ግንኙነቶች የሚገለጹት በቀጥታ ሳይሆን ፤ ግን በሸቀጦች አማካኝነት ፤ እና የሸቀጥ ግንኙነቶችን ጸባይ በመያዝ ነው ።

ካፒታሊስቶች ምርቶችን አንዱ ለአንዱ ይሸጣሉ እናም እርስ በእርሳቸው ጥሬ ዕቃ ፤ መሣሪያና ሌላም ሸቀጦች ይገዛሉ ። በካፒታሊስቶች መካከል ያሉት ግንኙነቶችም የሸቀጥ ግንኙነቶች ጸባይ ይወርሳሉ ።

ለመደምደም ፤ በካፒታሊስት ሕብረተሰብ የሸቀጥ ምርት ገዥ (የበላይነት)፤ ሁለንታዊ ጸባይ ሲወስድ ፤ በሰዎች መካከል ያሉት ግንኙነቶች ግን በነገሮች መካከል ያሉ ግንኙነቶች ሆነው ይቀርባሉ ፤ ሸቀጦች ።

ለሸቀጥ ምርት መምጣት ምክንያቶች

የሸቀጥ ምርት ሊመጣ የሚችለው የተወሰኑ ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜ ብቻ ነው ።ለሸቀጥ ምርት መምጣትና ሕልውና አስፈላጊ የሚሆነው በጣም ዋናኛው ሁኔታ የሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍል ነው ። ይህም ማለት የተለያዩ ምርቶችን የመሥራት ሁኔታ በተለያዩ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል የሥራ መከፋፈልን ነው ። ለምሣሌ ፤ አንዱ ቡድን ልብስ ሲሸምን ፤ ሌላው መጫሚያ ይሠራል ፤ ሶስተኛው የቤት ዕቃዎችን ፤ አራተኛው—ሌሎች ቁሳቁሶችን ወዘተ . . » እርግጥ ፤ እነዚህ ሰዎች የግለ—ሰብ ፍላጎቶቻቸውን ለማርካት የጉልበታቸውን ውጤት መለዋወጥ አለባቸው ። በዚህ መንገድ ሁሉም አምራቾች ባንድነት ተወስደው እያንዳንዱ አባል በሌላው ጥገኛ የሆነበት ትልቅ አምራች ክፍልን ይመሠርታሉ ።

ግን የሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍል ለሸቀጥ ምርት ሕልውና ከሚአስፈልጉት ሁኔታዎች አንዱ ብቻ ነው ። ሌላው ዓይነተኛ ሁኔታ በሕብረተሰቡ ውስጥ የተለያዩ የምርት መገልገያዎች ባለቤትነት መኖር ነው ። የሚቀጥለውን ሁኔታ እንውሰድ። አንድ ሰው አንድ ዕቃ ሠራና ለሆነ ሰው ለመሸጥ ፈለገ ። ሊአደርገው ይችላል ? አዎ ! ይችላል ፤ ግን ዕቃውን ለመሥራት ለተገለገለበት የምርት መገልገያ እና ለዕቃውም ጭምር ባለቤት ከሆነ ብቻ ነው ። ለምሣሌ ፤ በጥንታዊ ጋርዮሽ ውስጥ የሥራ ክፍፍል እንደነበር እውነት ቢሆንም ፤ የሸቀጥ ልውውጥ አልነበረም ። የቀበሌው ንዋ

ረዎች የጉልበት ውጤታቸውን ይለዋወጣሉ ፤ ግን አንዱ ላንደኛው አይሸጥም ፤ እንዲያ ሊአደርጉ አይችሉም ፤ ምክንያቱም ቀበሌው በአጠቃላይ የምርት መገልገያዎችንና የጉልበት ውጤቶችንም ያዘባቸው ነበርና ። የአንድን ቀበሌ የምርት ውጤት ከሌላው ቀበሌ የምርት ውጤት በሚለዋወጥ ጊዜ ልዩ ነበር ። በዚህ መንገድ የባለቤትነት ለውጥ ቦታ ወስደና የጉልበት ውጤትም ሸቀጥ ሆነ ።

ስለዚህ የሸቀጥ ምርት መሠረቱ የሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍልና በሕብረተሰቡ ውስጥ የምርት መገልገያዎች የተለያዩ ባለቤቶች መኖር ነው ። እነኝህ ሁለቱም ዓይነት ሁኔታዎች ሲኖሩ ብቻ ነው የሸቀጥ ምርትና የምርቶች ለውውጥ በሽያጭና በግገር መልክ ብቅ የሚሉት ።

*የቀላልና የካፒታሊስት ሸቀጥ ምርት*

የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት የሚመጣው የተወሰኑ የሕብረተሰቡ ሁኔታዎች ሲኖሩና በቀላል የሸቀጥ ምርት ላይ በመመሥረት ነው።

የቀላል ሸቀጥ ምርት ዓይነተኛ ቀደምት ተወካዮች ትናንሽ ገበሬዎችና የእጅ ባለሙያዎች ናቸው ። ምርታቸውን የሚመሠርቱት በግለ ሰብ ጉልበት ላይ ነው ማለትም እራሳቸው ይሠራሉ ፤ እናም የሌሎችን ጉልበት አይበዘብዙም ። እያንዳንዱ የቀላል ሸቀጥ አምራች ለራሱ የምርት መገልገያ ባለቤት ነው ፤ የሚአመርተውም ለራሱ ፍጆታ (ብሎት ) ሳይሆን ፤ ግን ለገበያ ነው ፤ ለሽያጭ ።

ቀላል የሸቀጥ ምርት ሁለት መልክ አለው ። ባንድ በኩል ፤ በግለሰብ ባለቤትነት በመመሥረቱ ፤ ትንሹ ገበሬ ወይም የእጅ ባለሙያ ባለንበረት ነው ፤ እናም ይህ ወደ ካፒታሊስቱ ሠፈር ያቀርባዋል ። በሌላ መንገድ ፤ ቀላል የሸቀጥ ምርት በግለ — ሰብ ጉልበት ላይ በመመሥረቱ ፤ ሸቀጥ አምራቹ ሠራተኛ ነው ፤ እናም ይህ እንደሱ ሳይሆን ምንም የምርት መገልገያ ከሌለው ፤ ከወዝ — አደሩ ሠፈር ያቀርበዋል ። እዚህ ላይ ነው ሠራተኛው መደብና ገበሬው የጋራ ዝንባሌ የሚኖራቸው ፤ ስለሆነም በመጨረሻ ኪዳን ለመፍጠር ያስችላቸዋል ።

በአንዳንድ የሕብረተሰብ ሁኔታዎች ፤ ቀላል የሸቀጥ ምርት የማለፊያ ነጥብና ለካፒታሊስት ምርት መነሻ መሠረት ሊሆን ይችላል ። እንዲህ ዓይነት ሁለት ሁኔታዎች ተደርገዋል ። መጀመሪያ ፤ የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት መኖር ነው ። ይህ ሁኔታ የታየው የጥንታዊ ሕብረተሰብ በተጨማተረበት ዘመን እንደ ሆነ እናውቃለን ። ሁለተኛ ፤ የጉልበት — ኃይል ወደ ሸቀጥነት መሸጋገር ነው ። ይህ የሆነው የመልከኛ ሕብረተሰብ ሲበታተን ነው ።

ቀላል የሸቀጥ የምርት ነዋሪ አይደለም ፤ በገበሬዎችና በባለ እጅ ሙያተኞች መካከል የመከፋፈል (በመደብ) ሂደት ሳያቋርጥ ቦታ ይወስዳል — አንዳንዶቹ (ጥቂቶች) ሀብታም እየሆኑ ሲሄዱ ፤ ሌሎቹ ግን (ብዙኃኑ) ወደድህነት ያሽቆለቁላሉ ። እላይ በተነሱት ሁኔታዎች እነዚህ ሂደቶች በገጠርም ሆነ በከተማ ቡርዧዊውንና ወዛደሩን ወደመመሥረቱ ይመራሉ ።

የካፒታተሊስት የሸቀጥ ምርት ፤ እንደቀላል የሸቀጥ ምርት ሁሉ ፤ የተመሠረተው በሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍልና በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ ነው ፤ ግን በተጨማሪም የተመሠረተው ለምርት መገልገያዎች ባለቤት የግል ጉልበት ላይ ሳይሆን ፤ በቅጥር ጉልበት ብዝበዛ ነው ። ከካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ውስጥ ካፒታሊስቱ የምርት መገልገያዎቹንና ገንዘብን በራሱ ቁጥጥር ሥር በማድረግ ራሱ አይሰራም ። በገንዘቡ የምርት መገልገያዎቹን ለማንቀሳቀስ የጉልበት— ኃይል ይገዛል ። የጉልበት — ኃይል ወደ ሸቀጥ መሸጋገር ማለት ፤ በካፒታሊዝም ውስጥ ፤ የሸቀጥ ምርት ይበልጥ ማደግና ሁለንታዊ መሆን ነው ። « የሸቀጥ ለውውጥ » ይላል ሌኒን « የሸቀጥ ልውውጥ እንደቀላል ፤ በጣም ተራ ፤ መሠረታዊ ፤ በጣም የታወቀና የቡርዧ ሕብረተሰብ የዕለት ተዕለት ግንኙነት (ሸቀጥ) ፤ ብዙ



ሺ ሚሊዮን ጊዜ የሚታይ ግንኙነት ነው ።»[1] ስለዚህ ሸቀጥ በእውነት ምን እንደሆነ — ይህን ሕዋሳዊ መልክ የካፒታሊስት ምጣኔ—ሀብት—መግለጽ አለብን።

## ፪. ሸቀጦችና ሸቀጥን የሚፈጥረው ጉልበት (ሥራ)

*የጠቀሜታ ዕሴት እና የሸቀጥ ዕሴት*

ሸቀጥ ከሁሉም በፊት አንዳንድ የሰብዓዊ ፍላጎቶችን የአሟላ ነገር ሆኖ እና ፤ ሁለተኛ ፤ የሚመረተው ለግላዊ ብሎት (ፍጆት)ሳይሆን ፤ ግን ለሽያጭ ፤ ለልውውጥ ነው ።

ለራሱ ብሎት አንድን ሸቀጥ የሚአመርት ሰው ምርት እንጂ የሚአመርተው ሸቀጥ አይደለም ። ምርቱ ሸቀጥ እንዲሆን አንዳንድ ሕብረተሰባዊ ፍላጎቶችን ማርካት አለበት ፤ ማለትም ፤ በሌላ ሕብረተሰብ አባላት ዘንድ ያለውን ተጠያቂነት ማርካት ይኖርበታል ። የሸቀጥ ግንዛቤ በውስጡ ሁለት በቅርብ የተገናኙ መልኮች ሁለት ጸባዮች ያሳያል ፤— የጠቀሜታ ዕሴትና ዕሴት የሚባሉ ።

አንዳንድ ሰብዓዊ ፍላጎቶችን የማርካቱ የሸቀጡ ጸባይ ሁኔታ ጠቀሜታ—ዕሴት ተብሎ ይጠራል ። የሸቀጡ የማርካት አስፈላጊነት የተለያዩ መልክ ሊኖረው ይችላል ። አንድ ሸቀጥ ተቀዳሚ ተፈላጊነት ሊኖረው ይችላል ፤ እንደዳቦ ፤ ልብስ ፤ ጫማ ። የድሎት ዕቃም ሊሆን ይችላል — ውድ የሆኑ ወይን ጠጆች ፤ ዕንቁዎች ፤ ወዘተ . . . ። የምርት መገልገያም ሊሆን ይችላል ፤ እንደማሺን ፤ የድንጋይ ከሰል ፤ ብረት እና ሌላም ።

እያንዳንዱ ዕቃ ከአንድ የበለጠ የጠቀሜታ ዕሴት ይኖረው ይሆናል ። ለምሣሌ ፤ የድንጋይ ከሰል እንደነዳጅ ወይም የኬሚካል ምርት ለማውጣት እንደ ጥሬ ዕቃ ሊጠቅም ይችላል ።

በሸቀጥ ምርት ውስጥ ፤ በተለያዩ የጠቀሜታ ዕሴቶች መካከልና ፤ በተወሰነ የብዛት ምጥነት ቀዋሚ ልውውጥ ይካሄዳል ። ለምሣሌ ፤ አንድ ምሣር በ20 ኪ. ግ. እህል ተለወጠ እንበል ። የአንድ ጠቀሜታ ዕሴት ከሌላው የተለወጠበት ምጥነት ( Proportion ) የሸቀጡ የልውውጥ — ዕሴት ነው ። የልውውጥ ዕሴትን ስናነሳ ወዲያውኑ ሁለት ጥያቄዎች ይነሳሉ — 1) በምን መሠረት ነው ፍጹም የተለያዩ ዓይነት የሆኑ ሸቀጦች አንዱ ካንዱ የሚመጣጠኑት ? እናም 2) ለምንድነው የተለያዩ ሸቀጦች አንዱ ካንዱ በተወሰነ ምጥነት ፤ በተወሰነ ብዛት ዕኩያነት የሚአገኙት ? እርስ በእርሳቸው ፍጹም ያልተመሳሰሉ ፤ የተለያዩ ሸቀጦች ፤ አንዱ ካንደኛው በልውውጥ ጊዜ እኩል እንደሆኑ ሆነው ከተወሰዱ ፤ በጋራ የሚካፈሉት (የሚመሳሰሉበት) አንድ ነገር አለ ማለት ነው ። ከአራተኛው ምዕተ ዓመት የክርስቶስ ልደት በፊት ዝነኛው የግሪክ ፈላስፋ አሪስ ጣጥሊስ ያለ እኩልነት ልውውጥ ሊካሄድ አይችልም፤እንደዚሁም እኩልነት በማይመጣጠኑ ነገሮች ውስጥ ሊኖር አይችልም ብሎ ነበር ።

ሁሉም ሸቀጦች በአጠቃላይ በተለያዩ ደረጃ የሚከተሉት ጸባዮች አሏቸው — ጠቃሚነቱ ፤ አንድ ዕቃ በመሆን ያለው የቀራቢነትና የተጠያቂነት (ችሎታው) ፤ ዕጥረቱ ፤ እና ጉልበት ።

ታዲያ ፤ የትኛው ጸባይ ነው የአንድን ሸቀጥ ዕሴት የሚወስነው ?

በመጀመሪያ አመለካከት « ጠቃሚነቱ » ለአንድ ሸቀጥ ዕሴት አስፈላጊ ነው ይባል ይሆናል ። አንድ ዕቃ የጠቃሚነቱን ያህል ፤ የበለጠ ዕሴት ሊኖረው

1 ቪ. አይ. ሌኒን ፤ "ስለዳያሌክቲክስ" ማርክስ - ኤንግልስ - ማርክሲዝም ሞስኮ ገጽ ፤ 334

ይገባል ። ይሁንና ፣ በማንኛውም ደረጃ « ጠቃሚነቱ » ዕሴትን እንደማይወስን እናያለን ። በጣም ጠቃሚ ነገሮች ሁልጊዜ (ለምሣሌ ፣ አየር) ምንም ዋጋ አያወጣም ወይም ቢአወጣም በጣም ጥቂት (ለምሣሌ ፣ ውሃ) ይሆናል ፤ ነገር ግን ለግለ — ሰብ አገልግሎት ዝቅተኛ ጠቃሚነት ያላቸው ሁልጊዜ ይበልጥ ዋጋ አላቸው (ለምሣሌ ፣ አልማዝ) ። እርግጥ ፣ የምርቶች ዕሴት በጠቃሚነታቸው ላይ ጥገኛ ቢሆን ፣ ታዲያ ዳቦና ውሃ እንደ አልማዞች ሁሉ የናረ ዋጋ ይኖራቸው ነበር ፣ እናም እንዲሁ የተገላቢጦሽ በሆን ነበር ። ስለዚህ ፣ ጠቃሚነት ፣ ወይም የጠቀሜታ ዕሴት ፣ የዕሴት ፣ ምክንያት ሣይሆን ፣ ሁኔታዊ (Conditional) ነው ። ምንም እንኳ ዕሴት ያለ ጠቀሜታ ዕሴት ሊኖር ባይችልም ፣ የኋለኛው ያለ ዕሴት መኖር ይችላል ( ለምሣሌ ፣ አየር ከፍተኛ ጠቀሜታ — ዕሴት አለው ፣ ግን ዕሴት በፍጹም የለውም ) ።

ቀራቢነትና ተጠያቂነት እሳ ዕሴትን ይወስናል ? በመጀመሪያ አመለካከት የሚችሉ ይመስላሉ ። የሸቀጥች ተጠያቂነት ማየል ፣ የሚወስንላቸው ተመንም ከፍተኛ እንደሚሆን ፣ እና ፣ በሌላ በኩል ፣ የማንኛውም ሸቀጥ ቀራቢነት ሲአይል የእነዚህ ሸቀጦች ወደ ገበያ በብዛት መምጣት ስለሚሆን ፣ ዋጋቸውም ዝቅ እንደሚል የተለመደ ነገር ነው ።

ግን ይበልጥ ጠልቀን ወደ ጥያቄው ባሕርይ ስርስረን ብንገባ ፣ የሸቀጦች ዕሴት በማቅረብና በተጠያቂነት ላይ ጥገኛ እንዳልሆነ ግልጽ ይሆንልናል ። ለምሣሌ ፣ ስኳርና ጨውን እንውሰድ ። እነኝህ ሸቀጦች በመቅረብና በተጠያቂነት ሕግ ነው የሚወሰኑት ። ተጠያቂነታቸው ከቀራቢነታቸው ጋር እኩል ከሆነ ፣ 1. ኪ. ግ. ስኳር አሁንም ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከ1. ኪ. ግ. ጨው ያይላል ፤ ይህም የመቅረብና የተጠያቂነት ምንም ፋይዳ እንደሌላቸው ያሳያል ። እርግጥ ፣ የመቅረብና የመጠየቅ መጠን (Amount) ለሸቀጦች ተመን አንዳንድ ልዩነቶችን ያመጣል ፣ ግን የሚወስነው የዕሴቱን መጠን አይደለም ፣ በተጠያቂነት ላይ ባለው የሸቀጥ ዕሴት አካባቢ የሚዋዥቀውን የገበያ ተመን ደረጃ እንጂ ። የአንድ ሸቀጥ ተጠያቂነት ሲጨምር ፣ ቀራቢነቱ ግን ይቀንሳል ፣ የገበያ ተመን ከዕሴቱ በላይ ይንራል ፣ እና ፣ በሌላ መንገድ ፣ የዚሁ ሸቀጥ ተጠያቂነት ሲቀንስ ፣ ቀራቢነቱ ይጨምራል ፣ የገበያ ተመንም ከዕሴቱ በታች ዱብ ይላል ። ተጠያቂነት ቀራቢነቱን ዕኩል ሲሆን ብቻ ፣ የገበያ ተመንም ከዕሴቱ ጋር ይስተካከላል ፤ ይስማማል ። ግን ይህ ሁኔታ በካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ውስጥ ሆኖ አያውቅም ። ይህም ማለት ቀራቢነትና ተጠያቂነት የሸቀጥን ዕሴት አይወስኑትም ነው ።

የአንድ ሸቀጥ መታጣት (ማጠር) እሳ ዕሴቱን መወሰን ይችላል ? በብዙ ሺ ተግባራዊ ምሣሌዎች አቅርቦ ማሳየት የሚቻል ይመስላል ። ወርቅን ፣ አልማዝን ፣ እና ዳቦን እንውሰድ ። ወርቅና አልማዝ የማይገኙ ነገሮች ናቸው ፣ በዚያውም ከፍተኛ ዋጋ ፣ ይኖራቸዋል ። ይሁንና ፣ ዕጥረት (አለመገኘት) ለከፍተኛ ዕሴት ምክንያት ነው ማለት አይደለም ። ለምሣሌ ፣ በድርቅ ዘመን ለረጅም ጊዜ ዝናም አልነበረም ፣ ሰዎች ብዙ ጠብቀዋል ፣ ተጠያቂነቱ እጅግ ትልቅ ነበር ፣ ቢሆንም ለመጥፋቱና ለጠቃሚነቱ ፣ በጣም ተፈላጊነቱ ቢአይልም ፣ በገንዘብ የሚገለጽ ምንም ዕሴት የለውም ።

ለማጠቃለል ፣ ጠቃሚነት ወይም ዕቃ በመሆን ያለው የተጠያቂነትና የቀራቢነት (ችሎታ) ፤ ወይም እጥረት የዕሴት ምክንያት አይደሉም ። ሆኖም ፣ የተለያዩ ዓይነት ሸቀጦች የጋራ የሆነ አንድ ጸባይ አላቸው ፣ ከጠቃሚነታቸው ፣ ዕቃ በመሆን ካላቸው ቀራቢነትና ተጠያቂነት ፣ እና ከዕጥረታቸው ነጻ የሆነ ። ይህ ጸባይ ሁሉም የጉልበት ውጤቶች መሆናቸው ነው ።

ጉልበት ብቻ ነው የዕሴት መሠረቱ ፣ ወይም ማርክስ እንዳስቀመጠው ፣ አካሉ ( the substance ) ። ለዚህ ወይም ለዚያ ሸቀጥ ምርት የበለጠ ጉልበት ሲጠየቅ የሚይዘው ዕሴት ያይላል ፣ ዋጋውም( cost ) ያየለ ይሆናል ። ወርቅ ከድንጋይ



ከሰል እጅግ የበለጠ ውድ ነው ፤ ይህ የሚሆነው ወርቅን ለማውጣትና ከእርሱ የተቀላቀሉ ማዕድኖችን ለማጥራት ያንኑ ያህል የድንጋይ ከሰል ለማውጣት ከሚአስፈልገው በላይ ጉልበት እንዲጠፋበት ስለሚአሻ ነው ።

ሁሉም ሸቀጦች የሰው ጉልበት ውጤቶች ናቸው ። አንዱ ካንደኛው ይወዳደራሉ ፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ ሸቀጥ የተወሰነ የጉልበት መጠን በውስጡ ስለሚይዝ ነው ። ሸቀጦች የጉልበት ውጤቶች ናቸው የሚለው ዕውነት ነው ዕሴታቸውን የሚሰጣቸው ።

« ዕሴት» በሸቀጦች የተካበበ (ውስጥ ያለ) የሸቀጥ አምራቾች ሕብረተሰባዊ ጉልበት ነው ። « የተካበበ » የሚለው ቃል የሚአተኩረው ጉልበት በሸቀጥ ውስጥ መጨመሩን ፣ የአንድ ዕቃን ወይም ሸቀጥን ቅርፅ መያዙን ነው ። ሸቀጦች የሚለዋወጡባቸው ምጥኖች እንደ የዕሴት መግለጫ ዘዴ (መልክ) ሆነው ያገለግላሉ ፤ አንድ ዓይነት የሆነ የጉልበት መጠን በተለዋወጡት ሸቀጦች ላይ ከጠፋ ፣ በዕሴት አንድ ዓይነት እንደሆኑ ነው የሚአሳዩን ።

የአንድ ሸቀጥ ዕሴት ሕብረተሰባዊ ፈርጅ ነው ፣ አይታይም ፤ ግን አንድ ሸቀጥ በሌላ በተለወጠ ቁጥር ፣ እና አንድ ሸቀጥ ከሌላው ሲመጣጠን ይታወቀናል ። ስለዚህ ፣ ሌኒን እንዲህ ይላል ፡— « ዕሴት በሁለት ሰዎች መካከል ያለ ግንኙነት ነው . . በነገሮች መካከል ያለ ግንኙነትን መስሎ የተላበሰ (ሽፍን) ግንኙነት ነው ።» [1]

የጠቀሜታ — ዕሴት ሁልጊዜም ኖሯል ወደፊትም ይኖራል ። ግን ሸቀጥ እንደ ዕሴት አከማችነት ሆኖ ብቻ ያለው በተወሰነ የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ነው ፣ የሸቀጥ ምርትና ሸቀጥ ወደ ሕልውና በመጡ ጊዜ ። ከሸቀጥ ምርት መጥፋት ጋር የሸቀጥ ዕሴትም አብሮ ይጠፋል ። ይህም ማለት ዕሴት ሕብረተሰባዊና ታሪካዊ ፈርጅ ነው ። ማለትም በተወሰነ የሕብረተሰብ የዕድገት ደረጃ የኖረ ነው ።

ስለዚህ ሸቀጥ ሁለት ጸባዮች እንዳሉት — የጠቀሜታ ዕሴትና የዕሴት ጥምረት እንደሆነ ግልፅ አድርገናል ።

ግልጽ እና ሥውር ሥራ

ታዲያ ፣ የሸቀጥ ሁለትነት አፈጣጠር ማብራሪያ ምንድነው ? ግልፅ እና የሸቀጥ ሁለትነት አፈጣጠር የሚወስነው ሸቀጥን በሚፈጥረው የጉልበት ሁለትነት ተፈጥሮ ነው ። በሸቀጥ የተካበበው የአምራች ጉልበት የሚቀርበው ፣ በአንድ በኩል እንደ ግልፅ ጉልበት ፣ በሌላ ደግሞ ፣ እንደ ሥውር ጉልበት (ሥራ) ነው ።

ግልፅ ጉልበት (ሥራ) በአንድ በተወሰነ ፣ ጠቃሚ በሆነ ፣ በጠቃሚነት መልክ የጠፋ ጉልበት ነው ። ሰው ብቻውን በጠቅላላ ሁሉንም (በአጠቃላይ) ሊሠራ አይችልም ። ሥራ በሚሠራበት ጊዜ ፣ የጫማ ሰፊ ሥራ ነው ፣ ወይም የገበሬ ፣ ወይም የማዕድን ቆፋሪ ፣ ሌላ ሌላም ።

ልዩ ልዩ ዓይነት ሥራ በዓይነት ይለያያል ፣ የእደ ጥበብ ዘዴዎች ፣ ቁሳቁሶች በጥቅም ላይ የዋሉት ነገሮች ፣ እና በመጨረሻ ፣ ውጤቶች ፣ ማለትም ፣ የመጨረሻ ምርቶች ፣ የጠቀሜታ ዕሴቶች ። ግልፅ ሥራ ነው የአንድን ሸቀጥ የጠቀሜታ — ዕሴት የሚአስገኘው ።

ሆኖም ፣ የተለያዩ ዓይነት ሥራዎችን ይበልጥ ቀረብ ብለን ብናያቸው ፣ አንድ የጋራ የሆነ ጸባይ እናገኛለን — በአጠቃላይ የጠፋው የሰብዓዊ ጉልበት ፤ ማለትም ፣ የጡንቻው መጠን ፣ አንጎል ፣ ነርቭ ፣ ወዘተ . . . ። ጉልበት ከግልፅ መልኩ ነጻ ሆኖ የተተኮረበት ፣ ሥራ (ጉልበት) እንደሰብዓዊ የጉልበት ኃይል መጥፋት (መፍ

1. ቪ. አይ. ሌኒን ማርክስ — ኤንግልስ — ማርክሲዝም ፣ ገጽ 33

ስስ) ያለው ፣ ሥውር ጉልበት (ሥራ) ነው ። ሥውር ጉልበት ነው የሸቀጥን ዕሴት የሚመሠረተው ።

ግልፅ ጉልበት ፣ ጠቀሜታ— ዕሴትን የሚአስገኘው ፣ ሁልጊዜም ኖሯል ወደፊትም ይኖራል። ግልፅ ጉልበት ሸቀጥ ምርት በሚኖርበት ጊዜም ሆነ በማይኖርበት ይኖራል። ሥውር ጉልበት በሸቀጥ ምርት ውስጥ ብቻ የሚሆን ነው። የተለያዩ ዓይነቶች የግልፅ ጉልበቶች ተመሳሳይ ወደሆነው ሥውር ጉልበት መውረድ፣ ማለትም ጉልበት በአጠቃላይ፤ የሚገለጸው (የሚብራራው) በሸቀጥ ምርት ሕልውና ነው፣ ቁም ነገሩ (የመውረዱ) ምርት የሚሠራው ለሺያጭ መሆኑ ነው። በእርግጥም፣ ለምሣሌ፣ አምራች አንድ ጥንድ ቦት ቢሠራ ፣ ወደገበያም ቢወስድ ፣ እንበልና በዳቦ እንዴት ነው የሚለዋወጡት ? እንደጠቀሜታ ዕሴታቸው ከሆነ ሁለቱ ምርቶች ተወዳዳሪዎች አይደሉም ። ስለዚህ ሊወዳደሩ የሚችሉት በጠፋባቸው ጉልበት ነው ። ጫማ ሰፊው አንድ ጥንድ ቦት ለ100 ኪሎ ግ. እህል ቢለውጥ ፣ ተመሳሳይ የሆነ የሥውር ጉልበት መጠን በጫማውና በእህሉ ወጥቶበት ነበር ማለት ነው ። ጫማዎቹ ለለውውጥ ባይሰሩ ኖሮ ፣ ግን በጫማ ሰፊው ቤተሰብ ውስጥ ለመጠቀም ቢሆን ፣ በእነሱ ላይ የፈሰሰውን የሥውር ጉልበት መጠን መወሰን አስፈላጊም ባልሆነ ነበር ። ከሸቀጥ ምርት መጥፋት ጋር የሥውር ጉልበት ፈርጅም አብሮ ይጠፋል ።

በሸቀጥ ምርት ውስጥ በግልና በሕብረተሰብ ጉልበት መካከል እንዳለ ቅራኔ ሆኖ ውጭ የሚወጣ ፣ ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ በግልፅ ጉልበትና በሥውር ጉልበት መካከል አለ ።

**ግላዊና ሕብረተሰባዊ ጉልበት**

በሸቀጥ ምርት ውስጥ እያንዳንዱ አምራች ልዩ የሆነ ሸቀጥ ነው የሚሠራው። በሕብረተሰብ ውስጥ ሥራ ይከፋፈላል ፣ ይህ መከፋፈል በጠለቀ ቁጥር ፣ የተለያዩ የምርት ዘርፎች ይኖራሉ ፣ የሸቀጥ አምራቾችንም የሚአስተሳስሯቸው ግንኙነቶች የዚያኑ ያህል ይሰፋሉ ። ከምላ ጉደል ሁሉንም ነገሮች የመሥራት ሁኔታ በሃያ ወይም በመቶ እንኳ የሚቆጠሩ ሰዎችን ሥራ ያዋህዳል ። ይህም የእያንዳንዱ የሸቀጥ አምራች ጉልበት የሕብረተሰቡ ጉልበት አነስተኛ ቅንጣት በመሆን ፣ ሕብረተሰባዊ ጸባይ ይወስዳል ማለት ነው ።

ግን የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ባለበት ሕብረተሰብ ውስጥ ሸቀጥ አምራቾች አንዱ ካንደኛው ነጻ በመሆን በምርት ላይ ይሠማራሉ ፣ የተበታተኑ ፣ (ያልተባበሩ) ናቸው ። ጉልበታቸውም ፣ በመሠረቱ የሕብረተሰብ ጉልበት የሆነው ፣ የግል ጉልበትን መልክ ይወስዳል ። እዚህ ላይ የጉልበት ሕብረተሰባዊ ጸባይ ተደብቋል ፣ በገበያ ልውውጥ ጊዜ ብቻ ነው ግልፅ የሚሆነው ። በሕብረተሰቡ ከተፈለገ ጊዜ ጀምሮ የሸቀጥ አምራቹ ግላዊ ጉልበት ከሕብረተሰቡ ጉልበት እንኳ ቅንጣት መሆኑ ቁልጭ የሚለው ፣ በትክክል በሸቀጦች ልውውጥ ፣ እነሱን በመሸጥና በመግዛት ጊዜ ነው ።

የሸቀጥ አምራቹ ጉልበት ፣ በቀጥታ ግላዊ ሲሆን ፣ ወዲያው ደግሞ ጸባዩ ሕብረተሰባዊ የመሆኑን ዕውነት ስንመለከት ፣ የቀላል ሸቀጥ ምጣኔ — ሀብት ዋና ቅራኔ ፣ ማለትም በግልና በሕብረተሰባዊ መካከል ያለው ብቅ ይላል ። ይህ ቅራኔ የሚገለጸው (የሚከሰተው) በልውውጥ ወቅት ነው ። ሸቀጥ አምራቾች ወደ ገበያ በሚሄዱ ጊዜ ፣ አንዳንዶቹ ሸቀጦቻቸውን ሲሸጡና ሌሎቹ ሳይሳካላቸው ሲቀር ይታወቃል ። ሳይሳካላቸው ሊቀር ይችላል ፣ ምክንያቱም ተጠያቂነት ስለማይኖራቸው ፣ ወይም ምክንያቱም በጣም ውድ ስለሚሆኑ ። ግን ሸቀጥ አምራቹ ሸቀጦችን በገበያ ውስጥ ለመሸጥ ሳይችል ቢቀር ፣ ጉልበቱ ሕብረተሰባዊ ተቀባይነት አላገኘም ማለት ነው ፤ አምራቹ ይከስራል ፣ እናም ፣ ይህ ዓይነት ሁኔታ ሁልጊዜ ከተደጋገመ ፣ ይጠፋል ። ከዚህ ላይ የምንደመድመው በግላዊና በሕብረተሰባዊ ጉልበት መካከል ያለ ቅራኔ ወደ አንዳንድ አምራቾች መውደምና ወደ ሌሎች መበልጸግ የሚመራን መሆኑን ነው ።



**የሸቀጥ ዕሴት ዋናነት**

የአንድ ሸቀጥ ዕሴት የሚገኘው በጉልበት ስለሆነ ፣ የዕሴቱ ዋናነት (ዓይነተኛነት የሚለካው) በሸቀጡ ውስጥ በፈሰሰው የጉልበት መጠን ነው ። ጉልበት በተራው ደግሞ የሚለካው በሚፈስበት (በሚጠፋበት) ጊዜ ይሆናል ፤ ማለትም ፤ በሥራ — ጊዜ ። ግን ብዙ ሸቀጥ አምራቾች አሉ ፣ እናም ተመሳሳይ ሸቀጦችን ለማምረት የተለያዩ የጉልበት መጠን ያጠፋሉ ። ስለዚህ የአንድ ሸቀጥ ዕሴት ዋናነት በእያንዳንዱ ግለሰብ አምራች በፈሰሰበት የጉልበት መጠን ሊለካ አይችልም ። የአንድ ሸቀጥ ዕሴት ዋናነት እያንዳንዱ አምራች ባፈሰሰው ጉልበት የሚለካ ቢሆን ኖሮ ለተመሳሳይ ሸቀጦች ነጠላ የእሴት ዋናነት አይኖርም ነበር ። ይሁንና ፣ በልውውጥ ጊዜ ተመሳሳይ ሸቀጦች ዕኩል ዕሴት አላቸው ። የአንድ ሸቀጥ ዕሴት ዋናነት የሚወሰነው በእያንዳንዱ አምራች በጠፋው ግላዊ የሥራ—ጊዜ ሳይሆን ፤ ግን አንድ የተወሰነ ሸቀጥን ለማምረት በፈሰሰው በሕብረተሰቡ አስፈላጊ በሆነ የሥራ—ጊዜ ነው ።

የሕብረተሰቡ አስፈላጊ የሥራ—ጊዜ (socially necessary labour-time) ማለት አንድን ነጠላ ሸቀጥ ለማምረት በተወሰነ የምርት ዘርፍ በሕብረተሰቡ የምርት ሁኔታ አማካይ ውስጥ የሚአስፈልገው ጊዜ ነው (አማካይ ቴክኒካዊ መሣሪያ ፣ የአምራች አማካይ ልምድና የጉልበት መታፈግ) ። እንደ ሕጉ ፣ የሕብረተሰቡ አስፈላጊ የሥራ — ጊዜ የሚወሰነው ከፍተኛ መጠን የሸቀጥ ዓይነቶች በሚሠሩበት በምርት ሁኔታ ነው ።

የሕብረተሰቡ አስፈላጊ የሥራ — ጊዜ ሳያቋርጥ ይለወጣል ፣ አብሮም የዕሴት ዋናነት ይቀየራል ። በሕብረተሰቡ አስፈላጊ የሥራ — ጊዜ ለውጦች የሚደርሱት በጉልበት አምራችነት ለውጦች ውጤት ነው ። የጉልበት አምራችነት የሚገለጸው በተወሰነ ክፍል የሥራ ጊዜ በሚፈጠረው የምርቶች መጠን ነው ። የአምራችነት መጨመር የሚጤነው ፤ ማንኛውም ለውጥ እንደማለት ነው ፣ በአጠቃላይ ፣ የእያንዳንዱን ሸቀጥ የጉልበት ፍሳሽ በሚቀንሰው የጉልበት ሂደት ነው ። በማንኛውም ሕብረተሰብ የአምራችነት ማየል ፣ ማለትም ፣ በተወሰነ ክፍለ — ጊዜ የሚሠሩት የእለቀላቸው ምርቶች መጠን ሲአድግ ፣ የሕብረተሰብ ጉልበት አምራችነት ይወርዳል ፣ የተወሰነን ሸቀጥ ለማምረት የሚጠየቀው የሕብረተሰቡ አስፈላጊ የሥራ-ጊዜ ሲአይል፣ ዕሴቱም ይንራል ። ስለዚህም የጉልበት አምራችነትና የእያንዳንዱ ነጠላ ሸቀጥ ዕሴት በመገለባበጥ አንዱ ላንደኛው ጥገኛ ይሆናሉ።

የጉልበት አምራችነት ከጉልበት መታፈግ ጋር ሊምታታ አይገባውም ። የጉልበትም መታፈግ የሚገለጸው በየክፍለ — ጊዜው በሚጠፋው ጉልበት ነው ። በአንድ ዓይነት የጊዜ ስፋት ውስጥ የሚጠፋው ጉልበት ማየል፣የ ሚመረተውም ምርት ቁጥር መብዛት ነው ፣ ግን ብዙ የጉልበት መጠን በብዙ የምርቶች ቁጥር ላይ ስለሚሰራጭ ፣ የአንድ ነጠላ ዕቃ ዕሴት ሊለወጥ አይችል ይሆናል ።

የሰለጠነም ይሁን ያልሰለጠነ ጉልበት ፣ የአንድ ሸቀጥ ዕሴት ዋናነት የሚደናቀፈው በጉልበት የውስብስብነት ደረጃ ነው ፣ ልዩ ልምምድ የሌለው የአንድ ሠራተኛ ጉልበት ቀላል፣ ያልሰለጠነ ጉልበት ነው ። ልዩ ዓይነት ልምድ የሚፈልግ ጉልበት ውስብስብ ወይም የሰለጠነ ጉልበት ይባላል ። ውስብስብ ጉልበት በእያንዳንዱ ክፍለ — ጊዜ ከቀላል ጉልበት የላቀ ዕሴት ይፈጥራል ። በዚህ ምክንያት ማርክስ « ውስብስብ ጉልበት ማለት ቀላል ጉልበት በአንድ ደረጃ (ዲግሪ) ከፍ ብሎ ፣ ወይም ተባዝቶ ነው » ይላል ።

በግል ንብረት ላይ በተመሠረተ የሸቀጥ ምርት ውስጥ ፣ የተለያዩ ዓይነት ጉልበት መቀነስ ፣ በተለያዩ የልምድ ደረጃ የገባ ጉልበት እና በአምራችነት የተለያዩ ጉልበት ፣ ለአንድ ነጠላ መለኪያ — ሥውር ጉልበት ፣ የሸቀጦችን ዕሴት የሚ

መሠረተው — ሸቀጡ በሚሸጥበት ወቅት በገበያ ላይ በግብታዊነት ቦታ ይወስ ዳል ። ዕሴት የሚገልጸው በሸቀጥ አምራቾች መካከል ያሉትን የምርት ግንኙነቶች የከንዋኔአቸውን የእርስ በእርስ ልውውጥ ነው ፤ ግን ላይላዩን ፤ እነኚህ ግንኙነቶች በነገሮች መካከል ያሉ ግንኙነቶች ሆነው ይቀርባሉ ።

## 3. የልውውጥ ማደግና የዕሴት መልኮች (ቅርጾች)

የልውውጥ — ዕሴት፣ ዕሴት ራሱን የሚገልፅበት መልክ

የሸቀጦች ዕሴት የሚፈጠረው እነሱን ለማምረት በጠፋው ጉልበት ነው ። ይሁንና ፤ ዕሴታቸው ራሱን በልውውጥ ሂደት አንድ ሸቀጥ ከሌላው ጋር በሚወዳደር ጊዜ ፤ ማለትም ፤ በልውውጥ — ዕሴት ውስጥ ግልጽ ያደርጋል ። ስለዚህ የአንድ ምሣር ዕሴት በቀጥታ በሥራው — ጊዜ ( labour-time ) አይደለም የሚገለጸው ፤ የሚብራራው በሌላው ሸቀጥ ሁኔታ ነው ። ለምሳሌ ፤ አንድ ምሣር 20 ኪ. ግ. እህል ይሁን ። አሁን እህሉ የሚአገለግለው እንደምሣሩ ዕሴት ገላጭ ሆኖ ነው ። ይህ አኳያነት የሚአመለክተው እኩል የሆነ ጉልበት እህሉንም ሆነ ምሣሩን ለማምረት እንደወጣ ነው ። አንድ ሸቀጥ ዕሴቱን በሌላ ሸቀጥ የሚገልጸው (በምሳሌአችን ፤ ምሣር) አንጻራዊ የሆነ ዕሴት አለው ። ሸቀጡ ፤ ዕሴቱ የሌላውን ሸቀጥ ዕሴት እንደመግለጫ ሆኖ ያገለገለው (በምሳሌአችን ፤ እህሉ) ፤ የአኳያነት መልክ ዕሴት አለው ።

የልውውጥ — ዕሴት ረጅም ታሪካዊ ዕድገት አቋርርጧል — ከዝቅተኛው ወይም ከዕሴት ድንገታዊ መልክ እስከ ዕሴት ገንዘባዊ መልክ ድረስ ።

የዕሴት ዝቅተኛው መልክ

በተፈጥሮአዊ ምጣኔ ሀብት ሰዎች ምርታቸውን የሚአመርቱት ለልውውጥ ማይሆን ግን ለራስ (ለግላዊ) ብሎት ነው ። በድንገት የተከማቹ ትርፍ ምርቶች ብቻ ነበሩ የሚለወጡት ። የሚለዋወጡት ምርቶች መጠንም የተወሰነ ነበር ። ማንኛውም ነጠላ ሸቀጥ ዕሴቱን በአንድ ሸቀጥ ብቻ በመግለጽ ፤ በቀጥታ ከሌላው ይለወጣል ። ለምሳሌ ፤ አንድ ምሣር=20 ኪ. ግ. እህል ፤ ወይም 20 ሜትር ጨርቅ=አንድ ኮት ። ልውውጡ የአጋጣሚ ሁኔታ እስከሆነ ድረስ ፤ የሸቀጦች ዕሴት ዋናነት በእኩልነት አይለካም ነበር ። በዚህ ሁኔታ ዝቅተኛው ነጠላው ፤ ወይም የዕሴት ድንገተኛው መልክ ነው ያለው ።

አጠቃላዩ ወይም የተስፋፋው አይነት ዕሴት

በጥንታዊ ሕብረተሰብ ውስጥ ፤ ከመጀመሪያው የሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍል መምጣት ጋር—የከብት አርቢነገዶች ከመሬት ሰንጣቂዎች መለየት—ልውውጥ ከብት ርባታን ፤ እህልን ፤ ወዘተ . . .ጨመረና ቀስ በቀስ ተዘውታሪ ሆነ ። ግን በልውውጥ ሂደት ጊዜ ፤ ብዙ ሰዎች አንድ ልዩ ሸቀጥ እንደሚፈልጉ ይበልጥ ግልፅ እየሆነ መጣ ። በተፈጥሮ ከዊነ—ነገሮች ውስጥ ፤ ይህ ከማንኛውም አንዱ የሆነና የተለያየ አሠራር ካላቸው ብዙ ሸቀጦች ጋር የሚለዋወጥ ከብት መሆኑ ተረጋገጠ ። ለምሳሌ ፤

1 በግ = 40 ኪ. ግ. እህል
ወይም
= 20 ሜትር ልብስ
ወይም
= 2 ምሣር
ወይም
= 3 ግ. ወርቅ ወዘተ . . .

ይህ መልክ ፤ የአንድ ሸቀጥ ዕሴት ተከታታይ በሆኑ የተለያዩ ሸቀጦች ሊገለፅ የሚችልበት ፤ አጠቃላዩ ወይም የተስፋፋው ዓይነት ዕሴት ይባላል ።



ዕሴት ሁለንታዊ መልክ

ከሸቀጥ ምርትና የልውውጥ ዕድገት ጋር ፤ በከፍተኛ ደረጃ ተጠያቂነት ያገኘው አንድ ሸቀጥ ተነጥሎ ወጣ ። ሁሉም ሸቀጦች ዕሴታቸውን አንድና በአንድ ዓይነት ሸቀጥ መግለፅ ጀመሩ ። ዕሴትን ለመግለጽ የሚአገለግለው ሸቀጥ የሁለንታዊ አኳያነትን ሚና ይጫወታል ፤ ማለትም ፤ ከሁሉም ሸቀጦች ጋር በዕሴት እኩል ይሆናል ። ከሁለንታዊ አኳያነት መከሰት ጋር ፤ የተስፋፋው የእሴት መልክ ወደ ሁለንታዊ የዕሴት መልክ ሽግግር ቦታ ወሰደ ። ይህ እንደሚከተለው ሊገለጽ ይችላል ።

40 ኪ. ግ. እህል =
ወይም
20 ሜትር ጨርቅ =
ወይም = } 1 በግ
2 ምሣር / ወይም /
3 ግራም ወርቅ ወዘተ...=

ይህ ሽግግር ወደ ሸቀጦች ዑደት መሢሢር መራ ። አሁን እያንዳንዱ የልውውጥ ድርጊት በሁለት ደረጃ ተከፍሏል ። በሽያጭና በግዢ ። ይሁንና ፤ በዚህ ደረጃ የሁለንታዊ አኳያነት ሚና አሁንም ከማንኛውም ነጠላ ሸቀጥ ጋር አልተያያዘም ። በአንድ‌ዳንድ ቦታዎች ከብቶች የሁንለታዊ አኳያነትን ሚና ተጫውተዋል ፤ በሌሎች ፤ ጨው ፤ ደግሞ በሌሎች ፤ ጸጉር ፤ ሌላ ሌላም ።

የሸቀጥ ምርትና ልውውጥ ከፍተኛ ዕድገት ወደ አንድ ነጠላ አኳያነት መሸጋገርን አስፈለገ ፤ በተለያዩ ሸቀጦች የሁለንታዊ አኳያነትን ሚና ስለሚጫወት ፤ የልውውጥ ዕድገት ተጐተተ ፤ እናም ይህ እያደገ የሚሄደው የገበያ ፍላጐት ጋር ተቃረነ ። ይህ ቅራኔ ሊወገድ የቻለው ውድ የሆኑ ብረታ ብረቶችን ፤ ብርና ወርቅን የሁለንታዊ አኳያነትን ሚና በመስጠት ነው ።

የዕሴት ገንዘባዊ መልክ

የሁለንታዊ አኳያነት ሚና ከአንድ ሸቀጥ ጋር ሲያያዝ ፤ ለምሳሌ ወርቅ ፤ የዕሴት ገንዘባዊ መልኩ ተከሰተ ። እንዲህ ሆኖ መገለጽ ይችላል ፡-

40 ኪ. ግ. እህል =
ወይም
20 ሜትር ጨርቅ = } 3 የወርቅ ግራሞች
ወይም
2 ምሣር / ወይም / =
1 በግ ፤ ወዘተ... =

የዕሴት ወደ ገንዘባዊ መልክ መሸጋገር የተከናወነው ሁለተኛውን የሥራ ክፍፍል ተከትሎ ነው — የእጅ ሥራዎች ከእርሻ መከፋፈል ጋር ። ወርቅና ብር ባላቸው ልዩ ባሕሪዎች (የመከፋፈል ፤ የጥንካሬ ፤ አንድ ዓይነት የመሆን ፤ ጥስቅ የማለት (compact)) ምክንያት ጠንከር ባለሁኔታ እንደገንዘብ ሆነው ተመሠረቱ ። ገንዘብ የሌሎችን ሸቀጦች ሁሉ ዕሴት የሚገልጽ ፤ የሕብረተሰቡን አሠራር የሚአሟላ ነው ። ከገንዘብ መከሰት ጋር ሁሉም ሸቀጦች ዕሴታቸውን በገንዘብ መለካት ጀመሩ ።

## 4 ገንዘብ

የገንዘብ አፈጣጠርና አሠራር

በሸቀጥ ምርትና ልውውጥ የታሪካዊ ዕድገት ጊዜ ነው ገንዘብ በግብታዊነት ብቅ ያለው ። ወደ ዕሴት ገንዘባዊ መልክና ወደ ገንዘብም መከሠት ያመራው በእርግጥ የዕሴት መልኮች ማደግ ነው ።

ወርቅና ብር ፤ የሚነጠሩና ቅርፅ የሚሰጣቸው ዲናሮች ፤ ወይም የነሱ መተኪያ የወረቀት ብር ፤ እንደገንዘብ ይጠቅማሉ ። ግን ይህ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ በአ

ንድ ጊዜ ወደ ሕልውና አልመጣም ፣ የረጅም ጊዜ ... ነገር ተለይቶ ወጣ ። መሪያ ከሸቀጦች መካከል ለልውውጥ በጣም የተለመደው ነገር ተለይቶ ወጣ ። ከረጅም ጊዜ የሸቀጥ ምጣኔ — ሀብት ዕድገት የተነሣ የገንዘብ ሚና (ተግባር) ጠንከር ባለ መንገድ ከወርቅ ጋር ተዛመደ ። በ19ኛው ምዕተ — ዓመት ፣ በሁሉም አገሮች ወርቅ እንደገንዘብ ሆኖ ሠራ ።

በዳበረ የሸቀጥ ምጣኔ — ሀብት ውስጥ ፣ ገንዘብ የሚከተሉትን አሠራሮች ያሟላል — እንደ ሸቀጦች የዕሴት መለኪያ ፣ እንደአዘዋዋሪ አማካይ ፣ እንደ ማጠራቀሚያ ወይም ማድለቢያ ዘዴ ፣ እንደመክፈያ ዘዴ ፣ እና ሁለንታዊ ገንዘብ በመሆን ። እስቲ እያንዳንዱን አሠራር እናጢን ።

የገንዘብ መሠረታዊ አሠራር(ተግባር) እንደዕሴት መለኪያ ነው ። የዚህ አሠራር ባሕሪ የሸቀጦች ሁሉ ዕሴት የሚለካው በገንዘብ መሆኑ ነው ። የዕሴት መለኪያ አሠራሩን ለማከናወን ፣ እራሱ ገንዘብ ዕሴት ሊኖረው ይገባል ። የአንድ አካል ክብደት በብረት መለኪያ ብቻ እንደሚለካ ሁሉ ፤ ምክንያቱም የመጨረሻው የራሱ ክብደት አለውና ፣ ስለዚህም የአንድ ሸቀጥ ዕሴት ሊለካ የሚችለው ዕሴት ባለው በሌላ ሸቀጥ ዕርዳታ ነው ። የአንድ ሸቀጥ ዕሴት የሚለካው በወርቅ ማዕከላዊነት ነው። ለአንድ ሸቀጥ የተወሰነ ተመን ለመስጠት ባለቤቱ በአእምሮው(ወይም ፣ ማርክስ እንዳስቀመጠው እንውሰደው ፣ በሀሳቡ) የሸቀጡን ዕሴት በወርቅ ይገልጻል ። አንድን ሸቀጥ ከተወሰነ የወርቅ መጠን ጋር ለማመጣጠን ይቻላል ። ምክንያቱም በሂደቱ በወርቁ ዕሴትና በሸቀጡ ዕሴት መካከል ሁልጊዜም የተወሰነ ግንኙነት አለና ። የዚህ ግንኙነት መሠረቱ ወርቁንና ሌላውን ሸቀጥ ለመሥራት የሚጠፋው

የሕብረተሰቡ አስፈላጊ ሥራ ነው ።

በገንዘብ መልክ የሚገለጸው የሸቀጥ ዕሴት «ተመን» ተብሎ ይጠራል ። ተመን

የሸቀጥ ዕሴት ገንዘባዊ መግለጫ ነው ።

ሸቀጦች ዕሴታቸውን የሚገልጹት በተወሰነ የወርቅ ወይም የብር መጠን ነው ። እነኝህ የገንዘብ ሸቀጥ መጠኖች እራሳቸውም መለካት ይኖርባቸዋል ። በገንዘብነት ያገለገለው (በክብደት) የተወሰነ መጠን ብረታ ብረት የገንዘብ መለኪያ አንዱ ክፍል ነው ። ለምሣሌ ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ፣ የገንዘብ ክፍሉ (unit) ዶለር ፣ በእንግሊዝ — ፓውንድ ስተርሊንግ ፣ እና በፈረንሣይ — ፍራንክ ይባላል ። ለማቀናጀት ፣ ሲባል እነኝህ ገንዘባዊ ክፍሎች ወደ ክፍልፋዮች ይከፋፈላሉ — ዶላር ወደ 100 ሳንቲሞች ፣ ፍራንኩ ወደ 100 ሤንቲሞች ፣ ፓውንድ ስተርሊንግ ወደ 20 ሺልንጐች ፣ እና ሺልንጐች ወደ 12 ፔንስ ።

የገንዘብ ክፍሉና ክፍልፋዮቹ እንደ ተመን መመጠኛ ያገለግላሉ ።

ሁለተኛው የገንዘብ አሠራር (ተግባር) እንደአዟዟሪ ማዕከላዊነት ነው ። ከገንዘብ መከሰት በፊት ፣ ቀላል የሸቀጦች ልውውጥ ተካሄደ ፣ ማለትም ፣ አንድ ሸቀጥ በቀጥታ በሌላ ሸቀጥ ይለወጥ ነበር ። ከገንዘብ መከሰት ጋር የአንድ ሸቀጥ ከሌላው መለዋወጥ በገንዘብ ርዳታ ተከናወነ ። በመጀመሪያ ሸቀጡ ለገንዘቡ ተለወጠ ፣ ከዚያ ገንዘቡ ሌላ ሸቀጥ ለመግዛት በጥቅም ዋለ ። በገንዘብ ዕርዳታ የተንቀሳቀው የሸቀጦች መለዋወጥ የሸቀጥ መዟዟር ተብሎ ይጠራል (ሸቀጥ — ገንዘብ — ሸቀጥ) ። ይሁንና ፣ አንድ ሸቀጥ ወደ ገዥው እጅ ሲተላለፍ ፣ የመዟዟርን አድማስ እንደሚተው መታወቅ አለበት ፣ ግን ገንዘብ ሳያቋርጥ በመዟዟር አድማስ ውስጥ ይቆያል ፣ ማለትም ፣ ከገዥው እጅ ተላልፎ ወደሻጩ ይገባል እናም እንደገና የተገላቢጦሽ ። በዚህ መንገድ በሸቀጦች መዟዟር ገንዘብ እንደ ማዕከላዊነት በመሥራትና የማዟዟርን ማዕከላዊነት አሠራር ያሟላል ። ይህን አሠራር ለማካሄድ ገንዘቡ ወዲያውኑ መኖር አለበት ።



ከመሠረቱ ፣ ሸቀጦች ሲለዋወጡ ፣ ገንዘብ የወርቅ ወይም የብር ቁራጭ (ጥምር) መልኮችን ያዘ ። ግን ይህ የተለያዩ ችግሮች አመጣ ። በየጊዜው ቁራጮች መመዘን፣ በትናንሽ ቁራጮች መቆራረጥ ፣ እና ለጥራታቸው መመርመር አለባቸው ። ስለ ዚህ ቀስ በቀስ የወርቅ ወይም የብር ቁራጮች ለዲናሮች ቦታ ለቀቁ ፣ አሠራራቸውም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆነ ። ዲናር የተወሰነ ቅርዕ ያለውና የተወሰነም ብረታ — ብረት የያዘ ነው ።

በማዟዟር ( ዑደት ) ሂደት ጊዜ ፣ ዲናሮች ይፋተጉና ካላቸው ዕሴት ይቀንሱ ጀመር ። ግን በሥራ ላይ የተፈተጉ ዲናሮች እንደ አዲሶቹ ሁሉ ጥሩ ናቸው ። ለመደምደም ፣ የማዟዟር ማዕከላዊነት አሠራር በብረታ — ብረት ወይም በወረቀት ገንዘብ ያልተጠናቀቀ ዕሴት ሊካሄድ ይችላል ።

ከሸቀጥ ምጣኔ — ሀብት ማደግ ጋር ፣ ገንዘብ የማድለብን ወይም የማጠራቀምን ዘዴ አሠራር ማሟላት ጀመረ ። ገንዘብ የሀብት ሁለንታዊ ማካበቢያ ነው ። በገንዘብ ማንኛውም ሸቀጥ ይገኛል ። ሸቀጥ አምራቾች የሚፈልጉትን ሸቀጥ ለመግዛት ገንዘብ ያጠራቅማሉ ። ይህ አሠራር ሊወገድ የሚችለው ሙሉ ዕሴት ባለው ገንዘብ ነው — ወርቅና ብር ዲናሮች ፣ ወይም የወርቅና የብር ዕቃዎች ።

ገንዘብ የመክፈያ ዘዴን አሠራር ያሟላል ። ሸቀጦች ሁልጊዜ ለተዘጋጀ ገንዘብ አይሸጡም ። አንዳንድ ጊዜ በተለያዩ የአከፋፈል ስልት በዱቤ ይሸጣሉ ይገዛሉ ። ግዥ በዱቤ ሲካሄድ ሸቀጡ ወደ ገዥው ወዲያውኑ ክፍያ ሳይደረግ ይሰጣል ። ገንዘቡ ፣ በስምምነት በተወሰነ የወደፊት ቀን ይከፈላል ። የመክፈያው ቀን ሲደርስ ፣ ገንዘብ ከገዥው ወደ ሻጩ እጅ ይተላለፋል ። በዚህ ዓይነት ገንዘብ እንደመክፈያ መንገድ ያገለግላል ።

የገንዘብ እንደአዟዟሪ ማዕከላዊነትና እንደመክፈያ ዘዴ አሠራሮች ለሸቀጦች መዟዟር የሚያስፈልገውን ጠቅላላ የገንዘብ መጠን የሚወስነውን ሕግ ለማብራራት ያስችላል ።

ለማዟዟር የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን ጥገኛነቱ ፤ በመጀመሪያ ፣ በመዟዟር ላይ ያሉት ሸቀጦች ጠቅላላ ተመን ድምር ፣ እና ፣ ሁለተኛ ፣ ገንዘቡ በሚዟዟርበት ድግግም ላይ ነው ። ገንዘብ በፍጥነት በተዟዟረ መጠን ፣ ለማዟዟር የሚአስፈልገው መጠን አነስተኛ ይሆናል ፣ እና የተጋላቢጦሹንም ። ለምሣሌ ፣ በአንድ ዓመት ውስጥ የተሸጡት ሸቀጦች ጠቅላላ ተመን 100,000 ሚሊዮን ብር ቢሆንና እያንዳንዱ ብር በአማካይ 50 ጊዜ ቢንቀሳቀስ ፣ ስለዚህ ለጠቅላላ ሸቀጦች መዟዟር 2,000 ሚሊዮን ብር ያስፈልጋል ፣ ይህ በሚከተለው ይተያል ፤—

$$\text{የገንዘብ መጠን} = \frac{\text{የሸቀጦች ተመን ጠቅላላ ድምር}}{\text{ገንዘቡ የሚለዋወጠበት ድግግም}} = \frac{100{,}000 \text{ ሚ}}{50} = 2{,}000 \text{ ሚ ብር}$$

እያንዳንዱ አምራች ከአንዱ ወደ አንዱ ለሚአስተላልፈው (ለሚአስፋፋው?) ዱቤ ምስጋና ይግባውና ፣ በሸቀጦች ተመን ጠቅላላ ድምር (በዱቤ በሚሸጡት) እና በመረዳዳት በሚወገዱት ጠቅላላ ክፍያዎች የገንዘብ አስፈላጊነት ቀንሷል ። የገንዘብ መዟዟር ሕግ ይኸውና ፤— ለሸቀጦች መዟዟር የሚአስፈልገው የገንዘብ መጠን በአማካዩ የገንዘብ ልውውጥ ድግግም ተካፍሎ ፣ የሁሉንም ሸቀጦች ተመን ጠቅላላ ድምር ዕኩል መምጣት አለበት ። ከዚህም በላይ ፣ ከሁሉም ሸቀጦች ተመን ጠቅላላ ድምር (በዱቤ የሚሸጡት) የጠቅላላ ሸቀጦች ተመን አጠቃላይ ድምር በመረዳዳት የሚወገዱት ክፍያዎች መቀነስ አለባቸው ፣ እናም በቀሪው ላይ ወደፊት በመጠናቀቅ ላይ ያሉት የእነኛ ክፍያዎች ጠቅላላ ድምር መጨመር ይኖርበታል ።

ይህ ሕግ የሸቀጥ ምርትና መዟዟር ባለበት የሕብረተሰብ አወቃቀር ሁሉ ይውላል ።

ገንዘብ የሁለንታዊ ገንዘብ አሠራርንም ያሚላል ። በዓለም ገበያ ላይ ገንዘብ ብሔራዊ የአለዋዋጭነት ልብሱን ያወልቅና ፣ ማርከስ እንዳስቀመጠው ፣ እንደዲናር ሳይሆን ፣ ግን እንደጥንታዊ ቅርፁ ሆኖ ይከሰታል — የወርቅ ወይም የብር ቡችላ ። በዓለም ገበያ ላይ ባሉት አገሮች መካከል በንግድ መዟዟር ፣ ወርቅ የመግዣና የመሸጫ ሁለንታዊነት መንገድ ነው ፣ እናም ለሕብረተሰብ ሀብት ሁለንታዊ ማካበቢያ ነው ።

እንኚህ ሁለ የገንዘብ ተግባሮች (አሰራሮች) ናቸው ፣ ስለሆነም የገንዘብን ባሕሪ እንደሁለንታዊ አኳያነት በተለያዩ መልክ በመግለጽ ፤ ውስጣዊ መተሳሰርና መያያዝ አላቸው ።

የሰውን በሰው ብዝበዛ ላይ በተመሠረተ ሕብረተሰብ ውስጥ (ባሪያ አሳዳሪ ፣ መልከኛነትና ካፒታሊዝም) ገንዘብ እንደመበዝበገ መሣሪያ በማገልገል ፣ መደባዊ ጸባይ ይይዛል (ይወስዳል) ።

ወርቅና የወረቀት ገንዘብ ፣ ንረት (inflation)

የወረቀት ገንዘብ በአሠራሩ እንደአዘዋዋሪ ማዕከላዊነትና እንደ መክፍያ ዘዴ የወርቅን ቦታ ለመውሰድና ለመወከል በመንግሥት የሚታተም ዋስትና ያለው ገንዘብነው ። በተግባሩ ፣ የወረቀት ገንዘብ የራሱ የሆነ ዕሴት የለውም ፤ ስለዚህም የሸቀጦችን ዕሴት የመለኪያ አሠራር አያካሂድም ።

የወረቀት ገንዘብ በመጀመሪያ የታተመው በቻይና ነው ። በአሜሪካ እንደ ሕጋዊ ገንዘብ ሆኖ የተከሠተው በ17ኛው ምዕተ — ዓመት መጨረሻና በፈረንሳይ ደግሞ በ18ኛው ምዕተ — ዓመት መጀመሪያ ላይ ነበር ። በሩሲያ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በ1769 ዓ. ም. ነው ።

ምንም እንኳ የወረቀት ገንዘቦች ቢታተሙም ፣ ሸቀጡ የተዘዋወረበትን የወርቅ መጠን ዕሴት የሚጠይቀውን ነው የሚወክሉት ። ሸቀጡ የተዘዋወረበትን ለመሸፈን ከሚጠየቀው የወርቅ መጠን ጋር ተመዛዝኖ የወረቀቱ ገንዘብ ከታተመ ፣ የወረቀቱ ገንዘብ የመግዛት ኃይል ከወርቁ የመግዛት ኃይል ጋር ይስማማል ፣ ይጣማል ። ግን አብዛኛውን ጊዜ የቡርዧዋው መንግሥት ተጨማሪ ገንዘብ ያትማል ፣ ምክንያቱም እንደደምብ ሆኖ ገቢው ከወጭው ስለሚአንስ ነው። ይህ በተለይ ዓይነተኛ የሚሆነው በጦርነቶች ፣ በቀውሶችና በልዩ ልዩ ወጭዎች ጊዜ ይሆናል ። ውጤቱ የወረቀት ገንዘብ ዕሴት መውደቅ ነው ።

የሚቀጥለውን ምሳሌ እንውሰድ ፦ የሸቀጦችን መዟዟር ለመሸፈን እያንዳንዳቸው አንድ ብር የሚአወጡ 5,000 ሚሊዮን የወርቅ ዲናሮች አስፈለገ እንበል ። መንግሥቱ በዑደቱ (በዙሪቱ) ውስጥ 5,000 ሚሊዮን የወርቅ ብር አስገብቷል ። ይህም ማለት እያንዳንዱ የወረቀት ብር አንድ የወርቅ ዲናር እንደሚወክል ነው ። አሁን የሸቀጦች መዟዟር አንድ ዓይነት ሆኖ ይቆያል እንበል ፣ ግን መንግሥት ሌላ 5,000 ሚ. ብር አሳተመ ። አሁን እያንዳንዱ የወርቅ ዲናር በሁለት ብር ተወከለ ፤ ግን አንድ ሰው በእነዚህ ሁለት ብሮች የሚገዛው ሬት በአንድ የወርቅ ዲናር ይገዛ የነበረውን ያህል የሸቀጥ መጠን ነው ። ስለዚህ የወረቀቱ ገንዘብ ዕሴት ዘቅጧል (አሽቆልቁሏል) ፣ የመግዛት ኃይሉም ወድቋል ።

ይህ ሂደት ንረት (የተመን) ይባላል ። የሸቀጦችን ተመን ወደላይ መውጣት ያስከትላል ። ግን በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሠራተኛው ሕዝብ ምንዳዕና ገቢ ከፍ ቢልም እንኳ እንደተመኑ በፍጥነት አያድግም ። በዚህ ምክንያት ሠራተኛው ሕዝብ ነው በንረት ምክንያት የሚሠቃየው ።



ከዚያም ፤ ንረት የሀገርን ምጣኔ—ሀብት ወደ ጽኑ መበታተን የሚአመራበት ደረጃ ያደርሳል ። ጤናማ የገንዘብ መዟዟርን እንደገና ለማምጣት የተለያዩ መንገዶች አሉ ። አንደኛው የገንዘባዊ ጥገና ዘዴ በአነስተኛ የአዲስ የገንዘብ መጠን ማለዋወጥ ነው ። ሌላው ዘዴ ደግሞ ፣ የገንዘብ የልውውጥ ዕሴት ላይ የወርቅ ይዘቱን ዝቅ በማድረግ ግልፅ የዕሴት ቅነሣ (ማውረድ) ነው ።

የገንዘባዊ ጥገናዊ አሠራረሮችና ዘዴዎች አካሄድ የሚወሰነው የገዥውን መደብ ጥቅም በመጠበቅ በቡርዧዋው መንግሥት ነው ። በቡርዧዎች የሚካሄደው የገንዘባዊ ጥገና አንዱ ውጤት የሰፊውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ዝቅ ማድረግ ይሆናል ።

ዱቤ ገንዘብ

ከወረቀት ገንዘብ በተጨማሪ በካፒታሊስት አገሮች ዱቤ ገንዘብ አለ ። ይህ የመጣው ከገንዘብ የመክፈያነት ዘዴ አሠራር ላይ ነው ። የዱቤ ገንዘብ ቀላሉ መልክ የልውውጥ ሰነድ ይባላል ። ውሱን በሆነ ክፍለ — ጊዜ ተበዳሪው የተወሰነ የገንዘብ ድምር ለመክፈል እንዲችል በሰነድ መልክ የተቋቋመ ነው ። የልውውጥ ሰነድ የገንዘብን ተግባር (አሠራር) ያካሂዳል ፣ ምክንያቱም በሸቀጦች ገዥና ሻጭ ጊዜ ከአንዱ ወደ አንዱ ይተላለፋልና ።

ከመጀመሪያ የግል የንግድ የልውውጥ ሰነድ እንደዱቤ ገንዘብ ይሰራ ነበር። ይህ በገዥው ሸቀጡን በሚመለከት ረገድ የሚቀርብ ሰነድ ነው ። ግን የግል የልውውጥ ሰነድ የተዟዟረው ይህን ያቀረበውን ሰው በሚአውቁት ሰዎች ዘንድ ስለነበር ተቀባይነት ያገኘው በጥቂት የሕዝብ ክፍሎች አካባቢ ነው ። ከዚያ ቀስ በቀስ እያደገ የግል ሰነድን የመቀበልና የመቀነስ የባንኮች ተግባር ሆነ ። ግን ባንኮቹ የባንክ ኖት በሚባሉ በራሳቸው ሰነዶች ተኳቸው ። የባንክ ኖት አምጭው በማንኛውም ጊዜ ከባንኩ ጥሬ ገንዘብ የሚቀበልበት የባንከኛው ሰነድ ነው ።

የባንክ — ኖቶች በማንኛውም ጊዜ በወርቅ ወይም በሌላ ዲናራዊ ገንዘብ ሊለወጡ ይችላሉ ። በእነዚህ ሁኔታዎች ፣ ባንክ — ኖቶች ከወርቅ ዲናሮች በእኩልነት ደረጃ ይዟዟራሉ እናም አያዘቅጡም ። ካፒታሊዝም እንደዳበረ ፣ በመዟዟር ውስጥ ባለው የወርቅ መጠን አንጻራዊ ቅናሽ ነበር ። ወርቅ በአማካይ አዳይ ባንኮች ውስጥ በመጠባበቂያ ክፍያ መልክ መጠራቀሙ እየጨመረ ሄደ ። በገውውር ላይ ያለው ወርቅ በባንክ — ኖቶች በኋላም በወረቀት ገንዘብ መተካት ጀመረ ። ምንም እንኳ በመጀመሪያ የባንክ ኖቶች ፣ እንደአጠቃላይ ሕግ ሆኖ ፣ ከወርቅ የሚለዋወጡ ቢሆንም ፣ በኋላ ሊለወጡ የማይችሉ የባንክ — ኖቶች ታተሙ ። ይህ ፣ በማመጣጠን ደረጃ ፣ የባንክ — ኖቶች ከወረቀት ገንዘብ እኩል እንዲሄዱ አደረገ ።

## 5. የዕሴት ሕግ - የሸቀጥ ምርት ምጣኔ - ሀብታዊ ሕግ ፤

ውድድርና የምርት ሥርዓተ—አልባነት

የግል ባለቤትነት በሰፈነበት ፣ የሸቀጦች ምርት የሚካሄደው በግብታዊ ነው ። ምን ሸቀጥ እንደሚመረትና ፣ በምንስ መጠን እንደሚመረት ተግባሩ መምራት (መጠቆም) የሆነ ምንም ዓይነት ተቋም የለም ወይም አይኖርም ። የግል ባለ ድርጅቶችና ገበሬዎች ምርታቸውን ከሌሎች ነጋዴዎች ወይም በላተኛ አያቀናጁም ። ሥርዓተ — አልባነት ፣ ማለትም ዕቅድ—አልባ ፣ የምርት ምስቅልቅልነት ነው የሚሰፍነው ።

የምርት ሥርዓተ — አልባነት የሚጠናከረው በውድድር ነው ፣ በግል ሸቀጥ አምራቾች መካከል ለከፍተኛ ጥቅም የማምረትና የመሸጥ ሁኔታዎች ፣ ለከፍተኛ ትርፍ ለሚደረግ መራራ ትግል ። የምርት ውድድርና ሥርዓተ — አልባነት

በግል ባለቤትነት ውስጥ የተመሠረተ የሸቀጥ ምርት ሕግ ነው ። እያንዳንዱ አምራች ፣ ገበሬ ፣ የእጅ ባለሙያ ወይም ካፒታሊስት (እርግጥ ፣ ካፒታሊስቱ እራሱ ገበያ ላይ እንደሸቀጥ አምራች ይሠራል ፤) የተቻለውን ያህል ትርፍ ከሸቀጡ ሽያጭ ለማግኘት ይሞክራል ። ግን አምራቹ ካፒታሊስት ሸቀጡን በመሥራት ላይ ሲውል ፣ አስቀድሞ ለሚአመርተው ነገር ምን ያህል ተጠያቂነት እንዳለው በትክክል አይመለከትም ። እንዲሁ የሚአወቀው ሸቀጡ በቅርቡ ከፍተኛ ተጠያቂነት እንዳለው ነው ፣ እናም የተቻለውን ያህል ለማምረት ይሞክራል ። ግን ሌላ ሸቀጥ አምራቾች በዚሁ መንገድ ይሠራሉ ። በመጨረሻም ፣ እያንዳንዱ በእራሱ ኪሣራ ይሠራል ፣ ዕድልን በማመን ። ሕብረተሰቡ ከሚጠይቀው በላይ አንድ ሸቀጥ በብዛት ሲመረት ሁልጊዜ ይታያል ።

ታዲያ ምንድነው ፣ የግል ንብረት በሠፈነበት ሕብረተሰብ ውስጥ ምርትን ሥርዓት የሚአሲዘው ? ሥርዓት የሚይዘው በዕሴት ሕግ ነው ።

የዕሴት ሕግ ፣ የሸቀጦች ልውውጥ በምርቱ ላይ በሚፈሰው የሕብረተሰቡ አስፈላጊ ጉልበት መጠን መሠረት አንድ ሁኔታ የሚደርስበት የሸቀጥ ምርት ምጣኔ—ሀብታዊ ሕግ ነው ። በሌላ አነጋገር ፣ የዕሴት ሕግ ማለት አንድ ሸቀጥ ከሌላው ሸቀጥ ጋር ባላቸው ዕሴት መሠረት ይለዋወጣሉ ነው ፣ ይህም ፣ የተለዋወጡት ሸቀጦች አንድ ዓይነት የሆነ የሕብረተሰብ አስፈላጊ ጉልበት ያላቸው እኩል ናቸው ነው ። በመጨረሻ ፣ ለአንድ ሸቀጥ የሚከፈለው ክፍያ (ተመን—የዕሴት ገንዘባዊ መግለጫ እንደሆነ እናስታውስ) ከዕሴቱ ጋር መስማማት ይኖርበታል ። ግን ፣ በትክክለኛው ዕውነት ፣ የሸቀጦች ተመን ከሸቀጦች ዕሴት ወይ ከፍተኛ ወይ ዝቅተኛ ነው ፣ ምክንያቱም በቀራቢነትና በተጠያቂነት ተፅዕኖ ነው ። በገበያ ላይ የሸቀጡ ማነስ ፣ እና ተጠያቂነቱ የቀራቢነቱን ብዛት እንዲጨምር ማድረግ ፣ ተመኑ እንዲንር ፣ እናም የተገላቢጦሽ (⇄) እንደሚሆን የታወቀ እውነት ነው ። በዚህ መሠረት ፣ የዕሴት ሕግ አይሠራም ማለት ይቻላልን ? አይደለም ። የማንኛውም ሕግ አሠራር የሚታወቀው ብዙ ዕውነቶችን ከመረመርን በኋላ ነው ። ለማንኛውም ሸቀጥ ለረጅም ጊዜ የተከፈለው የተለያዩ ክፍያ (ተመን) ከተተነተነ ፣ ከዕሴቱ በላይና በታች ያፈነገጡት ተሰርዘው እናገኛለን ፣ ስለዚህም በአማካዩ ፤ ተመኖች ከዕሴቱ ጋር ይስማማሉ ።

ከምስቅልቅሉ ሌላ ፣ በምርት መገልገያዎች የግል ንብረትነት ላይ በተመሠረተው የሸቀጥ ውስጥ ሕብረተሰብ የሰፈነው የምርት ሥርዓት — አልባነት ፣ የእኩያ ሁኔታ ፣ ወይም ትክክለኛ ምጥነት ፣ በተለያዩ የምጣኔ — ሀብት ቅርንጫፎች መካከል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደረሰ ነው ። የሸቀጥ ምጣኔ — ሀብት ፣ ምርትን ሥርዓት ለሚሰጠው ፣ እና በገበያ ውድድር ውስጥ ለሚሠራው ፣ ለእሴት ሕግ ነው ዓይነተኛነትን የሚከነው ። ኤንግልስ ሲጠቁም « ውድድር ሸቀጦቻቸውን በሚለዋወጡ በአምራቾች ሕብረተሰብ ውስጥ የሸቀጥ ምርትን የዕሴት ሕግ በአሠራር ላይ በማምጣት ፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች ሊሆን የሚችለውን በሕብረተሰቡ ተፈለገ ወይም አልተፈለገ ለግሉ — ሰብ ሸቀጥ አምራቾች በኃይል ወደ ቤታቸው ይመጣላቸዋል ፡» 1 ይላል ።

በምርት መገልገያዎች የግል ንብረትነት ላይ በተመሠረተ የሸቀጥ ምርት ውስጥ የዕሴት ሕግ አሠራር እራሱን በሚከተለው አኳኋን ግልፅ ያደርጋል ።

1. የዕሴት ሕግ የምርት መገልገያዎችንና የጉልበትን ሥርጭት በተለያዩ የምርት ቅርንጫፎች መካከል በግብታዊነት ያስተካክላል ።

1. ፍ. ኤንገልስ ፣ ለመጀመሪያው የጀርመን እትመት መቅድም «ካርል ማርክስ ፣ የፍልስፍና ድህነት» ተመልከት ፣ ሞስኮ ፣ ገጽ 21



የሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍል በተለያዩ የምርት ቅርንጫፎች መካከል የተወሰነ ምጥነታዊ ግንኙነት እንዲኖር ይጠይቃል ። ያለዚህ ዓይነት ግንኙነት ፣ ምርት ሊከናወን አይችልም ። የተመን መዋለል እና ውጤቱም ያነሰ ወይም የበለጠ የምርት ትርፍ መሆኑ የምርት መገልገያዎችንና ጉልበትን አንዳንዴ በተወሰነው የምርት ቅርንጫፎች ውስጥ አንዳንዴም ውጭ እንዲፈስ ምክንያት ይሆናል ።

2. የዕሴት ሕግ የግል ሸቀጥ አምራቾችን የምርት ኃይሎችን እንዲአሳድጉ ያስገድዳቸዋል ። የሸቀጥ ዕሴት ዓይነተኛነት የሚወሰነው በእርሱ ላይ በዋለው የሕብረተሰብ አስፈላጊ ሥራ (ጉልበት) እንደሆነ እናውቃለን ። ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙትና ምርታቸውም በተሻለ ሁኔታ የተቀናጀው ፣ ወዘተ . . ከሕብረተሰቡ አስፈላጊ ዋጋ ባነሰ ሸቀጦቻቸውን ይለውጧቸዋል ። ግን ሸቀጦቹ የሚሸጡት ከሕብረተሰቡ አስፈላጊ የሥራ (የጉልበት) መጠን ጋር በሚመጣጠን (በሚስማማ) ተመን ነው ። ውጤቱ በእነዚህ አምራቾች ትርፍርፍ ገንዘብ ማግኘትና መበልጸግ ነው ። ይህም ሌሎች አምራቾች በድርጅቶቻቸው ውስጥ ቴክኒካዊ መሻሻሎችን እንዲአስተዋውቁ ያስገድዳቸዋል ። በዚህ ሁኔታ ቴክኖሎጂ ተራመደ ፤ እናም የሕብረተሰብ የምርት ኃይሎች ዳበሩ ።

3. በተወሰኑ ሁኔታዎች ፣ የዕሴት ሕግ አሠራር ወደ ካፒታሊስት ግንኙነቶች መምጣትና መዳበር ያመራል ። በትክክለኛው ዕሴት ዙሪያ ግብታዊው የተመን መዋለል የምጣኔ — ሀብት መበላለጥንና በሸቀጥ አምራቾች መካከል ያለውን ትግል ያባብሰዋል ። ውድድራዊ ትግሉ ወደ አንዳንዶቹ ጥፋት ሲአመራ ፣ ሌሎቹ ይበለፅጋሉ ። የእሴት ሕግ አሠራር የሸቀጥ አምራችን ወደ ቡርዧ እና ወዛደር መከፋፈል ሲአደርስ ፣ በአንዳንድ ካፒታሊስቶች እጅ የሕብረተሰብ ምርት ከምንጊዜውም ይበልጥ መድለብን ፣ እና የሌሎች መውደምን አምጥቷል ።

በሸቀጦች አምላኪነት (Fetishism)

የእያንዳንዱ ሸቀጥ አምራች ጉልበት ፣ በተፈጥሮው ሕብረተሰባዊ ሆኖ እያለ ፣ በቅርፅ ግን እንደግላዊ ጉልበት መሆኑን ቀድሞውኑ አውቀናል ። የጉልበት ሕብረሰባዊ አሠራር (አፈጣጠር) ፣ በሸቀጥ አምራቾች መካከል የሕብረተሰብ ግንኙነቶች የአንዱ ባንዱ ላይ የእርስ በእርስ ጥገኝነት (ተደጋጋፊነት) የሚገለጹትና የሚንጸባረቁት ፤ ሸቀጦች በሚለዋወጡበት ገበያ ውስጥ ብቻ ነው ። እዚህ ሰዎች ሳይሆኑ ግን ሸቀጦች እርስ በእርሳቸው በግንኙነት ውስጥ የሚገቡ ይመስላል ። በእነዚህ ሁኔታዎች ሸቀጦች የሰዎች የሕብረተሰብ ግንኙነቶች ጸዋሪ — አሽከርካሪ (Vehicles) ይሆናሉ ። በሸቀጥ አምራቹ የተሠራው ነገር( ዕቃ) አንዴ ገበያ ላይ ከደረሰ እና ከሌሎች ሸቀጦች ጋር በግንኙነቶች ውስጥ ከገባ ባለቤቱን መታዘዝ ያቆማል ፣ ነጻ የሆነ ኑሮ መኖር ይጀምራል ፣ እናም የዚያን ገበያ በጣም ተለዋዋጭ የሆነ ኑሮ ይከተላል ። ዛሬ አንድ ሰው ለጥንድ ጫማ 20 ብር ይቀበል ይሆናል ፣ ነገ ደግሞ 15 ብር ብቻ ። ከነገ ወዲያ ለጫማው ልውውጥ የሚውል ምንም ነገር ላይገኝ ይችላል። በኋላ ደግሞ እንዲያውም ሰዎች ጫማ ለማግኘት እግራቸው እስኪላጥ ይንዙና ለጥንድ ጫማ ብዙ ገንዘብ ለመክፈል እንደሚዘጋጁ ግልፅ ይሆናል ።

ይህ ነጻ ፣ ሙሉ በሙሉ በገበያ ላይ የሸቀጥ አጋጣሚ ሕይወት ፤ ሰዎችን ሸቀጥ ከተፈጥሮው አብረውት ያልመጡ የተለዩ ጸባዮች እንዳሉት አድርገው እንዲቆጥሩ ያስገድዳቸዋል ። የሕብረተሰብ የምርት ግንኙነቶች በሚኖሩበት ቦታ ፣ ሰዎች የሚአዩት በነገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ነው ። በሰዎች መካከል ያሉት ግንኙነቶች ከነገሮች (ከዕቃዎች) ግንኙነቶች በስተጀርባ ይደበቃሉ ።

ይህ በምርት መገልገያዎች የግል ንብረትነት ላይ የተመሠረተው የሸቀጥ ምጣኔ — ሀብት ጸባይ የሆነው የምርት ግንኙነቶች መለወጥ በማርክስ « የሸቀጦች አምላኪነት » ተብሎ ይጠራ ነበር ።*

ከሸቀጥ ምርት ዕድገት ጋር ፤ የሸቀጦች አምላኪነት ጨመረና ይበልጥ እየ ተስፋፋ ሄደ ። ገንዘብ ሲመጣ ፤ በደንብ የተጠቃለለ መልኩን (ቅርጹን) ያዘ — የገንዘብ አምላኪነትን ። ሁሉም ነገሮች በወርቅ ሊገዙ ይቻላል ። እና ይህም እንደገንዘብ ተፈጥሮአዊ ጸባይ በመሆን ለሰዎች ዐይን ተከሰተ — እንደወርቅ ። በእውነታው ግን በሸቀጥ ምርት ውስጥ ፤ የተወሰኑ የሕብረተሰብ ግንኙነቶች ውጤት ነው ።

የሸቀጦችን አምላኪነት ምሥጢር ለመግለጽ (ዕርቃኑን ለማስረቀት) የመጀሪያው ሰው ማርክስ ነበር ። የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ሲወገድ ብቻ የሸቀጦች አምላኪነትም ይጠፋል ።

# ምዕራፍ ፫ ፣

# ካፒታል (ወረት) እና ትርፍ ዕሴት ምንዳዕ በካፒታሊዝም ውስጥ

በአንድ በተወሰነ የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ላይ ፤ የሸቀጥ ምርት ለካፒታሊዝም መምጣት መንገድ ይከፍታል ። ካፒታሊዝም ሲባል ምንድነው ? ሌኒን ቀላልና ቁርጥ ያለ መግለጫ ሰጥቶታል ። «ካፒታሊዝም» ይላል ፤ « መሬቱ ፤ ፋብሪካው ፤ መሣሪያው ፤ ወዘተ . . . ፤ በጣት ለሚቆጠሩ የመሬት ባለንብረቶችና ካፒታሊስቶች የሆነበትን ፤ ሠፊው ሕዝብ ግን ምንም ንብረት የማይገዝበት ወይም ቢኖረውም እንኳ በጣም አነስተኛ ንብረት ፤ እናም እራሱን እንደሠራተኛ ለማስቀጠር ለሚገደድድበት ሕብረተሰብሥርዓት የተሰጠ ስም ነው ። » 1 ይላል ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ሠራተኛ ሕዝቦች ግላዊ ነጻነት አላቸው ግን ከምርት መገልገያዎች ተገልለዋል ፤ ስለዚህም ከኑሮ መገልገያዎችም ጭምር ። በዚህ ምክንያት ለካፒታሊስቶች እንዲሠሩ ይገደዳሉ ፤ አለያም በረሃብ ይሞታሉ ።

በእርግጥ ፤ እንዴት ነው የምርት መገልገያዎች በጣት በሚቆጠሩ ጥቂት ቡድኖች እጅ የሚደልቡበት ሁኔታ የሚፈጠረው ?

## 1. የካፒታል (ወረት) ጥንታዊ ክምችት

ለካፒታሊዝም መምጣት ሁኔታዎች

የቡርዥዋ ርዕዮተ — ዓለማውያን ሆን ብለው የካፒታሊስቶችንና የወዝ አደሩን መደብ የአመጣጥ ታሪክ ያውከገረግሩታል ። ከሕረተሰብ ለምን በድኅና ሀብታም እንደተከፈለ የሚአሳየውን ትክክለኛ ያልሆነውን የቂሳዊ — ሀብት አከፋፈል ፤ የፈጠራ ተረት እርግጠኛ ለማድረግ የተቻላቸውን ያህል ያደርጋሉ ። ከታሪክ በመገንጠል ፤ ዓለም የተለያዩ ጸባዮች ባሏቸው ሰዎች ተሞልታ እንደነበር በማሰብ — አንዳንዱ ባለንብረትና ቆጣቢ ፤ ሌሎች ሰነፍ እንደሆኑ ይናገራሉ ። የመጀመሪያው ቀስ በቀስ ሁሉንም ዓይነት

---

* "አምላኪነት" (Fetishism) የሚለው ቃል የሚያመለክተው የነገሮችን ሃይማኖታዊ ጣዖትነት ነው ፤ ሰዎች እራሳቸው የሠሯቸውን ። እንደስዕድ አምልኮአውያን ሰዎች ከሆነ "ጣዖት" ኃይል—መለኮታዊ ሁሉን ሠሪነት ኃይል አለው ።

1. . ቪ.አይ. ሌኒን ፤ ጠቅላላ ሥራዎች ፤ ቅጽ ፋ—ዋ ከቡ ፤ ገጽ—311



መበልጸጊያ ሲአከማች ፤ ሁለተኛው ግን ሁሉም በነበሩበት ቀሩ — ለማኞች ሆኑ ይላሉ ። ይህ ለካፒታሊዝም አመጣጥ ምንጭ መግለጫ ከዕውነቶች ጋር ምንም የሚአገጣጥመው ነገር የለም ።

ለካፒታሊዝም መንስኤ ሁለት መሠረታዊ ሁኔታዎች አሉ — በመጀመሪያ ፤ ግላዊ — ነጻነት ያላቸው ግን የምርት መገልገያ ወይም የኑሮ መደጎሚያ የሌላቸው እና ስለዚህም ፤ የጉልበት ኃይላቸውን መሸጥ የሚኖርባቸው ሰዎች መኖር ፤ እና ሁለተኛ ፤ በተወሰኑ ግለሰቦች እጅ የምርት መገልገያዎችና መጠኑ እጅግ በርካታ ገንዘብ መድለብ ።

እነኝህ ሁኔታዎች ወደ ሕልውና የመጡት በትናንሽ አምራቾች መካከል የመከፋፈል ሂደት በተካሄደበት ፤ በመልከኝነት ነው ። የካፒታሊስት ሥልተ — ምርት መመሥረት እየጨመረ የሄደው በመሬት ባለቤቶች ፤ በአዲስ መጭው ቡርዧዋና በመንግሥት — ኃይል አካሎች ሰፊውን ሕዝብ በአሰቃቂ ሁኔታ የመጨንና የመጨቆን ሥልት ነው ።

የአምራች ከምርት መገልገያዎች መገለል ። የሀብት በጥቂቶች እጅ መከማቸት

ጥንታዊ ክምችት ተብሎ የሚታወቀው ሂደት ለካፒታሊዝም መምጣት የሚአስፈልጉትን ሁኔታዎች የሚፈጥሩትን አስገባ ። « ጥንታዊ ክምችት » ማርክስ ሲጽፍ ፤ «አምራቹን ከምርት መገልገያዎች ከማፋታት ታሪካዊ ሂደት በቀር ምንም አይደለም ። » 1 ይላል ።

ይህ ሂደት የካፒታልን (ወረትን) ቅድመ — ታሪክ ያጠቃልላል ። ጥንታዊ ክምችት ልዩ በሆነ መንገድ መልክ የያዘው የመሬት ከበርቴዎች የገበሬዎችን የጋራ መሬት በኃይል በያዙበትና ከዚያም አልፎ ከቤት ንብረታቸው ባባረሩበት በእንግሊዝ ነው ። የመሬት ከበርቴዎች ከገበሬዎች የወሰዱትን መሬት ወደ በጐች ግጦሽነት አዞሩት ወይም ለገበሬዎች አከናተሩት ። በዚያን ጊዜ ሱፍ እያደገ ለሄደው ጥጥ ፋብሪካ ከፍተኛ ተጠያቂነት ነበረው ።

አዲስ መጪው ቡርዧ የመንግሥት መሬትን ለመያዝና የቤተክርስቲያንን ንብረት ለመንጠቅ ከዚህም አልፎ ሄደ ። ከመኖሪያ ሕልውናዎች የተገለለ ሥፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ ተዘዋዋሪ ፤ ለማኝ እና የመንገድ ሰዎች ሆኑ ። የመንግሥት ባለሥልጣኖች በተበዝባገሮች ላይ ግፈኛ ሕጎች አወጡ ። በ15ኛው ምዕተ — ዓመት መዳፈያ ላይና በ16ኛው ምዕተ ዓመት ንብረታቸውን ለመከላከል ባሰቡት ገበሬዎች ላይ « ትርጉም የለሽ ሕጐች » በመባል የታወቁት በተላለፉበት ጊዜ ይህ በእንግሊዝ ዕውነት ነበር ። እነዚህ የጠፉት (የተደመሰሱት) ፤ የተዘረፉ ሰዎች በጋሉ ብረቶች በመጠበስ ፤ በመገረፍ ፤ በመሠቃየት ወደ ካፒታሊስት ድርጅቶች ተነዱ ።

በዚህ ኃይላማ የገበሬዎች ከመሬታቸው መባረ ርሁለት ውጤቶች ተገኝተው ነበር — በመጀመሪያ ከሌሎች ሲነጻጸሩ አነስተኛ ቡድን በሆኑ ሰዎች መሬት የግል ንብረት ሆኗል ፤ ሁለተኛ ፤ ቁጥሩ ይህ ነው የማይባል የምንዳዕ ሠራተኛ ወደ ኢንዱስትሪዎች መጉረፍ መድን አገኘ ። ስለሆነም የመጀመሪያው የካፒታሊዝም መምጣት አስፈላጊው ሁኔታ ተፈጠረ — የራሳቸው የግል ነጻነት ያላቸው ፤ ግን ከምርት መገልገያዎች የተገለሉ ፤ ንብረት — አልባ ሰፊ ሕዝብ መኖር ።

ትላልቅ የካፒታሊስት ድርጅቶችን (ይዞታዎችን) ለማቋቋም የሚአስፈልገውን ታላቅ ሀብት ለማድለብ የሚከተሉት መሠረታዊ ዘዴዎች እንዳሉ ማርክስ ይጠቁማል — 1/ ቅኝ ግዛታዊ ሥርዓት ኋላ — ቀር የሆኑትን የአሜሪካ ፤ እስያና አፍሪቃ ሕዝቦች መዝረፍና በጦርነት መጥመድ ፤ 2/ የግብር ዘዴ — የሞኖፖሊ

---

1 ኬ. ማርክስ ካፒታል ቅጽ 1. ገጽ 714

ሌሎችዎች መፈጠርና በሕዝቡ ላይ የተጣለውን የታክስ (ግብር) ክፍል የመውሰጃ ዘዴዎች ፡ 3/ የመከላከል ዘዴ — መንግሥት የካፒታሊስት ኢንዱስትሪን መዳበር ይደግፋል ፡ እና 4/ ጭካኔ የተሞላበት የብዝበዛ ዘዴ ናቸው ።

በዘውደኛይቱ ሩሲያ የጥንታዊ ክምችት ሂደት የተጀመረው ገባርነት ከመወገዱ ቀደም ብሎ ነው ፡ በሌሎችም አገሮች ይህንኑ መስመር ነው የተከተለው ።

ጥንታዊ ክምችት እናቱ ላይ የደረሰው በ1861 ዓ ም ለውጥ በሩሲያ ነው ። ገበሬዎች የተዘረፉበት ደረጃ ሊገመገም የሚችለው ከለውጡ 50 ዓመት በኋላ 30ሺ. የመሬት ከበርቴዎች 189 ሚሊዮን ኤከር (ገመድ) በቁጥጥራቸው ሥር ማድረጋቸው እንድ ዕውነት ነው ፡ ማለትም ፡ ለ10 ሚሊዮን ተኩል የገበሬ ቤተሰቦች ንብረት የነበረውን ያህል መሆኑ ነው ። ለመኖር ከፈለገ አርሶ — አደሩ ወደከተማ መሄድ ነበረበት ። የ1861 ዓ ም ጥገናዊ ለውጥን በመገምገም ፡ ሌኒን ፡ « ገበሬውን በመጸረር በእርሻ ውስጥ የመጣውን ካፒታሊዝም ዝንባሌ በመከተል የሰፊውን ሕዝብ መብት የመጣስ የመጀመሪያውን ክፍል ይወክላል ። » 1 ይላል ።

ስለዚህ ፡ ጥንታዊ ክምችት የግዙፍ የጉልበት ሠራዊት ፡ ከምርት መገልገያዎች የተገለለ ፡ እና ይህ ነው የማይባል እጅግ ብዙ ሀብት በጣት በሚቆጠሩ ግለ — ሰቦች የመካበት ውጤት ላይ ደረሰ ።

## ፪ የገንዘብ ወደ ካፒታል (ወረት) መለወጥ

የወረቱት አጠቃላይ ቀመር

ገንዘብ በራሱ ወረትን አይዝም ። ካፒታሊዝም ከመምጣቱ በፊት ይኖር እንደነበር የታወቀ ነው ። ገንዘብ ወደ ካፒታል (ወረት) የተለወጠው በተወሰነ የሸቀጥ ምርት ዕድገት ደረጃ ብቻ ነው ። ከካፒታሊዝም በፊት በሚቀጥለው ቀመር ዓይነት የሚገለጽ የሸቀጥ መዟዟር (ዑደት) ነበር፡— ሸ—ገ—ሸ— (ሸቀጥ—ገንዘብ—ሸቀጥ) ማለትም ፡ የአንድ ሸቀጥ መሸጥ ሌላ ለመግዛት ነው ። የካፒታል (ወረት) ቅስቃሴ የሚገለጸው በሌላ ቀመር ነው ፤ ገ—ሸ—ገ—(ገንዘብ—ሸቀጥ—ገንዘብ) ፡ ማለትም ፡ ግዥ ለመሸጥ ።

ሸ—ገ—ሸ የሚለው ቀመር የቀላል ሸቀጥ ምርት ጸባይ ነው ። በዚህ መልክ አንድ ሸቀጥ ከሌላው ሸቀጥ የሚለዋወጠው በገንዘብ ተወካይነት ነው ። ገንዘብ እንደአማካይ አለዋዋጭ ነው የሚሠራው ፡ ወረት አይደለም ። የሸቀጥ ልውውጥ ዓላማው ግልፅ ነው ። ለምሳሌ ፡ ጫማ ሠሪ ጫማዎቹን የሚሠራው ዳቦ ለመግዛት ነው ። ይህም አንድ ጠቀሜታ ዕሴት በሌላ ይለወጣል ነው ።

ገ—ሸ— ገ የሚለው ቀመር ፡ ሙሉ በሙሉ ልዩ የሆነ ጸባይ ያለውን ፡ ማርክስ የካፒታል (ወረት) ጠቅላላ ቀመር ብሎታል ። እዚህ ገንዘብ የመነሻ ነጥብ ነው እናም ለማካሄድ እንደመግዣ ነው የሚገለግለው ፡ ማለትም ፡ እንደካፒታል (ወረት) ይሠራል ። ካፒታሊስቱ በገንዘቡ እንደገና ወደገንዘብ ለመለወጥ የተወሰኑ ሸቀጦች ይገዛል ። የመጀመሪያና መጨረሻ ነጥቦች ይስማማሉ ፡ በመጀመሪያው ሂደት (ከመነሻው) ካፒታሊስቱ ገንዘብ አለው እናም በመጨረሻም እንደዚሁ ።

ግን በመጨረሻው ሂደት ካፒታሊስቱ የሚኖረው የገንዘብ መጠን እንደመጀመሪያው ከሆነ የካፒታል (ወረት) ቅስቃሴ ዓላማ — ቢስ ይሆናል ። የወረት ሕልውና አጠቃላይ ትርጉሙ ከዚህ ቅስቃሴ በኋላ ከመጀመሪያው የበለጠ ገንዘብ መኖር እንዳለበት ነው ። የካፒታሊስቱ ጠቅላላ ከንዋኔ የመጨረሻ (ዋና) ዓላማ ትርፍ መሰብሰብ (መምጠጥ) ነው ። ስለዚህ በካፒታሊስት ሁኔታዎች የገንዘብ ቅስቃሴ በሚከተለው ቀመር ተገልጿ ነበር፡- ገ—ሸ—ገ[1] ፡ 71 ፡ የቆመው ከመጀመሪያ ከወጣው ገንዘብ ፡ ሌላ የተወሰነ ጭማሪን ይዞ ነው ። ይህ ጭማሪ ወይም ከዋናው ገንዘብ በላይ ትርፍርፉን ፡ ማርክስ ትርፍ ዕሴት ብሎ ጠርቶታል ። ትርፍ ዕሴትን ለመወከል «S»ን በአማርኛ እንወስደውና « ት ዕ » ተጠቅሟል ።

1. ቪ. አይ ሌኒን የበሻል ዴሞክራቶች ገጠራዊ (ጉርፓ) ፕሮግራም በመጀመሪያው የሩሲያ አብዮት 1905—07 ሞስኮ ገጽ 182



ካፒታሊስቶች ገንዘብን የሚጠቀሙት በሸቀጥ ዝውረት (ዑደት) ውስጥ እንደአማካይ ሳይሆን ፡ ግን ትርፎችን የማግኛና ለግል መበልጸጊያ ዘዴ ነው ። በካፒታሊዝም ውስጥ ይህ የገንዘብ ቅስቃሴ ገንዘብ የሚጨምር ንብረት የሚሆንበት የማያቋርጥ ሂደት ነው ። በራሱ የሚአድግ እሴት ፡ ወይም ትርፍ ዕሴት የሚአስገኝ ዕሴት ፡ ካፒታል (ወረት) ተብሎ ይጠራል ።

ታዲያ ፡ እንዴት ነው የዚህ የወረት መጨመር የሚካሄደው ? በመዟዟር አድማስ ውስጥ በመግዛትና በመሸጥ (ትራንዛክሽን) መለዋወጥ ይሆን ? እንዲህ ብሎ ማሰብ ስህተት ይሆናል ፡ ምክንያቱም ይህ ትራንዛክሽን (መለዋወጥ) በማዟዟር አድማስ ውስጥ እንዲሁ የዕኩያዎች መለዋወጥ ነው ፡ በዋናነት (ዓይነተኛነት) እኩል የሆኑ እሴቶች ። ይሁንና ፡ ሁሉም ሻጮች ሸቀጦቻቸውን ሲሸጡ ያንኑ 10% ለሻጮች 10%ከዕሴታቸው በላይ አትርፈው ቢሆን ፡ ገዥዎች በሆኑ ጊዜ ፡ ያንኑ 10% ለሻጮች ይከፍላሉ እንበል ። ስለዚህ ፡ የሸቀጥ ባለቤቶች በሻጭነት የሚአገኙትን በገዥነታቸው ያጡታል ። ቢሆንም ፡ እውነቱን ከተከተልን ፡ በሁሉም የካፒታሊስት መደብ የካፒታል (የወረት) መጨመር እንደተጠበቀ ነው ።

ሸቀጦችን በዕሴታቸው የሚገዙትና የሚሸጡት ፡ በምንም ይሁን ትርፍ ዕሴት እንዴት እንደሚጨምቁ ጥያቄ ይነሣል ።

የካፒታል (ወረት) ጠቅላላ ቀመር ሁለት አካሎች ይኖሩታል — ገንዘብና ሸቀጥ የሚባሉ ። ስለዚህም ፡ የዕሴት ዕድገት የሚካሄደው በገንዘብ ወይም በሸቀጦች ውስጥ በሚፈጠረው ለውጥ አማካይነት ነው ። ይሁንና ፡ ገንዘብ በራሱ ዕሴቱን ሊለውጥና ጭማሪ ሊአስገኝ እንደማይችል ይታወቃል ። ይህም ማለት የዕሴት የመጨመር ምንጭ መታሰብ ያለበት ከሸቀጦች አንጻር መሆኑን ነው ።

ገንዘብ ወደ ካፒታል (ወረት) እንዲለወጥ ፡ ካፒታሊስቱ በሚጠቀምበት ጊዜ ራሱ ካለው ዕሴት የበለጠ ዕሴት ሊአስገኝ የሚችል ሸቀጥ በገበያ ላይ ማግኘት አለበት ። ይህ ሸቀጥ የጉልበት — ኃይል ነው ።

የጉልበት—ኃይል እንደሸቀጥ ፡ የጉሱ ዕሴትና ጠቀሜታ ዕሴት

የጉልበት — ኃይል ሰው ቁሳዊ — ሀብትን በሚአመርትበት ጊዜ ሁሉ የሚጠቀምበት ፡ የሰው አካላዊና አእምሮአዊ ችሎታዎች ሕብረት ነው ።በማንኛውም ሕብረተሰብ ፡ የጉልበት ኃይል ለምርት ዓይነተኛ ነገር ነው ። ይሁንና ፡ በካፒታሊዝም ውስጥ ብቻ ሸቀጥ ይሆናል ።

እንደሌሎች ሸቀጦች ሁሉ ፡ «የጉልበት—ኃይል» ዕሴትና ጠቀሜታ — ዕሴት ሊኖረው ይገባል ፡ አለውም ። የጉልበት — ኃይል ዕሴት የሚወሰነው ፡ እንደሌሎች ሸቀጦች ሁሉ ፡ እርሱን እንደገና ለማምረት በሚአስችለው የሕብረተሰቡ አስፈላጊ የሥራ — ጊዜ ነው ። የጉልበት — ኃይል የሰው የመሥራት ችሎታ ነው ። ሊኖር የሚችለው ባለቤቱ (ሠራተኛው) እስከኖረ ድረስ ነው ። እናም እራሱን ለመጠገን ፡ ሠራተኛው የተወሰነ የሕይወት መደጐሚያ ዘዴ ይሻል ። ስለሆነም ፡ የጉልበት— ኃይል ዕሴት የሚወሰነው ሠራተኛውን እራሱን ለመጠገን በሚአስፈልገው መደጐሚያ ዕሴት ነው ።

የሠራተኛው አስፈላጊ መደጐሚያዎች መጠንና ዓይነት ጥገኛ የሚሆኑት በተለያዩ አገሮች በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ነው በምጣኔ ሀብት

የተዋጋበት ጊዜ ርዝመትና ትግሉ ምን ያህል ድል እንዳገኘ (ግቡን እንደመታ) ።
የተዋጋበት ጊዜ ርዝመትና ትግሉ ምን ያህል ድል እንዳገኘ በአንድ ሀገር በተወሰነ የታሪክ
የጉልበት — ኃይል ዕሴት ሠራተኛው መደብ በአንድ ሀገር በተወሰነ የታሪክ ይጨምራል ። ማርክስ
ወቅት ያዳበራቸውን ሕብረተሰባዊና ባሕላዊ ፍላጐቶችንም ይጨምራል ። ማርክስ
ሲጠቁም « ስለዚህ ከሌሎች ሸቀጦች ጋር አነጻፅሮ በመለየት ውስጥ ፣ ታሪካዊና
ሞራላዊ አካል የጉልበትን — ኃይል ዕሴት ለመወሰን ይመጣል » 1 ብሏል ።

የጉልበት ኃይል በሠራተኛው ቤተሰቦች ነው የሚታደሰው ። በዚህ ምክንያት
የጉልበት ኃይል ዕሴት በሠራተኛው ቤተሰቦች የሚጠየቀውን የመደጎሚያ ዘዴ
ዕሴትንም መጨመር ይኖርበታል ።

በመጨረሻም ፣ እንድስው የሰለጠነ — ሠራተኛ ሆኖ አይወለድም ። የሠለ
ጠነ—የጉልበት ኃይል ለማግኘት ፣ የማሠልጠኛ ወጭ መኖር አለበት ። ይህ ወጭም
በጉልበት — ኃይል ዕሴት ውስጥ ይጨመራል ። በሌላ አባባል ፣ የጉልበት ኃይል
ዕሴት የሚወሰነው በአንድ በተወሰነ ሀገር የሠራተኛውን አካላዊ ጥንካሬ ለማቆየት
የእርሱንና የቤተሰቡን ሶሻላዊና ባሕላዊ ፍላጐቶች ለማርካትና የሙያ ጠበብትነቱን
የሚአገኝባቸውን ወጭዎች ለመሸፈን በሚአስፈልጉት ዓይነተኛ ነገሮች ዕሴት
ነው ። በገንዘብ መልክ የሚገለጽ (የሚብራራ) የጉልበት — ኃይል ዕሴት ፣ የጉልበት
ኃይል ተመን ይባላል ። በካፒታሊዝም ውስጥ ፣ ምንዳዎች የጉልበት ኃይል ተመኖች
ናቸው ።

የጉልበት ኃይል ፣ ሸቀጥ በመሆኑ የምንዳዕ — ሠራተኛው ከጉልበት — ኃይሉ
ዕሴት የበለጠ ዕሴት ለመፍጠር ባለው ሂደት ውስጥ ያለውን ችሎታ የያዘ የጠቀ
ሜታ — ዕሴትም አለው ። ይህ የጉልበት — ኃይል ጸባይ ነው የትርፍ — ዕሴት
ምንጭ በመሆን ካፒታሊስቶችን እንዲረባረቡ የሚስባቸው ።

## 3. የትርፍ — እሴት ምርት

### የካፒታሊስት ብዝበዛ

በካፒታሊዝም ውስጥ የሥራ ሂደት ልዩ ባሕሪዎች

የጉልበት — ኃይል ሁልጊዜም በተወሰነ ሕብረተሰባዊ መልክ
በሚከናወን የሥራ ሂደት ጊዜ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው ።
ይህ ሕብረተሰባዊ መልኩ የምርት ግንኙነት ተብሎ ነውየሚታወቀው ፣ እና የተመ
ሠረተውም በምርት መገልገያዎች የንብረትነት መልክ ነው ። የሥራ ሂደት ልዩ
ባሕሪዎች ጥገኛ የሚሆኑት በማንኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ የምርት መገልገያዎችን
ማን ያዝባቸዋል ? በሚለው ላይ ነው ። በካፒታላዊ ሁኔታዎች የምርት መገልገያዎች
የካፒታሊስቱ ናቸው ፣ ሠራተኛው ግን ከዚያ ተገልሏል ። በዚህ ምክንያት ፣ የሚከ
ተሉት የሥራ ሂደት ልዩ ባሕሪዎች የካፒታሊዝም ክስቶች ይሆናሉ ፣ —

በመጀመሪያ ፣ ሠራተኛው ፣ ጉልበቱ የካፒታሊስቶች የሆነው ፤ በካፒታሊስ
ቶች ተቆጣጣሪነት ይሠራል ። ካፒታሊስቱ ምን እንደሚመረት ፣ ምን ያህል እና
በምን ዘዴ እንደሚመረት ይወስናል ።

ሁለተኛ ፣ የሠራተኛው ጉልበት ብቻ አይደለም የካፒታሊስቱ ንብረት የሚ
ሆነው ፤ የጉልበቱም ውጤት ጭምር እንጂ ።

በካፒታሊዝም ውስጥ እነኝህ የሥራ ሂደት ልዩ ጸባዮች የሠራተኛውን ሥራ
ወደ ከባድና አስገዳጅ (የማይቀር) ሸክም ይለውጡታል ።

---

1. ኪ ማርክስ ፣ ካፒታል ፣ ቅጽ 1, ገጽ 171



የዕሴት ዕድገት ሂደት የካፒታሊስት ብዝበዛ

የካፒታሊስት ምርት የጠቀሜታ ዕሴትንና የዕሴትን ዕድገት
የመፍጠር ሂደት ጥምረት (ውህደት) ነው ።

በሸቀጥ ምጣኔ — ሀብት ውስጥ የጠቀሜታ — ዕሴት ፣ ዕሴት ሳይመረት ሊመ
ረት (ሊገኝ) አይችልም ። አንድ ሠራተኛ ሸቀጥ በሚሠራበት ጊዜ ጉልበቱን ያፈ
ሳል ። የጉልበት አፈጣጠር ሁለት መልክ አለው ። በአንድ በኩል ፣ ሥውር ጉልበት
ይሆንና የሸቀጡን ዕሴት ይፈጥራል ። በሌላ በኩል ፣ አካላዊ (ግልፅ) ጉልበት በመ
ሆን የጠቀሜታ — ዕሴትን ያስገኛል ። ለካፒታሊስቱ ፣ የጠቀሜታ ዕሴቶች ምርት
ዓላማውን የማግኛ ዘዴ ብቻ ነው ። ይህ ዓላማና ለከፒታሊስት ምርት ዋና ቀስቃሽ
(አነሳሽ) የትርፍ ዕሴት ምርት ነው ።

ትርፍ እሴት እንዴት እንደሚገኝ እንገንዘብ፦

ካፒታሊስቱ ሥራውን በሚጀምርበት ጊዜ ፣ ለማምረት የሚአስፈልገውን
ሁሉ ነገር ከገበያ ይገዛል — መኪና ፣ የማሺን ዕቃዎች ፣ ጥሬ ዕቃዎች ፣ ነዳጅና
የጉልበት ኃይል ። ከዚያ ማምረት ይጀመራል ። ማሺኑ እና የማሺን ዕቃዎች ይሰራሉ ፣
ሠራተኞች ጉልበት ያፈሳሉ ፣ ነዳጅ ይፈጃል ፣ ጥሬ ዕቃዎች ወደ አለቀለት ምርት
ይለወጣሉ ። ሸቀጡ ዝግጁ ሲሆን ካፒታሊስቱ ገበያ አውጥቶ ይሸጥና በተቀበለው
ገንዘብ የበለጠ ጥሬ — ሀብት ፣ ማሺኖች ፣ የጉልበት — ኃይል ፣ ወዘተ . . . ይገዛ
በታል ። በሌላ ቃል ፣ ዙረቱ ይደጋገማል ። ይህ ዙረት እንዲህ ሆኖ ሊታይ ይችላል።

ገ—ሸ <ጉ.ኃ / ም.መ . . . . . . . ም(ውጤት) . . ሸ1—ገ1

ገንዘብ — ሸቀጥ (የጉልበት ኃይልና የምርት መገልገያዎች) — ምርት — ሸቀጥ
ገንዘብ ።

ያለቀለት ሸቀጥ ዕሴት ምንድነው ?
ካፒታሊስቱ አንድ የልብስ ፋብሪካ ባለቤት ነው ብለን እናስብ ። ልብስ
ለማምረት የስፌት መኪኖች ፣ የሱፍ ጨርቅ ፣ ማሚያዎች (ገበር ፣ አዝራሮች ፤ ክር
ወዘተ . . . ) እና የጉልበት — ኃይል ይገዛል ። 500 ልብሶች ለመሥራት
1,500 ያርድ ሱፍ ጨርቅ እያንዳንዱን ያርድ 30 ብር ገዛ ፤ ማለትም ከ45,000
ብር ዕሴት ዕኩል የሚሆን ዕቃ ። በማሙያዎቹ በእያንዳንዱ ልብስ 30 ብር ፣ ማለ
ትም በአጠቃላይ 15,000 ብር አጠፋ ። የአምስት መቶ ልብሶች ምርት የስፌት
መኪናዎችን መበላትና ሌሎችንም ወጭዎች (የመብራት ፣ የማሞቂያ ፣ ወዘተ . . . )
እስከ 5,000 ብር ድረስ በውስጡ ያስገባል ። ጉልበትን ለመቅጠር የወጣው ወጭ
(500 ሠራተኞች ፣ እያንዳንዳቸው 5 ብር በየቀኑ የሚያገኙ ) 2,500 ብር ይሆናል ።

ስለዚህ ካፒታሊስቱ ለማምረት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ይዟል ። ለ500
ልብሶች ጠቅላላ ወጭው እንደሚከተለው ነው ፦

| | | |
|---|---|---|
| የሱፍ ልብሶች ዕሴት . . . . . | 45,000 | ብር |
| የማሙያዎች ዕሴት . . . . . | 15,000 | ,, |
| የዕቃ መበላት (ማለቅ) ዕሴት . . | 5,000 | ,, |
| የጉልበት — ኃይል ዕሴት . . . | 2,500 | ,, |
| ጠ ቅ ላ ላ . . . . , . | 67,500 | ,, |

የአንድ ሙሉ ልብስ ዕሴት (67,500 ፥ 500) 135 ብር ነው ። ካፒታሊስቱ
የዚሁ ተመሳሳይ የሆኑ ልብሶች በገበያ ላይ በ135 ብር ሲሸጡ ያያል ። ስለዚህ እር
ሱም ልብሱን በዚህ ተመን መሸጥ ይኖርበታል ። ለማምረት ፣ ካፒታሊስቱ 67,500
ብር እንዳወጣ (እንደፈጀበት) ይታወቃል ፤ እናም የተመረቱት ሸቀጦች ከተሸጡ

በኋላ ( 135 ብር) ያንኑ 67,500 ብር ብቻ ወስድዋል ። ምንም ትርፍ ዕሴት አልተፈጠረም ፤ ስለሆነም ገንዘብ ወደ ካፒታል (ወረት) አልተሸጋገረም ወይም አልተዛወረም ።

ታዲያ እንዴት ነው ትርፍ ዕሴት የሚገኘው ?

ማስታወስ ያለብን ነጥብ ሠራተኛው የጉልበት — ኃይሉን ዕሴት እንደገና የሚአመርተው በጠቅላላው የሥራ ቀን ውስጥ ሳይሆን ግን ከሥራው ቀን በተወሰኑ ጊዜ ውስጥ እንበልና በአምስት ሰዓት መሆኑን ነው ። ግን ካፒታሊስቱ በቀን ከአምስት ሰዓት የበለጠ እንዲሠራ ሠራተኛውን ያስገድደዋል ። ካፒታሊስቱ የጉልበት—ኃይሉን የቀን ዕሴት ከፍሏል እናም ለጠቅላላው የሥራ ቀን ጊዜ ለሸቀጡ ጠቀሜታ — ዕሴት ባለቤትም ነው ። በዚህ ምክንያት ሠራተኛውን ለስምንት ፣ ለአሥር ወይም ለሰባት ሰዓት እንዲሠራ ያስገድደዋል ። ይህ የሥራ ሂደትን ማራዘም የጉልበት — ኃይል ተብሎ ከሚታወቀው ሸቀጥ በላይ ሠራተኛው ይበልጥ ዕሴትን በመፍጠሩ ላይ ይከሠታል ።

ካፒታሊስቱ ሠራተኛውን ለአምስት ሰዓት ሳይሆን ለአሥር ሰዓት እንዲሠራ ያደርገዋል ብለን እንውሰድ ። በአስር ሰዓት ውስጥ ሠራተኞቹ (በምሣሌአችን ፣ 500 አሉ) የምርት መገልገያዎቹን ሁለቴ ይጠቀሙባቸውና ዕጥፍ ምርት ያመርታሉ ፣ ማለትም ፣ 1,000 ልብሶች ይሠራሉ ።

አሁን እስቲ የካፒታሊስቱን ወጭ እናጢን —

| | | |
|---|---|---|
| የሱፍ ልብሶች ዕሴት . . . | 90,000 | ብር |
| የማሙያዎች ዕሴት . . . | 30,000 | ,, |
| የዕቃ መበላት (ማለቅ) ዕሴት | 10,000 | ,, |
| የጉልበት — ኃይል ዕሴት . . | 2,500 | ,, |
| ጠቅላላ . . . . . . | 132,500 | ,, |

በአሥር — ሰዓት የሥራ ቀን ውስጥ ሠራተኞች 1,000 ልብሶች አምርተዋል ። በገበያ ላይ ሽያጫቸው (እያንዳንዱ 135 ብር) ለካፒታሊስቱ 135,000 ብር አስገኝቷል ። 132,500 ብር በማውራት 135,000 ብር አስገብቷል (ተቀብሏል) ። መጀመሪያ በሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ አሁን በ2,500 ብር አድጓል ። ይህ 2,500 ብር ድምር ትርፍ ዕሴት ነው ። ስለዚህ ገንዘብ ወደ ካፒታል ተሸጋገረ (ተዛወረ) ።

የትርፍ ዕሴት መገኘት የሚወሰነው ሠራተኞች የራሳቸውን የጉልበት ዕሴት እንደገና ለማምረት ከሚአስፈልገው በላይ በሚአፈሱት የሥራ ሰዓት ነው ። ስለሆነም ፣ ትርፍ ዕሴት በካፒታሊስቶች የሠራተኛው መደብ የመበዝበዝ ውጤት ነው ።

የሰውን በሰው ብዝበዛ በካፒታሊዝም የተፈጠረ አይደለም ፤ ከእርሱ በፊትም ይኖር ነበርና ። በባሪያ አሳዳሪና በመልከኛ ሕብረተሰብ ውስጥ ፤ የባሮችና የገባሮች ጉልበት የግዴታ ሥራ ነበር ፤ መበዝበዛቸው የተደበቀ ወይም ተላብሶ የቀረበ አልነበረም ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ሁኔታዎች የተለዩ ናቸው ። እዚህ ሠራተኛው በግለሰብ ደረጃ የሰው ጥገኛ አይደለም ፤ ለተወሰነ ካፒታሊስትም ንብረት አልነበረም ። ካፒታሊስቱ እንዲሠራም ሊአስገድደው አይችልም ። ግን ሠራተኛው ወይ የምርት መገልገያ ወይ የኑሮ መደጎሚያ የለውም ፤ ስለሆነም የጉልበት — ኃይሉን እንዲሸጥ ይገደዳል ። ርሃብ ሠራተኛውን ለካፒታሊስቱ እንዲሠራ ይጫነዋል ። ለዚህ ነው የጉልበት — ምንዳዕ ሥርዓት የምንዳዕ ባርነት ሥርዓት የሚሆነው ።



በካፒታሊዝም የተገደደው የጉልበት ጸባይ (መልክ) ተሸፍኗል ፣ ተላብሷል ። የካፒታሊስትን የብዝበዛ ምስጢር ልብሱን ካስወለቀው በኋላ ፣ ማርክስ ፣ የካፒታሊስትን ሥልተ—ምርት መሠረታዊ የምጣኔ — ሀብት ሕግ አገኘ ። የትርፍ ዕሴት ምርት የዚህ ሥልተ—ምርት ፍጹም የሆነ ሕግ ነው ።» [1] ሲል ጽፏል ።

የትርፍ ዕሴት ሕግ በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ የሚከናወነውን ሁሉንም ዓይነት ሂደትና ክስት ለማብራራትና ለመገንዘብ ያስችለናል ። የዚህን ሥልተ — ምርት የአበዛበዝ አፈጣጠር ያብራራል ። ይህ ሕግ የውድድርን መባባስ (መጠናከር) እናም የካፒታሊስትን ምርት ሥርዓት — አልባነት ፣ የሠራተኛ ሕዝቦችን ወደ ድሕነት ማሽቆልቆልን ፣ የካፒታሊዝም ሁሉም ዓይነት ቅራኔዎች እየጠለቁና እየተበ መሄድን ይወስናል ።

አስፈላጊና ትርፍ የሥራ—ጊዜ

በካፒታሊስት ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ቀኑ በሁለት ይከፈላል ፤— አስፈላጊ የሥራ ጊዜና ትርፍ — ጊዜ ተብሎ ። በአንጻሩም ፣ የሠራተኛው ጉልበትም አስፈላጊና ትርፍ ጉልበት (ሥራ) በመባል ይሸነሸናል ።

አስፈላጊ የሥራ — ሰዓትና አስፈላጊ ጉልበት ሠራተኛው የጉልበት — ኃይሉን ዕሴት እንደገና ለማምረት የሚአጠፋው ጉልበት እና የሥራ — ጊዜ ክፍሎች ናቸው ፤ ማለትም ፤ የመደጎሚያ ዘዴ ዕሴት ። ካፒታሊስቱ የሚከፍለው በምንዳዕ መልክ ለአስፈላጊው የሥራ — ጊዜ (ሰዓት) ነው ።

ትርፍ የሥራ— ጊዜና ትርፍ ጉልበት ሠራተኛው ትርፍ ዕሴትን ለማምረት የሚአጠፋው የሥራ — ጊዜና ጉልበት ናቸው ። በካፒታሊዝም ውስጥ ፣ ትርፍ ምርት ካፒታሊስቱ የሚሰበስበውን የትርፍ ዕሴት መልክ ነው የሚይዘው ። የትርፍ ጉልበት ወይም ትርፍ — የሥራ ጊዜ ምጥኔት ከአስፈላጊ ጉልበት ወይም ከአስፈለጊ የሥራ—ጊዜ ጋር ሲነጻጸር የሚገልጸው የሠራተኛውን የመበዝበዝ ደረጃ ነው ። ስለሆነም ፣ ትርፍ የሥራ — ጊዜና ትርፍ ጉልበት የሚገልጹት የምርት መገልገያ ባለቤት ካፒታሊስቶች ሠራተኛውን መደብ የሚበዘብዙበትን አንድ የተወሰነ ሕብረተሰብ ግንኙነት ጸባይ ይሆናል ።

የምርት መገልገያዎች ካፒታላዊ ባለቤትና የሚበዘበዘው የምንዳዕ ጉልበት የቡርዧ ሕብረተሰብን በሁለት ተጻራሪ መደቦች ይከፍለዋል ።

የቡርዧዋ ሕብረተሰብ የመደብ አወቃቀር ፤

ማርክስና ኤንግልስ ሕብረተሰብ በመደቦች የተከፋፈለው የምርት መገልገያዎች በግል ንብረትነት መከሠት ፣ ማለትም — የመሬት ፣ የመሬት ማኅጸን (ገበቴዎች) ፣ የተግባር መገልገያዎች ፣ በአጠቃላይ ፣ ሰዎች ቁሳዊ — ሀብትን ለማምረት የሚአስፈልጓቸው ነገሮች— ብቻ እንደሆነ አረጋግጠዋል ። የሕብረተሰቡ አንዱ ክፍል — አነስተኛው (ጥቂቱ) — የምርት መገልገያ ዎችን ያዝባቸዋል ። ይህስለሆነ ፣ ከምርት መገልገያዎች የተወገደውን የሕብ ረተሰብ ክፍል ለመበዝበዝ ይችላል ።

በበዝባዥ ሕብረተሰብ ውስጥ «መደቦች ፤» ይላል ሌኒን ፣ «በምርት መገልገያዎች ላይ ባላቸው የተለያዩ ግንኙነቶች ምክንያት አንዱ የአንደኛውን ጉልበት የሚዘርፉበት የሰው ቡድኖች ናቸው ። »

የመጀመሪያው የሕብረተሰብ የመደብ መከፋፈል በባሪያ — አሳዳሪውና በባሪያው ነበር ። ከባሪያ አሳዳሪነት ወደ መልከኛነት ሥርዓት መሸጋገር ጋር ይህ በመልከኛ መኳንንት መደብና በገባሩ መደብ መከፋፈል ተተካ ።

1. ኬ. ማርክስ ፤ ካፒታል ፣ ቅጽ 1 ገጽ 678

የቡርዧ ሕብረተሰብ ባሕርይ የሁለት መሠረታዊ ተጻራሪ መደቦች ሕልውና ነው — ቡርዧውዋና ወዛደሩ ። ቡርዧዋው የምርት መገልገያዎችን የሚአገባ ቸውና ሠራተኛውን መደብ ትርፍ ዕሴት ለመጭመቅ ሲል ፤ ለመበዝበዝ የምርት መገልገያዎችን የሚጠቀምባቸው መደብ ነው ። ወዝ — አደሩ ከምርት መገልገያ ዎች የተወገደ እና ስለዚህም ለካፒታሊስቱ ብዝበዛ ጥገኛ የሆነ ፤ የምንዳዕ — ሠራተ ኛው መደብ ነው ። ከቡርዧዋውና ከወዝ — አደሩ ሌላ በካፒታሊዝም ውስጥ የመ ሬት ከበርቴዎችና የገበሬው መደብ ፤ የፊተኛውን (የመልከኝነትን) ሥርዓት ጠባ ቂዎች በመሆን ይኖራሉ ።

ቡርዧዋውና ወዝ አደሩ ተጻራሪ መደቦች ናቸው ፤ ማለትም ፤ ዝንባሌዎቻ ቸው የተቃረኑ እና የማይታረቁ ጠላት መደቦች ። ካፒታሊዝም ሲስፋፉ ፤ ወዝ — አደሩም በጥንካሬው ፡ ለመደብ ዝንባሌው ንቃተ — ሕሊናውን እየጨመረ በመ ሄድና ቡርዧዋውን በመጻረር ለመታገል እየተደራጀና እየዳበረ ፤ ያድጋል ። የቡርዧዋውን ሕብረተሰብ ልዩ የሚአደርገው ዋና ፀባይ የወዝአደሩ መደብ ቡር ዧውን በመጻረር የሚአደርገው ትግል ነው ። በዚህ ሕብረተሰብ ውስጥ እጅግ አብዮታዊና የካፒታሊዝምን መቃብር ቆፋሪ መደብ ወዝ — አደሩ ነው ።

የቡርዧዋው መንግሥት በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን የሕብረተሰብ ምጣኔ —ሀብትና ፖለቲካዊ መበላለጥን ይንከባከባል ። የምርት መገልገያዎችን ካፒታ ላዊ የግል ንብረትነት ይጠብቃል ፤ ለሠራተኛ ሕዝቦች መበዝበዝ መሣሪያ ነው፤ እናም ወዛደሮች የካፒታሊስትን ሥርዓት በመቃወም የሚአካሂዱትን ትግል ያፍናል።

የቡርዧ ሶሲዮሎጂስቶችና ጠበቆች የቡርዧዋውን መንግሥት ከመደቦች በላይ እንዳለ — ከሕብረተሰቡ በላይ አድርገው ያቀርባሉ ። ይሁንና ፤ ሀቁ ግን የቡርዧዋው መንግሥት ምጣኔ—ሀብቱን የሚቆጣጠረው መደብ ፖለቲካዊ ድርጅት ነው ፤ የቡርዧዋው አምባገነንነት ።

## 4. ካፒታልና (ወረት) ሌሎች አካሎቹ ፤

ካፒታል (ወረት) እንደኅብረተሰብ የምርት ግንኙነት

የቡርዧ ኤኮኖሚስቶች ማንኛውም የተግባር መገልገያ ፤ ከጥንታዊው ሰው ድንጋዮችና ዱላዎች አንስቶ ፤ ካፒታል (ወረት) ናቸው በማለት ያውጃሉ ። ትክክለኛው ግን የም ርት መገልገያዎች በእራሳቸው ካፒታል (ወረት) እንዳልሆኑ ነው ፤ ለማንኛ ውም ሕብረተሰብ አስፈላጊ ናቸው ፤ እናም በዚሁ መንገድ ከመደቦች ጋር የሚ ወዳደር አይደለም ።

የምርት መገልገያዎች ካፒታል (ወረት) የሚሆኑት የካፒታሊስቶች የግል ንብረት ሲሆኑና ሠራተኛውን መደብ ለመበዝበዣ ሲውሉ ብቻ ነው ። ካፒታል (ወረት) የተወሰነ የገንዘብ ድምር ወይም ደግሞ የምርት መገልገያ አይደለም ፤ ግን በታሪክ የተወሰነ የሕብረተሰብ አምራች ግንኙነት ውስጥ የምርትና የተግባር መገ ልገያዎች ፤ እንዲሁም መሠረታዊ የሕይወት መደጎሚያዎች ፤ የካፒታሊስቱ መደብ ንብረት የሆኑበት ፡ ሠራተኛው መደብ ግን የሕብረተሰቡ ዋና አምራች ኃይል ከም ርት መገልገያዎችና ከሕይወት መደጎሚያዎች የተገለለበት ነው ፤ ስለሆነም የሠራ ተኛው መደብ የጉልበት — ኃይሉን ለካፒታሊስቶች መሸጥ ይኖርበታል ፤ እናም የብዝበዛን በትር ይሸከማል ። በሌላ ቃል ፤ ካፒታል (ወረት) የምንዳዕ ጉልበትን በመበዝበዝ ትርፍ ዕሴት የሚአስገኝ ዕሴት ነው ።

የካፒታልን (ወረት) ባሕርይና የካፒታሊስትን ብዝበዛ አሠራር ለማብራራት ዋናው አስፈላጊ ነገር የካፒታል በቀዋሚና በተለዋዋጭ ካፒታል (ወረት) መከፋፈል ነው ። ይህ ክፍፍል ነው ትርፍ ዕሴት ከየት ይመጣል ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚአስችለን ።



ቀዋሚና ተለዋዋጭ ካፒታል (ወረት)

ካፒታሊስቱ ማምረት ሲጀምር ፤ ከወረቱ ከፊሉን የፋብሪካ ሕንጻ ለማቆም ፤

መሣሪያዎችና ማሽኖች ፤ ነዳጅ ፤ ጥሬ ዕቃና መለዋወጫ ፤ ቅባት ለመግዣ ያውለዋል ። ይህ የወረት (ካፒታል) ክፍል ፤ በምርት መገልገያዎች ውስጥ ያለው ፤ በሥራ ሂደቱ ጊዜ ዋናነቱን (ዓይነተኛነቱን) አይለውጥም ። የምርት መገልገያውን መበላት (መፉ ጨት) አጠቃሎ አዲስ ወደተመረተው ሸቀጥ ብቻ ነው የሚዞረው ። ለምሣሌ — የጥሬ ዕቃዎች፤ መለዋወጫና ቅባቶች እንዲሁም የነዳጅ ዕሴት ሙሉ በሙሉ በእ ያንዳንዱ የምርት አሠራር ጊዜ ወደ አዲሱ ምርት ነው የሚሸጋገረው (የሚለወ ጠው) ። አንድን ማሽን ብንወስድ በምርት ሂደት ውስጥ ለአስር ዓመታት ያገለግ ላል አንበልና በዚሁ ሁኔታ በየዓመቱ ከዕሴቱ 10%ወደ አዲሱ ምርት ያስተላ ልፋል እንበል። በምርት መገልገያዎች (ማሺኖች) የማሽን ዕቃዎች፤ ጥሬ ዕቃዎች ፤ ወዘተ . . . . ላይ የጠፋው የካፒታል (ወረት) ክፍል እና ዋናነቱ (ዓይነተኛነቱ) የማ ይለወጠው፤ ቀዋሚ ካፒታል ተብሎ ይጠራል ። ማርክስ ፤ ቀዋሚ ካፒታልን ለማመ ልከት ‘C’ በአማርኛ እንውሰድውና - ቀ - የሚለውን ፊደል ተጠቅሟል ።

ካፒታሊስቱ ሌላውን የካፒታሉን (ወረቱን) ክፍል የጉልበት ኃይል ለመግ ዛት ይጠቀምበታል ። በምርት ሂደቱ መጨረሻ ላይ በድርጅቱ ውስጥ በሠራተኞች የተመሠረተ አዲስ ዕሴት ይቀበላል ። አዲሱ ዕሴት ከጉልበት — ኃይሉ ዕሴት ፤ ካፒታሊስቱ በምንዳዕ መልክ ከከፈለው ፡ የላቀ ነው ። የጉልበት — ኃይልን ለመ ግዛት የጠፋው የካፒታል (ወረት) ክፍል ፤ በምርት ሂደት ጊዜ በሠራተኞች በሚፈ ጠረው ትርፍ ዕሴት የሚአድገው ፤ ተለዋዋጭ ካፒታል ተብሎ ይጠራል ። ማርክስ ተለዋዋጭ ካፒታልን ለማመልከት - ‘U’ በአማርኛ እንውሰደውና - ተ- የሚለውን ፊደል ተጠቅሟል ።

ማርክስነው ለመጀመሪያ ጊዜ ካፒታልን(ወረትን) በቀዋሚና በተለዋዋጭ ክፍሎች የከፋፈለና ፤ ተለዋዋጭ ካፒታል(ወረት) ብቻ ትርፍ ዕሴት እንደሚአስ ገኝ የካፒታልን(ወረት) ምስጢር ዕርቃኑን ያስቀረ ።

የቡርዧ ኤኮኖሚስቶች የካፒታልን(ወረት) በቀዋሚና በተለዋጭ አካሎች መከፋፈል አይቀበሉም ። የካፒታሊዝም ጠበቃ በመሆን የበዝባዥነት ጸባይ እን ደሌለው ለማድረግ ይሻሉ ። እነሱ የሚቀበሉት ካፒታሊስቱ በንግድ ሂሣብ አያያዝ ላይ የሚጠቀምበትን የካፒታል (ወረት) ክፍያ ነው — የካፒታል በነባር (fixed) እና በተዘዋዋሪ (Circulating) መከፋፈልን ። ይህ የወረት መከፋፈል ፤ የምርትን አሠራር ለመግለጽ ሲረዳ ፤ የካፒታሊስትን ብዝበዛ ሸፋፍኖ ያልፈዋል ።

ነባርና ተዘዋዋሪ ካፒታል (ወረት)


ውጤታማ ካፒታል ዕሴቱን ወደ አለቀለት ምርት የማሸጋገሪያው መንገድ — በፍጥነትም ይሁን በደረጃ — የካፒታልን (ወረትን) በነባርና በተዘዋ ዋሪ መከፋፈል መሠረቱ ያደርጋል ።

ነባር ካፒታል (ወረት) ማለት ዕሴቱን ወደ አለቀለት ምርት በደረጃ እየተበላ ሲሄድ (ፋብሪካው ያለበት ፤ ማሺኑ ፤ የማሺን ዕቃዎች) የሚአሸጋግረው የካፒታል (ወረት ) ክፍል ነው ። ተዘዋዋሪ ካፒታል ሲባል ደግሞ የጉልበት ኃይልን ጥሬ ሀብትን ፤ መለዋወጫና ቅባትን ፤ ነዳጅን ወዘተ . . . ለመግዛት የሚጠፋውን በአ ንድ የተወሰነ የምርት ወቅት ሙሉ በሙሉ ሸቀጡ ከተሸጠ በኋላ ለካፒታሊስቱ በገንዘብ መልክ የሚመለሰው የካፒታል (ወረት) ክፍል ነው ።

የወረት በነባርና በተዘዋዋሪ ካፒታል (ወረት) መከፋፈል ሙሉ በሙሉ በምርት መገልገያዎችና በጉልበት ኃይል መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት ይደብቃል ። እዚህ የጉልበት — ኃይል እንደ ጥሬና መለዋወጫ ፤ ዕቃዎች ፤ ነዳጅ ፤ ወዘተ . . በአንድ ርዕስ ሥር ይመጣል ፤ እናም ከነዚህ ጋር አንድ ላይ በመሆን ከሌሎች የም

ርት መገልገያዎች ጋር ይነጻጸራል። ይህ ክፍፍል ትርፍ ዕሴትን ለማሳደግ በጉልበት— ኃይል የተወሰደውን ልዩ ሚና ይደብቃል ፣ ስለሆነም የካፒታሊስትን ብዝበዛ ልብስ በማልበስ ያቀርበዋል ።

እነኝህ የካፒታል(ወረት) በሁለት መንገዶች መከፋፈል እንደሚከተለው ሊታዩ ይችላሉ —




የትርፍ ዕሴት ብዛትና (መጠን) ደረጃ ትርፍ ዕሴት የተወሰነ ዓይነተኛነት (ፍጹማዊም ይሁን አንጻራዊ) አለው ። የትርፍ ዕሴት ፍጹማዊ ዓይነተኛነት የትርፍ ዕሴት መጠን (ብዛት) ይባላል ። የጥገኛነቱ በብዝበዛው ደረጃ ላይና በሚበዘበዙበት ሠራተኞች ቁጥር ላይ ነው ። የትርፍ ዕሴት አንጻራዊ ዓይነተኛነት የሚገለጸው በትርፍ ዕሴቱ ደረጃ ወይም በብዝበዛው ደረጃ ነው ።

የካፒታልን (ወረት) በቋሚና በተለዋዋጭ መከፋፈል በመግለፅ ፣ ማርክስ የካፒታሊስትን የብዝበዛ አሠራር ብቻ ማይሆን ግልፅ ያደረገው ፣ ግን የብዝበዛን ደረጃ (ዲግሪ) የመለኪቱን ዘዴም አሳይቷል ።

ቀዋሚ ካፒታል(ቀ) ትርፍ ዕሴት ሊፈጥር አይችልም ፣ ስለሆነም ፣ የትርፍ ዕሴት ደረጃ በሚወሰንበት ጊዜ መጨመር የለበትም ። ተለዋዋጭ ካፒታል (ተ) ትርፍ ዕሴት ይፈጥራል ። በዚህ ምክንያት ፣ የትርፍ ዕሴት አንጻራዊ ዓይነተኛነትን ለመወሰን ፣ የኋለኛው ከተለዋዋጭ ካፒታል ጋር በማነጻጸር መወሰድ ይኖርበታል ፣ ስለዚህም የትርፍ ዕሴት ደረጃን እናገኛለን ። ለጉልበት — ኃይል የብዝበዛ ደረጃ ትክክለኛ መግለጫ ነው ። (ትዕ1) እንደትርፍ ዕሴት ደረጃ ብንወስድ ፣ « ትዕ » ለትርፍ ዕሴት በመቆም የሚቀጥለውን እኳያነት እናገኛለን (ፕሮብሌም?) ፦

$$ትዕ1=\frac{ትዕ}{ተ} \times 100\%$$

። ይህን ለማብራራት አንድ ምሳሌ እንመልከት ። አንድ ካፒታሊስት የሚቀጥለውን ድምር (በብር) ሸቀጦችን ለማምረት ቢአወጣ ፦— 100,000 ቀ + 20'000 ተ = 120,000 ። በሠራተኞቹ የተመረቱትን ሸቀጦች በ$ 140,000 ሸጠ ። ይህም ማለት $ 20,000 ትርፍ ዕሴት ወሰዶ ነው ።

የትርፍ ዕሴቱ ደረጃ ምን ያህል ይሆናል ?

$$ትዕ\ 1 = \frac{ትዕ}{ተ} \times 100\% = \frac{20,000}{20,000} \times 100\% = 100\%$$

ምሳሌው የሚአሳየው እዚህ ላይ የሠራተኛው ጉልበት በአስፈላጊና በትርፍ ጉልበት እኩል መከፋፈሉን ፣ ማለትም ፣ የሥራውን ቀን ግማሽ ለራሱ መሥራቱንና ሌላውን ግማሽ በምንዳዕ ለካፒታሊስቱ መሥራቱን ነው ። የትርፍ ጉልበት ምጥነት ከአስፈላጊው ጉልበት በአየለ መጠን ፣ የብዝበዛው ደረጃ ያኑ ያህል ይኀራል ።

ካፒታሊዝም ሲዳብር የትርፍ ዕሴት ደረጃም ያድጋል ። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በማዕድን ቁፈራና ማንጠር የኢንዱስትሪዎች የትርፍ ዕሴት ደረጃ ፣ ከታወቁ ስታትስቲኮች እንደተወሰደው ፣ በ1889 ዓ.ም.145% በ1919 ዓ. ም. 165% በ1929




ዓ.ም. 210% ፤ በ1939 ዓ.ም. 220% በ1947 ዓ.ም. 260% አካባቢና ፣ በ1955 ዓ.ም. 306.3% (በማንጠሪያ ኢንዱስትሪዎች ብቻ) ደርሶ ነበር ።

በካፒታሊዝም ውስጥ እንዴት ነው የጉልበት የመበዝበዝ ደረጃ ዕድገት የሚገኘው ?

## 5. የሠራተኛውን መደብ የመበዝበዝ ደረጃ ለመጨመር ሁለት መንገዶች ፤

ፍጹም ትርፍ ዕሴት ከዚህ በፊት በካፒታሊዝም ውስጥ የሥራ - ቀንን በሁለት መከፈል ተከትሎ ነው የሚሄደው —1) ከፈሰሰው የጉልበት—ኃይል ዕሴት እኩል የሆነ የተወሰነ ሸቀጥ መጠን ለማምረት የሚአስፈልገው አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ፣ እና 2) ሠራተኛው ለካፒታሊስቱ በመሥራት ትርፍ ዕሴት የሚፈጥርበት ፣ ትርፍ የሥራ — ጊዜ ነው ብለን ነበር ።

ለምሣሌ — 5ቱ ሰዓት አስፈላጊ የሥራ — ጊዜና 5ቱ ሰዓት ትርፍ የሥራ— ጊዜ የሆነበት 10 ሰዓት የሥራ ቀን እንውሰድ ። ይህን በሥዕል እንግለጸው—




በዚህ መልክ የትርፍ ዕሴቱ ደረጃ፦

$$ትዕ1 = \frac{ትዕ}{ተ} = \frac{5\ ሰዓት\ ትርፍ\ ጊዜ}{5\ ሰዓት\ አስፈላጊ\ ጊዜ} \times 100\% = 100\%$$ ይሆናል ።

አስፈላጊው የሥራ — ጊዜ በነበረው ከቆየ ፣ የሥራ ቀኑን በማራዘም ትርፍ የሥራ ጊዜ የበለጠ ይራዘማል ። ይህም የትርፍ ዕሴቱ ደረጃ ፣ የሠራተኛው የመበዝበዝ ደረጃ መጨመር ማለት ነው ። የሥራ ቀኑ ከ10 ወደ 12 ሰዓት ቢራዘም ፣ ትርፍ የሥራ — ጊዜው 7 ሰዓት እንጂ 5 ሰዓት አይሆንም ። ሁኔታው ይህ ስለሚሆን ፣ የትርፍ ዕሴቱ ደረጃ የሚሆነው ፦ $7/_5 \times 100\% = 140\%$ ነው ።

የሥራ ቀኑን በማራዘም የሚመረተውን ትርፍ ዕሴት ማርክስ ፍጹማዊ ትርፍ ዕሴት ብሎ ጠርቶታል ። የካፒታሊስቱ የትርፍ ዕሴት ጥማት መጨረሻ ስለሌለው፣ እስከ መጨረሻው ደረጃ የሥራ ቀኑን ርዝመት ለመጨመር ይስገበገባል ።

እስከምን ድረስ ነው ካፒታሊስቶች የሥራ ቀኑን ማራዘም የሚችሉት ? ከቻሉ ፣ ሠራተኞችን 24 ሰዓት ሙሉ እንዲሠሩላቸው ያስገድዳሉ ። ግን ይህ ሊሆን አይችልም ፣ ምክንያቱም ሰው በየቀኑና በየሌሊቱ ከቀኑና ከሌሊቱ የተወሰነ ክፍል ለዕረፍት ፣ ለመኝታና ለመብያ ማጥፋት ይኖርበታልና ። ከአካላዊ ወሰኑ ሌላ ፣ እንደ ሕብረተሰብ አባልነቱ ሞራላዊ ወሰኖችም ይኖሩታል ፣ ሠራተኛው ባሕላዊና ሕብረተሰባዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት (መጻሕፍትና መጽሔቶችን ማንበብ ፣ ወደሲኒማ መሄድ ፣ ወደ ስብሰባዎች ወዘተ . . .) ጊዜ ይፈልጋል ። ግን ሁሉም አካላዊና ሞራላዊ ወሰኖች ለሥራው ቀን ሊወጠሩ ፣ ሊሳቡ ስለሚችሉ ፣ በካፒታሊዝም ውስጥ የሥራው ቀን 8 ፤ 10 ፤ 12 ፤ ሰዓት ወይም ከዚያ የበለጠ ሊወስድ ይችላል ።


በካፒታሊዝም የቀድሞ ደረጃ ፣ መንግሥት የቡርዧዋዎችን ዝንባሌ በመከተል የሥራ ቀኑን ለማራዘም ሕጎች ያውጃል ። በኋላ ፣ ከማሺን ምርቶች መሠራጨትና የሥራ — አጥነት ማደግ ጋር ፣ የሥራ ቀኑን ለማራዘም ሕጋዊ አስፈላጊነት ጠፋ ። አሁን ካፒታሊስቱ መሥራት እስከሚቻልበት የመጨረሻው የሰዓት መጠን ድረስ ለማሠራት የምጣኔ — ሀብትን ማስገደጃነት መጠቀም ችሏል ።

ስለዚህ ሠራተኛው መደብ የሥራ ቀኑን ለማሳጠር መራራና መንቻካ ትግል ማካሄድ ጀመረ ። በመጀመሪያ ትግሉ የዳበረው በእንግሊዝ ነው ። በተለይም መራራ የሆነው ከመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ኮንግሬስና በ1866 ዓ.ም. የሠራተኞች ስብሰባ የስምንት ሰዓት የሥራ ቀን የሚጠይቀው መፈክር ከወጣ በኋላ ነው ። የሠራተኛው መደብ ትግል በአብዛኞቹ የካፒታሊስት አገሮች የታየው የሥራ ቀኑን ለመወሰን ሕግ በማውጣት ነበር። ታዲያ እንዴት ነው ፣ የሥራ ቀኑ በግልፅ ሊራዘም ካልቻለ ካፒታሊስቱ የትርፍ ዕሴትን ከፍተኛ መጠን ችግር የሚወስነው ?

*አንፃራዊ ትርፍ ዕሴት*


አንጻራዊ ትርፍ ዕሴትን ለመጨመር ሁለተኛው መንገድ የሥራ ቀኑን ርዝመት ሳይለወጥ በማቆየት ፣ የትርፍ የሥራ — ጊዜውን መጠን ለመጨመር ፣ አስፈላጊውን የሥራ — ጊዜ ማሳጠር ነው ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ? የጉልበት — ኃይል ዕሴት የሚወሰነው የሠራተኛውን የኑሮ (የሕይወት) መደጉሚያ ለማምረት መፍሰስ ባለበት የጉልበት መጠን መሆኑን እናስታውስ ። የብሎት (ፍጆት) ዕቃዎችን ለማምረት የጉልበት አምራችነት ዕድገት (ጭማሪ) ካለ ፣ የእነኝህ ዕቃዎች ዕሴት ይቀንሳል ። ይህም የጉልበት — ኃይል ዕሴት ትንሳና ፣ ስለዚህም ፣ የአስፈላጊው የሥራ ጊዜ ማሽቆልቆል ማለት ነው ። እናም ይህ የትርፍ ሥራ ጊዜን መጨመር ያስገኛል ።

10 ሰዓት የሥራ ቀንን በ5 ሰዓት አስፈላጊ የሥራ ጊዜና በ5 ሰዓት ትርፍ የሥራ — ጊዜ እንከፈለው እንበል ። ከዚህም በላይ ፣ በጉልበት አምራችነት መጨመር የተነሣ አስፈላጊው የሥራ ጊዜ ከ5 ሰዓት ወደ 3 ሰዓት አሽቆለቆለ እንበል ። ስለዚህ ትርፍ የሥራ ጊዜው ያለምንም ጥርጣሬ ከ5 ሰዓት ወደ 7 ሰዓት ያድጋል ። ምንም እንኳ የሥራ ቀኑ ያልተለወጠ ቢሆንም ፣ የብዝበዛው ደረጃ (ወይም የትርፍ ዕሴቱ ደረጃ) የናረ ይሆናል ። በዚህ መንገድ የሥራ ቀኑ በሚከተለው አኳኋን ይገለጻል :-




ከመቶ ይህን ያህል ተብሎ የተገለጸው የትርፍ ዕሴት ደረጃ የሚሆነው :—

ትዕ1 = 5/5 X 100% = 100 ፐርሰንት /%/ ይሆናል ነው ።




የትርፍ ዕሴቱ ደረጃ ትዕ1 7/3 X 100 % = 233 % (ፐርሰንት) ይሆናል ።

በምሣሌአችን የትርፍ ዕሴቱ ደረጃ ከ100% ወደ 233% በሥራ ቀኑ ፍጹም መጨመር የተነሣና በአስፈላጊውና በትርፍ ጉልበት ጊዜ መካከል ባለው የምጥነት ለውጥ ምክንያት ንሯል ።

በአስፈላጊው የሥራ ጊዜ መቀነስና ከእርሱ አንጻር በሚአድገው ትርፍ የሥራ — ጊዜ የሚመነጨው ትርፍ ዕሴት ፣ የጉልበት አምራችነት የማደግ ውጤት የሆነው ፣ አንጻራዊ ትርፍ ዕሴት ይባላል ።

በአንዳንድ ሁኔታዎች መንስኤ ካፒታሊስቶች ተጨማሪ ትርፍ ዕሴትም ያገኛሉ።

*ተጨማሪ ትርፍ ዕሴት*

ተጨማሪ ትርፍ ዕሴት የአንጻራዊ ትርፍ ዕሴት የተለዩ መልኩ ነው። ማንኛውም ካፒታሊስት እስከቻለው ድረስ የቻለውን ያህል ትርፍ ለመምጠጥ ይመኛል ። በዚህ ምክንያት አዲስ ማሺኖችንና ቴክኖሎጂን ያስተዋውቃል ፣ ስለሆነም ከፍተኛ የጉልበት አምራችነትን ይሰበስባል ፣ ስለዚህ ውጤቱ በእርሱ ድርጅት ውስጥ የሚመረተው የእያንዳንዱ ዕቃ ዕሴት ተመሳሳይ በሆኑ ሌሎች ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከሚመረቱት ሸቀጦች አማካይ እሴት ዝቅ ያለ መሆኑ ነው ። የአንድ ሸቀጥ የገበያ ተመን የሚወሰነው በምርት ላይ በሰፈነው አማካይ ሁኔታ ስለሆነ ፣ ከፊተኛው ሲነጻጸር ካፒታሊስቶቹ ከፍተኛ ትርፍ የዕሴት ደረጃ ይወስዳሉ ።

ተጨማሪ ትርፍ ዕሴት በሸቀጡ ሕብረተሰባዊ ዕሴትና በዝቅተኛው ነጠላ ሸቀጥ መካከል ያለው ልዩነት ነው ። ሁለት ልዩ ባሕሪዎች አሉት — በመጀመሪያ ፣ የሚገኘው አዳዲስ ከፍተኛ አምራች ማሺኖችን ለመጀመሪያ በተጠቀሙት ግለሰብ ቀጣሪዎች ነው ። ሁለተኛ ፣ ተጨማሪ ትርፍ ዕሴት የሚገኘው ቀደም ብሎም ይሁን ወይም ኋላበድርጅቱ ውስጥ የሚገቡትን ማሺኖች በጠየቀው ካፒታሊስት ለጊዜው ብቻ ነው ፤ግን በመጀመሪያ ማሺኑን (አዲሱን) የተጠቀመበት ካፒታሊስት ተጨማሪ ትርፍ ዕሴት ማግኘቱ ያቆምና ጥቅሙ ይቀርበታል ። ይሁንና ፣ ከአንድ ድርጅት በመጥፋት ይህ ዓይነት ትርፍ ዕሴት በሌላው ይከሰታል ፣ ማለትም አዲስና ይበልጥ የተሻሻለ መኪና በገባበት ፋብሪካ ።

ተጨማሪ ትርፍ ዕሴት በካፒታሊዝም ዕድገት ውስጥ ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል ። ይህን ለማግኘት ያለው መገፋፊያ የሚከሰተው (የሚታየው) በቴክኖሎጂ ግብታዊ ዕድገት ነው ። እየንዳንዱ ካፒታሊስት በራሱ መበልጸግ ላይ ስለሚአተኩር ፣ በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ እንዳይገቡ በመከላከል (በማገድ) ፣ የእርሱን አዲስ ማሺኖችና የምርት ቴክኖሎጂ ምስጢር አድርጎ ለመጠበቅ ይሞክራል ። ይህ በካፒታሊስቶች መካከል ውድድርን በማስነሳት በመካከላቸው ያላቸውን ትራኔ ያባብሰዋል ። የመጨረሻውም ውጤት የአንዳንድ ቀጣሪዎች መጥፋትና የሌሎች መበልጸግ ነው ።

በሌላ አባባል ፣ የምርት ኃይሎች ማደግ መሣሪያዊ ቢሆንም ፣ የተጨማሪ ትርፍ ዕሴት ማባረር ዕድገታቸውን ይቀንሰዋል ።

*በኢንዱስትሪ ውስጥ የካፒታሊስት ዕድገት ሦስት ደረጃዎች*

የአንጻራዊ ትርፍ ዕሴት ምንጭ የጉልበት አምራችነት ማደግ ነው ። ስለዚህ የዚህ ዕሴት ትንተና በካፒታሊዝም ውስጥ ያሉ ሶስት ታሪካዊ የምርት ዕድገት ደረጃዎችን ግልፅ ያደርጋል፡—ቀላል የሕብረት (Co-operation) ድርጅትን *1 የመጀመሪያውና በጣም ዝቅተኛው መልክ ዕቃ ማምረትንና *2 የማሺን ምርት *3 የጉልበት አምራ ችነት ካፒታላዊ ቀላል የሕብረት ድርጅት (Capitalist Simple co-operation) ነው ። ዋና ባሕሪው የተመሠረተው ካፒታሊስቱ በሥራ ድርጅቱ ውስጥ በአንድ ጊዜ ከድርጅቱ ተመጣጣኝ የሆኑ ብዙ ሠራተኞች ሁሉም አንድ ዓይነት ሥራ የሚአካሂዱ በመቅጠሩ ላይ ነው ።

ብዙ ሠራተኞች ባንድነት አንድ ዓይነት የሆነ ሥራ ሲአካሂዱ እጅግ በፍጥነት ይከናወናል ። እያንዳንዱ ሠራተኛ ከሌሎች ጋር በመወዳደር ሲሰራ ውጤቱ የጉልበት አምራችነቱ ማየል ይሆናል ። የአምስት ቅጥር ሠራተኞች ባንድ ጊዜ አጠቃላይ አምራችነት ለየብቻቸው ተገነጣጥለው ከሚሠሩት ጠቅላላ ምርት እጅግ የናረ ነው ። ይህ አዲስ ምርት ለካፒታሊስቱ ምንም አያወጣለትም ፣ ምክንያቱም ፊት በተናጠል ለእያንዳንዱ የጉልበት — ኃይል ይከፍል እንደነበረው ይከፍላልና ፣ በተጨማሪም ፣ ሥራ በብዙ ግን አንዶ ምርቱ ከአደገ የበለጠ ትርፍ ይጨምቃል ። ...

*1. ግለሰብ አምራቾችን ( ሸማኔ ፣ ቀጥቃጪ ፣ወዘተ . . . ) የመሳሰሉትን አንድ ላይ በመሰብሰብ በአንድ ከበርቴ ሥር በአንድ የሥራ መሥሪያ ውስጥ (Work shop) ምንዳዕ በመስጠትና ፣ ጥሬ ሀብት በማቅረብ ሕብረታዊ ምርት የማስመረት ዘይቤ ነው ። ምርቱና ሽያጩ በጠቅላላ የሚገባው ለዚህ ቀጣሪ ነው ። መሣሪያዎች ወደፊት ከምንገልጻቸው ሲነጻጸሩ ኋላ ቀር ናቸው ።

*2. ይህ ቀላል በእጅ የሚንቀሳቀሱ መሣሪያዎችን በመጠቀም ደረጃና ሌሎች ግዙፍ ማሺን የሚሆኑ መሣሪያዎችን ለማምረት የሚችሉ በጽሑፋችን ውስጥ « አፈብራኪነት » በሚል መጠሪያ የተጠቀምንባቸውን ነው የሚአመለክተው ። ይህ ደረጃ ሁለተኛው የካፒታሊዝምን (በለፋብሪካነት ነው የሚአሳየው ።

*3. ይህ ብዙውን ጊዜ አውቶማቲክ የሆኑትንና ግዙፍ ማሺኖችንም መለለው ለማምረት የሚያስችሉትን ውስብስብና ( Sophisticated ) የተያያዙ ራስ ተንቀሳቃሺ (ባለቁልፍ — ( buttons) ማሺኖችን ነው የሚያመለክተው

ሠራተኞች ሲከናወን ፣ ካፒታሊስቱ፡ የሕንጻ ፣ የመብራት ፣ የሙቀት ወዘተ ቁጠባ ያካሂዳል ። አንዳንድ ሰዎች በአንዳንድ ሥራዎች ላይ የተሻሉ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በሌላው የተሻሉ ሆነው ሲገኙም ይገለጻል ። ስለዚህም ካፒታሊስቱ፡ ሠራተኛውን በተሻለ መንገድ ሊሠራ በሚችልበት መመደቡ ይበልጥ ጠቃሚ መሆኑን ይገነዘበዋል ። በዚህ መንገድ የሥራ ክፍፍል በሥራ ቦታዎች ቀስ በቀስ ይቋቋማሉ ። በሥራ ክፍፍል እና በእጅ ሥራ ጥበብ ላይ የተመሠረቱ፡ የካፒታሊስት ድርጅቶች ዕቃ አምራቾች (አፈብራኪዎች) (manufactories) ይባላሉ ።

በአፈብራኪዎች ውስጥ የሥራ ክፍፍል ወደ ከፍተኛ የጉልበት አምራችነት ዕድገት መራ ። የመድፌ መመረት ግልፅ የሆነ ምሣሌ ይሰጠናል ። በ18ኛው ምዕተ ዓመት አንድ አፈብራኪ ( manufactory ) ዕቃ አውጭ — 10 ሠራተኞች በመቅጠር 48,000 መርፌዎች በቀን አወጣ ፣ ማለትም 4,8000 በእያንዳንዱ ። ሆኖም ያለ ሥራ ክፍፍል አንድ ሠራተኛ ሊአመርት ይችል የነበረው በቀን 20 መርፌዎች ብቻ ነው ። አምራችነት 240 ጊዜ ነው የተባዛው ።

በዕቃ አውጭዎች(አፈብራኪዎች) ውስጥ የሥራ ሁኔታ በጣም ከባድ ነበር ። የማያቋርጥ የአንድና አንድ ዓይነት የሆነ እንቅስቃሴ መደጋገም ሠራተኛውን በአካልም ሆነ በሞራሉ ያደነዝዘዋል ። የሥራ ቀኑ 18 ሰዓት ወይም ከዚያ በላይ ሲደርስ ፣ ምንዳዕ ግን ፍጹም ዝቅተኛ ነበር ።

አፈብራኪነት የከፍተኛ ደረጃ የማሺን አምራችነት ሽግግር አስፈላጊ ሁኔታዎች ተብለው የሚጠሩትን አዘጋጀ — 1) የአሠራር ሁኔታዎች መቃለል የሠራተኛውን እጅ በማሺን ተካ ፣ 2) የተነጣጠሉ አሠራሮች መጠናቀር (መሟላት) የሥራ መሣሪያዎችን ወደ መሥራት ጠበብትነት አመራ ፣ በዚህ ምክንያት በእጅ ከሚንቀሳ ቀሉ መሣሪያዎች ወደ ማሺን የመሸጋገር ዕድገትን አስቻለ ፣ 3) አፈብራኪነት ለማሺን ኢንዱስትሪ ብዙ የሰለጠኑ ሠራተኞችን አዘጋጀ ። በዚህ አባባል አፈብራኪነት ታሪካዊ ሚና ተጫውቷል ።

አፈብራኪነት ወደ ፋብሪካ የሚመራ የመሸጋገሪያ መልክ ነበር ። መጀመሪያ «ሠራተኛው» ማሺን ተብሎ የሚጠራው ተከሰተ (መጣ)።ቀድሞ በሠራተኞች ይካሄዱ የነበሩትን ዓይነት ሥራዎች ነው የሚአከናውነው ። ግን ይህን ማሺን ለማንቀሳቀስ ከአንድ ሰው የጡንቻ ጥንካሬ በላይ ነው ።ከዚያም የሞተር አሠራር— የእንፋሎት መንኰራኩር — ተሠራ ። ብዙ ሠራተኛ ማሺኖችን ለማንቀሳቀስም አገለገለ ። በመጨረሻ እነዚህ ሁሉ ፣ ሸቀጦችን ለማምረት በጥቅም ላይ የሚውሉ እርስ በእርሳቸው የተያያዙ ማሺኖች ክፍል በካፒታሊስት ፋብሪካ ውስጥ መጡ።

የማሺኖች ጥቅምና መሻሻል ከዚህ በፊት ያልታዩ የጉልበት አምራችነት ዕድገትና ሸቀጦችን የማርከስ ሁኔታዎችን አሳዩ ። እየጨመረ በሄደው በማሺኖች የመጠቀም ውጤት የተነሣ ፣ ብዙ አነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች እንዲጠፉና በእጅ ሥራ የሚጠቀሙ የመሣሪያ ሱቆችን መዘጋት አመጣ ።

የካፒታሊስት ፋብሪካ በካፒታል(በወረት)የጉልበት ባርነትን ምልክት ሰጠ። እዚህ ሠራተኛው ከማሺኑ ጋር የተጣበቀ ሚና ነው የሚጫወተው ። የማሺኖችካፒታላዊ አጠቃቀም የሚአመራው ወደረጅም የሥራ ቀን ፣ የሴቶችና የሕጻናት በምርት ውስጥ መቀጠርን፣የሥራ—አጥነት መመሥረትንና የወዛደሩን ሥቃያማ ኑሮ ነው።

ካፒታሊስቱ ሁልጊዜ ማሺኑን አይጠቀምበትም ። የአጠቃቀሙ መወሰን የሚደራጀው ካፒታሊስቱ ፣ ማሺን የሚጠቀመው ፣ ሠራተኞቹን አባሮ የሚተካው ማሺን ተመን (መግዣ) ከምንዳው አነስተኛ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው ። ካፒታሊስቱ



የሚጠቀምበት ከጥቅሙ ጋር ከተስማማለት ብቻ ነው ። ስለዚህ የማሺን አመራረት በእጅ የሚከናወንን ሥራ አያጠፉም ። የጉልበት ሥራ በአሁኑ ዘመን በኢንዱስትሪ በዳበሩ አገሮችም ቢሆን እንኳ ፣ እንደዩናይትድ ስቴትስና እንደ እንግሊዝ ባሉት በሰፊው ሥራ ላይ ይውላል ።

ከአፈብራኪነት ወደ ፋብሪካ ሽግግር የካፒታሊስትን ሥልተ — ምርት የመጨረሻ መመሥረት ዓይነተኛ አድርጎታል ። ከፍተኛ የማሺን ምርት የጉልበትንና የምርትን የግብታዊ ሂደት ሕብረተሰብአዊነት መሠረት ሰጠ ። አነስተኛ የመሥሪያ ሱቆች በእጅ የሚንቀሳቀሱ መኪኖችን የሚጠቀሙት ብዙሺ ሠራተኞችን በተለያዩ መስክበሚቀጥሩ ትላልቅ ፋብሪኮች ተተኩ።

የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ

የሥራ ክፍጥል ይበልጥ ተስፋፋ ። ሁሉም ድርጅቶች ፣ ሁሉም ኢንዱስትሪዎች ተወሳሰቡ ፣ አንዱ ባንዱ ጥገኛ ሆኑ ።ለምሣሌ ፣ መሐንዲስ ነክ ፋብሪካ (ብረታ—ብረትና የሕንጻ) ያለ ብረትና ያለአረብ ብረት ምርቶች መከናወን አይችሉም ፣ ይህም በተራው ያለድንጋይ ከሰል ፣ የድንጋይ ከሰል ማዕድኖች ደግሞ ጥገኝነታቸው በመሐንዲስ ነክናበሌሎች ፋብሪካዎች ነው ። በዚህ ሁኔታ ምርት ሕብረተሰባዊ መልክ ወሰደ ።

በመጨረሻ ሁሉም ድርጅቶች ፣ መሬትና የመሬት ጸጋ ሁሉ በግል ንብረትነት ቀሩ ። የሕብረተሰብ ጉልበት ውጤቶች በካፒታሊስቶች ተዘረፉ ። ይህ በምርት ሕብረተሰባዊ ጸባይና በምርት ውጤቶች ግላዊ ፣ ካፒታላዊ ብዝበዛ መልክ ያለውን ቅራኔ ዕድገት አመጣ ። ይህ ነው የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ ።

የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ ሳያቋርጡ በሚአድጉት የምርት ኃይሎችና በካፒታሊስት የምርት ግንኙነቶች መካከል ያለውን ቅራኔ ይገልጻል ። የምርት ሕብረተሰባዊነት እያደገ ሲሄድ ፣ ካፒታሊዝም በሕብረተሰብ የምርት ኃይሎች ከፍተኛ መስፋፋት ላይ ደንቃራ ይሆናል ። ይህን ደንቃራ ለማስወገድ ፣ ካፒታላዊ ንብረት መወገድ ይኖርበታል ። የምርት ኃይሎችን በማሳደግ ካፒታሊዝም የራሱን መቃብር ቆፋሪ ይፈጥራል — ወዝአደሩን — የግል ባለቤትነትን ለማስወገድ የተወሰነ ኃይልና በምትኩም ሕብረሰባዊ ባለቤትነትን በቦታው የሚተካ ነው ።

## ፮ ምንዳዕ በካፒታሊዝም ውስጥ ፡

የምንዳዕ አስፈላጊ ተፈጥሮዎች

በካፒታሊዝም ውስጥ የጉልበት — ኃይል እንደሌላው ሸቀጥ ሁሉ እሴት እንዳለው ቀድሞውኑ አረጋግጠናል ። በገንዘብ የሚገለጸው የጉልበት — ኃይል ዕሴት የጉልበት — ኃይል ተመን ነው ።

የካፒታሊዝምን የብዝበዛ ዕውነት ለመደበቅ ፣ የቡርዧ ኤኮኖሚስቶች ምንዳዕ የጉልበት ተመን እንደሆነ አድርገው ያቀርባሉ ። ሠራተኛው ፣ በካፒታሊስት ፋብሪካ ውስጥ የሚሠራው ፣ የተለያዩ ሸቀጦችን ያመርታል በተራውም ለጉልበቱ የሚሆነውን የጉልበት ተመን (ክፍያ) ይቀበላል ፣ ማለትም ፣ ምንዳውን ።

ይህ ለተሠራው ሥራ እንደመክፈያ የሆነው ምንዳዕ መከሰት አመጣጡ ሠራተኛው ለተወሰነ ክፍለ — ወቅት ለሚሠራበት ከሚቀበለው ምንዳዕ ነው ። በተጨማሪም ፣ ምንዳዕ የሚወሰነው ወይም በተሰራው ጊዜ መጠን መሠረት (ሰዓት ፣ ቀን ፣ ሳምንት) ወይም በተመረቱት ዕቃዎች ብዛት መሠረት ነው ። በእውነቱ ፣ ምንዳዕ ፣ ማርከስ እንዳስቀመጠው ፣ መልኩን የሚለውጥ ፣ ማለትም ፣ የሚደብቅ ፣ የዕሴት የተሸፋፈነ መልኩ ፣ ወይም የጉልበት — ኃይል ተመን ነው ።

ጉልበት እራሱ ሸቀጥ አይደለም እናም በዚህ ምክንያት ዕሴት ወይም ተመን የለውም ። ጉልበትን ለመሸጥ ፣ ከሽያጭ በፊት መኖር ይኖርበታል ። አንድ ሰው የሌለን ነገር መሸጥ አይችልም ። አንድ ጫማ ሰፊ ጫማዎቹን ገበያ ሲአወጣ ፣

አዚያው ላይ ይኖራሉ እናም ሊሸጡ ይችላሉ ። ግን ካፒታሊስቱ ሠራተኛውን ሲቀጥረው ጉልበት ሕልው ሆኖ አይታይም ። ያለው የሠራተኛው የመሥራት ችሎታ ፣ የጉልበት — ኃይል ነው ። ይህን ነው ሠራተኛው ለካፒታሊስቱ የሚሸጠው ። የኋለኛው ያን ሲገዛና ገንዘብ ሲከፍል ፣ ፍላጎቱ ይበልጥ በትክክል ሠራተኛውን ሳይሆን ፣ ትርፍ ዕሴት ለመፍጠር የሚአስችለውን የሠራተኛውን የሥራ ችሎታ ነው።

እስካሁን ድረስ በካፒታሊዝም ውስጥ ምንዳዕ የጉልበት ክፍያ ውጫዊ መልክን እንደያዘ፣ ጠቅላላ ጉልበት ሙሉ በሙሉ እንደሚከፈለው ሆኖ በማይቀር ሁኔታ አምነቱ ይፈጠራል። ሠራተኛው የኑሮ መደጐሚያውን ለራሱ እናለቤተሰቡ ለማግምረት ፣ በሕብረተሰቡ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ስድስት ሰዓት ያስፈልጋል እንበል ። ከዚህ ውስጥ አንዱ ሰዓት በአንድ ብር ቢገለጽ ፣ የጉልበት — ኃይሉ ዕሴት ከስድስት ብር ጋር እኩል ይሆናል ። ካፒታሊስቱ ለሙሉው የጉልበት — ኃይሉ ዕሴት ይከፍላል — ስድስት ብር ፣ ግን ሠራተኛውን 12 ሰዓት እንዲሠራ ያስገድደዋል ። ስለዚህ ምጥኑቱ (Rate) በሰዓት 50 ሳንቲም ብቻ ነው የሚሆነው ። ምንዳዕ ፣ ካፒታሊስቱ ከሥራ ቀኑ ለከፈሉ እንጂ ለቀረው እንደማይከፍል ያለውን ዕውነት ይደብቃል ። ስለሆነም ፣ ምንዳዕ ሁሉንም ዓይነት የሥራ ቀን በአስፈላጊና በትርፍ የሥራ — ጊዜ በተከፈለና ባልተከፈለ የሥራ — ጊዜ ክፍፍልን ይሸፍናል ። ምንዳዕ ፣ በምንዳዕ ሠራተኛው የፈሰሰውን ጠቅላላ ጉልበት ሙሉ በሙሉ የሚከፈል ስለሚአስመስል ቡርዧዎች ብዝበዛን እንዳይታይ መጋረዳቸውን እንዲገለፅ ያደርጋል ። ይህ ነው ካፒታሊዝምን ከሁሉም በዝባዥ ሕብረተሰቦች ቀድመው ይኖሩ ከነበሩት ሁሉ ልዩ የሚአደርገው ።

የምንዳዕ መልኮች በካፒታሊዝም ውስጥ ምንዳዕ የተለያዩ መልኮች ይኖሩታል ። የጊዜ—ምንዳዕ በተሠራው የጊዜ ርዝመት መሠረት —በቀን ፣ በሳምንት ወይም በወር—ለጉልበት—ኃይል የመክፈያ መልክ የተሠራ ነው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ የጊዜ — ምንዳዕን ትክክለኛ ሀሳብ ለመረዳት ፣ ከሥራ ቀኑ ርዝመት ጋር በመነጻጸር መጤን ያስፈልገዋል ። ለምሣሌ ፣ ካፒታሊስቱ አንደን ሠራተኛ በቀን 10 ብር ይከፍለውና ሠራተኛውም 10 ሰዓት ይሠራል ። ስለዚህ የአንድ የሥራ ሰዓት አማካይ ተመን አንድ ብር ነው ። ካፒታሊስቱ የሥራ ቀኑን ርዝመት ከ10 ወደ 12 ሰዓት ያራዝመው እንበል ። በዚህ መንገድ የሥራ ሰዓቱ ተመን (ክፍያ) ከአንድ ብር ወደ 83 ሳንቲም ያሽቆለቁላል ። የጊዜ — ምንዳዕ የካፒታሊስት ብዝበዛን የማጠናከሪያ ዘዴ እንደሆነ ከዚህ መረዳት ይቻላል ። ከጊዜ ምንዳዕ ሌላ ፣ የምንዳዕ ሌላ መልክም አለ ፤ ቁራጭ—ምንዳዕ የሚባል ።

የሠራተኞች ክፍያ መጠን በሸቀጦች መጠን (ብዛት) ወይም በተወሰነ ክፍለ ጊዜ (በቀን ወይም በሰዓት) በሚመረተው ክፍል ላይ ጥገኛ የሚሆነው የምንዳዕ መልክ ቁራጭ ምንዳዕ(የውጤት ክፍያ) ተብሎ ይጠራል ።

ማርክስ ቁራጭ ምንዳዕን ሲጠራው የጊዜ ምንዳዕ የተሻሻለ መልኩ ነው ብሎታል ። ምክንያቱም ለእያንዳንዱ ክፍል የክፍያውን ደረጃ ለመወሰን ካፒታሊስቱ የሚአጤነው ፣ በመጀመሪያ የሠራተኛውን የየቀኑን የጊዜ ምንዳዕና ሁለተኛ ደግሞ ጠንካራውና ይበልጥ የሰለጠነው ሠራተኛ በአንድ ቀን ውስጥ የሚአመርተውን የቁራጭ ቁጥር ነው (Number of parts) ።

የየቀኑ የጊዜ መጠን አስር ብር ቢሆንና በሠራተኛው የሚመረተው ቁራጭ ብዛት 20 ከሆነ ፣ ታዲያ ላንዱ ቁራጭ (ክፍል) ቁራጭ ድርሻ ደግሞ የብር ግማሽ ነው የሚሆነው ። ስለዚህ ካፒታሊስቱ ቁራጭ ምንዳዕ የጊዜ ምንዳዕን እንደማይበልጥ ያረጋግጣል ። ታዲያ ነገሩ እንዲህ ከሆነ ፣ ለምንድነው ካፒታሊስቶች ቁራጭ ምንዳዕን ያመጡት ? ይህን የሚአደርጉበት ምክንያት ከቁራጭ ምንዳዕ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ባሕሪዎች ለካፒታሊስቶች ከሌላ የምንዳዕ መልኮች የበለጠ ከፍ



ተኛ ጥቅም ስለሚሰጡ ነው ። ለምሣሌ — በቁራጭ ምንዳዕ የሥራው ጥራት በአለቀለት ምርት ስለሚታይ (ስለሚረጋገጥ) ነው ። ካፒታሊስቱ የሚከፍለው ለከፍተኛው ወይም ለመካከለኛው ጥራት እንጂ ለውራጁ አይደለም ። ይህ ዓይነት ምንዳዕ በሠራተኛው ጉልበት ላይ ተጨማሪ ጥረት ያመጣና እያንዳንዱ ሠራተኛ የበለጠ ገንዘብ ለማግኘት ሲል ውጤቱን ለመጨመር ይታትራል ። ግን ወዲያው ሁሉም ሠራተኞች ምርታቸውን እንዲጨምሩና ጥራት እንዲሰጡት ፣ ካፒታሊስቶች ለእያንዳንዱ ክፍል የሚሰጠውን ክፍያ ያወርዱታል ፣ እናም ይህ ትርፋቸውን ይጨምራል ። ለዚህ ነው ማርክስ ሠራተኛው የበለጠ በሠራ መጠን ፣ ያነሰ ምንዳዕ ነው የሚቀበለው ያለው ።

ካፒታሊስቶች የተለያዩ የምንዳዕ መልኮችን የሚጠቀሙበት ተጨባጭ ሁኔታዎችን ለማርካት (ለማሟላት) ነው ።

በታሪካዊ ሂደቱ የጊዜ — ምንዳዕ የተከሰተው ከቁራጭ ምንዳዕ በፊት ነው። የመጀመሪያው የተስፋፋው ሠራተኞች የሥራ ቀን በማራዘም ትርፍ ዕሴትን በሚጨምሩበት ሁኔታ ላይ ባሉበት በጥንታዊው የካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ነው ። ይህ ዓይነት አከፋፈል የተለያየ ጥቅም እንዲአገኙ አድርጓቸዋል ። በኋላ ፣ የሥራ ቀኑ ርዝመት በሕግ በተወሰነበት ጊዜ ቀጣሪዎች ቁራጭ — ደረጃን በሰፊው ተያያዙት ። የዛሬው ዘመንም የጊዜ ደረጃን የጉርሻ ዘዴ (Time - rate -bonus system) የተለያዩ መልኮች ዕድገት ያረጋግጣል ። ስለዚህ ፣ ወደ 1957 ዓ. ም. መጨረሻ ላይ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከኢንዱስትሪ ሠራተኞች 70 በመቶው የተሻሻለ የጊዜ ምንዳዕ ተቀብለዋል ።

ከጊዜ — ምንዳዕ ወደ ቁራጭ — ምንዳዕ ሽግግር መግለጫው ምንድነው ? ነገሩ ፣ የዘመናዊ ካፒታሊስት ኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች በተወሰነ ደረጃ ከሚንቀሳቀስ ቺንጋ (Conveyor belt) ጋር «የፍሳሺ» ዘዴን ማቅረቡ ነው ። ይህም ማለት የምርት ፍጥነት ጥገኝነቱ በሠራተኛው ላይ ሳይሆን ፣ የሚወሰነው በማከታተል የቺንጋውን የበለጠ ፍጥነት በመጨመር ወይም በምርት ቴክኖሎጅ ልዩ አፈጣጠር ላይ ነው ። የጉልበት በሰፊው መታፈግ በሠራተኞች ምንዳዕ - ጭማሪ የተካበበ አይደለም ።

የክፍያ ፣ የጊዜና የቁራጭ መልኮች ሁልጊዜም የሚውሉት ባንዴና ባንድ ዓይነት ድርጅት ነው ። በካፒታሊዝም ፣ እነዚህ ሁሉ የምንዳዕ መልኮች የሠራተኛውን መደብ የመበዝበዝ ማጠናከሪያ የተለያዩ ዘዴዎች ብቻ ናቸው ።

ካፒታሊስቶች ጭማሪ ትርፍ ዕሴት ለመሰብሰብ ባላቸው ፍላጐትና ምርትን ለማቀናጀትና ምንዳዕን ለመክፈል የተለያየ የመጭመቂያ (የማንጠፍጠፊያ) ሥርዓቶችን ያወጣሉ ። የእነዚህ ሥርዓቶች ባሕሪ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከሠራተኛው ላይ የቻሉትን ያህል ጉልበት ለመጭመቅ ነው ። ለምንዳዕ ክፍያ በደርዘን የሚቆጠሩ የመጭመቂያ ሥርዐቶች አሉ ።

ከነዚህ ሥርዓቶች የመጀመሪያው አንዱ ይህን በተጠቀመበት የአሜሪካዊው ኢንጂኒዬር ኤፍ ቴይለር ስም የተሰየመው ቴይለራዊነት ነው ። የቴሌራዊነት ባሕሪ እንደሚከተለው ነው ። ጠንካሮችና ይበልጥ የሰለጠኑ ሠራተኞች በድርጅቱ ባለቤት በሆነው ካፒታሊስት ይመረጡና እስከመጨረሻ «ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ» የሥራ ፍጥነት ድረስ እንዲሰሩ ይገደዳሉ ። የተለያዩ አሠራሮች አካሄድ የሚወሰነው በሰከንድና በሰከንድ ክፍልፋዮች ነው ። የተገኘው ሠንጠረዥ ወደልዩ ቴክኒካዊ ቦርድ ፣ ማለትም ከጥናት በኋላ ፣ በድርጅቶች ውስጥ ላሉ ሠራተኞች ሁሉ የጊዜ — ደረጃና የምርት ሥልጣን ለሚወስኑት ይተላለፋል ። ሁለት የክፍያ ደረጃዎች ቀርበዋል ፣ ሥራውን ላሟሉ ከፍተኛውን ደረጃና ዝቅተኛ ደረጃ ደግሞ ላላሟሉት ። ይህ የምንዳዕ አከፋፈል ለጉልበት አምራችነት ከፍተኛ ዕድገት ሲሰጥ ፣ ምንዳዎች ግን አልፎ አልፎ እንኳን አይጨምሩም ፣ ስለዚህ የጉልበት የመበዝበዝ ደረጃ በሰፊው ይንራል ።

ሌላው ዓይነት የመጭመቂያ ዘዴ ፎርዳዊነት ነው ። ዓላማው እንደቀድሞው ነው ። ይህ የሚገኘው የቮንጋውን ቀበቶ ፍጥነት በመጨመር ነው ። በፊት ግን ፣ ለምሳሌ ፣ በደቂቃ ሶስት ሜትር ነው የሚንቀሳቀሰው ፣ አሁን ደግሞ ከአራት እስከ አምስት ሆኗል ። በዚህ ሁኔታ ሠራተኛው ወደደም—ጠላ (Willy-nilly) የበለጠ ኢነርጂ እንዲጠቀሙና የበለጠ እንዲሠራ ይገደዳል ፣ ግን የሠራተኛው ምንዳዕ በቀድሞ ደረጃው ይቆያል እናም ለሚያጠፋው ጉልበት ተመጣጣኝ አይደለም ። የዚህ ውጤት ብዙ ሠራተኞች ከ40— 45 ዕድሜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ መላሸት እናም በቀጣሪያቸው መባረር ነው ።

በተጨማሪም ፣ በቮንጋው ቀበቶ የሚከናወነው የተቃልሎ አሠራር ካፒታሊስቶችን ያልሰለጠኑ ሠራተኞችን ለመቅጠር፣ ዝቅተኛ የአከፋፈል ደረጃን ለመወሰን፣ እናም ስለዚህ ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት አስቻላቸው ።

የ« ትርፍ ክፍያ » አሠራርም በምንዳዕ የመጭመቂያ ሥርዐቶች መካከል ሊመደብ ይችላል ። እዚህ ካፒታሊስቶቹ የቀጠሯቸውን ሠራተኞች ከሌሎች ቀጣሪዎች ያነሰ እንደሚከፍሏቸውና በየዓመቱ መጨረሻ ግን ፣ የሥራው ሚዛን በሚነጥርበት (በሚታወቅበት) ጊዜ ፣ ደህና አድርገው የሰሩት ሠራተኞች ከትርፉ ድርሻ እንደሚሰጣቸው ያስታውቋቸዋል ።

የዚህ ዓይነት አሠራር የጉልበትን የመሥራት ኃይል ከፍ ሲአደርግ ፣ የሠራተኞችን መደብ ንቃተ — ሕሊና ዕድገት ይጎትታል ፣ ትጋታቸውን ያደድባል ፣ ካፒታሊስቶችን በመጻረር የሚአካሂዱትን ትግል ይከፋፍልና ወደ ኋላ ይስባል። የ« ትርፍ — ክፍያ » አሠራር ሠራተኞች የካፒታሊስት ድርጅትን ትርፍ ከፍ የማድረግ ዝንባሌ ይኖራቸዋል የሚል ጉም ዘገና ሀሳብ ይፈጥራል ።

*ስማዊና እውነተኛ ምንዳዕ*

በካፒታሊስት ዕድገት የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ምንዳዕ በገንዘብ መልክ ለሠራተኞች የሚከፈለው አልፎ አልፎ ነበር ። ካፒታሊስቶች ሠራተኞችን የምግብና የብሉት (ፍጆት) ዕቃዎች ከፋብሪካ ሱቆች በዱቤ እንዲገዙ በሚገደዱበት ሁኔታ ያስቀምጧቸዋል ። በወር ወይም በመንፈቅ መጨረሻ ላይ ፣ ካፒታሊስቱ ሠራተኛው ምን ያህል እንደሚአገኝና ምን ያህል ዕቃ እንደሚወስድ ሂግብ ያደርጋል ።ሂግቡ ሲሰራ ሠራተኛው ምንም ገንዘብ ማግኘት የማይችል ፣ ቢአገኝም እጅግ ጥቂት ይሆናል ።

በዛሬው ጊዜ ፣ በዓይነት ክፍያ በተለይ በሰፊው የተስፋፋው በምጣኔ — ሀብት ወደ ኋላ በቀሩት አገሮች ነው ።

ይሁንና በዳበሩ የካፒታሊስት አገሮች የገንዘብ ምንዳዎች አሁን ሰፍነው የሚታዩ መክፈያዎች ናቸው ።

በገንዘብ መልክ የሚገለጽ ምንዳዕ ስማዊ ምንዳዕ ተብሎ ይጠራል ። ግን ስማዊ ምንዳዎች ሠራተኛው የሚወስደውን ትክክለኛውን የክፍያ ደረጃ ሊአሳዩ አይችሉም ። እውነተኛ ምንዳዕ ተብሎ የሚጠራው ፅንሰ — ሀሳብ ይህን ደረጃ ለመወሰን ይውላል ። እውነተኛ — ምንዳዎች የሠራተኛውን የሕይወት መደጎሚያ በሚመለከት ረገድ የሚገለጹ ምንዳዎች ናቸው ። በአንድ ቃል ፣ እውነተኛ ምንዳዎች ምንና ምን ያህል የኑሮ መደጎሚያዎችን ሠራተኛው ለራሱና ለቤተሰቡ በተቀበለው ገንዘብ ሊገዛ እንደሚችል ያሳያሉ ።

እውነተኛ ምንዳዎችን ለመወሰን የስማዊ ምንዳዎች መጠን ፣ የብሉት ዕቃዎች ተመንና አገልግሎቶች ፣ የግብር ሚና ፣ ኪራይና ዕዳ መጠን አለባቸው ። ካፒታሊዝም ሲዳብር እውነተኛ ምንዳዎች ወደ መውደቅ ያጋድላሉ ።

በካፒታሊዝም ውስጥ የእውነተኛ ምንዳዎች የሚያሽቆለቁለው በተለያዩ ምክንያቶች ነው ። ከነዚህም የመጀመሪያው የአደገው ተመን ነው ። የሠራተኛው



ስማዊ ምንዳዎች በትንሹ ይቀንሱ ይሆናል ፣ ግን የዕቃዎች ተመን በሰፊው ከአሻቀበ ፣ እንደበፊቱ ያህል ዕቃዎችን ሊገዛ አይችልም ፣ ይህም ፣ እውነተኛ ምንዳው ወድቋል ማለት ነው ። ለምሳሌ፣ በፈረንሣይ በ1938 እና 1954 መካከል የሁሉም ዓይነት ዕቃዎች ተመን ከ32 ጊዜ እጥፍ በላይ ጨምሯል ፣ የገንዘብ ምንዳዎች የጨመሩት በ21 እጅ እጥፍ ብቻ ነው ። ውጤቱ በ1954 የፈረንሣይ ሠራተኞች በ1938 እንዳደረጉት ሁሉ ለመግዛት አለመቻል ነበር ። በሌሎች ካፒታሊስት አገሮችም ሁታኔው እንዲሁ ነበር ።

ሌላው የማሽቆልቆል ምክንያት (የዕውነተኛ ምንዳዎች) የግብርና የዕዳዎች (ኪራይ ፣ የማሞቂያ ፣ የመብራትና ሌሎች ክፍያዎች) ማደግ ነው ። ይህ የአደገ ክፍያ በሠራተኞች እውነተኛ ምንዳዕ ላይ ይህ ነው የማይባል ቅነሳ አምጥቷል ። በዩናይትድ ስቴትስ ፣ ለምሳሌ ፣ ከሕዝብ የሚሰበሰበው ግብር በ1959 አሥራ ሁለት ጊዜ ያህል እጥፍ የ1939ቹን ፣ እና የ1958 ኪራዮች ከክፍያው (ከምንዳው) ከ25—30 እጅ በመቶ ይዘውታል ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ለሠራተኞች መደብ እውነተኛ ምንዳዕ መውደቅ ከምክንያቶች ጥቂቶቹ እነኚህ ናቸው ።

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ በወንዶች መካከል እንዳለው ሁሉ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ በሴቶችና በወንዶች የለም ።ሴቶች ከወንዶች እኩል ሥራ ቢሰሩም የማይመጣጠን አነስተኛ ምንዳዕ ነው የሚከፈላቸው ።

ለምሳሌ ፤— በዩናይትድ ስቴትስ የዘር መድልዎ ለካፒታሊስቶች ከፍተኛ ትርፍ ምንጭ ነው ፣ ስለሆነም ጥቁር ሠራተኞች ከነጭ ሠራተኞች ይልቅ ባነሰ ያሠራር ሁኔታ ነው የሚኖሩት ። በተለይ የሚቀጠሩት እጅግ አስቸጋሪ ፣ ጉጅና አደገኛ ሥራ ላይ ነው ። ለጥቁር ሠራተኞች የሚከፈለው ከነጮቹ እጅግ ያነሰ ነው ።

በተለያዩ የካፒታሊስት አገሮች የምንዳዕ ደረጃ አንድ ዓይነት አይደለም ። ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶች አሉት ። እርግጥ ባንዳንድ አገሮች ውስጥ ያሉ ካፒታሊስቶች ከሌሎች ይልቅ ለሠራተኞች የተሻለ አገምጋሚያ አላቸው ብሎ ማሰብ ስህተት ይሆናል ። በየትም ምንዳዕን ለማውረድ ይፍጨረጨራሉና ። ግን በተለያዩ አገሮች ያሉትን ምንዳዎች በምናወዳድር ጊዜ ሠራተኛው መደብ የተመሠረተበትን ሁኔታ ፣ የሚአስፈልጉት ተለምዶአዊ (ባሕላዊ) ደረጃዎች ፣ የሰለጠነ ጉልበት ለማፍራት የሚወጡት ወጭዎች ፣ የጉልበት አምራችነት ፣ በሚመለከተው አገር ውስጥ ያለው የመደብ ትግልና ጸባይ መጨን አለባቸው — ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ ፣ ካፒታሊዝም ያደገው ያጉልበት እጥረት ባለበት ጊዜ ነው ፣ ይህ እውነት ደግሞ ምንዳዎችን ከፍ እንዲሉ አደረገ ። በእንግሊዝ የሠራተኛው መደብ ለመደራጀትና ካፒታሊስቶችን ለመቋቋም የመጀመሪያው ነበር ። በዚህ ምክንያት በእንግሊዝ የሠራተኞች ምንዳዕ ፣ ከአየር ላንድ ሲነፃፀር የበለጠ ነው ።

*ለከፍተኛ ምንዳዕ የሠራተኛው መደብ ትግል*

የበለጠ ትርፍ ለመጭመቅ፣ ካፒታሊስቶች የሠራተኞችን ክፍያ ለማውረድ ይታትራሉ ። ቡርጂዋው ከሠራተኛው መደብ ጋር ባለው ትግሉ የመንግሥትንዕርዳታ ፣ ሕግን ፣ ቤተክህነትን ፣ ጋዜጦችን ሬዲዮን ፣ ቴሌቪዥንን ፣ ወዘተ . . . ይጠቀማል ። ካፒታሊስቶችም ጸረ — ሠራተኛ የሆነ ግንባር ለመፍጠር በቀጣሪዎች ማኅበር ውስጥ ይተባበራሉ ።

በሌላ በኩል ፣ ሠራተኞችም የወረትን ጥቃት ለመቋቋምና የምጣኔ — ሀብታዊ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በሙያ ማኅበራቸው ይተባበራሉ ።

ዛሬ የሠራተኛውን መደብ ድርጅታዊ ጥንካሬ መጠቆሚያ የሚሆነው በ1960 በመላው ዓለም ጠቅላላው የሙያ ማኅበር አባላት 180 ሚሊዮን ሲሆኑ ፣ ከዚህም 100 ሚሊዮን ሠራተኞች የዓለም ፌዴራል የሙያ ማኅበር አባል መሆናቸው ነው።

የምንዳዎች ደረጃ የሚመሠረተው በወዛደሩና በቡርዧዋው መካከል በሚደረገው መራራ የትግል ውጤት ነው ። በአድማ ውስጥ የሠራተኞች ግትርነትና ቆራጥነት በሚገለጽበት ጊዜ ካፒታሊስቶች ሁልጊዜም ፍላጐታቸውን ለማሟላትና ደመወዝ ለመጨመር ይገደዳሉ ። የሠራተኞች መደብ ትግል የኑሮ ሁኔታቸውን ለማሻሻል ሲባል በቅርቡ እጅግ በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች — ዩናይትድ ስቴትስ ፣ እንግሊዝ ፣ ፈረንሣይ ፣ ጣሊያን ፣ ምዕራብ ጀርመንና ጃፓን—በሰፊው ተቀጣጥሎ ነበር ። በ1949 በምጣኔ — ሀብታዊና በፖለቲካ ግጭቶች የተካፈሉ ሠራተኞች ቁጥር 41 ሚሊዮን ፣ በ1960 — 54 ሚሊዮን ፣ እና በ1961—ከ70 ሚሊዮን በላይ ነው።ታሪክ ሁልዜጊም በሰፊው የፈረንሣይ ፣ የጣሊያን ፣ የቤልጅግ ፣ የአሜሪካንና የእንግሊዝ ሠራተኛ የተወሰደውን እርምጃ ያስታውሰዋል ። በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ለምጣኔ — ሀብታዊና ለሰሻል መብታቸው የሠራተኞች ትግል ከቀን ቀን እየተባባሰ ነው ።

የወዛደሩ ምጣኔ — ሀብታዊ ትግል ከፍተኛ ዓይነተኛነት አለው ። ሆኖም ይህን እውነት በምናጤንበት ጊዜ ፣ ማርክሲዝም —ሌኒኒዝም ፣ ይህ ብቻውን ሠራተኞችን ከብዝበዛ ነጻ እንደ ማያወጣ ያስተምረናል ። የካፒታሊስትን ሥልተ — ምርት በአብዮታዊ ፣ በፖለቲካዊ ትግል ማስወገድ ብቻ ነው የሠራተኛውን ምጣኔ— ሀብታዊና ፖለቲካዊ ጭቆና ክትመት የሚሰጠው ።

ምዕራፍ ፬

## የወረት መከማቸትና የወዛደሩ ኑሮ እያሽቆለቆለ መሄድ ፤

ቀደም ብለን ትርፍ ዕሴት የሚመረተው በወረት (ካፒታል) እንደሆነ አግኝተናል ። ግንወረትም በተራው የሚመጣው ከትርፍ ዕሴት ነው ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ስለካፒታሊስት ዕርባታ አሠራር አንዳንድ ነገሮችን መማር አለብን ።

### 1 የወረት መከማቸትና የሥራ አጡ ሠራዊት ፤

ዕርባታና የወረት መከማቸት

ስለ ምርት ስንናገር ፣ ቁሳዊ ሀብት የመፍጠርን ሂደት ማለታችን ነው ። በካፒታሊዝም ውስጥ ፣ ይህ ማለት ካፒታሊስቱ የምርት መገልገያዎችንና የጉልበት ኃይልን በገበያ ላይ ገዝቶ ፣ ከዚያም ቁሳዊ ሀብት በሰዎች ይፈጠራል ነው ። ስለ ዚህም የምርት ሂደት ተፈጸመ ። ግን ይህ ከእንግዲህ ቁሳዊ ሀብትን ማምረት አያስፈልግም ማለት ነው ? አይ ! እንዲያ ማለትስ አይደለም ። ሕብረተሰብ ቁሳዊ ሀብት ማምረትን አያቆምም ፣ እንዲያ ማድረግ ሕልውናውን አደጋ ላይ ይጥለዋልና ። ስለዚህ ምርት ማይቋረጥ ይሄዳል ፣ ማለትም ፣ አንድ ዓይነት ደረጃዎች ብዙ ጊዜ ይደጋገማሉ ። ይህ ያልተቋረጠ የቁሳዊ ሀብት ምርት የመታደስና የመደጋገም ሂደት ዕርባታ ተብሎ ይጠራል ።

ዕርባታ በማንኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ ይካሄዳል ፣ ግን ከዕርባታ በስተጀርባ ያሉት መገፋፊያ ኃይሎች ከአንዱ ሕብረተሰብ ወደሌላው ይለያያሉ ። በካፒታሊዝም ውስጥ ገፋፊው ኃይል የካፒታሊስቶች ትርፍ ዕሴት ስብሰባ ነው ። ቁሳዊ ሀብት የሠራተኛውን ሕዝብ ፍላጐት ለማርካት ማይሆን የሚመረትና የሚራባው ፣ ካፒታሊስቶች እንዲያተርፉ ነው ።

በካፒታሊስቶች የሚወሰደው ትርፍ ዕሴት የሚፈጠረው በካፒታሊስት ዕርባታ ሂደት ጊዜ ነው ። ግን ስለትርፍ ዕሴት አወሳሰድ ብቻ አይደለም ፍላጐታችን ፣



በጥቅም ላይ እንዴት እንደሚውልም ነው ፣ ማለትም በምን ላይ እንደሚጠፋ ። ካፒታሊስቱ ጠቅላላ ትርፍ ዕሴቱን ለግላዊ ፍላጐቱ የሚአጠፋው ከሆነ ፣ ቀላል ዕርባታ ተብሎ የሚጠራው ነው ማለት ነው ። ካፒታሊስቱ የ $200,000 ወረት በሥራ ላይ አዋለ እንበል ፣ ከዚህ ውስጥ ቀዋሚ 160,000 ተለዋዋጭ ደግሞ 40,000 ይሁን ፣ በ100 ከመቶ ደረጃ ትርፍ ዕሴት ፣ የተመረቱት ሸቀጦች $240,000 ዕሴት ይኖራቸዋል ፣ ይህን የምንለው ሁሉም ቀዋሚ ወረቱ ከውጤቱ ዕሴት ውስጥ እንደገባ በማሰብ ነው (160,000 ቀ + 40,000†40,000ትዕ= 240,000) ። ይህ $240,000 መጀመሪያ ላይ በሥራ የዋለውን $ 200,000 በተጨማሪ በምርት ሂደት ጊዜ በሠራተኞች ጉልበት የተፈጠረውን ትርፍ ዕሴት $ 40,000 ይይዛል ።

በቀላል ዕርባታ ውስጥ ትርፍ ዕሴት በሙሉ የሚጠፋው በካፒታስቶች ዕለታዊ(ግላዊ) ፍላጐትና በቤተሰቡ ስለሆነ ፣ የዕርባታው ሂደት በሚቀጥለው ዓመት በዚያው ደረጃ ይታደሳል ። በሦስተኛውና በአራተኛውና ቀጥሎም ያው ይሆናል ። ምንም እንኳ በቁሳዊ ሀብት ቀላል ዕርባታ ውስጥ በመጠን ሳይለያይ ቢደጋገምም ስለዚሁ ትንታኔ ማድረግ የካፒታሊስቶችን የብልፅግና ምንጭ ግልፅ ያደርጋል ።

በምርት ሂደት ጊዜ መጀመሪያ በሥራ ላይ የዋለው ወረት ይራባል ፣ እናም ትርፍ ዕሴቱ ካፒታሊስቱ ለግላዊ ፍላጐቱ የሚአጠፋው ይፈጠራል ።

ካፒታሊስቱ ትርፍ ዕሴቱን የማይወስደው ቢሆን ኖሮ ፣ ከጊዜ በኋላ ለሥራ ያወጣውን ወረት ሁሉ ለግላዊ ፍላጐት ይጠቀምበትና ይጨርሰው ነበር ። በምሣሌአችን ካፒታሊስቱ በየመቱ $ 40,000 ያጠፋል ፣ መጀመሪያ በሥራ ላይ የዋለው ወረት $ 200,000 ከሆነ ፣ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ምንም አይቀረውም ማለት ነው ። ሆኖም ይህ አይደረግም ፣ ምክንያቱም ካፒታሊስቱ ለግላዊ ፍላጐቱ የሚአጠፋው የገንዘብ ድምር ባልተከፈለው የሠራተኞች ጉልበት የሚፈጠረውን ትርፍ ዕሴት ነውና ።

መጀመሪያ በሥራ ላይ የዋለው ወረት ምንጩ ምንም ይሁን ፣ ቀድሞውኑ በቀላል ዕርባታ ጊዜ ከጊዜ ብዛት ይህ ወረት በሠራተኞች ጉልበት የሚፈጠር ዕሴትና ሳይመለስ በካፒታሊስቶች የሚወሰድ ነው ።

ከዚህ አንድ በጣም ዓይነተኛ ነጥብ ይመጣል ። ያ ነው በሶሻሊስት አብዮት ጊዜ ፣ ሠራተኛው መደብ ካፒታሊስቶችን የሚወስድባቸው ፣ ፋብሪካዎቻቸውን የሚነጥቃቸው ፣ ሌላ አይደለም ! የሠራተኛው መደብ ትውልዶች የፈጠሩትን ብቻ ነውመልሶ የሚወስድ ። የካፒታሊስት ግላዊ ባለቤትነት መወገድ ሕጋዊ ክንውን ነው ፣ የታሪካዊ ፍትህ ክንውን ነው ።

ካፒታሊስቱ ሁሉንም ትርፍ ዕሴቱን በግላዊ ፍላጐት እንደሚአጠፋው አስበን ነበር ። ግን ይህ ሁኔታ እስከመጨረሻው ይኖራል ? በካፒታሊስት ዕድገት የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ተደጋግሞ የሚታየው ይህ ነበር — ስለዚህም ካፒታሊስቱ የሚበዘብዘው ጥቂት ሠራተኞችን ሆኖ አልፎ አልፎም እራሱ ይሠራ ነበር ። የካፒታሊስት ድርጅቶች ሲስፋፉ ሁኔታው ተለወጠ ፣ ስለሆነም ካፒታሊስቱ በመቶና በሺ የሚቆጠሩ ሠራተኞችን መበዝበዝ ጀመረ ። ካፒታሊስቱ 1,000 ሠራተኞችን ቀጥሮ በዓመት 2 ሚሊዮን ብር ዕሴት ይከፍላል እንበል ። እነዚህ ሠራተኞች በየመቱ 2 ሚሊዮን ብር የሚሆን ዕሴት (በ100 ከመቶ የትርፍ ዕሴት ደረጃ) ይፈጥሩለታል ። አሁን ፣ ቀጣሪው ከእንግዲህ ሁሉንም አያጠፋም ፣ የሚአጠፋው ለግላዊ ፍላጐቱ የተወሰነውን ክፍል ብቻ ነው— ሌላው ምርት ለማስፋፋት ፣ ሌላ ማሺንና ጥሬ ዕቃ ለማግኘትና የበለጠ ጉልበት ለመቅጠር ይውላል ። በዚህ ሁኔታ ዕርባታን ወይም የወረት ክምችት የሚባለውን አስፋፍተናል ።

የትርፍ ዕሴትን ወደ ካፒታል (ወረት) የመሸጋገር ሂደት እስቲ እንመርምር ። ካፒታሊስቱ 10 ሚሊዮን ብር የሚሆን ወረት አለው እንበል ። ከዚህ ውስጥ

8 ሚሊዮኑን ለቀዋሚ ወረትና 2 ሚሊዮኑን እንደተለዋዋጭ ወረት አዋለው ። የትርፍ ዕሴቱ ደረጃ 100 ፐርሰንት ይሆናል ። የምርት ሂደቱ ከተከናወነ በኋላ ቀዋሚ ካፒታሉ (ወረቱ) በሙሉ በምርቱ ዕሴት ላይ እንደገባ በማሰብ ፣ የ12 ሚሊዮን ሸቀጥ ይመረታል (8 ሚሊዮን ‘ ቀ + 2 ሚሊዮን ‘ተ’ + 2 ሚሊዮን ‘ትዕ’) ።

በካፒታሊስቱ የ2 ሚሊዮን ብር ትርፍ ዕሴት እንደሚከተለው ተወሰነ እንበል ፣— ምርትን ለማስፋፋት — 1 ሚሊዮን ፣ ለግል ብሎት — 1 ሚሊዮን ። ከሴላም በኩል ፣ ምርትን ለማስፋፋት የዋለው የትርፍ ዕሴት ክፍል ድሮውኑ ከመጀመሪያ ወረቱ እንደዋለበት ሥልት ሁሉ በቀዋሚና በተለዋዋጭ ወረት ይከፋፈላል ፣ ማለትም—4 ፡ 1 (800,000 ቀ+ 200,000 ተ) ።

ውጤቱ ድርጅቱ በሁለተኛው ዓመት 11 ሚሊዮን (8,800,000ቀ+2,2000,000 ተ) እንዲንቀሳቀስ አድርጐ ይሆናል ። የትርፍ ዕሴቱ ደረጃ 100 ፐርሰንት ከሆነ የሁለተኛው ዓመት ሸቀጥ የ13.2 ሚሊዮን ያህል ሊመረት ይችላል(8,800,000 ቀ+ 2,200,000 ተ+2, 200,000 ትዕ) ።

በሁለተኛው ዓመት በምርት መጠንና በትርፍ ዕሴት ብዛት መጨመር በመጀመሪያው ዓመት ትርፍ ዕሴቱ ወደወረት ከተሸጋገረ ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ መስፋፋት ተደርጓል ። ስለዚህ ትርፍ ዕሴት የወረት መከማቸት ምንጭ ነው ። በካፒታሊዊነት ዘዴ ማለትም በወረቱ ላይ የትርፍ ዕሴት መጨመር ፣ ካፒታሊስቱ በካፒታሉ (በወረቱ) ላይ እየጨመረበት ይሄዳል ።

ለግል ብልፅግና ዕርካታ የሌለው የትርፍ ዕሴት ጥማት ካፒታሊስቱን የምርቱን ደረጃ ሳያቋረጥ እንዲያስፋፋ ይገፋፋዋል ። በሌላ በኩል ፣ ውድድር እያንዳንዱን ካፒታሊስት እንዳይጠፋ ፣ ምርትን እንዲአስፋፋና ቴክኒኩን እንዲ አራምድ ያስገድደዋል ። የቴክኒክን ዕድገትና የምርት መስፋፋትን መገቱት መጥራት ማለት ኋላ ቀርነት ፣ እናም ኋላ ቀር የሆኑትም የተወዳዳሪዎቻቸው ምርኮኞች መሆን ነው።

ካፒታሊስቶቹ ምርታቸውን ሳያቋርጡ ካስፋፉ ፤ ለግላዊ ፍጆታ ይጠፉ የነበረውን የትርፍ ዕሴት ክፍል ይቀንሳሉ ማለት ነው ? አይ ! አይሆንም ። የካፒታሊስቱ መደብ ሀብት ሲጨምር ፣ ካፒታሊስቶች ለግላዊ ፍላጐት ማርኪያ የሚጠቀሙበት ትርፍ ዕሴት መጠንም ይጨምራል ። ዛሬ በዩናይትድ ስቴትስ ፣ ካፒታሊስቶች ከገቢአቸው 25 ፐርሰንቱን የሚአጠፉት ለግላዊ ፍላጐት ነው ። የአንዳንድ ባለጸጋ ቤተሰቦች የተለያዩ ያማሩ ቤቶች ፣ ውድ የሆኑ ተንሳፋፊ ጀልባዎች ፣ የራሳቸው አውሮፕላኖችና በደርዘን የሚቆጠሩ የምቾት መኪናዎች አሏቸው ። ዛሬ የአሜሪካን ባለጸጐች የተትረፈረፈ ኑሮ የሚታየው በየወቅቱ ከ60ዎቹ ባለጸጋ ቤተሰቦች ባንዱ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በሚደረገው ታላቅ ሪሴፕሺን ነው ፤ አምስት ተራ ቤተሰብ ለጠቅላላ ኑሮው የሚአስፈልገውን ያህል ገንዘብ በዚያ ግብዣ ይጠፋል ። ይህ ሁሉ ነጥብ የሚአመለክተው የካፒታሊስቱ መደብ የተትረፈረፈ ኑሮና ድምመጣጭነት ጐን ለጐን ከካፒታል (ወረት)መከማቸት ጋር የሚአድግ መሆኑን ነው።

የጠማማ ቡርዧ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ተወካዮች እንደሚገልጹት በካፒታሊስቶች አንጻር የካፒታሊስት ክምችት በቁጠባ እንደሚመጣ ፣ ስለሕብረተሰብ ጥሩ አሳቢ በመሆን ፣ ፍላጐቶቻቸውን በመግታት እንደሆነ ነው የሚናገሩት ።

የዚህ አመለካከት ዓይነተኛ አንጧራቂ (BLATANT) ተሟጋቾች መካከል አንዱ በ19ኛው ምዕተ—ዓመት የእንግሊዝ ኤኮኖሚስት ሲኒየር ነበር ። «ካፒታል (ወረት) ለሚለው ቃል የተካሁትን፣ ኩስትር ብሎ በመናገር ፣ «እንደምርት መሣሪያ በመቁጠር ከማንኛውም ነገር መወገድ (ገለልተኛ) የሚለውን ቃል ነው» ይላል[1] ።

1 ኬ ማርክስ ካፒታል ቅጽ 1 ገጽ 596



« ከማንኛውም ነገር መወገድ » በሚለው ሁኔታ ላይ ማርክስ በቀልድ መልክ ካፒታሊስቱ ፍላጐቱን የሚገታው የእንፋሎት ሞተሮችን ፣ ሐዲዶችን ማዳበሪያዎችንና እራሱንም ከመጥቀም ፋንታ የተግባር መገልገያዎችን ለሠራተኞች «ባዋስ» ጊዜ እንዲሆን ጠቁሟል ። እነዚህን ስንኩል ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ማርክስ ሲአጋልጥ ፣ «ቀላል ሰብዓዊ ርኀራኄ» ካፒታሊስቶች ሠራተኞችን ከምርት መገልገያ ባለቤትነት በመከልከል «ከአስቀያሚ መስዋዕትነት» ነጻ እንዲሆኑ መጠየቅ እንደሚመስል በጥብቅ አመልክቷል ።

በ19ኛው ምዕተ — ዓመት መጨረሻ ላይ የሲኒየር ንድፈ — ሀሳብ በተሻሻለ መልክ በእንግሊዙ ኤኮኖሚስት አልፍሬድ ማርሻልና በአሜሪካዊው ኤኮኖሚስት ቶማስ ካርቨር ፣ እንዲሁም ብቻ «ከማንኛውም ነገር መወገድ» ን ( Abstinence ) «በተስፈኝነትና» «በቆይታነት» ( « Perspectiveness » and « Waiting ») በተኩት ታድሶ ነበር ።

እነዚህ ሁሉ ንድፈ ሀሳቦች የአተኰሩት ካፒታሊዝምንና የካፒታሊስት ብዝበዛን ትክክለኛ በማድረግ ነው ። ሆኖም ፣ የወረት መከማቸትና የክምችቱ ስፋት ጥገኛ የሚሆነው የቡርዧ ርዕዮተ ዓለማውያን እንዳሰቡት ሁሉ በካፒታሊስቶች « ከምንም ነገር መወገድ » ላይ ሳይሆን ግን በሠራተኛው መደብ መበዝበዝ ነው ፤ ለምሣሌ 8,000 ቀ+2,000 ተ የሚአህል ወረት እንውሰድ ። የ100 ፐርሰንት ትርፍ ዕሴት 2,000 ትዕ ፣ እና የ200 ፐርሰንት የትርፍ ዕሴት ደረጃ — 4,000 ትዕ ይሰጣል ። ስለሆነም ፣ የብዝበዛው ደረጃ በናረ መጠን የሚፈጠረው ትርፍ ዕሴት ይንራል እናም ያንኑ ያህል የክምችት መስፋፋትም ። የጉልበት — ኃይል የብዝበዛ ደረጃ የሚአድገው የሥራ ቀንን በማራዘም፣ የጉልበትን መታፈግ (Intensity) ከፍ በማድረግ ፣ ምንዳዕን ከጉልበት ኃይል ዕሴት በታች በማውረድ ፣ ወዘተ ፣ . . . ነው።

የጉልበት አምራችነትን መጨመር ለወረት ክምችት መፍጠን ዓይነተኛ ጠባይ ነው።ለካፒታሊስቱ ፣— ሀ/ የጉልበት ኃይል ሸቀጥን ዕሴት ለመቁረጥ ፣ ማለትም በዚያው መጠን ተለዋዋጭ ወረት ሕያው የሆነ ከፍተኛ ጉልበት በእንቅስቃሴ ላይ እንዲውል ሲአስችል ፣ ስለዚህም ከፍተኛ ምርት ፣ በመጨረሻም ፣ የበለጠ ትርፍ ዕሴት እንዲመረት ፣ ለ/ ለተስፋፋው ምርት የሚአስፈልገውን የትርፍ ዕሴት ክፍል ሳይቀንስ ግላዊ ፍጆቱን እንዲጨምር ፣ እና ሐ/ እንደወረት የሚጠቀምበትን ትርፍ ዕሴት ሳያሳድግ ፣ ርካሽ ማሺኖችን በመጠቀም በፍጥነት ምርትን እንዲአስፋፋ በማስቻል ወደ ርካሺ ሸቀጦች ያመራዋል ።

በመጨረሻ ፤ የተከማቸው ወረት መጠን ፤ በተግባር ላይ እንዲውል በተደረገው ወረት ይደናቀፋል ። የወረቱ መጠን ሲበዛ ፤ በቀዋሚና በተለዋዋጭ ወረት መከፋፈል ያለው ምጥነት ያው ሲሆን ፤ የተለዋዋጭ (ወረት) ካፒታልም ከፍተኛ ይሆናል ። ስለሆነም ፤ የወረቱ ክምችት መጠን ፤ ሌሎች ሁኔታዎች ያው ሆነው ፤ መጀመሪያ በሥራ ላይ ከተሰማራው ወረት መጠን በቀጥታ ይመጣጠናል ።

እነኚህ ናቸው የወረትን ክምችት መጠን መሠረታዊ ሁኔታዎች የሚወስኑ ።

እንዴት ነው የወረት ክምችት ለሠራተኛው መደብ የኑሮ ሁኔታ ደንቃራ የሚሆነው ? ይህን ጥያቄ ለመመለስ በመጀመሪያ የማርክስን የወረትን ይዘት አዋዋል (አመጣጥ) ንድፈ — ሀሳብ ማወቅ ይኖርብናል ።

**የካፒታል (ወረት) አካላዊ ይዘት**

ማርክስ ትርፍ ዕሴት በሚባለው ንድፈ — ሀሳቡ የወረትን በቋሚና በተለዋዋጭ ወረት መከፈሉን ግልጽ አድርጓል ፤ ስለሆነም የትርፍ ዕሴትን እውነተኛ ምንጭ አጋልጧል ። በማከታተልም ፤ ማርክስ በዚህ አስተሳሰብ ላይ የካፒታልን (ወረትን) አካላዊ ይዘት ንድፈ ሀሳብ ጨምሯል ።

የወረት ይዘት ከሁለት አቅጣጫ ሊጤን ይችላል — ከተፈጥሮ ቁሳዊነትና በዕሴት መሠረት ።

በዕሴት መሠረት የወረት ይዘት የሚወሰነው በወረት የቀዋሚና የተለዋዋጭ መከፋፈል ምጥነት ላይ ነው ።

በቁሳዊ መልኩ ፤ በምርት ሂደት ውስጥ የሚሠራው ወረት የሚከፋፈለው በምርት መገልገያና በጉልበት ኃይል ነው ። ባገልግሎት ላይ በዋሉት የምርት መገልገያዎች ዝምናና እነርሱን ለማንቀሳቀስ በሚአስፈልገው የጉልበት መጠን መካከል የሚወሰነው የካፒታል (ወረት) መገንባት የወረት (ካፒታል) ቴክኒካዊ ይዘት ተብሎ ይጠራል ። ይህ ግንኙነት ጥገኝነቱ በጥያቄው ውስጥ ያለው ድርጅት ቴክኒካዊ መሟላት ላይ ነው ።

በዕሴት መሠረት ያለው ይዘትና የወረት ቴክኒካዊ ይዘት በቅርብ የተያያዙ ናቸው ። በጠቅላላ አነጋገር የካፒታል ቴክኒካዊ ይዘት ለውጥ ሲደረግ ወደ ዕሴት መሠረት ለውጥም ያመራል ። ስለዚህ ፤ በቀዋሚና በተለዋዋጭ ወረት መካከል ያለ ግንኙነት ፤ ማለትም ፤ በዕሴት መሠረት የወረት ይዘት ፤ በወረት ቴክኒካዊ ይዘት እስከ ተወሰነ ድረስና የእርሱንም ለውጥ እስከ አንጸባረቀ ድረስ ፤ ማርክስ የወረት አካላዊ ይዘት ብሎ ሰይሞታል ።

ስለሆነም ፤ የወረት አካላዊ ይዘት የ«ቀ» (ቀዋሚ) እና የ«ተ» (የተለዋዋጭ) ወረት ግንኙነት ነው ። ለምሳሌ ፤ ወረቱ 800 ቀ + 200 ተ ቢሆን ፤ አካላዊ ይዘቱ 4:1 (ከአራት አንድ) ይሆናል ። በዕሴቱ መሠረት የወረቱ ይዘት ከአካላዊ ይዘቱ ሊምታታ አይገባውም ። የመጀመሪያው በገበያው የምርት መገልገያዎችና የጉልበት ኃይል ተመን መዋለል ጋር ሳያቋርጥ ሊለወጥ ይችላል ። የወረት አካላዊ ይዘት ሊለወጥ የሚችለው በቴክኒካዊ ዕድገት ለውጥ ተጽዕና ሲሳብ ብቻ ነው ። ከካፒታሊዝም ድብሪትና ከወረት ክምችት ዕድገት ጋር በወረት አካላዊ ይዘት ላይ የማይቋረጥ ዕድገት አለ ። ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በሥራ ላይ ባሉት ኢንዱስትሪዎች የወረት አካላዊ ይዘት በ1889 ዓ.ም. 4.5 : 1 ፤ በ1939 ዓ.ም. 6 : 1 እና በ1955 ዓ.ም. ደግሞ 8 : 1 ነበር ።

ይህ በአካላዊ ይዘት ውስጥ ያለው ዕድገት የሚአንጸባርቀው ምርት ሲአድግ በምርት ላይ ከዋለው የጉልበት ኃይል ሲመጣጠን የጥሬ — ሀብት ፤ የማሺን ፤ የመሳሪያዎችንና ሌሎች ዕቃዎችም ብዛት እንደሚጨምር ነው ። ለምሳሌ — የወረት አካላዊ ይዘት ከመጀመሪያ 1 :1 ከሆነ ፤ ኋላ 2 : 1 ፤ ከዚያም 3 : 1 : አልፎም 4 : 1 ፤ እንዲያም ሲል 5 : እያለ ይመጣል ። ይህም ማለት የተለዋዋጭ ወረቱ ከአጠቃላዩ ወረት ምጥነቱ ሲታይ ከ1/2 ወደ 1/3 ፤ 1/4 ፤ 1/5 ፤ 1/6 ወዘተ.. እንደሚሆን ነው ። ግን የጉልበት አስፈላጊነት (ተጠያቂነት) የሚወሰነው ባጠቃላይ ወረት ሳይሆን ፤ በተለዋዋጭ ክፍሉ እስከሆነ ድረስ ፤ የተለዋዋጭ ወረት አንጻራዊ መጕረድ (መሸፈን) ማለት ሠራተኞች ወደ ምርት የሚሳቡበት ደረጃ እንደሚያዘቀዝቅና ከወረት ክምችት በስተኋላ እንደሚጐተት ነው ።

ውጤቱ፡ብዛቱ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ የሠራተኛ ክፍልን ለሥራ—አጥነት መዳረግ ነው ። ከካፒታሊስት ክምችት አንጻር ሲታይ የሠራተኛው መደብ ከፊሉ የማይፈለግ ፍሳሺ ይሆናል ። ስለዚህም«ፍሳሺ ሕዝብ» ወይም አንጻራዊ ፍሳሽ ሕዝብ ተመሠረተ — ሥራ አጥነት ።

ቀዋሚ የሆነ አንጻራዊ ፍሳሺ ሕዝብ መኖር ማለት በማርክስ የተገኘው የካፒታሊስት የሕዝብ ሕግ መግለጫ ነው ። የዚህ ሕግ ባሕሪ አዲስ የተፈጠረው ትርፍ ዕሴት ሲአድግ የወረት ክምችት ማየል እናም የአካላዊ ይዘቱ መናር ይሆናል ። ግን የወረት ክምችት ከፍ ሲል እናም አካላዊ ይዘቱ ከናረ ፤ ወደምርት ሂደት የሚገባው የጉልበት ኃይል መጠን አነስተኛ ነው ።



ከምርት ተግባር ውስጥ የሠራተኞች መባረር ሥራ የሌለውን ሠራዊት ያመጣል ።

**የኢንዱስትሪው ተጠባባቂ ሠራዊትና መልኩ**

የኢንዱስትሪው ተጠባባቂ ሠራዊት መመሥረት ዋና ምክንያት በወረት አካላዊ ይዘት ማደግ ነው ። ግን ከዚህም ሌላ ፤ ሥራ — አጥነትን የሚአጠናክሩ ሌሎች ምክንያቶችም አሉ ። ከነዚህም ፡ — ሀ/ረዥምም ሰዓትና እጅግ በጣም የታፈገ ጉልበት ነው ። ካፒታሊስቶቹ የሥራ — አጡን ሠራዊት መኖር በመጠቀም የተቀጠሩትን ሠራተኞች የሁለት ወይም የሶስት ሠራተኞችን ሥራ እንዲሰሩ ያስገድዷቸዋል ። እናም ይህ የኢንዱስትሪውን ተጠባባቂ ሠራዊት እንዲአድግ ያደርገዋል ፤ ለ/በሰፊው የሴቶችና የሕጻናት ጉልበትን መተዋወቅ ሌላው ነው ። ቴክኒካዊ ለውጦችና የአሠራር ሥልት መቃለል በምርት ውስጥ ቀላል ክፍያ የሚከፈላቸው ሴቶችና ወጣቶች እንዲሳተፉ አስቻለ ፤ ይህም በሥራ ላይ የነበሩ ጐልማሳ ወንድ ሠራተኞችን እንዲባረሩ አደረገ ፤ ሐ/የትናንሽ አምራቾች መጥፋት — ወረት ሲከማች ፤ ይህ ሂደት ተባባሰ ፤ ገበሬዎችና የእጅ ሙያተኞች ምርትን እንዲለቁ ተገደዱና የሥራ — አጡን ደጃፈ አሳበጡት ።

በኢንዱስትሪ ውስጥ የሥራ ተጠባባቂ ሠራዊት በተቀጠሩት ሠራተኞች ላይ ሥልታዊ ግፊት በመጫን ለካፒታሊዝም ዓይነተኛ ነው ፤ ካፒታሊስቱ ሠራተኞችን እንዲባረሩ በማስፈራራት ምንዳዕን ዝቅ እንዲአደርግና የጉልበት መታፈግን በመጨመር ፤ ወዘተ . . . . የሠራተኛን መበዝበዝ እንዲአጠናክር ያስችለዋል ። ለዚህ ነው ካፒታሊስቶች የሥራ አጥነትን የተወሰነ ደረጃ ለማጠናከር ዝንባሌ የሚአሳዩት ።

አንጻራዊ ፍሳሽ ሕዝብ ፤ ወይም ሥራ — አጥነት ፤ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የተለያዩ መልኮች ይይዛል ። ሶስት ዓይነት መልኮች አሉ — ተንገዋላይ (Floating) ሽፍን (latent) ፤ ዕካች ( Stagnant ) የሚባሉ ። እያንዳንዳቸውን እንመልከታቸው (እናመዛዝን) ።

ተንገዋላይ ( ተንሳፋፊ ) ፍሳሽ ሕዝብ የሚውለው ቀደም ሲል በምርት ላይ ተሠማርተው የነበሩና አሁን የተወገዱ ብዙኃን ሠራተኞች ላይ ነው ፤ ስለሆነም በአጠቃላይ ሁልጊዜ የተወሰነ የሥራ — አጥ ቁጥር ይኖራል ። እነዚህ ሠራተኞች ወደ ምርት ተሰማርተው የነበር በምርት መስፋፋት ፤ በአዲስ ድርጅቶች መጀመር ሲሆን ተወርውረው የተጣሉት ምርት ሲደነዝዝ ፤ አዲስ ማሺኖች ሲተዋወቁ ፤ ድርጅቶች ሲዘጉ ወዘተ . . . . ነው ። ይህ ዓይነት ሥራ — አጥነት ይበልጥ በሰፊው የተስፋፋው በከተሞችና በኢንዱስትሪ አካባቢዎች ነው ።

ሽፍን ፍሳሺ ሕዝብ ወይም የእርሻ ፍሳሺ ሕዝብ የሚመለከተው በእርሻ ውስጥ የሚገኘውን ቀዋሚ ፍሳሽ ሠራተኛን ነው ። ይህ ፍሳሺ የሚከሰተው ምክንያቱም ትናንሽ ገበሬዎች ፤ ባላቸው ቁራጭ ማሳ ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ መሠቃየትና ሁልጊዜም ገዥ ቢአገኙ የጉልበት ኃይላቸውን ለመሸጥ በሚዘጋጁበት ጊዜ ነው ።

ያኔውንም ፤ በገበሬው መካከል የመለያየት ሂደት ይመጣል ፤ በድሃና በሀብታም መካከል ። ለገጠሬው ቡርዧ የርሻ ሥራ የሚአካሂድ የእርሻ ወዝ — አደር በብዛት ይመሠረታል ። ግን እጅግ ሰፋፊ መሬት በእጃቸው ያስገቡ ካፒታሊስት እርሻዎች በማሺን መጠቀምን ያአሳድጋሉ ፤ ስለሆነም ፤ በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማራው የሕዝብ ቁጥር እጅግ ይቀንሳል ። ርሀብን ለመከላከል ፤ የእርሻ ሠራተኞች ወደ ከተማ ና ኢንዱስትሪ አካባቢዎች ይሂዳሉ ፤ በዚያም የሥራ — አጡን ሠራዊት ያበዙታል ።

የዕካች ( Stagnant ) መልክ አንጻራዊ ፍሳሽ ሕዝብ የሚአመለከተው ቀዋሚ የሆነ ሥራ የሌላቸውን ብዙኃን ሠራተኞች (በቤት ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ሰዎችን ፤ ጊዜአዊ ሠራተኞችን ፤ ወዘተ . . .) ነው ፤ የእነዚህ ሠራተኞች የኑሮ ደረጃ ከአጠቃላዩ የሠራተኛ መደብ ኑሮ ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው ።

ከነዚህ መሠረታዊ መልኮች ሌላ ፤ከአንጻራዊ ፍሳሽ ሕዝብ ጋር የሚዳመሩ ይበልጥ ዝቅተኛ ክፍሎች አሉ ። እነኝህም ሴትኛ አዳሪዎች ፤ለማኞች ፤ ወንጀለኞች ወዘተ . . . ናቸው ።

ካፒታሊዝም ሲዳብር አንጻራዊ ፍሳሽ ሕዝብ ይጨምራል ። ሥራ—አጥነት በካፒታሊዝም ውስጥ ሊካድ የማይችል እውነት ነው ። ስለሆነም የቡርዧ ኤኮኖሚስቶች የሥራ—አጥነትን አመጣጥና ሕልውና የመግለጽ ተግባር ፊት ለፊት ይጋተራቸዋል ።

የማልተስ ስብዓዊ ጥላቻ ንድፈ ሃሳብ

ብዙኃኑ የቡርዧ ኤኮኖሚስቶች ሥራ አጥነትና ድህነትን የተፈጥሮ ዝንተ — ዓለም ሕጎች አድርገው ለመግለጽ ይሻሉ ። ከነኝህ ኤኮኖሚስቶች መካከል በ1798 ዓ. ም. አድሃሪ ንድፈ — ሀሳቡን እየገሠተተ የመጣው የእንግሊዙ የቤተክህነት መሪ ማልተስ ነው ።

ማልተስ «ያበረከተው» በኩረ — ጽሑፍ (Thesis) ከሰብዓዊ ሕብረተሰብ መጀመሪያ አንስቶ ሕዝቡ በጂኦሜትሪ አረማመድ እየጨመረ ( 1,2,4,8,16 ፤ ወዘተ . . . )እንደሚሄድ ፤የኑሮ መደጐሚያ ግን ፤የተፈጥሮ ምንጮች የተወሰኑ በመሆናቸው ፤በሂሣባዊ አረማመድ (1,2,3,4. ወዘተ ..) እንደሆነ ነው የሚገልጸው ። በማልተስ አስተያየት ፤ይህ ምጥነት (ድርሻ) እጅግ ሰፊ ሕዝብ በዓለም ውስጥ መትረፍረፉን ፤እናም ሥራ ወይም ምግብ እንደማያገኝ ያሳያል ። ይህ መደምደሚያ የተወሰደው ስህተት ከተሞላበት ስታትስቲካዊ ቅንብር ነው ።

የማልተስን ንድፈ ሀሳብ ገርደፍዳፋነት ፤የካፒታሊዝምን መርገሞች ሁሉ የመከላከያ ማጠየቂያ (ማረጋገጫ) ስላቀረበ ቡርዧዎች እጃቸውን ዘርግተው ተቀበሉት። ሥራ — አጥነት መጤን የሚኖርበት እጅግ በጥድፊያ በሚአድገው የሠራተኛ መደብ መባዛት ሲሆን ፤ ድህነት ደግሞ እጅግ በብዛት የሚመገቡ ሰዎች መፈጠርና የኑሮ መደጐሚያዎች እጥረት ነው ። እንደ ማለተስ አባባል ፤ወዝአደሩ ራሱን ከሥራ — አጥነት ፤ ከድህነትና ከርሃብ ነጻ ሊአወጣ የሚችለው የካፒታሊስትን ሥርዓት በማስወገድ ሳይሆን ፤ግን ከጋብቻ በመታገድና የወሊድ ቁጥጥርን በማካሄድ (መውለድን በማቆም) ነው ።በተጨማሪም፤ማልተስ እንደ ጥፋት፤ጦርነትና ወረርሽኝ ያሉትን ለሰው ልጅ ርግማን ከፈጣሪ የተሰጡ ናቸው ፤ስለሆነም እነዚህ ፍሳሽ ሕዝብን ያስወግዳሉ (ይገላሉ) ፤ የሰው ልጅን ዘር ከኑሮ የተሰጡ መደጐሚያዎች እኩል በመስመር ያመጣሉ ይላል ።

በየትም አገር ያሉ ተራማጅ ሰዎች ወዲያውኑ በማልተስ የንድፈ — ሀሳብ ትምህርት ላይ በትራቻውን አነሱ ። ለዚህ «ሰብዓዊ ጥላቻ» ንቁ ተቀዋሚ ከሆኑት መካከል ልናነሳቸው የሚገቡ የሩሲያ ዲሞክራቶች ቼርኒሼቪስኪ (1828 — 1889) እና ፒሳሬቭ (1840 — 1868) ናቸው ።

የማልተስ ስህተትማ አስተሳሰቦች ሙሉ በሙሉ የተጋለጡት በካፒታል (ወረት) ክምችት ንድፈ — ሀሳቡ ውስጥ በማርክስ ነው ። ሆኖም ማልተሳዊነት በካፒታሊስት ዓለም ውስጥ አሁንም ይሰበካል ፤እና በሰፊው በዩናይትድ ስቴትስ ተሠራጭቷል ። «ለመኖሪያ መንገድ (ዘዴ)» ተብሎ በታተመው የዊሊያም ቮግት መጽሐፍ ውስጥ— (በዩናይትድ ስቴትስ) መሬት ከ500 — 900 ሚሊዮን ሰዎች በላይ ልትረዳ እንደማትችልና ሌሎቹ ሰዎች በሙሉ ፍሳሽ ስለሆኑ መወገድ (መጥፋት) እንዳለባቸው ተነግሯል ። «ሰብዓዊ ልማት ፦ ዘመናዊው ጭንቀት (Human Fertility፦ The modern dilemma)» ተብሎ በርበርት ኩክ በተጻፈው መጽሐፍ ፤ የሕዝብ ብዛት የሚአመለክተው ለሚቀጥለው የሰው ልጅ ሕልውና አደገኛ ነገር መሆኑን ነው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ እርገጠኛ የሥራ — አጥነት ፤የድህነት እና የርሃብ ምክንያት በሳይንሳዊ መልክ የተገለጸው በማርክሲዝም — ሌኒኒዝም መሥራቾች ነው ። የካፒታሊስት ሥልተ — ምርት ነው ፤በወረት ክምችት ጥማት ምክንያት ፤ለሠራተኛው ሕዝብ ሥራ አጥነትና ርሃብ ማደግ መንገድ የጠረገ ። እነኝህን መርገሞች ለማስወገድ፤የካፒታሊዝም በአብዮት መጥፋት የሶሻሊስት አገሮች ማደግ የዚህ ማረጋገጫ ምሣሌዎች ናቸው ።



## 2 የካፒታሊስታዊ ክምችት አጠቃላይ ሕግ

የካፒታሊስታዊ ክምችት አጠቃላይ ሕግ ባሕሪ

የሠራተኛው መደብ የኑሮ ሁኔታ ማሽቆልቆልና የሥራ—አጥነት ማደግ ምክንያት በተፈጥሮ ሕጐች ጭቆና የመጡ አይደሉም ፤ግን በካፒታሊስት የምርት ሕግ የሚገለጹ እንጂ ። «የሕብረተሰብ ሀብት ሲአይል ፤ በሥራ ላይ ያለው ወረት ፤ የዕድገቱ ኃይልና ስፋቱም ያንኑ ያህል ይሆናል ፤ እናም የወዛደሩ ፍጹም ብዛትና የጉልበቱ አምራችነት ሲመጥቅ ያንኑ ያህል የእንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት ይጨምራል . . . . ግን በሥራ ላይ ካለው ሠራዊት ጋር ሲመጣጠን የዚህ ተጠባባቂ ሠራዊት ማየል ፤ችግሩ (ሥቃዩ) በሥራ ላይ ከዋለው ጉልበት ጋር የሚመጣጠን ባንድ ቦታ የተከማቸውን ፍሳሽ ሕዝብ ብዛት ነው የሚአሳየው ። ይበልጥ ሲስፉ በመጨረሻ ላይ ዝቅተኛው ክፍል ( Iazarus - Layers ) 1 የሠራተኛ መደብ እና የኢንዱስትሪው ተጠባባቂ ሠራዊት ይታይና እጅግ ( ይበልጥ ) ግልጽ የሆነ ዝርፊያ (ብዝበዛ) ይመጣል ። ይህ ነው የካፒታሊስት ክምችት ፍጹም ሁለንታዊ ሕግ የሚባለው »2 ሲል ማርክስ ጽፏል ።

የካፒታሊስታዊ ክምችት አጠቃላይ ሕግ የሚአመለክተው ባንድ በኩል የወረት ክምችት ፤ የሀብትን ማደግ እንደሚወስነው ነው ፤ማለትም ፤ በካፒታሊስቱ መደብ እጅና በሌላ በኩል በሠራተኛው መደብ መካከል ሥራ አጥነትና ሰላም ማጣት ። የካፒታሊስታዊ ክምችት አጠቃላይ ሕግ የካፒታሊዝም መሠረታዊ የምጣኔ — ሀብት ሕግ ጭቆና ተጨባጭ መግለጫ ነው ፦—ማለትም የትርፍ ዕሴት ሕግ ። የትርፍ ዕሴት አካሄድ (አሠራር) ነው የብልጽግናን ፤የድሎትን ፤የደም መጣጭነትን ፤የተትረፈረፈ ኑሮን በቡርዧዎች በኩል እንዲከማች የሚመራ ። በቡርዧዎች የሀብት ክምችት መብዛት ፤የሥራ—አጡ ሠራዊት እንዲአድግ ሲአደርግ የተቀጠሩት ሠራተኞች የመበዝበዝ ደረጃ መናርንና የኑሮ ሁኔታቸውን ይበልጥ መበላሸት ያመጣል ። ስለዚህ የወረት መከማቸትና የወዛደሩ ኑሮ ማሽቆልቆል የካፒታሊስት ሕብረተሰብ የማይነጣጠሉ ሁለት ክፍሎች (ገጾች) ናቸው ።

አንጻራዊና ፍጹማዊ የወዛ አደሮች የኑሮ ሁኔታ ማሽቆልቆል

የወዛደሩ አንጻራዊ የድሕነት ሂደት የሚመጣው ከካፒታሊዝም ዕድገት ጋር ነው ። ይህም ማለት የሕብረተሰብ ሀብት ሲጨምር በሕብረተሰቡ ውስጥ ከሚፈጠረው አዲስ ዕሴት ላይ ለሠራተኞች ያላቸው ድርሻ (ማለትም ከብሔራዊ ገቢው) ያነስ ሲሆን የካፒታሊስቶች ድርሻ ግን ይጨምራል ነው ።

የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ፤ ዩናይትድ ስቴትስ ፤ እንግሊዝ ፤ ፈረንሳይ ፤ እና ሌሎችም እያደገ የሚሄደውን የሠራተኛ መደብ አንጻራዊ ድህነት ግልጽ አድርገው በማሳየት ምሣሌዎች ናቸው ። በ1890 ዓ.ም. የአሜሪካ ሠራተኛ ሕዝቦች ከብሔራዊ ገቢው ላይ ያላቸው ድርሻ 56 ፐርሰንት ፤በ1923 — 54 ፐርሰንት ፤እና አሁን ደግሞ ከ40 ፐርሰንት ዝቅ ብሏል ። በእንግሊዝ የሠራተኛው ሕዝብ ብሔራዊ ገቢ በ1924 ወደ 45 ፐርሰንት ፤በ1954 ወደ 40 ፐርሰንት ወርዷል። በፈረንሳይም ከጦርነት በፊት የሠራተኛው ምንዳዕ ከብሔራዊ ገቢው 40 ፐርሰንት የነበረው በ1951 ዓ.ም. ወደ 29 ፐርሰንት አሽቆልቁሏል ። ከአስር ዓመታት በፊት የፈረንሳይ የኢንዱስትሪ ም

1. የሕብረተሰብ ዝቅተኛው ክፍል — ድህነት ያጠቃው ሥራ — አጥ ፤ ለማኝ ፤ በአለታዊ ሥራ የሚኖሩ ቤት የለሽ ሰዎች ወይም በማዕድ ትራፊ ፤ በቁራሽ እንጀራ የሚኖሩትን ነው ።

2. ኬ.ማርክስ ፤ ካፒታል ፤ ቅጽ 1. ገጽ 644.

ርት በ50 ፐርሰንት ሲጨምር የሠራተኞች እውነተኛ ምንዳዕ ግን በ14 ፐርሰንት ብቻ አድጓል ። እነኝህ ቁጥሮች የወዛደሩን አንጻራዊ ድህነት በቃላት ከመናገር ይበልጥ ግልጽ አድርገው ያሳያሉ ።

የሠራተኛው መደብ በብሔራዊ ገቢው ላይ ያለው ድርሻ ሲአሽቆለቁል ፤ የካፒታሊስቶች ግን በአፋጣኝ ይጨምራል ። ለምሣሌ በዩናይትድ ስቴትስ በ1923 ዓ.ም. የካፒታሊስቶች ድርሻ 26% ሲሆን ፤ ዛሬ ከ60% በላይ ነው ። በእንግሊዝ በ19 24 ዓ. ም. ከነበረው 55% በ1954 ወደ 60% አድጓል ።

የሠራተኛው መደብ አንጻራዊ ድህነት የሚንጸባረቀው ለሠራተኛው መደብ መዳጫ፤ ለካፒታሊስቶች ጥቅም በሆነው የምንዳዕ ከትርፍ ጋር ባለው የምጥነት (Ratio) ለውጥ ነው ።

የካፒታሊስት ክምችት አጠቃላይ ሕግ ለሠራተኛው መደብ ፍጹማዊ የቁሳዊ ሁኔታ ማሽቆልቆልና ለፍጹማዊ ድህነት ዝንባሌ መንገድ ይጠርጋል ።

በካፒታሊዝም የሠራተኛው ዕጣ የወደፊቱ የኑሮ ሁኔታ ምን እንደሚአመጣበት ሳያውቅ ያለ እምነት መኖር ነው ። የወረት ክምችት በማከታተል ሠራተኛውን የምንዳዕ ቅጥር እንዲሆን ያደርጋል ፤ በጉልበት ገበያ ውስጥ ይወረውረዋል ፤ የብዝበዛ ነባሪ (ዕቃ) ያደርገዋል ። በሌላ በኩል ፤ እጅግ ብዙ የሠራተኛ መደብን እጅግ በጣም ለከባድ ሥራና እስከፊ ወደሆነ ብዝበዛ እንዲገባ ያስገድደዋል ፤ በሌላው አንጻር ደግሞ ሰፊ ሥራ — አጥ ሠራዊትን ይፈጥራል ።

ፍጹማዊ ድህነት ማለት የሠራተኞች የኑሮና የሥራ ሁኔታ ማሽቆልቆል ነው ፤ ዕውነተኛ ምንዳዕ ይንዘቃዘቃል ፤ የኑሮ ደረጃ ይንራል ፤ በገጠርና በከተማ የሥራ — አጡ ሠራዊት ያብጣል ፤ የጉልበት መታፈግ ይጨምራል ፤ የቤት ሁኔታ ይበለሻሻል ፤ ወዘተ . . . . ። ከነዚህ ሁኔታዎች ጥቂቶቹን እንመርምር ።

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የኑሮ ሁኔታ እየናረ ነው ። ለምሣሌ ፤ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የኑሮ ሁኔታ ከ1947-49 ዓ ም 100 ቢሆን፤ በ1950 ደግሞ 103፤ በ1955 ወደ 115 ፤ እና በ1960 ወደ 126.4 ደርሷል ። ከዚህ የምንወስደው በዩናይትድ ስቴትስ የኑሮ ደረጃ በ1947 እና በ1961 ዓ.ም. በ26.4 ማደጉን ነው ።

በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በሄለር ኮሚቴ ዝርዝር አቀራረብ መሠረት አራት ሰው ያለው አንድ ቤተሰብ (ከእጅ ወዳፍ በመመገብ) የዓመት ባጀቱ በ1954 ዓ.ም. 5,335 (የአሜሪካ ዶላር) ደርሷል ። ግን በዚሁ ዓ.ም. ከጠቅላላው የአሜሪካን ቤተሰቦች 32% የዓመት ገቢአቸው 3,000 ዶላር ፤ እና 31% ደግሞ በ3,000 እና በ5,000 ዶላር መካከል ነበር ። ስለዚህ በ1954 በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ 63% ቤተሰቦች ከኑሮ መደጉሚያ (ከእጅ ወዳፍ) በታች የወረደ ገቢ ነበር ያላቸው ። በመስከረም 1958 ፤ «የሔለር በጀት» በዓመት ወደ 6,087 ዶላር ሲአድግ ፤ ከአጠቃላዩ የአሜሪካ ቤተሰቦች 45%ቱ ገቢአቸው ከ4,000 ዶላር ያነሰ ነበር ፤ ማለትም ከኑሮ መደጉሚያ አጋማሽ ጥቂት ከፍ ያለ ነው ።

በእንግሊዝ የ1938 ዓ.ም. የኑሮ ደረጃ 100 ሆኖ ሲወሰድ ፤ በ1950 ዓ.ም. 185 ፤ እና በ1955 በ246 ላይ ቆሟል ። ስለዚህ በእንግሊዝ የኑሮ ደረጃው ከፍታ በ1955 በ1938 የነበረውን ሁለት ተኩል ጊዜ መጥቋል ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የኑሮ ደረጃ እያደገ ነው የሄደው ። የ1956 ዓ.ም. የኑሮ ደረጃ ከፍታ ሲወሰድ 100 ቢሆን ፤ በ1958 ወደ 108 ፤ እና በ1960 — 110.7 ይደርሳል ። የመኖሪያው መንገድ ደረጃ ከፍ ማለት የሠራተኛው ሕዝብ የመግዛት ኃይሉ መቀነስ ነው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ የሠራተኛው መደብ ፍጹማዊ ድህነት አዝማሚያ ወሳኙ ዋናና ዓይነተኛ ምክንያት የሥራ — አጥነት ማደግ ነው ። ከአርባ ዓመት በፊት በካፒታሊስት አገሮች ሥራ — አጥነት ቀዋሚና አስቸጋሪ ሆኗል ። ከአጠቃላዩ ሥራ



— አጥ ሌላ ፤ ለአጭር ቀን ወይም ሳምንት የሚሠሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ግማሽ ሥራ — አጦችም አሉ ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በዩናይትድ ስቴትስ የዓመቱ ፍጹም ሥራ — አጥ ቁጥር 2 ወይም 3 ሚሊዮን ነበር ፤ ግን በ1962 ወደ 4 ሚሊዮን ተሸግሯል ። በዚያው በዓመት በተጨማሪም ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ግማሽ ቅጥረኞች (ለ15 ሳምንታት ከሥራ ውጭ የሚሆኑ) 14 ሚሊዮን ነበሩ ።

ሥራ — አጥነት ማለት ከሥራ ውጭ ለሆኑት መታረዝና መሰቃየት ብቻ አይደለም ፤ ባጠቃላይ የሠራተኛውን መደብ የኑሮ ሁኔታ ብልሽትሽቱን ያወጣዋል፤ ምክንያቱም ካፒታሊስቶቹ ተቀጥረው ከሚሠሩት ላይ ምንዳዕን ያወርዱታልና ።

የሠራተኛውን መደብ የኑሮ ደረጃ ሁኔታ ማሽቆልቆል የሚጠቁመው በካፒታሊስት ድርጅቶች ውስጥ ያልተቋረጠ የጉልበት መታፈግ እየተባባሰ መሄድ ነው ። እጅግ ከፍተኛ የጉልበት መታፈግ የትክክለኛ ጤንነት እጦትን ፤ በሰፊው ሠራተኛ ላይ የኢንዱስትሪ አደጋ እንዲደርስ ያደርጋል ። ለምሣሌ በዩናይትድ ስቴትስ ፤ በየሶስቱ ደቂቃ አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ ይሞታል ወይም ሽባ ይሆናል ፤ በየ11 ሴኮንድ ደግሞ አንድ ሠራተኛ አንድ ዓይነት መቁሰል ይደርስበታል ። በዩናይትድ ስቴትስ የሠራተኞች የስታትስቲክስ ቢሮ ዝርዝር መሠረት ፤ በ1950 እና በ1960 ዓ.ም.መካከል ወደ 22 ሚሊዮን አሜሪካውያን ሠራተኞች የኢንዱስትሪ አደጋ ምርኮኞች ሆነዋል ፤ ይህም ሁለት ሚሊዮን በዓመት መሆኑ ነው ።

የፍጹማዊ ድህነትን አዝማሚያን ጥያቄ ስንመረምር ፤ ኤምፔሪያሊዝም የድህነትና የከፍተኛ ሞት ውርስ የተወባቸውን በቅኝና በጥገኛ አገሮች ውስጥ ያሉ የሠራተኛ መደቦችን የኑሮ ሁኔታና በሁሉም የካፒታሊስት አገሮች ከመሠረታዊ ሰፊ ሕዝቦች መካከል የገበሬዎችንና የእጅ ሙያ ሠራተኞችን ጥፋትና ድህነት ማጤን ይኖርብናል።

እነኝህ ባጭሩ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያሉትን የሠራተኞች ሕዝቦች ፍጹማዊ ድህነት ከሚአመጡት ምክንያቶች ፤ ጥቂቶች ናቸው ።

ፍጹማዊ ድህነት ከዓመት ዓመት ከቀን ቀን እንደአፋጣኝ ፤ ሁለንታዊ የሠራተኞች የኑሮ ደረጃ ሁኔታ ማንዘቃዘቂያ ሆኖ መወሰድ አይገባውም ። የሠራተኞች የኑሮ ደረጃ በአንድ አገር ወይም በተለያዩ አገሮች ውስጥ በአንድነት የኑሮ ደረጃውን በጠቅላላ በዓለም ካፒታሊስት ምጣኔ — ሀብት ላይ ዝቅ በማድረግ ከፍ ሊል ይችላል ። በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሠራተኞችን የኑሮ ደረጃ በመገምገም ላይ በማንኛውም ጊዜ የሠራተኛው መደብ ቁሳዊ መደጉሚያ ደረጃ የሚወሰነው በቡርዧውና በወዛደሩ መካከል ባለው የመደብ ኃይል ግንኙነት መሆኑ መታወስ ይኖርበታል። በካፒታሊዝም የታሪክ ሂደት ሁሉ ሠራተኞች የኑሮ ሁኔታቸውን ለማሻሻል መራራ ጦርነት ሲአካሂዱ ነበር ። ይህም ትግል ነው የሠራተኛውን መደብ የኑሮ ሁኔታ ማሽቆልቆል የሚቃወም ።

በካፒታሊስት ዓለም ውስጥ ከዓመት ዓመት የትግሉ እንቅስቃሴ ይስፋፋል ። በዓላማው በተለይ ሰፍቶ የታየው በዩናይትድ ስቴትስ ከጦርነት በፊት ባለፈው አስር ዓመት (1931 — 40) እና ከጦርነት በኋላ (ከ1945—55) ማወዳደር ሲወሰድ ያድማው ቁጥር ከ22,021 — 43,159 ሲሆን በነዚህ አድማዎች ውስጥ የተሳተፉት ሠራተኞች ቁጥር ከ9.5 ሚሊዮን ወደ 26.5 ሚሊዮን አድጓል ፤ በዚሁ የጠፋው የሥራ ቀንም ከሠራተኛው አንጻር ሲታይ ከ145 ሚሊዮን ወደ 434 ሚ. ጨምሯል ። በ1960 ዓ.ም. በዩናይትድ ስቴትስ 3,250 አድማዎች ሲካሄዱ በዚህ የተሳተፉት ሠራተኞች 1.5 ሚ. ነበሩ ። አድማዎቹ ይበልጥ የተራዘሙና መራራ እየሆኑ ነው የሄዱት ።

በመላው የካፒታሊስት ዓለም በ1960 እና በ1962 መካከል በአድማው ውስጥ የተሳተፉት ሠራተኞች እና ሌሎች ተቀጣሪዎች ቁጥር ከ54 . ሚ. ወደ 70 ሚ. አድጓል ። በሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ክንዋኔም ውስጥ ፈጣን ዕድገት ነበር — በ1958 በግምት 45% ከጠቅላላው አድማ በፖለቲካዊ ክንዋኔ ውስጥ ሲሳተፍ ፤ በ1960 ደግሞ 3/4 ያህሉ ገብቶበታል ።

የቡርዧዋና የቀኝ—ክንፍ ሶሻሊስት ምጣኔ — ሀብታውያን የተቻላቸውን ያህል የካፒታሊዝምን ገጽ ለማሳመር ሲጥሩ በአንጻሩ የማርክሲስት — ሌኒንስትን የሠራተኞችን የአንጻራዊና ፍጹማዊ የኑሮ ደረጃ ማሽቆልቆል ምክንያት የሚገልጸውን ትምሀርት አፈር ሊአለብሱት ጥረዋል ።

በቅርብ ጊዜ ከአቀጠቀጡት እጅግ ውሸትማ ንድፈ — ሀሳቦች አንዱ "የሕዝቦች ካፒታሊዝም» ነው ። ይህ ሠራተኛ ሕዝቦችን ለማታለል የወጣ የኢምፔሪያሊዝም ግልጽ ንድፈ — ሀሳብ ነው ። ለምሣሌ በዩናይትድ ስቴትስ የዚህን ንድፈ — ሀሳብ ፕሮፖጋንዳ የሚአሠራጭ የመንግሥት ልዩ የዜና ወኪል ተቋቁሟል።እናም ከኀላፊዎቹ አንዱ «የሕዝቦች ካፒታሊዝም» በዛሬው የአሜሪካ ካፒታሊዝምና ከ100 ዓመታት በፊት ማርክስ ካጻፈለት በአውሮጳ ከነበረው ካፒታሊዝም ጋር ያለውን ልዩነት የሚአሳይ በጣም ዓይነተኛ እንደሆነ አስታውቋል ።

የዚህ ንድፈ — ሀሳብ ጠበቆች በካፒታሊዝም ውስጥ የሠራተኞች ምንዳዕ በአፋጣኝ እንደሚጨምርና በሠራተኞችና በካፒታሊስቶች መካከል ያለው ልዩነት በአስቸኳይ እንደሚጠፉ አስታውቀዋል ። ሠራተኞች በደመወዛቸው መኪና ፤ ቤት ፤ አክሲዮን ፤ ይገዛሉ ፤ በቁጠባ ባንኮች ገንዘብ ያስቀምጣሉ ፤ በብዙ ድርጅቶች ውስጥ ሠራተኞች ትርፍ ይካፈላሉ ። «የሕዝቦች ካፒታሊዝም» ይህን የካፒታሊዝም ተሟጋችነት ያውጃል፤በሀብታምና በድሀ የኑሮ ሥልት መካከል የልዩነት ማጥበቢያ ምክንያት የሆነውን «የገቢ ላይ አብዮትን» የቁሳዊ ሀብትም በሕብረተሰቡ እኩል የሚከፋፈል መሆኑን ይሰብካል።በመጨረሻም የመደብ ተጻራሪነት ለዕኩልነት መንገድ እየጠረገ ነው፤የማርክሲስት—ሌኒኒስት የመደብ ትግል ንድፈ—ሀሳብ ግን ፍጹም አስፈላጊ አይሆንም ፤ምክንያቱም እያንዳንዱ ሠራተኛ ባለኢንዱስትሪና ቆጣቢ በመሆን ካፒታሊስት ሊሆን ታውጆለታል ፤ ተነግሮታልና ይላል ። እንዲህም የለ ! (ከተርጓሚው)

ስለ «ሕዝቦች ካፒታሊዝም» ንድፈ — ሀሳብ ሀሳዊነት (Falsity) ሊወገዱ የማይችሉ ማረጋገጫ ዕውነቶች አሉ ፤ እናም የዚህ ዋናው ማረጋገጫ የሠራተኛው ሕዝብ ያደግ ትግሎች ማደግ ነው ። «የመደብ ሰላም» ፤ «የመደብ ኪዳን» ጠበቆች ሠራተኛው መደብ ለመሠረታዊ ፍላጐቶቹ፣የሚአካሂደውን ትግል ለመቅጨት፤ የተደራጀውን የሠራተኛ መደብ እንቅስቃሴ ለመከፋፈል ፤የካፒታሊስትን ሥርዓት ያለአብዮታዊ ትግል ጠርጐ ይጣላል በሚል በማይጨበጥ ትምህርት የሕዝቡን አእምሮ ለመሙላትና ሠራተኛውን ትጥቁን ለማስፈታት ፤ ሊረጋገጥ የማይችለውን ሊአረጋግጡ ይፈልጋሉ ።

የካፒታሊስታዊ ክምችት ታሪካዊ አዝማሚያ

ማርክስ ፤ ከወረት ክምችት ጥልቅ ትንተናው በኋላ ፤ የካፒታሊስታዊ ክምችትን ታሪካዊ አዝማሚያ አሳይቷል ።

የካፒታሊስት ንብረት መምጣት የመጀመሪያ መነሻ ነጥብ የትናንሽ ሸቀጥ አምራቾች የግል ንብረት ነው ። በመልከኛነት ዘመን አነስተኛ የሸቀጥ ደረጃ መበታተን ጀመረ እና ለካፒታሊስት ሕልውና ምክንያት ሆነ ። ግን ይህ የመበታተን ሂደት እጅግ ዘገምተኛ ነበር ፤ የተጠናከረው (የተፋጠነው) በጥንታዊ የወረት ክምችት ዘመን የትናንሽ ሸቀጥ አምራቾች በኃይል መነጠቅ ነው ። የዚህ ንጥቂያ (የንብረት ማዛወር) ውጤት የካፒታሊስት ንብረት እንዲሰፍን አደረገ ።

የቡርዧዋዎች የምርት ግንኙነት ፤ በምርት መገልገያዎች የትላልቅ ንብረት ባለቤትነት ላይ የተመሠረተው ፤ የምርት ኃይሎችን ዕድገት አፋጠነ — ቴክኒካዊ መሻሻል ነበር ፤በመቶና በሺ የሚቆጠሩ ሠራተኞች ጉልበት ባንድነት መጣና የሕብረተሰባዊ ባሕሪ ያዘ ።



ይህ ሕብረተሰባዊ የአመራረት ጸባይ በካፒታሊዝም የምጣኔ — ሀብት ሕግ ውስጣዊ አሠራር ምክንያት አሁንም እየተባባሰ ሄዶ ነበር ። የካፒታሊዝም መሠረታዊ የምጣኔ — ሀብት ሕግ — የትርፍ ዕሴት ሕግ — የተጠናከረ የወረት መከማቸትን የሚአስከትል የሠራተኞች የመበዝበዝ ንረት መንገድ ሰጠ ። በካፒታሊስታዊ የክምችት ሂደት ውስጥ የወረት አካላዊ ይዘት ያድጋል ፤ውጤቱም እጅግ ሰፊ ምርት ይሆናል ።

ይህ የምርት ሕብረተሰባዊነት ሂደት ከካፒታሊስት የባለጸጎች ቁጥር የማያቋርጥ ትነሳ ጋር ጐን ለጐን ይሄዳል ፤ ቢቀንሱም እጅግ ሰፊ የሕብረተሰብ ሀብት ይቆጣጠራሉ ፤ እናም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሠራተኞችን የተጠራቀመ የጉልበት ፍሬ ይዘርፋሉ ።

ካፒታሊዝም ሲዳብር የምርት ሂደቱ ሕብረተሰባዊ ጸባይ ከካፒታሊስቱ የግላዊ ንብረት መልክ ጋር ግጭቱ እየጨመረ ይሄዳል ። የግል ባለቤትነትም ለምርት ኃይሎች ዕድገት ደንቃራ (እንቅፋት) ይሆናል ።

በወረት (በካፒታል) የጉልበት ሕብረተሰባዊ መሆን የካፒታሊዝምን ማክተም ቅድመ — ሁኔታዎች ያዘጋጃል ። እንደገናም የካፒታሊዝም የውስጣዊ ሕግ አሰራር ፤ በተጨማሪ ለካፒታሊዝም መደምሰስ ስሜታዊ (አማናዊ) ቅድመ — ሁኔታዎችን ይፈጥራል ። ከምርት ደረጃ መጨመርና ከወረት ማደግ ጋር የሠራተኛው መደብ በቁጥር ሳያቋርጥ ያድጋል ፤ እናም በካፒታሊስት የምርት አሠራር ምክንያት ፤ ይተባበራል ፤ ይደራጃል ፤ ስለሆነም ራሱን ለአዲሱ የሾሳሊስት ሕብረተሰብ የምርት አያያዝ ያዘጋጃል ። በካፒታሊስታዊ ክምችት ሂደት ወቅት ፤ ሥራ—አጥነት ያድጋል ፤ የሠራተኛው የኑሮ ደረጃ ሁኔታ ያሽቆለቁላል ፤ በመሆኑም ትግሉ ያድጋል ። ሠራተኛው መደብ ርሃብን ፤ ድህነትን እና ብዝበዛን ለማስወገድና መብቱን ለማስጠበቅ ካፒታሊዝምን ጠርጐ ለመጣል መንገዱ አብዮት ብቻ እንደሆነ ከጊዜ ወደጊዜ እየተገነዘበው ነው ።

ስለሆነም ፤ ካፒታሊዝም ራሱ ለራሱ መጥፋት ነባራዊና ስሜታዊ (አማናዊ) ቅድመ — ሁኔታዎችን ያዘጋጃል ። ይህ ነው የካፒታሊስታዊ ክምችት ታሪካዊ አዝማሚያ ዋና ነጥብ — የካፒታሊስት የግል ንብረት መነጠቅ - ለካፒታሊዝም መውደቅና ለሶሻሊዝም ድል ማድረግ አስፈላጊ ሁኔታዎች ሁሉ ዝግጅት ።

የማይቀረው የካፒታሊዝም መውደቅ የሚረጋገጠው በጠቅላላው የታሪካዊ ዕድገት ሂደት ነው ። ስለሆነም በ1917 የሩሲያ ሠራተኛ መደብ ፤ከድሀ ገበሬዎች ጋር በቅርብ በመተባበር ፤ በሌኒን በተመራው የኮሚኒስት ፓርቲ መሪነት የጥቅምቱን አብዮት አካሄደ ።

በአብዮቱ በመጣው የመሸጋገር ወቅት ፤ የሶቪየት ሕብረት የሠራተኛው መደብ ቡርዧዎችን ሥልጣን ነጠቀ ፤ የምርት መገልገያዎችን የግል ባለቤትነት አስወገደ ፤ በምትኩም የምርት መገልገያዎችን የሕዝብ ንብረትነት መሠረተ ። ከዚህ መመሥረት ጋር በሕብረተሰቡ አባላት መካከል አዲስ የምርት ግንኙነቶች መጥተዋል ፤ በሴቶችና ወንዶች መካከል የሕብረት ድርጅቶችና የዕርዳ ተራዳ ሥራ ግንኙነቶች ከብዝበዛ ነጻ አውጥተዋል ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሌላ የብዙ አገር ሕዝቦች የሥር — ነቀል ምጣኔ— ሀብታዊ ሽግግሮችን መንገድ ተከተሉ ፤ እናም አሁን በትክክል ሶሻሊዝምን እየገነቡ ናቸው ።

ምዕራፍ ፭

# የትርፍ ዕሴት ወደ ትርፍ አለዋወጥና በተለያዩ የበዝባዥ ቡድኖች መካከል መሠራጨት (መከፋፈል)

## 1. የወረት (ካፒታል) ልዩ መልኮች

ያለፉት ምዕራፎች የሚመለከቱት በወዛደሩና በኢንዱስትሪው ቡርዧዊ መካከል ያለውን ግንኙነት ነው ። ሌሎች በዝባዥ ቡድኖች መኖራቸውን ወደጐን አድርገነው ነበር — የንግድ ቡርዧዎችን ፤ ባንከኞችን ፤ የእርሻ ቡርዧዎችንና ትላልቅ የመሬት ከበርቴዎችን ማለት ነው ። ሁሉም ሠራተኛውን መደብ ለመበዝበዝ አንድ ላይ ይተባበራሉ እናም በሠራተኛው መደብ የሚመረተውን ትርፍ ዕሴት ይከፋፈላሉ። የቡርዧዎች በተለያዩ ቡድኖች መከፋፈል መታሰብ ያለበት ባለው የካፒታሊስት ምርት ሁኔታ ነው ።

የወረት ሁኔታዊ እንቅስቃሴ

ወረት በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ላይ ነው ። የወረትን እንቅስቃሴ ማቆም ወይም ማዘግየት ማለት ለካፒታሊስቱ ዕድገት መንስኤ የሆነውን ትርፍ ዕሴት ሙሉ በሙሉ ማጣት ወይም መቀነስ ይሆናል ።

ወረት በሚንቀሳቀስበት ወቅት የተለያዩ ደረጃዎችን አልፎ ልዩ መልክ ይይዛል ። በመጀመሪያ ደረጃው ወረት በገንዘብ መልክ በመዟዟር አድማስ ውስጥ ይሠራል ። ካፒታሊስቱ በገንዘቡ የምርት መገልገያዎችና የጉልበት ኃይል ለካፒታሊስት ምርት ሂደት ዝግጅት ይገዛል ። በዚህ ደረጃ የወረት እንቅስቃሴ በሚከተለው ቀመር ይታያል —

ጉ.ኃ
ገ — ሸ
ም. መ

(ገ — ገንዘብ ፤ ሸ — ሸቀጥ ፤ ጉ.ኃ — የጉልበት ኃይል ፤ ም.መ — የምርት መገልገያ) ስለሆነም ወረት በመጀመሪያ ደረጃው ከገንዘባዊ መልክነቱ ወደ አምራች ወረትነት መልኩ አለፈ ።

በሁለተኛው ደረጃ ወረት በምርት አድማስ (ም) መሥራት ጀመረ ። እዚህ ቅጥር ጉልበት ከምርት መገልገያዎች ጋር ተወሃደ ። በዚህ ደረጃ የሠራተኞች ጉልበት አዲስ ዕሴት በመያዝና ትርፍ ዕሴትን በመጨመር አዲስ ሸቀጦችን ይፈጥራል።በዚህደረጃው የወረት እንቅስቃሴ ይኸውና —

ጉ.ኃ
ሸ ........ም.......... ሸ1
ም. መ

ስለዚህ ወረት በዚህ ሁለተኛ ደረጃው ከአምራችነት መልኩ ወደ ሸቀጥ ወረትነት መልኩ ይለወጣል ።

በሶስተኛው ደረጃው ወረት እንደገና በመዟዟር አድማስ ውስጥ ይሠራል። የሸቀጥ ወረት ወደ ገንዘብ ወረት ይለወጣል ። በዚህ ደረጃ የወረት እንቅስቃሴ እንደሚከተለው ሊታይ ይችላል —



ስለሆነም ወረት እንቅስቃሴውን በገንዘብ መልክ ጀመረና እንደገና ወደ ገንዘባዊ መልክ ተለወጠ ፤ ግን ካፒታሊስቱ በመዘዋወር ላይ ካስገባው ወረት የበለጠ ገንዘብ ያገኛል ።

ባጭሩ የወረትን ጠቅላላ እንቅስቃሴ እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል ፡—

ጉ. ኃ
ገ — ሸ ......ም.....ሸ1 — ገ1
ም. መ

ይህ የወረት እንቅስቃሴ ፤ ማለትም ፤ ከአንደኛው ወደ ሌላኛው መልክ ግቡን የመታ መለወጡና በሶስት ደረጃዎች የማለፉ ሁኔታ የወረት መሽከርከር ይባላል ።

የወረት መሽከርከር በሁለት ደረጃ ዑደትና በአንድ የምርት ደረጃ ይከፈላል ። ከዚህም የካፒታሊስት ምርት የዑደትና የምርት ሂደት ጥምር መሆኑ ይታያል ። ምንም እንኳ እነዚህ ሁለቱ አንድነት ቢፈጥሩም ፤ ትርፍ ዕሴት የሚመረተው በእርሱ ሂደት ነውና ምርት ወሳኝ ነው ።

የወረት የተለያዩ መልኮች አመሠራረትና የካፒታሊስት ቡድኖች

ሶስት ዓይነት የወረት መልኮች ከኢንዱስትሪ ወረት ሶስት የመሽከርከር ደረጃዎች ጋር ይስማማሉ፡- የገንዘብ ወረት ፤ አምራች ወረት ፤ እና የሸቀጥ ወረት ከሌ የሚባሉት ። ካፒታሊዝም ሲዳብር እያንዳንዱ የወረት መልክ (ገጽ) በግልጽ ሎቹ ይለያያል ። የንግድና የብድር ወረት በምርት ውስጥ ከሚሠራው ወረት ነጻ ይሆኑና ባንድነት በንግድና በዱቤ የአሠራር አድማስ ውስጥ ብቻ መሥራት ይጀምራሉ።ይህ የወረት የተገነጠለ (የተገለለ) ገጹ ከተለያዩ የቡርዧዋ ቡድኖች ጋር ይስማማል — ከኢንዱስትሪያሊስቶች ፤ ነጋዴዎችና ከባንከኞች ጋር ።

የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች አሠራር ትርፍ ዕሴትን በማምረት ጊዜ የሠራተኛውን መደብ ትርፍ ጉልበት በመንጠቅ የተሞላ ነው ። የነጋዴዎች አሠራር የሸቀጥ ወረትን ወደ ገንዘብ ወረት በማዛወር ሲሆን፤የአበዳሪ ካፒታሊስቶች ተግባር ደግሞ በገንዘባዊ መልክ ያለውን ወረት ማድለብና ማስቀመጥ ይሆናል ። እያንዳንዱ የካፒታሊስት ቡድን በሠራተኛው መደብ የተፈጠረውን የትርፍ ዕሴት ድርሻውን ይቀበላል ። 1

ከካፒታሊስት ቡድኖች ሌላ ፤ አሁንም ከበዝባዥ መደቦች በኩል ያሉ አሉ ፡— የመሬት ከበርቴዎች የሚባሉ ፤ እነኝህ ከምርት መገልገያዎች ውስጥ በጣም ዓይነተኛ የሆነውን ስለያዙ—መሬትን—በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ልዩ ቦታ አላቸው፤ እነሱም ከትርፍ ዕሴቱ አጠቃላይ ድምር ድርሻቸውን ያገኛሉ ።

የሕብረተሰብ ወረት ነጠላ ክፍሎች ነጻ በሆነ የወረት አሠራር መለያየት (መከፋፈል)-የኢንዱስትሪ ፤ የንግድ ፤ እና የብድር ወረት — እና የትላልቅ የመሬት ከበርቴዎች መኖር ትርፍ ዕሴትን ለመዝረፍ ጠንካራ የሆነ ውድድር በበዝባዦች መካከል እንዲመጣ ምክንያት ነው ። በእያንዳንዱ ካፒታሊስት የሚዘረፈው ትርፍ ዕሴት የትርፍ መልክን ይይዛል ። የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች የኢንዱስትሪ ትርፍ ፤ ነጋዴዎች ፤ — የንግድ ትርፍ ፤ እና ባንከኞች — የብድር ወለድ (አራጣ) ያገኛሉ ። ትላልቅ የመሬት ከበርቴዎች ደግሞ የመሬት ኪራይ ይወስዳሉ ።

1 እላይ ከተዘረዘሩት ቡድኖች ሌላ ፤ በእርሻ ላይ የተሠማሩ ካፒታሊስቶችም አሉ ። ይሁንና እነዚህን በቡድን ማስቀመጡ በመሠረቱ ከኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች ስለማይለዩ አስፈላጊ አይደለም ።

## 2 አማካይ ትርፍና የምርት ተመን

ዋጋ (Cost Price) እና ትርፍ (Profit) የትርፍ ደረጃ መጠን (rate of Profit)

በካፒታሊስቶች ድርጅት ውስጥ የተመረተው ሸቀጥ ዕሴት በሶስት ክፍሎች ይከፈላል ፡— 1)ቀ— የቀዋሚ ወረት ዕሴት (የማሽኑና ማሙያዎች ከፊል ዕሴት ፤የጥሬ ዕቃ ፤ ነዳጅ ፤ ወዘተ .... ዕሴት (2) ተ — የተለዋዋጭ ወረት ዕሴት ፤እና 3) ትዕ — ትርፍ ዕሴት ።

ከነዚህ ሶስት ክፍሎች ካፒታሊስቱ የከፈለው ለመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ብቻ ነው ፤ እነዚህ ዋጋውን ያስገኙለታል ። ስለዚህ ፤የካፒታሊስት ዋጋ በቀዋሚና በተለዋዋጭ ወረት ላይ የጠፋውን ድምር ይይዛል (ቀ + ተ) ።

አንድ ካፒታሊስት በፋብሪካው ውስጥ የተመረተን ሸቀጥ በሚሸጥበት ጊዜ ትርፍ ዕሴት ከካፒታሊስቱ ዋጋ በላይ ንሮ ይታያል ። ካፒታሊስቱ የድርጅቱን አትራፊነት ለመወሰን የጠፋውን ወይም በሥራ ላይ የዋለውን ወረት ይህን ትርፍ በአንጻሩ ያመጣዋል ፤ማለትም ፤ከመሸጫ ዋጋው አንጻር ። ከጠቅላላው ወረት አንጻር የሚታይ ትርፍ ዕሴት የትርፍ መልክን ይይዛል ። ትርፍ በምርት ላይ በወጣው ጠቅላላ ወረት አንጻር የሚወሰድ (የሚታይ) ትርፍ ዕሴት ነው ፤እናም በዚያ ወረት እንደተመረተ ሆኖ ይቀርባል ። በእውነተኛው መንገድ «ትርፍ» ማለት ትርፍ ዕሴት ነው ፤ የሚመረተው በወረት ተለዋዋጭ ክፍል ብቻ ነው ። ስለዚህ ነው ማርክስ ትርፍን የትርፍ ዕሴት የተለወጠ መልኩ ነው ያለው ።

የካፒታሊስት ድርጅት የአትራፊነት ደረጃው የሚለካው በትርፉ መጠን ነው ። የትርፍ መጠን የትርፍ ዕሴቱ በሥራ ላይ ከዋለው ጠቅላላ ወረት አንጻር በፐርሰንት የሚገለጸው ምጥነት ነው ። ለምሳሌ ፤በሥራ ላይ የዋለው ወረት (ቀ+ተ) 200,000 ብር ቢሆን (160,0000ቀ + 40.000ተ) ፤ትርፍ ዕሴቱ (ትዕ) ደግሞ በዓመት 40,000 ብር ከሆን ፤የትርፉ መጠን (ደረጃ) የሚሆነው ቀጥሎ ያለው ነው —

$$\text{ም} = \frac{\text{ትዕ}}{\text{ቀ} + \text{ተ}} \times 100\% \qquad \frac{40,000}{200,000} \times 100\% = 20\%$$

በትርፍ መጠን (ደረጃ) እና በትርፍ ዕሴት ደረጃ መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ መሆን አለበት ። በማንኛውም ድርጅት የትርፉ መጠን ሁልጊዜም ከትርፍ ዕሴቱ መጠን ያነሰ ነው ። በዚህ ሁኔታ የትርፍ ዕሴቱ መጠን እንደሚከተለው ይሆናል ፡—

$$\text{ትዕ} = \frac{\text{ትዕ}}{\text{ተ}} \times 100\% = \frac{40,000}{40,000} \times 100\% = 100\%$$

የትርፍ መጠን ከካፒታሊስቱ ምርት በስተጀርባ መገፋፊያ ኃይል ነው ። በካፒታሊዝም ውስጥ የትርፍ መጠን ሚና የተጠቃለለው በእንግሊዛዊው የሠራተኛ ማኅበር መሪና ጋዜጠኛ በቲ.ጄ. ዱኒንግ ሆኖ እንደሚከተለው ነው ፡— «የ10% እርግጠኝነት በየትም ቦታ ቀጣሪነትን ያረጋግጣል ፤ 20% እርግጠኝነት ጉጉትን ይፈጥራል ፤ 50% ሙሉ ድፍረትን ፤100% ሰብዓዊ የመብት ሕጎችን ለመረምረም ያዘጋጃል ።300% የማያ ካሂደው ምንም ዓይነት ወንጀል ወይም የማይገባበት ምንም ዓይነት አደጋ ፤ባለቤቱ እስከሚሰቀል ድረስ እንኳ ቢሆን ፤ የለም ።» 1

1. ካ ማርክስ፥ ካፒታል ቅጽ 1 ገጽ 760



ይህ መግለጫ ሙሉ በሙሉ የተገኘው በዛሬው ዘመን የካፒታሊስት ድርጊት ነው ። የአሜሪካ ባለብዙ ሚሊዮን ጌቶች ሀብትና ኃይል —ሞርጋን ፤ ሮኪፌለር ፤ ዱፓንት ፤ ወዘተ . . . . የመጡትና የተጠገኑት የሁሉንም የሰብአዊ መብት ሕጎች በመርገጥ በመረምረም ነው ።

አማካይ የትርፍ ደረጃና የምርት ተመን አመሠራረት

የካፒታሊስት ምጣኔ — ሀብት ሁሉንም ዓይነት ሸቀጦችን የሚአመርቱ ብዙ የተለያዩ ድርጅቶችን የያዘ ነው ። አንድ ዓይነት ምርትን የሚሠሩ ድርጅቶች ሁሉም በአንድ ዓይነት ሁኔታ አይሰሩም ። በግዝፈት ፤በቴክኒካዊ መሣሪያዎች ደረጃ እና በምርት አቀነጃጀት ይለያያሉ ። ስለሆነም ፤ በተለያየ ድርጅት የሚመረተው ሸቀጥ ግላዊ ዕሴት አንድ አይደለም ። ግን በአንድ የኢንዱስትሪ ክፍል ያለ ውድድር የሸቀጦችን ተመን የሚወስነው በምርታቸው ላይ ባወጡት ልዩ ጉልበት ወይም በልዩ ዕሴታቸው ሳይሆን ፤ የነዚህ ሸቀጦች የገበያ (የሕብረተሰብ) ዕሴት ነው ።

የሸቀጦች ተመን የሚወሰነው በገበያ ዕሴታቸው እስከሆነ ድረስ ከፍተኛ ደረጃ ቴክኖሎጂና የጉልበት አምራችነት ያላቸው ድርጅቶች በአመቺ ሁኔታ ላይ ይሆናሉ። ተጨማሪ ወይም ትርፍርፍ ትርፍ ይወስዳሉ ። ግን በነጻ ውድድር መሠረትይህ ሁኔታ ብዙ ሊቆይ አይችልም ። ከፍተኛ ትርፍ ሁሉንም ይማርካል ። ካፒታሊስት የድርጅት ባለቤቶች ፤ የቴክኒክ ደረጃው ከፍተኛ ባልሆነበት ከፍ ለማድረግ ይሞክራሉ ፤ ቴክኒካዊ መሻሻሎችን ያስተዋውቃሉ ፤ አምራችነትን ከፍ ያደርጋሉ ፤ እናም የሠራተኞችን ጉልበት ያፍጋሉ ። ስለዚህ በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የተመረቱት ሸቀጦች ዕሴት የሚመዘነው በመሪ ድርጅቶች ነው ፤እናም ይህ ዕሴት ነው የገበያ (የሕብረተሰብ) ዕሴት የሚሆነው ። በመሆኑም ፤በፊት ትርፍርፍ ምርት ይወስዱ የነበሩ ከእንግዲህ አያገኙትም ። ግን እነዚህ ድርጅቶች ትርፍርፍ ምርት እንዲአገኙ እንደገና አዲስ ቴክኒካዊ መሻሻሎች ይፈጠራሉ ።

ባንድ ቅርንጫፍ ውስጥ ውድድር እንዳለ ሁሉ ፤ በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ዘንድ በቅርንጫፎች መካከልም ውድድር የተለመደ ነው ፤ማለትም ፤በተለያዩ ቅርንጫፎች ወረታቸውን ባዋሉ ካፒታሊስቶች መካከል እንደማለት ነው ። ይህ ዓይነት ውድድር በተለያዩ የኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች ውስጥ የትርፍ መጠን (ደረጃ) እኩል እንዲሆን ያደርጋል ፤ ወይም ፤ እኩል የሆኑ ወረቶች (ካፒታሎች) እኩል የትርፍ መጠን ያገኛሉ ።

በካፒታሊስቶች መካከል የትርፍ ደረጃ አኳያነት እንዴት እንደሚመጣ እንመልከት ። በሕብረተሰቡ ውስጥ ሶስት የኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች አሉ ብለን እንውሰድ፡— የቆዳ ሥራ ፤ ጨርቃ ጨርቅ እና ኢንጅነሪንግ ። ሁሉም እኩል የወረት መጠን አሰማርተዋል ፤ የወረቱ አካላዊ ይዘት ከመለያየቱ በቀር ። በእነኝህ ድርጅቶች በእያንዳንዳቸው 100 ሚ. ብር በሥራ ላይ ውሏል እንበል ። የቆዳ ሥራው ወረት የ70 ሚ. ቀዋሚ ወረትና የ30 ሚ. ተለዋዋጭ ወረት ሲኖረው ፤ የጨርቃ ጨርቁ ደግሞ 80 ሚ. ቀዋሚ ወረትና የ20 ሚ. ተለዋዋጭ ወረት አለው ፤የኢንጅነሪንግ ግን የ90 ሚ. ቀዋሚ ወረትና የ10 ሚ. ተለዋዋጭ ወረት ይዟል ። በሁሉም ቅርንጫፎች ውስጥ የትርፍ መጠን (ደረጃ) እኩል ይሁን — 100 ፐርሰንት ። ስለዚህ ፤በቆዳ ሥራ ኢንዱስትሪው ውስጥ 30 ሚ. ብር ትርፍ ዕሴት ይመረታል ፤ በጨርቃ ጨርቅ — 20 ፤ እና በኢንጅነሪንግ — 10 ይገኛል ። በመጀመሪያው ኢንዱስትሪ የሸቀጦች ዕሴት 130 ፤ በሁለተኛው — 120 ፤ እና በሶስተኛው 110 ይሆንና በሶስቱም ጠቅላላ — 360 ይመጣል ።

ሸቀጦች በዕሴታቸው ከተሸጡ ፤በቆዳ ሥራ ኢንዱስትሪው ውስጥ የትርፍ ደረጃ መጠን 30% ለጨርቃ ጨርቅ 20% ፤ እና በኢንጅነሪንግ ደግሞ 10% ሆነ ማለት ነው ። ይህ የትርፍ አሠረጫጨት ይበልጥ ጠቃሚ የሆነው ገንዘባቸውን በቆዳ ኢንዱ

ስትሪው ላይ ላዋሉት ካፒታሊስቶች ይሆናል ፤ በኢንጂነሪንግ ውስጥ ላዋሉት ግን አይደለም ። የትርፍ አመጣጡ (አሠራሩ) ሁኔታ የኋለኛው ገንዘቡን ወደቆዳ ሥራ ኢንዱስትሪ እንዲያዞር ያደርገዋል ። ወደቆዳ ሥራ ኢንዱስትሪ የተጨማሪ ገንዘብ መፍሰስ ምክንያት ፤ ይህ ኢንዱስትሪ ከሚጠየቀው (ከሚፈለገው) ዕቃ በላይ ማምረት ይጀምራል ። የቆዳ ዕቃዎች ተመንም ይወርዳል ፤ በትርፍ ደረጃው መጠን ከዚያው ጋር የሚስማማ እንበል 20% ይወርዳል ።

እንዲሁም የኢንጂነሪንግ ምርት ይቀንሳል ፤ ግን የሸቀጡ ተጠያቂነት እንደበፊቱ እንዳለ ይቆያል ። የቀራቢነትና የተጠያቂነት ግንኙነት መለዋወጥ በኢንጂነሪንግ ውስጥ ያሉትን ካፒታሊስቶች የምርታቸውን ተመን ከፍ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል ከዚሁ ጋር ለመስማማት የትርፍ መጠኑ ይነሳል ፤ ለምሣሌ — ከ10% ወደ 20% ይደርሳል ።

ስለዚህ የወረት ከአንድ የኢንዱስትሪ ቅርንጫፍ ወደሌላው መፍሰስ የተለያዩ የትርፍ ደረጃን አማካይ የትርፍ መጠን በመስጠት ወደማስተካከሉ ያመራል ። አማካይ የትርፍ ደረጃ ማለት በተለያዩ የኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች ላይ በዋሉ አንድ ዓይነት (እኩል መጠን ባላቸው) በሆኑ ወረቶች ላይ ዕኩል ትርፍ ማግኘት ነው ። ከአማካይ የትርፍ ደረጃ መመሥረት (መምጣት) ጋር ፤ ሸቀጦች የሚሸጡት በዕሴት ላይ ሆን (ቀ+ተ+ትዕ) ግን ዋጋውንና አማካይ ትርፉን በያዘ (ቀ+ተ+ም) ተመን ነው ። የሸቀጡን ዋጋና አማካይ ትርፍ የያዘው ተመን የምርት ተመን ተብሎ ይጠራል ።

የተለያዩ የትርፍ ደረጃዎች ተመጣጥነው ወደ አማካይ ትርፍ መለወጥና የምርት ተመን አመሠራረት በሚከተለው ሠንጠረዥ ሊታይ ይችላል ፤—

| ኢንዱስትሪ | የወረት አካላዊ ይዘት | የትርፍ ዕሴት ደረጃ % | ትርፍ ዕሴት | የትርፍ ደረጃ መጠን % | የሸቀጥ ዕሴት | አማካይ የትርፍ ደረጃ % | የምርት ተመን | የምርት ተመን ከምርት ዕሴት መለያየት /ልዩነት/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቆዳ ሥራ | 70ቀ + 30ተ | 100 | 30 | 30 | 130 | 20 | 120 | —10 |
| ጨርቃ ጨርቅ | 80ቀ + 20ተ | 100 | 20 | 20 | 120 | 20 | 120 | 0 |
| ኢንጂነሪንግ | 90ቀ + 10ተ | 100 | 10 | 10 | 110 | 20 | 120 | + 10 |
| ጠቅላላ | 240ቀ + 60ተ | 100 | 60 | 20 | 360 | 20 | 360 | — |

ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው የተለያዩ የትርፍ ደረጃዎች ወደ አማካይ ደረጃ ተስተካክለው እናያለን ። የምርት ተመኖች ከሸቀጡ እሴት አፈንግጠዋል ። በአንዱ ኢንዱስትሪ ከዕሴቱ በላይ ወጥተው ፤ በሌላው ከዕሴቱ በታች ወርደዋል ።

ዝቅተኛ የወረት አካላዊ መልክ ባላቸው ኢንዱስትሪዎች (በምሣሌአችን በቆዳ ሥራ ኢንዱስትሪው ውስጥ) ፤ የምርት ተመን ከዕሴቱ በታች ሆኖ ሲታይ ፤ ትርፉ ከተመረተው ትርፍ ዕሴት ያነሰ ነው ። አማካይ የወረት አካላዊ ይዘት ባላቸው ኢንዱስትሪዎች ፤ የምርት ተመኖች ከዕሴቱ ጋር ተስማምተው ፤ ትርፍ ደግሞ ከተመረተው ትርፍ ዕሴቱ ተጣምቶ እናያለን ። ከፍተኛ የወረት አካላዊ ይዘት ባላቸው ኢንዱስትሪዎች (ኢንጂነሪንግ ፤ በምሣሌአችን) የምርት ተመኖች ከዕሴቱ በላይ ኀረው ፤ ትርፉም ከተመረተው ትርፍ ዕሴት በላይ አሻቅቧል ። ይህ የምርት ተመን መጠን ከዕሴቱ በላይ እጅግ መቆለል የተፈጠረው ዝቅተኛ የወረት አካላዊ መልክ ባላቸው ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በሚሠሩ ሠራተኞች ነው ፤ ግን የሚወስደው ከፍተኛ የወረት አካላዊ መልክ ባላቸው የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች ይሆናል ።



ስለዚህ ሠራተኞች የተበዘበዙት በቀጣሪያቸው ብቻ ሳይሆን ፤ ግን በካፒታሊስቱ መደብ በአጠቃላይ ነው ። በጠቅላላው የካፒታሊስቱ መደብ አማካይ ትርፍን ከፍ ስለሚአደርግለት የሠራተኞችን የመበዝበዝ ደረጃ ከፍ የማድረግ ዝንባሌ አለው ። ለዚህ ነው ካፒታሊስቶች ሠራተኛውን በመጻረር የሕብረት ግንባር የሚመሠርቱት ። ሠራተኛው መደብ በካፒታሊስቶች በአጠቃላይ የሚበዘበዘው ፤ የመደብ አንድነት በመመሥረት የሕብረት ግንባር መፍጠር ይኖርበታል ። ለአንድ ክፍል ሠራተኞች ዝንባሌ ትግል ከግለሰብ ካፒታሊስቶች ጋር የሚደረግ ትግል ፤ ለሠራተኞች የኑሮ ሁኔታ መሠረታዊ ለውጥ አያመጣም ። ሠራተኛው መደብ የካፒታሊዝምን ቀንበር በመወርወር ግቡን የሚመታው የካፒታሊስትን ስርዓት ጠርጎ ሲጥል ብቻ ነው ። በዚህ መደምደሚያ ላይ ለወዛደሩ የመደብ ትግል ዓይነተኛው በማርክስ የተተነተነው የአማካይ ትርፍ — ንድፈ ሀሳብ የፖለቲካዊ ትግል ነው ።

እንዳየነው ፤ በካፒታሊዝም ውስጥ ሸቀጦች የሚሸጡት በዕሴታቸው ሳይሆን ፤ ግን በምርት ተመናቸው መሠረት ነው ። ግን የዕሴት ሕግ መሥራት አቁሟል ማለት አይደለም ። የምርት ተመን የዕሴት የተሻሻለ መልኩ ነው ። አንዳንድ ካፒታሊስቶች ሸቀጦቻቸውን የሚሸጡት ከዕሴታቸው በላይ በሆነ ተመን ሲሆን ሌሎች ከዕሴቶች በታች ሆኖ ፤ ግን በሙሉ ካፒታሊስቶች ባጠቃላይ የሸቀጦቻቸውን ሙሉ ዕሴት ይቀበላሉ ፤ እናም የጠቅላላው የካፒታሊስት መደብ ትርፍ በሕብረተሰቡ ውስጥ ከተመረተው ጠቅላላ የትርፍ ዕሴት ድምር ጋር የተጣማ ነው ። ከጠቅላላው የሕብረተሰብ ደረጃ ሲታይ ፤ የምርት ተመኖች ድምር ከሸቀጦች ዕሴት ድምር ጋር እኩል ነው ፤ የትርፉ ብዛት ደግሞ ከትርፍ ዕሴቱ ብዛት ዕኩል ይሆናል ። በዚህ መንገድ የዕሴት ሕግ በምርት ተመን አማካኝነት ይሠራል ማለት ነው ።

**የትርፍ ደረጃ የመውደቅ አዝማሚያ**

ካፒታሊዝም ሲዳብር ፤ የወረት አካላዊ ይዘት ይንራል ። ይህም በድርጅቶች ውስጥ በጥሬ — ሀብት ፤ በማሺን እና በመሣሪያ ብዛት ጭማሪ አለ ማለት ነው ። እንዲሁም ፤ እጅግ አፋጣኝ አይሁን እንጂ የሠራተኞች ቁጥርም ይጨምራል ። ስለዚህ ተለዋዋጭ ወረት ከቀዋሚ ወረት በዘገምተኛነት ያድጋል ። ግን የወረት አካላዊ ይዘት ከፍተኛ በሆነ ቁጥር ፤ የትርፉ ደረጃ ዝቅ ይላል ። ይሁንና ይህ ጠቅላላ የትርፍ መጠን ብዛት ይወርዳል ማለት አይደለም ። አንድ ምሣሌ እንውሰድ ። 100ሺ ሚሊዮን የሚሆን የሕብረተሰብ ወረት ፤ ከ70ቀ +30 ተ ከተሰራ በ20 ዓመት ውስጥ የዚህን እጥፍ ሆኖ 200ሺ ሚሊዮን ብር ይደርሳል ። አካላዊ ይዘቱ አድገና 160ቀ+40 ተ ሆነ ። የትርፍ ዕሴት ደረጃ 100% ሆኖ ፤ የትርፉ መጠን በመጀመሪያው ምሣሌ 30ሺ ሚ. ብር ነበር ፤ በሁለተኛው ላይ—40 ሺ. ሚ. ብር ሆነ ። በዚያው ጊዜም የትርፉ ደረጃ ከ30% ወደ 20% ዝቅ ብሏል ። በወረት አካላዊ ይዘት ላይ ጭማሪ እንደሚኖር ሁሉ በትርፍ ደረጃ ላይም መውረድ የማይቀር ነገር ነው ። ሆኖም ይህን በመጻረር የሚሰሩ ሌሎች ምክንያቶች አሉ ።

የትርፍ ደረጃን መውደቅ በመጻረር ከሚሰሩት ምክንያቶች ዓይነተኛው የሠራተኞች የመበዝበዝ ደረጃ ከፍ ማለት ነው ። ወደ ምሣሌአችን እንመለስ ። በሁለተኛው ምሣሌአችን የብዝበዛ ደረጃው ጨምሯል ብለን እናስብና 200% እናድርገው ። አሁን ትርፉ ብር 80 ሺ ሚሊዮን ሲሆን ፤ የትርፍ ደረጃው ግን

$$\frac{80}{100+40} \times 100\% = \underline{\underline{40\ \%}}$$

ይሆናል ። ስለዚህ የሠራተኛው መደብ መበዝበዝ መጠናከር ወደትርፍ መጨመር ያመራል ።

ከትርፍ ደረጃ መውደቅ ባሻገር በተጻራሪነት የሚሠሩ ሌሎች ምክንያቶችም አሉ ፤— ከጉልበት ዕሴት በታች ምንዳዕን ማውረድ ፤ በሠራተኞች ኑሮና ጤና ኪሣራ ቀዋሚን ካፒታል መጠበቅ (መቆጠብ) ፤ ወዘተ. . . .

ግን እነዚህ ምክንያቶች ሁሉ የትርፍ ደረጃን የማሽቆልቆል ጸባይ እየሰጡ ያባብሳሉ እንጂ አያስወግዱም ።

የትርፍ ደረጃን በደንብ የመውደቅ አዝማሚያ የሚአባብሰው የካፒታሊዝም ቅራኔ ነው ። በቡርዧዋውና በወዛደሩ መካከል ያለው ቅራኔ በቡርዧዎች የትርፍ ደረጃን መውደቅ ለማዘግየት የሠራተኞችን መበዝበዝ ስለሚአጠናክሩ ይበልጥ ይተባል ። እንዲሁም በካፒታሊስቱ ሠፈር መካከልም ቅራኔው ይስላል ። ካፒታሊስቶች ወረታቸውን ከፍተኛ የትርፍ ደረጃ ወዳሉአቸው ኢንዱስትሪዎች ያሯሩጣሉ ። ይህ ደግሞ በካፒታሊስቶች መካከል መራራ ውድድር ያመጣና በመጨረሻ የአንዳንዶቹ መጥፋት የሌሎች መበልጸግ ይከስታል ። ስለዚህ በካፒታሊስት ኃይሎች መካከል ቅራኔው ይባባሳል።በከፍተኛ የትርፍ ደረጃ አሠራር ምክንያት ፤ወረት በኢንዱስትሪ ከዳበሩ አገሮች የጉልበት ኃይል እርካሽ በሆነባቸው የወረት አካላዊ ይዘት ዝቅ በሚልባቸው ወደ ኋላ ቀር አገሮች ይሸጋገራል ።

የካፒታሊዝምን ቅራኔ በማባባስ የትርፍ ደረጃ የመውደቅ ሕግ ግልጽ መሆን የሚአመለክተው የካፒታሊስትን ሥልተ—ምርት ታሪካዊ ውሱንነትና አላፊነት ተፈጥሮ ነው ።

## 3. የንግድ ትርፍ ።

የኢንዱስትሪና የንግድ ወረት

ትርፍ ዕሴት የሚፈጠረው በምርት ሂደት ጊዜ በሠራተኛው ጉልበት ነው ። በመጀመሪያ ደረጃ የሚወስደው በድርጅቱ ባለቤት በኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ይሆናል ። ከእርሱ ነው ሌሎች ሁሉ በዝባዥ መደቦች ፤የንግድ ካፒታሊስቶችም በመዳመር ትርፍ ዕሴት የሚቀበሉት ። ለምንድነው የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ከትርፍ ዕሴቱ የተወሰነ ክፍል ለነጋዴው የሚሰጠው ? በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ሸቀጦች የሚመረቱት ለሽያጭ ነው ። ስለዚህ ሸቀጡ መመረት ብቻ በቂው አይደለም ፤መሸጥም አለበት ። እንደአጠቃላይ ሕግ ሆኖ ፤ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ሸቀጡን የሚሸጠው ለነጋዴው ነው ፤ከነጋዴውም ሸቀጡ ለተጠቃሚው ተዛውሮ ያየዋል ።

የንግድ ካፒታሊስቱ ተግባር ሸቀጥን ወደ ገንዘብ ወረት መለወጥ ነው ። የንግድ ካፒታሊስቶች ባይኖሩ ኖሮ ፤የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች የንግድ ዝግጅትን ለማሟላት ፤ሻጮችን ለመቅጠር ፤ወዘተ. . . . ተጨማሪ ወረት ያስፈልጋቸው ነበር ። ግን ኢንዱስትሪያሊስቶች ይህን ሁሉ ለነጋዴው ተውለት ። በሕብረተሰብ ደረጃ ስንመለከተው ፤የንግድ ወረት ከኢንዱስትሪ ወረት የተለየን ተጨማሪ ወረት ነው የሚመስለው ፤በዚህም ከፊሉን ትርፍ በሚወስዱት እንደ ንግድ ካፒታሊስቶች ወረት ሆኖ ይመጣል ። ወደእነሱ የሚሄደውም ትርፍ የንግድ ትርፍ ተብሎ ይታወቃል ።

የንግድ ትርፍ ምንጭ

የንግድ ትርፍ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ( አፈብራኪው ) ለሸቀጦቹ ሽያጭ ለነጋዴው የሚሰጠው የትርፍ ዕሴት ክፍል ነው ። የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች ሸቀጦቻቸውን ለነጋዴዎች የሚሸጡት ከምርት ተመኑ ዝቅ አድርገው ነው። ከዚያም ነጋዴዎች በምርት ተመኑ ይሸጣሉ።ስለዚህ እነሱም እንደኢንዱስትሪያሊስቶች ልዩነቱን በመውሰድ፤በወረታቸው ላይ አማካይ ትርፍ ይቀበላሉ። የነጋዴው ትርፍ ከአማካይ ትርፉ በታች ከወረደ ፤ንግድ ትርፍ የሌለው ሥራ ይሆናል ፤እናም ነጋዴው ወረቱን ወደ ኢንዱስትሪ ያዛውራል ። ሁሉም ኢንዱስትሪያሊስቶችና ነጋዴዎች አማካይ ትርፍ ይወስዳሉ ። ግን ይህ ሁሉም እኩል የትርፍ መጠን ያገኛሉ ማለት አይደለም ። በመሠረቱ ኢንዱስትሪያሊስቱ ከነጋዴው የሸቀጥ ሽያጭ የበለጠ ወረት የሚአጠፋው የበለጠ የትርፍ መጠን ያገኛል ። ግን ዕኩል ለሚጠፉ ወረት ዕኩል ትርፍ ያገኛሉ ።

ትርፍ ዕሴት የንግድ ትርፍን መልክ ሲይዝ ይበልጥ ይላበሳል (ሥውር ይሆናል)። የነጋዴው ወረት በምርት ላይ አይሳተፍም ፤እናም ስለዚህ ትርፍ የሚመነጨው ከዚያው ከንግዱ ይመስላል ።



የመዚዚር (ዑደት) ዋጋ

ሸቀጥን የመገንዘብ ሂደት የተወሰነ ወጭ ያስፈልገዋል ። ይህ የሚአስመለክተው የዑደትን ዋጋ ነው ።

ሁለት ዓይነት የካፒታሊስት የዑደት ዋጋዎች አሉ ። የዑደት ንጹህ ዋጋ (Net Costs of Circulation ) በቀጥታ የተያያዘው ሸቀጦችን ከመሸጥና ከመግዛት ሂደት ጋር ነው ። ሸቀጦችን ወደ ገንዘብ ፤ ገንዘብን ወደሸቀጥ መለወጥንም ውጫዊ መያያዝ ይጨምራሉ ። እንደገናም በዚሁ ውስጥ የምናገኘው ለንግድ ተቀጣሪዎች ጉልበት የሚከፈለው ሠፊው የወጭ ክፍል ፤ ለማስታወቂያ ፤ የንግድ ቢሮዎችን መጠገኛ ፤ ለውድድርና ሀሳብን ለመሰብሰቢያ (ለመደራደሪያ) የሚአስፈልገውን ወጭ ሁሉ ይይዛል ። የዑደት ንጹህ ዋጋዎች ለሸቀጡ ምንም ዕሴት አይጨምሩም ፤ እናም በካፒታሊስቶች ትርፍ ዕሴት ፤ ከኢንዱስትሪያሊስቱ ከሚአገኙት ማለት ነው ፤ ይሸፈናሉ ። ንጹህ ዋጋዎች የሚጤኑት በካፒታሊስቱ ንግድ በሚመጣው ከፍተኛውን ክፍል በያዘው የዑደት ዋጋዎች ነው ።

ወደ መዚዚር አድማስ ከሚሰፋፋው የምርት ሂደት ከሚመነጩት ዋጋዎች መካከል አንዱ በሕብረተሰቡ አስፈላጊ አሠራሮች ላይና ከካፒታሊስት ኤኮኖሚ ልዩ ጸባዮች ነጻ ሆኖ የሚወጣው ወጭ ማለትም ፤የሸቀጦች ማከማቸትን ፤የመጨረሱን ፤ የማጓጓዙና የማሸጉን ሂደት ጭምር ነው ። አንድ ምርት ለጠቀሜታ ተዘጋጅቷል የሚባለው ለተጠቃሚው ሲደርስ ( ሲታደል ) ብቻ ነው ። ሸቀጥን አምርቶ በመጨረስ ፤በማጓጓዝና በማሸግ የሚጠፋ ጉልበት መጀመሪያውኑ ባለው የሸቀጦች ዕሴት ላይ አዲስ ዕሴት ይጨምራል ፤በዚህም ምክንያት የመዚዚር ዋጋ ከምርት ዋጋ በምንም መንገድ አይለይም ።

በካፒታሊዝም ውስጥ የመዚዚር ዋጋ ሳያቋርጥ ይጨምራል፤መጀመሪያ ከሁሉም በፊት በተለይ ከማስተዋወቅ ጋር የተያያዙት የመዚዚር ንጹህ ዋጋዎች በ1961 ዓ.ም. ዩናይትድ ስቴትስ በማስታወቂያ ያወጣችው ወጭ ወደ 12,000 ሚ. ሲሆን ይህም ከ1950 ደረጃ ከእጥፍ በላይ መሆኑ ነው ። የመዚዚር ዋጋዎች መጨመር የሚአመለክተው በቡርዧው ሕብረተሰብ ውስጥ የደም መጣጭነት ጸባይ እያደገ መሄዱን ነው ። በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የመዚዚር ዋጋዎች ከአጠቃላዩ የንግድ መዚዚር (የዕቃዎች መለዋወጥ ፤ መሸጥ) ⅓ኛውን ያህል ይይዛል ፤እናም ለሠራተኛው ሕዝብ ከባድ ሸክሞች ናቸው ።

የካፒታሊስት ንግድ መልኮች—የውጭ ንግድ

በዛሬው የካፒታሊስት ምጣኔ — ሀብት ሁለት ዓይነት የሀገር ውስጥ ንግዶች አሉ — ጅምላና ችርቻሮ የሚባሉ ። የጅምላ ንግድ የሚባለው በካፒታሊስቶች መካከል ያለው ንግድ ሲሆን (በኢንዱስትሪያሊስቶችና በነጋዴዎች) ችርቻሮ ደግሞ በቀጥታ ለሕዝብ የሸቀጦች መሸጥ ነው ።

በጅምላ ሺያጭ ውስጥ ዋናነት ያለው የሸቀጥ ልውውጥ ነው ። ይህ ፤ንግድ በናሙና (ሳምፕል) መሠረት ፤የሸቀጦች ተጠያቂነትና ቀራቢነት በሀገር አቀፍ ደረጃና እንዲሁም በመላ የካፒታሊስት ዓለም ደረጃ የሚደልቡበት ልዩ ዓይነት ገበያ ነው ።

የውጭ ንግድ የዕቃዎችን ከሀገር ውስጥ የመላክና ወደሀገር ውስጥ የማስመጣትን ሂደት የያዘ ነው ። በመካከላቸው ያለው ግንኙነት (በተመኖች) የንግድን ሚዛን ያስተካክላል ። የንግድ ሚዛን በቶሎ ተለዋዋጭ ወይም ዕርጋታ ያለው ሊሆን ይችላል ። ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ከሀገር ውስጥ የሚወጣውን ከበለጠ ፤የንግዱ ሚዛን ፈጣን (ተለዋዋጭ) ነው ፤የተገላቢጦሹ ከሆነም ዕርጋታ አለው ።

ካፒታሊስቶች ሸቀጦችን በውጭ ገበያ በመሸጥ ምርትን ለማስፋፋትና ከዚያም ትርፋቸውን ለመጨመር ይችላሉ ። ንግድ በተለይም በምጣኔ ሀብት ወደኋላ ከቀሩ አገሮች ጋር ማካሄድ በኢንዱስትሪ ለዳበሩ አገሮች ካፒታሊስቶች ብዙ ጥቅም አለው። ይህም የሚሆነው የተፈበረኩ ዕቃዎች ለነዚያ አገሮች በጣም ከፍተኛ በሆነ ተመን

ስለሚሸጡ ሲሆን ፣ ጥሬ ዕቃዎች ግን ከነርሱ የሚገዙት በዝቅተኛ ተመን በመሆኑ ነው ። የውጭ ንግድ የዳበሩ የቡርዧ አገሮች ያልዳበሩ አገሮችን የምጣኔ — ሀብት ጥገኛ አድርገው ለመያዝ የሚጠቀሙበት መንገድ ነው ።

## 4 የብድር ወረት (ካፒታል) ። የተዋሃዱ (ጥቅል) —ግዙፍ ኩባንያዎች

የብድር ወረትና ወለድ

በወረት መዘዋወር ጊዜ ፣ ተገንጥሎ (ተለይቶ) የሚቀረው የንግድ ወረት ብቻ ሳይሆን ፣ የብድር ወረትን መልክ በሚይዝበት ጊዜ የገንዘብ ወረት ም ነው ። ከየት ነው ተጠባባቂ የገንዘብ ወረት የሚመጣው ? አንድ ባለኢንዱስትሪ ያለቀለት ሸቀጡን በየወሩ ቢሸጥ ፣ እንበልና ፣ ግን ጥሬ — ሀብት የሚገዛው በዓመት ሁለት ጊዜ ቢሆን ፣ በእጁ ለአምስት ወራት ያህል መጠባበቂያ ገንዘብ ይኖረዋል ። ካፒታሊስቱ ለነባር (ካፒታል) ወረት ( Fixed Capital) መበላት መተኪያ የሚሆን ገንዘብ ቢአጠራቅም ፣ አሁንም ጊዜአዊ መጠባበቂያ ገንዘብ ይኖረዋል ። እነዚህ የገንዘብ ድምሮች ከብዙ ዓመታት ማለት (ለዕቃው — ለማሺኑ) በኋላ ብቻ አዲስ ማሺን ለመግዛት ይውላሉ ።

በሌላ ጊዜ ካፒታሊስቱ ገንዘብ የሚአስፈልገው ይሆናል ፣ ለምሣሌ ፣ ያለቀላቸውን ሸቀጦቹን ሳይሸጥ ይቀርናና ግን ወዲያውኑ ጥሬ ዕቃ ሊገዛ በሚፈልግበት ጊዜ ማለት ነው ።

እንዲሁም አንዴና በዚያው ጊዜ አንድ ካፒታሊስት ጊዜአዊ ትርፍ የገንዘብ ወረት ይኖረዋል ፣ ግን ሌላው ደግሞ በሚፈልግበት ሁኔታ ይሆናል ። እንደልብ ገንዘብ ያለው ካፒታሊስት ለጊዜአዊ ጥቅም ለሌላው ካፒታሊስት ያበድረዋል ። የብድር ወረት ለተወሰነ ክፍል በብድር ጊዜ የሚሰጥና በተወሰነ የጊዜ ግንዛቤም (ወለድ ተብሎ በሚታወቅ) የሚመለስ የገንዘብ ወረት ነው ።

ወለድ (አራጣ) ማለት ኢንዱስትሪያሊስቱ ወይም ነጋዴው ለአበዳሪው ካፒታሊስት በመበደሩ ምክንያት ማስገኘትና መስጠት ያለበት የትርፍ ክፍል ነው ። ኢንዱስትሪያሊስቱ ወይም ነጋዴው የተበደረውን ገንዘብ በምርት ወይም በንግድ ላይ ያውለዋል ። ስለዚህም የብድር ወረት መለያ ገጹ ባለቤት የሆነው ካፒታሊስት የሚገለገልበት አለመሆኑ ነው ። ኢንዱስትሪያሊስቱ ፣ የተበደረውን ወረት በመጠቀም ሠራተኞችን ይቀጥራል ፣ እናም ትርፍ ዕሴት ይጨምቃል ። ከትርፉ በከፊል ለአበዳሪው በወለድ መልክ ይከፍላል ። ስለዚህ ወለድ (አራጣ) የትርፍ ዕሴት መልክ ነው ።

ይህን ምሣሌ እንውሰድ፡- አንድ ባለኢንዱስትሪ ካፒታሊስት የ100,000 ብር ብድር ወለድ በ20 ፐርሰንት አማካይ የትርፍ ደረጃ ተቀበለ ፣ በዚህ ወረት የተገኘው ጠቅላላ ትርፍ20,000 ብር ነው ። ከዚህ ትርፍ ውስጥ ኢንዱስትሪያሊስቱ ለአበዳሪው ካፒታሊስት አራጣ ይከፍልለታል ። በብድሩ ላይ ያለው አራጣ ደረጃ ወይም መጠን 1* ቢሆን በ100,000 ብር ፣ 3,000 ብር ከ20,000 ብር ትርፍ ይከፍላል ማለት ነው ። ቀሪው ትርፍ ፣ 17,000 ብር በኢንዱስትሪያሊስቱ ይወሰዳል ። ይህኛው የትርፍ ክፍል የድርጅቱ ትርፍ ተብሎ ይታወቃል ።

አማካይ ትርፉ በአራጣና በድርጅቱ ትርፍ የሚሸነሸንበት ምጥነት ጥገኛ የሚሆነው የብድሩ ን ወረት በሚመለከተው ተጠያቂነትና ቀራቢነት ላይ ነው ። የገንዘብ ወረት ተጠያቂነት ሲአይል ፣ አራጣውም ይንራል ፣ እንዲሁም ተጠያቂነቱ ዝቅ ሲል ፣ አራጣው ይወርዳል ። አራጣ የአማካይ ትርፍ ክፍል ብቻ ነውና የአራጣ ደረጃ (መጠን) ከአማካይ የትርፍ መጠን ሊወጣ አይችልም ።

ካፒታሊዝም ሲአድግ ፣ የአራጣው መጠን የመውደቅ አዝማሚያ ያሳያል ። ለዚህ ሁለት ምክንያቶች ይኖሩታል ፡— 1/አማካይ የትርፍ ደረጃ ለመውደቅ ያዘነብላል 2/ ጠቅላላው የብድር ወረት መጠን ካለው ተጠያቂነት በ ይ በፍጥነት ያድጋል ።

*1. የአራጣ መጠን በብድር ላይ ለሚሰጠው ወረት ብዛት መጠን ነው ።



የብድር ወረት እንቅስቃሴ በዱቤ መልክ ነው የሚካሄደው ።

የካፒታሊስት ዱቤ ፣ ባንኮችና የባለ ባንኮች ትርፍ

የካፒታሊስት ዱቤ ሁለት መልኮች አሉት ። የንግድና የባንኮች ዱቤ የሚባሉ ።

የንግድ ዱቤ ኢንዱስትሪያሊስቶችና ነጋዴዎች እርስ በእርሳቸው ሸቀጦችን በዱቤ ሲሸጡ ፣ ሻጩ፣ ገዥው ለተወሰነ ቀን የተወሰነ የገንዘብ መጠን እንዲከፍል የሚአስገድድ የልውውጥ ሰነድ በሚቀበልበት ጊዜ የሚሰጥ ዱቤ ነው ።

የባንከኞች ዱቤ በኢንዱስትሪ ወይም በንግድ ሥራ ለሚካሄዱ ካፒታሊስቶች በባንከኞች የሚሰጥ የባንክ ዱቤ (ብድር) ነው ። የባንከኞች ዱቤ በባንክ ውስጥ ከተቀመጠው ጊዜአዊ ተጠባባቂ ገንዘብ ነው የሚሰጠው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ «ባንክ» ተግባሩ በተበዳሪና በአበዳሪ መሃከል አደራዳሪ የሆነ የካፒታሊስት ይዞታ ነው ። የባንክ ተግባሩ ተጠባባቂ ፣ የማይንቀሳቀስ ወረትንና (ገንዘብን) ገቢን መሰብሰብና ሥራን ለሚአካሂዱ ካፒታሊስቶችና እንዲሁም ለቡርዧው መንግሥት ማዘጋጀት ነው ። በተጨማሪም ባንከኞች በቀጥታ ወረትን የሚአውሉት በኢንዱስትሪያዊና ንግድ ድርጅት ውስጥ ይሆናል ። ስለዚህም ወዲያውም ሠራተኛ (አከናዋኝ) ካፒታሊስቶች ይሆናሉ ።

የባንክ አሠራር ፣ እንደሌሎች የካፒታሊስት ድርጅቶች ሁሉ ፣ ትርፍ የመሥራት ነባሪን ነው የሚአገለግለው ። በባንክ የሚገኘው ትርፍ ምንጩ በምርት ጊዜ የሚፈጠረው ትርፍ ዕሴት ነው ። የባንከኞች ትርፍ በባንኩ በተሰጠው ወረት በሚታሰበው አራጣና ባንኩ ለአስቀማጮች በሚከፍለው አራጣ መካከል ያለው ልዩነት ነው ። ተቀማጭ (Deposit) ፣ ጊዜአዊ ተጠባባቂ የገንዘብ ምንጭ የሆነ በካፒታሊስቶች ነጋዴዎች ፣ መሬት ከበርቴዎች እና በሌሎችም የሕዝብ ክፍሎች በባንክ ውስጥ የሚቀመጥ ነው ። ባንኩ አበድሮ ከሚአገኘው አራጣ ያነሰ ለተቀማጩ ገንዘብ ይከፍልና ልዩነቱን ይወስዳል ። ከዚህ ውስጥ በባንክ አሠራር ውስጥ ያለውን ወጭ ባንከኛው ይሸፍናል ፣ ቀሪው ደግሞ ትርፉ ይሆናል ። የራሱ የካፒታሊስት ውድድር በራሱ በባንኩ ወረት ላይ በአማካይ የትርፍ ደረጃ መጠን በማምጣት ይህንን ትርፍ ያወርደዋል ። ከባንኩ ወረት እጅግ ብዙው በተቀማጭነት የተገኘ ብድር ወረት እንደሆነ አንረሳውም ።

እንደአዋዋይ (አማካይ) ሆኖ ከመሥራቱ ሌላ ፣ ባንኩ ፣ በካፒታሊስቶች መካከል ያለውን ሂሣብ በማስተካከል ሁሉንም ዓይነት ገንዘባዊ ኮሚሽንም ይሠራላቸዋል ። ስለሆነም ፣ ባንኩ ለብዙ ካፒታሊስቶች እንደገንዘብ ከፋይና ተቀባይ ሆኖ ነው የሚሠራው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ባንኮች የሚሰሩት ገንዘባዊ ምንጮችን በካፒታሊስቶች የተለያዩ የምጣኔ — ሀብት ቅርንጫፎች መካከል በግብታዊ መልክ የሚአደላድሉ እንደ ልዩ ተቋም በመሆን ነው ። ግን የሚደለድሉት በሕብረተሰቡ ፍላጎት ሳይሆን ፣ በካፒታሊስቶች ነው ። የካፒታሊስትን ዱቤ ፣ የተለያዩ የምጣኔ— ሀብት ቅርንጫፎችን በቅርብ በማያያዝ ፣ የሥራን (ጉልበትን) ሕብረተሰባዊነት ከፍተኛ እድገት ያሸጋግራል ። ግን የሥራ ሕብረተሰባዊ መሆን የሚካሄደው በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት መሠረት ይሆናል ። በዚህ ምክንያት የዱቤ ዕድገት አሁንም (በተጨማሪ የካፒታሊስቱን ሥልተ — ምርት ቅራኔ ያባብስና የካፒታሊስት ምርትን ሥርዓተ አልባነት ያሳድገዋል ።

የተዋሃዱ ግዙፍ ኩባንያዎች

ካፒታሊዝም ሲገባ ፣ ፋብሪኮች የተጀመሩት በግለሰቦች ባለቤትነት ነው ። ይሁንና በኋላ እንደወደቦችና የባቡር መስመሮች የመሳሰሉት ትላልቅ ድርጅቶች በግለሰብ ገንዘብ ሊሟሉ አልቻሉም ። በኢንዱስትሪ ፣ በባቡር ሃዲድ ሥራ ፣ እና በባንክ ውስጥ ጥምር ግዙፍ ኩባንያዎች በኢንዱስትሪ ፣

ሊሰሩ ጀመሩ ። በስፊው የተስፋፉት በ19ኛው ምዕተ — ዓመት 2ኛ አጋማሽ ላይ ነው ። የተቀሃደ (የተጣመረ) ግዙፍ ኩባንያ የድርጅት መልክ የሆነ ካፒታሉ (ወረቱ) ከኩባንያው አባላት የተሰበሰበ (ባወጡት ወረት መጠን የተወሰነ ዕጣ በሚኖራቸው ሰዎች) ነው ።

እጣ (ድርሻ) አንድ ባለንብረት በድርጅቱ ውስጥ የተወሰነ ገንዘብ ያስገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ (ዋስትና) ነው ። ድርሻው ለባለቤቱ ( Holder ) ከድርጅቱ ገቢ የተወሰነውን ክፍል እንዲወስድ መብት ይሰጠዋል ። ከባለድርሻው የሚወሰደው መጠን ክፍያ ይባላል ። ዕጣዎች (ድርሻ) በጥቅል ልውውጥ ጊዜ ኮታ (መጠን) ተብለው በሚታወቁት መሠረት በተወሰነ ተመን ይሸጣሉ ይገዛሉ ። የጥቅል ልውውጥ በቀደምትነት (ለድርሻ) ለዕጣ ፤ የዋስትና ገበያ ነው ። እዚህ ላይ ነው ዕጣዎች

የሚገዙ የሚሸጡትና ኮታም የሚመዘገበው ።

መጠን (ኮታ) ወይም የድርሻዎች (ዕጣ) ተመን ጥገኛ የሚሆነው በሁለት መንገዶች ነው :— 1 ባንኮች ለተቀማጭ (Deposit) በሚከፍሉት የአራጣ ደረጃ ፤ እና 2) በእያንዳንዱ ዕጣ (ክፍያ) በዓመት በሚመጣው ገቢ ይሆናል ። የ100 ብር ዕጣ በዓመት የሚያስገኘው ገቢ 10 ብር ቢሆን፤ በባንክ ውስጥ ቢቀመጥ በዓመት 10 ብር ሊያስገኝ በሚችል ገንዘብ ይሸጣል ። ባንክ በዓመት ለተቀማጭ 5% ይከፈል ብለን እንውሰድ ፦ በዚህ መንገድ ዕጣው የሚሸጠው 200 ብር ነው ፤ ምክንያቱም ባለድርሻው ይህን ገንዘብ በማስቀመጥ በዓመት 10 ብር ያገኝበታልና ።

ለተወሃዱ ግዙፍ ድርጅቶች ቁጥጥርና ጥንካሬ ሲባል የባለድርሻዎች አጠቃላይ ስብሰባ የሥራ አስኪያጅ ቦርድ ባለሥልጣኖችን ምርጫ በማካሄድ ይሾማሉ ። በአጠቃላይ ስብሰባ የድምጽ ብዛት የሚወሰነው ባላቸው ዕጣ ነው ። እናም እንደደንቡ ሆኖ የዕጣዎች ብዙው ክፍል በጥቂት ትላልቅ ካፒታሊስቶች እጅ ስለሆነ እነሱ ናቸው ጥምር ግዙፍ ድርጅቶችን የሚቆጣጠሩ ። ሙሉ ቁጥጥር በጥምር ግዙፍ ድርጅቶች ላይ እንዲኖር ካስፈለገ ከጣዎቹ ከግማሹ በታች መያዝ ብቁ እንደሆነ በተግባር የታዩ ነው ። በጥምር ግዙፍ ኩባንያዎች ውስጥ አንድ ሰው እንደተመኘው ለመሥራት በቂ ድርሻ (ዕጣ) ከያዘ ዋናውን አራጣ ይዟል ማለት ነው ። ይህ ለሌሎችም ቡድን ሰዎች ይውላል ።

በባለቤትነት መረጃ (ድርሻ ፤ ዋስትና) መልክ ያለ ወረትና ለባለቤቱ ገቢ የሚያስገኘው ስማዊ ወረት ( Fictitious Capital ) ተብሎ ይጠራል ፤ ምክንያቱም የባለቤትነት መረጃዎች ( Securities ) በራሳቸው ዕሴት የላቸውምና እንዲሁ ብቻ በተዘዋዋሪ የእውነተኛውን ወረት እንቅስቃሴ ነው የሚያንጸባርቁት ።

የተዋሃዱ ጥቅል ኩባንያዎች ፤ መሠራጨት ካፒታሊስቶችን በየጊዜው ወደወለድ ተቀባይነትና ተካፋይነት ሲያሻግራቸው ፤ የኢንዱስትሪ ምርት አመራር ግን በተቀጠሩ ሹማምንት — ሥራ አስኪያጆች ፤ ዲሬክተሮች ነው የሚካሄደው ። ስለዚህ የካፒታሊስት ባለቤትነት ደም— መጣጭ ጸባይ ከቀን ቀን ግልጽ እየሆነ ይመጣል ።

ድርሻዎች (ዕጣዎች) ከሁሉም የሕዝብ ክፍሎች በተውጣጡ ሰዎች ተይዘዋል። ይህም የካፒታሊስቶችን ጥቅም ነው የሚያጎላው — ምክንያቱም ብዙ ዕጣዎች ሲገዙ በከፍተኛው መደብ ያሉ የተዋሃዱ ጥቅል ኩባንያዎች ን የሚቆጣጠሩ ዕጣ የያዙት ይበልጥ ያደልባሉና ። ሆኖም ዕጣዎች በሠራተኛ ቡድኖች መያዛቸው (መግዛታቸው) ለቡርዧ ርዕዮተ — ዓለማውያን ለ «ወረት ዲሞክራሲያዊነት» ንድፈ ሀሳባቸው መሠረት ሰጥቷል ። ይህ ሃሳዊ ንድፈ — ሀሳብ የተዋሃዱ ጥቅል መልክ ድርጅቶች ማደግ ምክንያት የካፒታሊዝም አወቃቀር ይለወጣል እናም ዕጣዎች ን የሚገዛ ማንኛውም ሠራተኛ ሰው የኩባንያው አንድ ባለቤት ይሆንና በአስተዳደሩም ላይ ድርሻ ሊወስድ ይችላል የሚል ገለጻ ያቀርባሉ ። እንደእውነቱ ከሆነ ፤ የተዋሃዱ



ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ በትላልቅ ካፒታሊስቶችና ከኩባንያው ወረት ድርሻም ጥቅም በሚያገኙት ቁጥጥር ውስጥ ነው ። ከዕጣዎች ኢምንት የሆነ ድርሻ ያላቸው ሠራተኞች ግን በተዋሃዱ — ጥቅል ኩባንያዎች አመራር ውስጥ ምንም ሚና አይጫወቱም ፤ ሊጫወቱም አይችሉ ።

እላይ ትርፍ ዕሴት እንዴት ወደትርፍ እንደሚሻገርና ኢንዱስትሪያሊስቶች ፤ ነጋዴዎች እና ባንከኞች እንዴት እንደሚወስዱት አጢነናል ። ሆኖም በካፒታሊዝም ውስጥ አሁንም ሌላ በዝባዥ መደብ አለ — ትላልቅ የመሬት ከበርቴዎች የሚባሉ ። እነሱም ከትርፍ ዕሴቱ ድርሻቸውን ይቀበላሉ ። ይህም የካፒታሊስትን የመሬት ኪራይ መልክ ይይዛል ።

## 5. በካፒታሊዝም ውስጥ የመሬት ኪራይና እርሻ ነክ ግንኙነቶች ።

የካፒታሊስት የመሬት ኪራይ

የመሬት ኪራይ ከየት ነው የሚመጣው ፤ ማን አመጣው ፤ እናስ እንዴት ነው ለመሬት ከበርቴው የሚደርሰው ? ማርክሲዝም — ሌኒኒዝም ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሲሰጥ መነሻ ነጥብ አድርጎ የሚወስደው የቅጥር ጉልበትን በመበዝበዝ የሚካሄድ የካፒታሊስት እርሻ መኖርን ነው ። በተጨማሪም ባለመሬቱና ካፒታሊስቱ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ናቸው ተብሎ ይታሰባል ።

የመሬት ባለቤት እራሱ በእርሻ ላይ አይሰማራም ። ወረቱን በእርሻ ምርት ላይ ለማዋል ለፈለገ ካፒታሊስት መሬቱን ያኮናትራል ። ካፒታሊስቱ በምርት ሂደት ጊዜ ትርፍ ዕሴት የሚያስገኙ የእርሻ ሠራተኞችን ይቀጥራል ። ይህ ትርፍ ዕሴት በመጀመሪያ ትርፍ ዕሴቱን በሁለት ለሚከፍለው ጢሰኛ ገበሬ ለሆነው ካፒታሊስት ይገባል ። እርሱም ከፊሉን ላወጣው ወረት አማካይ ትርፍ እኩል የሚሆን ትርፍ ለራሱ ፤ ሌላውን ደግሞ በመሬት ባለቤቱ የሚወሰድ ከአማካዩ ትርፍ የበለጠና በላይ አድርጎ ይከፍለዋል።ይህ የትርፍ ዕሴቱ ሁለተኛው ክፍል ነው የመሬት ኪራዩን የሚመሠርተው። ለምንና በምን ምክንያት ነው የመሬቱ ባለቤት በካፒታሊስቱ ጢሰኛ ገበሬ በተቀጠሩት ሠራተኞች የተገኘውን የትርፍ ዕሴት ክፍል ለራሱ የሚወሰደው?የመሬቱ ባለቤት እርሱ ስለሆነ ብቻ እና ያለእርሱ ፈቃድ ደግሞ ማንም መሬቱን የማረስ መብት ስለሌለው ነው ። ለዚህ ነው የመሬት ኪራይ የመሬት የግል ባለቤትነት የሚታወቅበት ምጣኔ — ሀብታዊ መልክ የሚሆነው ። ካፒታሊስቱ እራሱ የመሬት ባለቤት ቢሆን ኖሮ በእርሻ ሠራተኞች የተገኘውን ሁሉንም ትርፍ ዕሴት በወሰደ ነበር ።

የካፒታሊስት የመሬት ኪራይ ከመልከኛ መሬት ኪራይ ይለያል ።በመልከኛነት ዘመን ፤ ኪራይ በማንኛውም መልኩ (የጉልበት — ኪራይ ፤ የዐይነት ኪራይ ፤ የገንዘብ ኪራይ) የመልከኛነት የምርት ግንኙነቶችን በሁለት ዋና መደቦች መካከል — በመሬት ከበርቴዎችና ገባር ገበሬዎች — ይገልጻል ። በካፒታሊዝም ዘመን ፤ የመሬት ኪራይ የሚገልጸው ሶስት መደቦችን የያዙ ግንኙነቶችን ነው — የመሬት ከበርቴዎችን ፤ የካፒታሊስት ጢሰኛ ገበሬዎችን ፤ እና ቅጥር የእርሻ ሠራተኞችን ።በመልከኛነት ዘመን የመሬት ኪራይ የሚጠቅሰው በገበሬዎች የሚፈጠረውን ጠቅላላ ትርፍ ዕሴት ነው ። በካፒታሊዝም ዘመን ትርፍ ዕሴት ለሁለት በዝባዥ መደቦች ፡— በካፒታሊስት ጢሰኛ ገበሬ እና በመሬት ከበርቴው — ይከፋፈላል ።

በሁለቱ ዓይነት ኪራዮች መካከል ልዩነቶች ግልጽ መሆን ይኖርባቸዋል ፡— የልዩነት ኪራይና ፍጹም ኪራይ ( differential and absolute ) ተብለው ። ሌኒን እንዳሳየው ፤ የእነዚህ ሁለት ዓይነት ኪራዮች መኖር ከሞኖፖሊ የሁለትነት ጸባይ ጋር የተያያዘ ነው ፡— ለልዩነት ኪራይ ምንጭ ከሆነው ከመሬት ሞኖፖሊ እንደምጣኔ— ሀብታዊ ክንዋኔ ነባሪ በመሆንና ለፍጹም ኪራይ መነሻ ከሆነው የመሬት የግል ባለቤትነት ሞኖፖሊ ማለት ነው ።

የልዩነት ኪራይ

በኢንዱስትሪ ውስጥ የአንድ ሸቀጥ ዕሴትና የምርት ተመን የሚወስኑት በምርት የአማካይ ሁኔታዎች ነው ። በእርሻ ውስጥ ፤ የእርሻ ውጤቶች የምርት ተመን የሚወስነው በምርት አማካይ ሁኔታዎች ሳይሆን ፤ ግን በጠፍ መሬት ምርት አማካይ ሁኔታዎች ነው ። የመሬት ስፋት የተወሰነ በመሆኑ ፤ በዘፈቀደም ለማስፋት ስለማይቻል ፤ ጥሩውን መሬት የያዙት ጢሰኞች ወይም መካከለኛውን የተከራዩት በጠፍ መሬት ላይ ካሉት ይልቅ በተሻለ ሁኔታ ይገኛሉ ። እነኚህ ሞኖፖሊ ጢሰኞች እንደምጣኔ — ሀብታዊ ክንዋኔ ሆኖ የተለያዩ ማሳ ስላላቸው በገቢ በኩል ልዩነት እንዲመጣ መንገድ ይከፍታሉ ። የልዩነት ኪራይ ፤ በተሻለ ሁኔታ ውስጥ በሚሠሩት እርሻዎች ከሚገኘው አማካይ ትርፍ የበለጠና በላይ የሆነ ትርፍርፍ ትርፍ ነው ። ግን መሬቱ እራሱ አይደለም የኪራይ ምንጭ የሚሆነው ። በጥሩ መሬት ላይ የዋለ ጉልበት ይበልጥ ምርታማ በመሆኑና ተጨማሪ ትርፍ ስለሚሰጥ ነው ።

የልዩነት ኪራይ ለማግኘት የሚያስችሉ ሶስት ምክንያቶች አሉ ። እነዚህም ፤ 1/ በተለያዩ ማሳዎች ውስጥ የአፈሩ ለምነት መበላለጥ 2) ከገበያ አካባቢ አንጻር የማሳዎች ርቀት 3/ በመሬቱ ላይ ከዋለው ተጨማሪ ወረት የሚገኘው የምርት ልዩነት ናቸው ።

ከመሬት ለምነትና አቀማመጥ ልዩነት የተያያዘው የልዩነት ኪራይ በማርከስ አጠራር የልዩነት ኪራይ ይባላል ። እስቲ ይህን እንመርመር ።

ለምሳሌ በለምነት የተለያዩ ግን በስፋት እኩል የሆኑ ሶስት ማሳዎችን እንውሰድ። በእያንዳንዱ ማሳ ጢሰኛው ሠራተኞችን ለመቅጠር ፤ ዘርና ማሺን ለመግዛት ፤ ወዘተ. . . 100 ብር — ያጠፋል ። ግን ማሳዎቹ በለምነት ስለሚለያዩ የሚመረተው እህል አንድ አይሆንም ፤ ከማሳ ቁ. 1—10 ኩንታል ፤ ከማሳ ቁ.2 — 15 ኩንታል እና ከማሳ ቁጥር 3 — 20 ኩንታል ሊገኝ ይችል ይሆናል ።

አማካይ የትርፍ መጠን (ደረጃ) 20 ፐርሰንት ነው ብለን እናስብ ። በዚህ ሁኔታ የሁሉም እህል የምርት ተመን (የምርት ዋጋና አማካይ ትርፍ) በእያን ዳንዱ ማሳ 120 ብር ይሆናል ። ግን የአንድ ኩይንታል እህል ተመን ምን ያህል ይሆናል ? በማሳ ቁጥር 1 የአንድ ኩይንታል እህል ምርት 12 ብር (120 : 10) ሲአወጣ በማሳ ቁጥር 2 8 ብር (120 : 15) እና በማሳ ቁጥር 3—6 ብር (120 : 20) ሆኗል ።

ግን በገበያ ላይ የእህል ተመን የሚወሰነው በጠፉ መሬት የተመን ደረጃ ማለትም ኩይንታሉን በ12 ብር ሂሣብ ነው ። ተመኑ በመካከለኛው ማሳ ደረጃ 8 ብር ቢወሰን በጠፉ ማሳ ላይ ያለው ካፒታሊስት ጢሰኛ ገበሬ የሚአገኘው 80 ብር ብቻ (10+8) ብር ነው ፤ ማለትም ለአወጣው ወጭ ምላሽ አይኖረውም ፤ ትርፍማ ፍጹም የለውም ። ይህም ማለት በጠፉ መሬት ላይ ያሉ ጢሰኛ ገበሬዎች እርሻ እርግፍ አድርገው ይተዋሉ ነው ። ወደመካከለኛው ወይም ወደተሻለው መሬት ሊዛወሩ አይችሉም በሌላ የካፒታሊስት ጢሰኛ ገበሬዎች ተይዘባቸዋልና ። በጠፍ መሬቶች ላይ ምርትን ማቋረጥ በጠቅላላው የእህል ምርት ላይ ቀውስ ያመጣል ። የእህል ተመን ማደግ ይጀምራል እናም በኩይንታል 12 ብር ሲደርስ በጠፉ መሬት ላይ እንኳን ማረስ እንደገና ጠቃሚ ይሆናል ።

ስለዚህ የማሳ ቁጥር 1 ጢሰኛ ምርቱን በ120 ብር ፤ የማሳ ቁጥር 2 በ180 ብር እና የማሳ ቁጥር 3 ደግሞ በ240 ብር ይሸጣሉ ። ከምርት ተመን በላይ ያለው ትርፍርፍ—ለማሳ ቁጥር 2—60 ብር ፤ እና እና ለማሳ ቁጥር 3—128 ብር የልዩነት ኪራዩን ይይዛሉ ።

የበለጠ ለማብራራት ይህን ምሳሌ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ እናቅርብ ፤



| ማሳዎች | ወጭ የሆነ ወረት $ | አማካይ ትርፍ $ | ምርት በኩንታል | የምርት የተናጠል ተመን $ | | የምርት የህብረተሰብ ተመን $ | | የልዩነት ኪራይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ጠቅላለ ምርት | 1 ኩንታል | 1 ኩንታል | ጠቅላላ ምርት | |
| 1 | 100 | 20 | 10 | 120 | 12 | 12 | 120 | — |
| 2 | 100 | 20 | 15 | 120 | 8 | 12 | 180 | 60 |
| 3 | 100 | 20 | 20 | 120 | 6 | 12 | 240 | 120 |

ከዚህ የምንወስደው የልዩነት ኪራይ ከአማካይ ትርፍ የበለጠና በላይ ትርፍርፍ መሆኑን ነው ። የተገኘው በእርሻ ሠራተኞች ጉልበት ነው ። የሠራተኞች ጉልበት (ሥራ) በለምነት በሚለያዩ ማሳዎች ላይ በሚውልበት ጊዜ በአምራችነቱ ይለያያል ፤ እናም በዚህ ምክንያት የተለያዩ የትርፍ ውጤት መጠን ያመርታሉ ።

የልዩነት ኪራይ I አመጣጡ ከእርሻዎች አቀማመጥም ጋር የተያያዘ ነው ። ከትላልቅ ከተሞች ፤ ወንዞች ፤ ከባሕር ጠረፎችና ከባቡር ሐዲድ ያለው ርቀት እዚህ ላይ ያቃውሳል ። ከገበያ ማዕከሎች የቀረቡ እርሻዎች በርቀት ያለውን ምርት ለማምጣት የሚወስደውን ጉልበትና ትራንስፖርት ወጭ ይቀንሳሉ ፤ ምርቶቻቸውን ከሩቅ ከመጡት ጋር በአንድ ዓይነት ተመን በመሸጥ ተጨማሪ ትርፍ እንዲአገኙ ይሆናሉ ።

በተጨማሪም የልዩነት ኪራይ የሚመነጨው ተጨማሪ ወረት ባለው ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ለመጠቀም ፤ መሬት ለማሻሻል ፤ የተሻሻሉ መሣሪያዎች ፤ ወዘተ . . . በመሬቱ ላይ ሲውል ነው ። ከተጠናከረና ከተሻሻለ እርሻ የሚመጣው ተጨማሪ ትርፍ የኪራይ ልዩነት II ይባላል ።

የልዩነት ኪራዮች I እና II በጢሰኛ ገበሬውና በመሬት ከበርቴው ይከፋፈላሉ ፤ እናም እያንዳንዱ የሚወስደው ድርሻ ጥገኛ የሚሆነው በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ነው ። እንደምጣኔ — ሀብታዊ ክንዋኔ ነባሪ በመሆን የመሬት ተጠያቂነትና ሊገኝ የሚችለው መሬት መጠን መሆኑ ነው ። የመሬት ተጠያቂነት ከፍ ሲል ኪራዩም ይንራል ፤ እንዲህ እያለ ይለዋወጣል ። እነኚህ ሁኔታዎች የሚንጸባረቁት በመሬት ኮንትራት ስምምነት ላይ ነው ፤ ኮንትራት በሚወሰድበት ጊዜ እንደደንብ ሆኖ የመሬት ከበርቴው ባለፈው ጊዜ ከማሳው ላይ ያገኘውን የልዩነት ኪራይ የሚጨምር ኪራይ ይወስናል ።

ስለሆነም ፤ የልዩነት ኪራይ የሚወሰደው በመሬት ከበርቴው ነው ። ግን ወደፊት ምናልባት ፤ ካፒታሊስቱ ጢሰኛ ገበሬ በኪራዩ ከተሸፈነው በላይ የሆነ የልዩነት ኪራይ ቢአገኝ ፤ በምንም መንገድ ይሁን አዲስ የኮንትራት ስምምነት ካልተፈረመ በቀር ለጢሰኛው ገበሬ ነው የሚገባው ።

ከልዩነት ኪራዮች I እና II የመሬት ከበርቴው በተጨማሪ ፍጹም ኪራይም ይወስዳል ።

ፍጹም ኪራይ።

የመሬት ተመን

በካፒታሊዝም ውስጥ መሬት በግለሰብ ባለንብረቶች የግል ንብረትነት ነው የተያዘው ። ስለዚህ ወረት በእርሻ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ፤ በመጀመሪያ የመሬት ከበርቴው ፈቃድ መገኘት ይኖርበታል ። የመሬት የግል ባለቤትነት ሞኖፖሊ የወረትን ከኢንዱስትሪ ወደ እርሻ ያለምንም እንከን መፍሰስ ይከላከላል ። በዚህ ምክንያት የወረት አካላዊ ይዘት ከኢንዱስትሪ ይልቅ በእርሻ ዝቅተኛ ነው ። ይህም በእርሻ ላይ የዋለ አንድ ዓይነት ወረት ከኢንዱስትሪው ይበልጥ ትርፍ ዕሴት ያስገኛል ማለት ይሆናል ። የወረት አካላዊ ይዘት ከኢንዱስትሪው ወደ እርሻ በነጻ መፍሰስ ቢኖር ኖሮ ፤ በዝቅተኛ የወረት አካላዊ ይዘት ምክንያት በእርሻ ውስጥ የተፈጠረው ተጨማሪ ትርፍ ዕሴት በኢንዱስትሪና በእርሻ

የልዩነት ኪራይ

በኢንዱስትሪ ውስጥ የአንድ ሸቀጥ ዕሴትና የምርት ተመን የሚወሰኑት በምርት የአማካይ ሁኔታዎች ነው ። በእርሻ ውስጥ ፤ የእርሻ ውጤቶች የምርት ተመን የሚወሰነው በምርት አማካይ ሁኔታዎች ሳይሆን ፤ ግን በጠፍ መሬት ምርት አማካይ ሁኔታዎች ነው ። የመሬት ስፋት የተወሰነ በመሆኑ ፤ በዘፈቀደም ለማስፋት ስለማይቻል ፤ ጥሩውን መሬት የያዙት ጪሰኞች ወይም መካከለኛውን የተከራዩት በጠፍ መሬት ላይ ካሉት ይልቅ በተሻለ ሁኔታ ይገኛሉ ። እነኝህ ሞኖፖሊ ጪሰኞች እንደምጣኔ — ሀብታዊ ክንዋኔ ሆና የተለያዩ ማሳ ስላላቸው በገቢ በኩል ልዩነት እንዲመጣ መንገድ ይከፍታሉ ። የልዩነት ኪራይ ፤ በተሻለ ሁኔታ ውስጥ በሚሠሩት እርሻዎች ከሚገኘው አማካይ ትርፍ የበለጠና በላይ የሆነ ትርፍርፍ ትርፍ ነው ። ግን መሬቱ እራሱ አይደለም የኪራይ ምንጭ የሚሆነው ። በጥሩ መሬት ላይ የዋለ ጉልበት ይበልጥ ምርታማ በመሆኑና ተጨማሪ ትርፍ ስለሚሰጥ ነው ።

የልዩነት ኪራይ ለማግኘት የሚአስችሉ ሶስት ምክንያቶች አሉ ።እነዚህም ፤ 1/በተለያዩ ማሳዎች ውስጥ የአፈሩ ለምነት መበላለጥ 2) ከገበያ አካባቢ አንጻር የማሳዎች ርቀት 3/ በመሬቱ ላይ ከዋለው ተጨማሪ ወረት የሚገኘው የምርት ልዩነት ናቸው ።

ከመሬት ለምነትና አቀማመጥ ልዩነት የተያያዘው የልዩነት ኪራይ በማርከስ አጠራር የልዩነት ኪራይ ይባላል ። እስቲ ይህን እንመርመር ።

ለምሣሌ በለምነት የተለያዩ ግን በስፋት እኩል የሆኑ ሶስት ማሳዎችን እንውሰድ። በእያንዳንዱ ማሳ ጪሰኛው ሠራተኞችን ለመቅጠር ፤ ዘርና ማሺን ለመግዛት ፤ ወዘተ. . . 100 ብር — ያጠፋል ። ግን ማሳዎቹ በለምነት ስለሚለያዩ የሚመረተው እህል አንድ አይሆንም ፤ ከማሳ ቁ. 1—10 ኩንታል ፤ ከማሳ ቁ.2 — 15 ኩንታል እና ከማሳ ቁጥር 3 — 20 ኩንታል ሊገኝ ይችል ይሆናል ።

አማካይ የትርፍ መጠን (ደረጃ) 20 ፐርሰንት ነው ብለን እናስብ ። በዚህ ሁኔታ የሁሉም እህል የምርት ተመን (የምርት ዋጋና አማካይ ትርፍ) በእያን ዳንዱ ማሳ 120 ብር ይሆናል ። ግን የአንድ ኩይንታል እህል ተመን ምን ያህል ይሆናል ? በማሳ ቁጥር 1 የአንድ ኩይንታል እህል ምርት 12 ብር (120 : 10) ሲአወጣ በማሳ ቁጥር 2 8 ብር (120 : 15) እና በማሳ ቁጥር 3—6 ብር (120 : 20) ሆኗል ።

ግን በገበያ ላይ የእህል ተመን የሚወሰነው በጠፉ መሬት የተመን ደረጃ ማለትም ኩይንታሉን በ12 ብር ሂሣብ ነው ። ተመኑ በመካከለኛው ማሳ ደረጃ 8 ብር ቢወሰን በጠፉ ማሳ ላይ ያለው ካፒታሊስት ጪሰኛ ገበሬ የሚአገኘው 80 ብር ብቻ (10+8) ብር ነው ፤ ማለትም ለአወጣው ወጭ ምላሽ አይኖረውም ፤ ትርፍማ ፍጹም የለውም ። ይህም ማለት በጠፉ መሬት ላይ ያሉ ጪሰኛ ገበሬዎች እርሻ እርግፍ አድርገው ይተዋሉ ነው ። ወደመካከለኛው ወይም ወደተሻለው መሬት ሊዛወሩ አይችሉም በሌላ የካፒታሊስት ጪሰኛ ገበሬዎች ተይዘባቸዋልና ። በጠፍ መሬቶች ላይ ምርትን ማቋረጥ በጠቅላላው የእህል ምርት ላይ ቀውስ ያመጣል ። የእህል ተመን ማደግ ይጀምራል እናም በኩይንታል 12 ብር ሲደርስ በጠፉ መሬት ላይ እንኳን ማረስ እንደገና ጠቃሚ ይሆናል ።

ስለዚህ የማሳ ቁጥር 1 ጪሰኛ ምርቱን በ120 ብር ፤ የማሳ ቁጥር 2 በ180 ብር እና የማሳ ቁጥር 3 ደግሞ በ240 ብር ይሸጣሉ ። ከምርት ተመን በላይ ያለው ትርፍርፍ — ለማሳ ቁጥር 2 — 60 ብር ፤ እና እና ለማሳ ቁጥር 3 — 128 ብር የልዩነት ኪራዩን ይይዛሉ ።

የበለጠ ለማብራራት ይህን ምሳሌ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ እናቅርብ ፤

| ማሳዎች | ወጭ የሆነ ወረት $ | አማካይ ትርፍ $ | ምርት በኩንታል | የምርት የተናጠል ተመን $ | | የምርት የህብረተሰብ ተመን $ | | የልዩነት ኪራይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ጠቅላለ ምርት | 1 ኩንታል | 1 ኩንታል | ጠቅላላ ምርት | |
| 1 | 100 | 20 | 10 | 120 | 12 | 12 | 120 | — |
| 2 | 100 | 20 | 15 | 120 | 8 | 12 | 180 | 60 |
| 3 | 100 | 20 | 20 | 120 | 6 | 12 | 240 | 120 |

ከዚህ የምንወስደው የልዩነት ኪራይ ከአማካይ ትርፍ የበለጠና በላይ ትርፍርፍ መሆኑን ነው ። የተገኘው በእርሻ ሠራተኞች ጉልበት ነው ። የሠራተኞች ጉልበት (ሥራ) በለምነት በሚለያዩ ማሳዎች ላይ በሚውልበት ጊዜ በአምራችነቱ ይለያያል ፤ እናም በዚህ ምክንያት የተለያዩ የትርፍ ውጤት መጠን ያመርታሉ ።

የልዩነት ኪራይ I አመጣጡ ከእርሻዎች አቀማመጥም ጋር የተያያዘ ነው ። ከትላልቅ ከተሞች ፤ ወንዞች ፤ ከባሕር ጠረፎችና ከባቡር ሐዲድ ያለው ርቀት እዚህ ላይ ያታውሳል ። ከገበያ ማዕከሎች የቀረቡ እርሻዎች በርቀት ያለውን ምርት ለማምጣት የሚወስደውን ጉልበትና ትራንስፖርት ወጭ ይቀንሳሉ ፤ ምርቶቻቸውን ከሩቅ ከመጡት ጋር በአንድ ዓይነት ተመን በመሸጥ ተጨማሪ ትርፍ እንዲአገኙ ይሆናሉ ።

በተጨማሪም የልዩነት ኪራይ የሚመነጨው ተጨማሪ ወረት ባለው ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ለመጠቀም ፤ መሬት ለማሻሻል ፤ የተሻሻሉ መሣሪያዎች ፤ ወዘተ . . . በመሬቱ ላይ ሲውል ነው ። ከተጠናከረና ከተሻሻለ እርሻ የሚመጣው ተጨማሪ ትርፍ የኪራይ ልዩነት II ይባላል ።

የልዩነት ኪራዮች I እና II በጪሰኛ ገበሬውና በመሬት ከበርቴው ይከፋፈላሉ ፤ እናም እያንዳንዱ የሚወስደው ድርሻ ጥገኛ የሚሆነው በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ነው ። እንደምጣኔ — ሀብታዊ ክንዋኔ ነባሪ በመሆን የመሬት ተጠያቂነትና ሊገኝ የሚችለው መሬት መጠን መሆኑ ነው ። የመሬት ተጠያቂነት ከፍ ሲል ኪራዩም ይንራል ፤ እንዲህ እያለ ይለዋወጣል ። እነኝህ ሁኔታዎች የሚንጸባረቁት በመሬት ኮንትራት ስምምነት ላይ ነው ፤ ኮንትራት በሚወሰድበት ጊዜ እንደደንብ ሆኖ የመሬት ከበርቴው ባለፈው ጊዜ ከማሳው ላይ ያገኘውን የልዩነት ኪራይ የሚጨምር ኪራይ ይወስናል ።

ስለሆነም ፤ የልዩነት ኪራይ የሚወሰደው በመሬት ከበርቴው ነው ። ግን ወደፊት ምናልባት ፤ ካፒታሊስቱ ጪሰኛ ገበሬ በኪራዩ ከተሸፈነው በላይ የሆነ የልዩነት ኪራይ ቢአገኝ ፤ በምንም መንገድ ይሁን አዲስ የኮንትራት ስምምነት ካልተፈረመ በቀር ለጪሰኛው ገበሬ ነው የሚገባው ።

ከልዩነት ኪራዮች I እና II የመሬት ከበርቴው በተጨማሪ ፍጹም ኪራይም ይወስዳል ።

ፍጹም ኪራይ።

የመሬት ተመን

በካፒታሊዝም ውስጥ መሬት በግለሰብ ባለንብረቶች የግል ንብረትነት ነው የተያዘው ። ስለዚህ ወረት በእርሻ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ፤ በመጀመሪያ የመሬት ከበርቴው ፈቃድ መገኘት ይኖርበታል ። የመሬት የግል ባለቤትነት ሞኖፖሊ የወረትን ከኢንዱስትሪ ወደ እርሻ ያለምንም እንከን መፍሰስ ይከላከላል ። በዚህ ምክንያት የወረት አካላዊ ይዘት ከኢንዱስትሪ ይልቅ በእርሻ ዝቅተኛ ነው ። ይህም በእርሻ ላይ የዋለ አንድ ዓይነት ወረት ከኢንዱስትሪው ይበልጥ ትርፍ ዕሴት ያስገኛል ማለት ይሆናል ። የወረት አካላዊ ይዘት ከኢንዱስትሪው ወደ እርሻ በነጻ መፍሰስ ቢኖር ኖሮ ፤ በዝቅተኛ የወረት አካላዊ ይዘት በኢንዱስትሪና በእርሻ ምክንያት በእርሻ ውስጥ የተፈጠረው ተጨማሪ ትርፍ ዕሴት

ሊከፋፈል በቻለ ነበር ። ግን የመሬት የግል ባለቤትነት በካፒታሊስቶች መካከል እንደገና እንዳይከፋፈል ያግዳሉ ። የመሬት ከበርቴዎች ይህን ተጨማሪ ትርፍ ዕሴት የሚወስዱት በእርሻ ላይ ወረቱን ከሚአጠፋው ካፒታሊስት ነው ።

ካፒታሊስቱ ለመሬት ከበርቴው የመሬት ጥቅም ሳይከፍል የእርሻ ምርትን ሊአ ቀናጅ (ሊአጠናቅር) አይችልም ። የመሬት ከበርቴው በመሬት የግል ባለቤትነቱ ባለው መብት ምክንያት የሚቀበለው ክፍያ ፍጹም ኪራይ ይባላል ።

ፍጹም ኪራይ እንዴት እንደሚመሠረት ለማወቅ የሚቀጥለውን ምሣሌ እንመርምር ። በኢንዱስትሪ ውስጥ የወረት አካላዊ ይዘት 4፥1 ቢሆንና ጠቅላላው ወረት 80ቀ ተ 20ተ ቢሆን ፤ የ100 ፐርሰንት ትርፍ ዕሴት ደረጃ ቢይዝ ፤ የ$ 20 ትርፍ ዕሴት ይሠራል ማለት ነው ። የጠቅላላው ምርት ዕሴት $ 120 ነው ። ምናልባትም 60ቀ + 40ተ ፤ማለትም 1.5፥ 1 በመሆን በእርሻ ውስጥ ያለው የወረት አካላዊ ይዘት ከኢንዱስትሪው ያነስ ሆነ ። በ100 ፐርሰንት የትርፍ ዕሴት ደረጃ $ 40 ትርፍ ዕሴት ይፈጠርና የጠቅላላው የእርሻ ምርት ዕሴት $ 140 ይሆናል ። ካፒታሊስቱ ጢሰኛ ገበሬ እንደኢንዱስትሪያሊስቱ ሁሉ $ 20 የትርፍ አማካይ ይቀበላል ። ስለዚህ የእርሻ ውጤቱ የእርሻ ተመን (የምርት ዋጋ + አማካይ ትርፍ) $ 120 (100 + 20 )ሲሆን ፤ የምርቱ እሴት ግን (የሚሸጥበት) $ 140 ነው ። በእርሻ ውጤቱ የምርት ተመንና ዕሴቱ መካከል ያለው ልዩነት (በምሣሌአችን 140 — 120 = 20) በመሬት ባለቤቱ የሚወሰደውን ፍጹም ኪራይ ያስገኛል ። እንግዲህ ፍጹም ኪራይ ፤ ከሕብረተሰብ የምርት ተመን በላይ የእርሻ ውጤት ዕሴት ትርፍርፍ መሆኑ ነው ።

ስለሆነም የመሬት የግል ባለቤትነት ሞኖፖሊ አቀማመጡንና ለምነቱን ሳይመለከት ለእያንዳንዱ ማሳ ለሚከፈለው የፍጹም ኪራይ ሕልውና ኃላፊ ምክንያት ነው ።

መሬት የተፈጥሮ ስጦታ ነው እናም ዕሴት የለውም ፤ግን በካፒታሊዝም ውስጥ መሬት ይሸጣል ፤ይገዛል ፤ ማለትም ፤ ሸቀጥ ይሆናል ። ታዲያ ምኑ ነው መሬት በሚሸጥበት ጊዜ ተመኑን የሚወስነው ?

የአንድ ማሣ ተመን ጥገኝነቱ በሁለት ምክንያቶች ላይ ነው :—1) በዓመት በሚ አስገባው ገቢ (ኪራይ) እና 2/በብድር ላይ ያለው የወለድ ደረጃ ። የመሬት ባለቤቱ በዓመት $ 10,000 ኪራይ ቢቀበል ፤ መሬቱን የሚሸጠው ገንዘቡ በባንክ ቢቀመጥ በዓመት $ 10,000 የሚአስገኝ ሆኖ በሚአገኘው የገንዘብ ድምር ነው ። ባንኩ ለተቀማጭ ገንዘብ 4 ፐርሰንት ይከፍላል ብለን እናስብ ። የመሬት ባለቤቱ መሬቱን የሚሸጠው $ 250,000 ነው ፤ምክንያቱም ይህ የገንዘብ መጠን ነው በባንክ ቢቀመጥ በ4 ፐርሰንት የ$ 10,000 ገቢ የሚአስገኝለት ። ስለሆነም ፤የመሬት ተመን ካፒታላዊ የሆነ ኪራይ ነው ፤ማለትም ፤በአራጣ መልክ ገቢ የሚአስገኝ ወደ ወረት የተለወጠ ኪራይ ። ካፒታሊዝም ሲዳብር ፤ከኪራይ መጨመር እና በብድር ላይ ካለው የአራጣ መጠን መቀነስ ጋር በመያያዝ የመሬት ተመን ይጨምራል ።

በእርሻ ውስጥ የካፒታሊስት ዕድገት ልዩ ገጾች

በእርሻ ውስጥ ካፒታሊዝም በኢንዱስትሪ ውስጥ ባሉት ምጣኔ ሀብታዊ ሕጎች መሠረት ያድጋል ።

እንዲሁም ካፒታሊዝም በእርሻ ውስጥ ተጨባጭ በሆኑ ታሪካዊ ሁኔታዎች ላይ ጥገኛ በመሆን በተለያዩ መንገዶች ይዳብራል ። ይበልጥ የሚታወቁት ሁለት መንገዶች ነበሩ ።

የመጀመሪያው የመልከኛነት ኩዳድ ለብዙ ጊዜ መቆየትና የቀስ በቀስ ለውጥ ምክንያት ወደካፒታሊስት እርሻ መሸጋገር ነበር ። ለምሣሌ—ካፒታሊዝም በዚህ መንገድ ያደገው በጀርመን ፤በሩሲያ እና በኢጣልያ ነው ።

ሁለተኛው ፤ በቡርዧዊ አብዮት አማካኝነት የመልከኛ ኩዳድ መወገድ ፤የመሬት መወረስና ለገበሬዎች መሸጥ ነው ። በዚህ መንገድ ነው ካፒታሊዝም በፈረንሳይ



እርሻ ውስጥ የዳበረው ። ለምሣሌ በሌሎች አገሮች ፤ዩናይትድ ስቴትስ የካፒታሊስት ምርት በፍጥነት ባደገበት እርሻዎች ዳብረዋል ።

ግን ካፒታሊዝም በእርሻ ውስጥ በምንም መንገድ ይደግ ፤ ሁልጊዜም የመሬት ሀብትን በጥቂት ትላልቅ ቡርዧዎች እጅ የማድለብ ሂደት ነበር ። የአነስተኛ ገበሬ ባለቤትነትና የመልከኛ መሬት ከበርቴ ባለቤትነት ለቡርዧ ባለቤትነት መንገድ ጠረገ ። ለምሣሌ በዩናይትድ ስቴትስ በ1954 ዓ.ም. ከእርሻዎቹ 73.4 በመቶ ከአጠቃላዩ መሬት 19.6 በመቶ ሲይዙ ፤ከእርሻዎቹ 26.6 በመቶ ግን ከመሬቱ 80.4 በመቶ ይይዛሉ ፤ ከዚህ ውስጥ ትላልቅ የእርሻ ድርጅቶች (ከጠቅላላ እርሻዎች 2.7 በመቶ) የመሬቱን 45.9 በመቶ ያዛሉ ።

ካፒታሊዝም በእርሻ ውስጥ ሲዳብር ምርት ይበልጥ ይደልባል ። ይህ ለትናንሽ ገበሬ እርሻዎች በግዙፍ እርሻ ምርቶች እንዲከበቡ ያደርጋል ፤ምክንያቱም የኋለኛው በመጀመሪያው ላይ የተለያዩ ወሳኝ ጥቅሞች ስለሚኖሩት ነው ። ግዙፍ ምርት ማለት እስከተቻለ ድረስ በሰፊው የእርሻ ማሺኖች በተግባር ላይ መዋል ነው ። በግዙፍ እርሻዎች የጉልበት አምራችነት ከፍተኛ ነው ። የግዙፍ ምርት ዓይነተኛ ጥቅም በአንድ ወይምበተለዩ ቅርንጫፍ ውስጥ—መሬት በማረስ ወይም በከብት ርባታ—ከፍተኛ የንግድ ገበያ ማስገኘቱ ላይ ነው ። አነስተኛ ምርት ሊጠፉ የሚችለው ከግዙፍ ምርት ጋር በሚአደርገው ውድድር ይሆናል ። ስለሆነም ፤ በ1948 እና በ1958 ዓ.ም. መካከል ከአንድ ሚሊዮን ትናንሽ ገበሬዎች በላይ በዩናይትድ ስቴትስ ጠፍተዋል ።

በኢንዱስትሪ ውስጥ ሁልጊዜም ግዙፍ ምርት በአነስተኛ ምርቶች ላይ መስፈኑ ሊወገድ የማይችል ዕውነት ነው ። የካፒታሊዝም ተሟጋቾች እንኳን ይህን መቀበል አለባቸው ። ግን ስለ እርሻ — ሲገልጹ እንዲሁ የገጠር መታደል ሁኔታ አድርገው ሲሆን ፤ «የትናንሽ ገበሬን አይጠፌነት» የውሸት ፍልስፍና ያስፋፋሉ ። እንደእውነቱ ከሆነ ትናንሽ እርሻ በምንም መንገድ ነዋሪ አይሆንም ፤ግን መጥፋቱን ብቻ ይቀጥላል ፤ ምክንያቱም ሊታመን በማይችል ድህነትና መታረዝ ምክንያት ገበሬውና ቤተሰቡ ከመጠን በላይ ስለሚሰሩ ነው ።

ካፒታሊዝም በገጠርና በከተማ መካከል ያለውን ቅራኔ ጥልቀት ይሰጠዋል ያባብሰዋል ። የዚህ ቅራኔ ምጣኔ — ሀብታዊ መሠረቱ በከተማው ቡርዧ የገጠሩ ገበሬ መበዝበዝ ፤ በኢንዱስትሪ ፤ በንግድ ፤ በዱቤና በግብር ሥርዓት የእድገት ሂደት ምክንያት የብዙኃኑ ገጠሬ በድህነት መውደቅ ነው ። በምጣኔ — ሀብታዊ ፤ በፖለቲካዊና በባሕላዊ መንገድ ገጠሩ ከከተማው ወደኋላ ይጐተታል ።

ከባድ የኑሮ ሁኔታቸው ገበሬዎች የካፒታሊስትን ሥርዓት ጠርገው የመጣልን ሁኔታ እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል ። በዚህም ምክንያት የብዙኃኑ ገበሬ መሠረታዊ ዝንባሌ ከወዝ — አደሮቹ ዝንባሌ ጋር ይጣማል ። እዚህ ላይ ነው ካፒታሊዝምን ስመዋጋት ባላቸው የጋራ ዝንባሌ በወዝ አደሩና በሠራተኛው ገበሬ መካከል ያለውን የምጣኔ — ሀብታዊ መሠረት ሕብረት የምናገኘው ።

የመሬት ኪራይና የመሬት ውርስ

የመሬት የግል ባለቤትነት ለእርሻ ከኢንዱስትሪ ወደኋላ መቅረት ዋናው ምክንያት ነው ።

ከዚህ ቀደም እንደታተተው ፤የመሬት የግል ባለቤትነት የወረት ከኢንዱስትሪ ወደ እርሻ በነጻ ሂደት መፍሰስን ይጐትታል ። ይህም ማለት ካፒታሊስቱ ጢሰኛ ፤ ገበሬ በእርሻ ላይ (ማዳበሪያ ፤ የመስኖ ተቋሞች ፤ ወዘተ . . .) ተጨማሪ መዋዕለ— ንዋይ ለማዋል ፈቃደኛ አይሆንም ፤ ምክንያቱም ከመዋዕለ ንዋይ ሁሉም ጥቅም ፤ አንዴ የኮንትራት ጊዜው ካለፈ ፤ ወደ መሬት ከበርቴው ነው የሚሄደው ። የመሬት የግል ባለቤትነት በመሬት ከበርቴዎች (ባለቤቶች) በደም መጣጮነት ለሚሰበሰበው የፍጹም ኪራይ ምንጭ ነው ። ይህ የሚአመለክተው የመሬት የግል ባለቤትነት ለካፒታሊዝም የምርት ኃይሎች ዕድገት እንቅፋት መሆኑን ነው።ስለሆነም የመሬትን የግል

ባለቤትነት ጠርጎ መጣል እጅግ አስፈላጊነት ይኖረዋል ። ይህንም ለማምጣት አንዱ መንገድ መሬትን መውረስ ነው ፤ ማለትም መሬትን ወደ መንግሥት ንብረትነት ማዞር ነው ።

በካፒታሊዝም የቀድሞ ዘመን አንዳንድ የቡርዧ አፈቀላጤዎች የመሬትን መወረስ ያስተጋቡ ነበር ። የመሬትን የግል ባለቤትነት ማስወገድና (በዚያን ወቅት መሬት በቡርዧዋው መንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲውል አሳሰቡ ። በካፒታሊስት ሁኔታ እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ ምን ዓይነት ውጤት ያመጣ ነበር ? አንዴ መንግስት መሬትን በቁጥጥሩ ስር ቢአደርግ ኑሮ የፍጹም ኪራይ ሕልውና ይቆም ነበር ፤ ምክንያቱም ምንጩ የመሬት የግል ባለቤትነት ነውና ።

በዚህ ምክንያት የመሬት በቡርዧዋው መንግስት መወረስ ቡርዧዎች ሊአካሄዱት ያልፈለጉትን ካፒታሊዝምንና የምርት ኃይሎችን ዕድገት እንዲቀጥል ያደርጋል። በመጀመሪያ የመሬት የግል ባለቤትነት መወገድ በአጠቃላይ የግል ንብረትን (የካፒታሊስቱን በመጨመር) መሠረት ሁሉ ያናጋል ። ሁለተኛ ፤ ካፒታሊዝም ሲአድግ ቡርዧዎች እራሳቸው መሬት መያዝ ጀመሩ ፤ ስለዚህ የቡርዧዋውና የመሬት ከበርቴው ዝንባሌ እንደድር የተታታ ይሆናል ።

በዳበረ ካፒታሊዝም ዘመን የመሬት የግል ንብረትነት ሊአከትም የሚችለው በአጠቃላይ የግልንብረትንነትን መወገድ በሚዋጋው መደብ ብቻ ነው ። ያም መደብ አብዮታዊው ወዝ አደር ነው ። ግን የመሬት ወዛደራዊ ውርስ ለካፒታሊዝም ዕድገት አይደለም መንገድ የሚጠርገው ፤ እንዲያውም የካፒታሊዝም ተጠርጎ መጣል የመጀመሪያ ደረጃ ነው ፤

በሶቪየት ሕብረት የመሬት መወረስ በአንድ በትር የመሬት የግል ባለቤትነትንና ፍጹም ኪራይን አጠፋ ። ይህም እርምጃ ለሶሻሊስት ግዙፍ እርሻዎች ዓይነተኛ ፈጣን ዕድገት ከሆኑት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ነው ።

* * * *

አሁን በወረት መሽከርከር ምክንያት በትርፍ ዕሴት የተገኙት የተለያዩ መልኮችን መርምረናል ። የሁሉም ቡርዧ ቡድኖችና የመሬት ከበርቴዎች ገቢ ዋና ምንጭ ትርፍ ዕሴትን የሚፈጥረው የተቀጠሩት ሠራተኞች ጉልበት መሆኑን ግልጽ አድርገናል ። በትርፍ ዕሴት የተገኙት ልዩ መልኮች (ገጾች) በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ በመደቦች መካከል ያለውን መሠረታዊ ቅራኔ ይደብቃሉ (ይሸፍናሉ) በቡርዧዋውና በወዝ አደሩ መካከል ያለውን ።

ማርክስ በትርፍ ዕሴት ውስጥ የገባውን ሂደት ፤ የካፒታልን (የወረትን ) መድለብና የወዛደሩን መራቆት ፤ እንዲሁም የትርፍ ዕሴትን መከፋፈል ሲተነትን አመቺ በሚሆንበት አቅጣጫ ሁሉ ፤ በወዝአደሩና በቡርዧዋው መካከል ያለውን መሠረታዊ የመደብ ቅራኔ እያጤነ ነበር ። በመጨረሻም የሠራተኛው መደብ ታሪካዊ ተግባር ይህን ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ መፍትሔ መስጠት መሆኑን በማስገንዘብ ደምድሟል፤ ማለትም የካፒታሊዝምን ሥልተ—ምርት ማክተምና ለምንጊዜም ብዝበዛን ጠርጎ መጣል ።



ምዕራፍ ፯

## የሕብረተሰብ ወረት ዕርባታና የምጣኔ—ሀብት ቀውስ

የካፒታሊስት ምጣኔ ሀብት ብዙ የተለያዩ ነጻ ድርጅቶችን የያዘ ነው ። እያንዳንዱ ካፒታሊስት በተወሰነ ጊዜ ከፍተኛ ትርፍ ሊአስገኝለት የሚችል ሸቀጥ ነው የሚአመርተው ፤ በዚህም ምክንያት ፤ ምርት ያለዕቅድ በምስቅልቅል ሁኔታ ነው የሚአድገው ። በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ የምርት ሥርዓተ — አልባነት ከሸቀጦች መሸጥ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ይፈጥርና ከሚፈለገው በላይ በማምረት ምክንያት የምጣኔ — ሀብት ቀውስ እንዲመጣ ያደርጋል ።

### 1. የሕብረተሰብ ወረት ዕርባታ

**ገላጭና ሕብረተ ሰብአዊ ወረት** በካፒታሊዝም ውስጥ የሕብረተሰብ ምርት በአንድ ላይ የተጠቃለለ አይደለም ፤ በግለሰብ ካፒታሊስት ድርጅቶች መካከል የተከፋፈለ ነው ። እያንዳንዳቸውም በአንድ ወይም በሌላ ካፒታሊስት በግል ይያዛሉ እናም ከሌሎች ድርጅቶች አንጻር እንደነጻ የምርት ክፍል ሆነው ይሠራሉ ። ወዲያውም በእያንዳንዱ የተለያዩ ድርጅት ውስጥ ዕርባታ ጥገኛ የሚሆነው በሌሎች ዕርባታ ላይ ነው ። ስለዚህ የተሽከርካሪ መኪናዎች ሥራ ዕርባታ ጥገኛ የሚሆነው በሌሎች ካፒታሊስቶች የሁሉም ዓይነት መሣሪያዎች ፤ ዕቃዎች ፤ መለዋወጫ ቁሳቁሶች ፤ ነዳጅ ፤ ለሠራተኞች የፍጆት ዕቃዎች ወዘተ . . . ምርት ላይ ነው ። የተለያዩ ካፒታሊስቶች አሠራር ፤ እናም የተለያዩ ወረት እንቅስቃሴዎች እርስ በእርሳቸው ይወሳሰባሉ ።

የተለያዩ ግለሰብ ወረቶች ማለትም የእርስ በርስ ጥገኝነታቸውና በይነ ግብራቸው ጠቅላላ ድምር ባጠቃላይ የሕብረተሰብ ወረት ተብለው ይጠራሉ ። በዚህ የተለያዩ ነጻ የወረት እንቅስቃሴዎች መወሳሰብ ነው — ከጠቅላላው የሕብረተሰብ ወረት አካል የሆኑት—በካፒታሊዝም ውስጥ ዕርባታ የሚካሄደው።ዕርባታ እንዲካሄድ እንዲሁ ግለሰብ ካፒታሊስቱ ሳይሆን ሁሉም በሕብረተሰብ ውስጥ ያሉት ካፒታሊስቶች የሚአመርቷቸውን ሸቀጦች በገበያ ላይ መሸጥና እዚያም ደግሞ እነሱ የሚፈልጓቸውን ሸቀጦች ለመግዛት መቻል አለባቸው ።

አጠቃላዩ የሕብረተሰብ ወረት ዕርባታ እንዴት እንደሚካሄድ ለማግኘት ፤ ስለጥቅሉ የሕብረተሰብ ምርት ይዘት እንመልከት ።

**ጥቅል የሕብረተሰብ ምርት** ጠቅላላው የቁሳዊ ሀብት ይዘት (መኪኖች ፤ የማሺን ዕቃዎች ፤ ነዳጅ ፤ ዳቦ ፤ ልብስ ወዘተ . . .) በተወሰነ ወቅት በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚመረተው ፤ ለምሳሌ በዓመት ፤ ጥቅል የሕብረተሰብ ምርትን ይመሠርታል ።

በዕሴት አንጻር ሲታይ ፤ ጥቅሉ የሕብረተሰብ ምርት የሚከፈለው ፤ 1/የጠፋውን በሥራ ላይ የዋለውን ቀዋሚ ወረት በሚተካው ዕሴት ፤ ማለትም ፤ የመሣሪያውን መበላትና መበጣጠስ የሚሸፍነው በጥቅም ላይ የዋሉት የጥሬና የመለዋወጫ ቁሳቁሶች ዕሴት ወዘተ . . 2/ ተለዋዋጭ ወረትን በሚተካው ዕሴት ማለትም በጉልበት ዕሴት እና (3) በትርፍ ዕሴት ነው ። በሌላ አባባል ፤ የጥቅል የሕብረተሰብ ምርት ኃይል ዕሴት ይሆናል ፦ ቀ + ተ + ትዕ (ቀዋሚ ተ ወረት + ተለዋዋጭ ወረት ተ ትርፍ ዕሴት) ።

ጥቅል የሕብረተሰብ ምርት እያንዳንዱ የተለያዩ ክፍል በምርት ሂደት ጊዜ የሚጫወተው የተለዩ ሚና ነው ። ቀዋሚ ወረት የምርትን ሂደት ለማገልገል መቀጠል ይኖርበታል ። ተለዋዋጭ ወረት ሠራተኞች የጉልበት ኃይላቸውን ለማራባት የሚአስችላቸውን ነገር ለማግኘት ወደሚከፈላቸው ምንዳዕ ይለወጣል ። በቀላል ዕርባታ

ውስጥ ትርፍ ዕሴት ሙሉ በሙሉ የካፒታሊስቶችን ግላዊ ፍላጐት ለማርካት ይውላል ። በተስፋፋ ዕርባታ አንዱ ክፍል ለካፒታሊስቶች ሲውል ፤ ቀሪው ክፍል እንደገና አዲስ የምርት መገልገያዎች ለመግዛትና ተጨማሪም ጉልበት ለመቅጠር ይውላል ። ውስጥ ትርፍ ዕሴት ሙሉ በሙሉ የካፒታሊስቶችን ግላዊ ፍላጐት ለማርካት ይውላል ። በተስፋፋ ዕርባታ አንዱ ክፍል ለካፒታሊስቶች ሲውል ፤ ቀሪው ክፍል እንደገና አዲስ የምርት መገልገያዎች ለመግዛትና ተጨማሪም ጉልበት ለመቅጠር ይውላል ።

የሕብረተሰብን ጠቅላላ ወረት ዕርባታና ዑደት በምንተነትንበት ጊዜ ቁሳዊ መልክ ያለው ጥቅል የሕብረተሰብ ምርት ታላቅ ዓይነተኛነት ይሰጠዋል ።

ጥቅል የሕብረተሰብ ምርት በቁሳዊ መልኩ ሲጤን የምርት መገልገያዎችንና የፍጆታ ዕቃዎችን በውስጡ ይዞ ይገኛል ። በአንጻሩም ጠቅላላ የሕብረተሰብ ምርት በሁለት ዋና ክፍሎች ይከፈላል ። ክፍል I የምርት መገልገያዎች ምርት ሲሆን ፤ ክፍል II ደግሞ የብሉት ዕቃዎች ምርት ነው ።

እንኚህ ጥቅል የሕብረተሰብ ምርት ክፍሎች በቁሳዊ መልካቸው የሚለያዩ ፤ በዕርባታ ሂደት ጊዜ የተለያዩ ሥራን ያሟላሉ ። የምርት መገልገያዎች ተጨማሪ ምርትን ሲአገለግሉ የፍጆት ዕቃዎች ደግሞ ግላዊ ፍላጐት ለማርካት ይውላሉ ።

የመገንዘብ ችግር

የሕብረተሰብ ወረት ዕርባታ ቀደም አርጐ የሚወስደው እያንዳንዱ ተናጠል ወረት ከዚያም የሚገኘው ጠቅላላ የሕብረተሰብ ወረት ሳያቋርጥ መዘዋወሩን መፈጸም እንዳለበት ነው ፤ ማለትም ፤ ከገንዘብ ወደምርት መልክ ፤ ከምርት መልክ ወደሸቀጥ መልክና ከሸቀጥ መልክ ወደ ገንዘብ መልክ እያለ ። ይህ መዟዟር ሊካሄድ የሚችለው ሁሉም ካፒታሊስቶች እያንዳንዳቸው በተናጠል ያለቀለት ምርታቸውን ( Finished Product ) ሲአውቁት ብቻ ነው ። የመገንዘብ (የማወቅ) ሂደት ማለት እያንዳንዱ እራሱን የቻለ የሕብረተሰብ የዓመት ምርት — ሁሉም በዕሴትና በቁሳዊ መልክ ያለው — ተጠቃሎ እንዳለ ይለዋወጥና በምርት ሂደት ጊዜ ያለውን አሠራሩን ያሟላል ።

እስከምን ሁኔታዎች ድረስ ነው ሁሉም የዓመት ውጤት ተጤኖ የሚረጋገጠው? የሚል ጥያቄ ይመጣል ። የማርክሲስት ሌኒኒስት የዕርባታ ንድፈ — ሀሳብ ይህንን ሁኔታ ይገልጽና የካፒታሊስት ምርት በሚአድግበት ጊዜ ፤ እንኚህ ሁኔታዎች ሳያጠራጥሩና ሳያቋርጡ በመጓዝ ከሚፈለገው በላይ በማምረት ወደኤኮኖሚ ቀውስ እንደሚዳፉ ያሳያል ።

በቀላል ካፒታሊስት ዕርባታ ውስጥ የመገንዘብ ሁኔታዎች

በቀላል ዕርባታ ውስጥ የምርት ሂደት በአንድዓይነት ደረጃ እንደቀድሞው ይደጋገማል ፤ እናም ሁሉም ትርፍ ዕሴት የሚጠፋው ለካፒታሊስቶች የግል ፍላጐት ነው ።

ጥቅል የሕብረተሰብ ምርትን ግንዛቤ በቀላል ዕርባታ መንገድ እንመልከት ። የቀዋሚው ወረት ዕሴት በክፍል I በሚሊዮን ብር ሲገለጽ 4,000 ፤ የተለዋዋጭ ወረት ዕሴት 1,000 እና ትርፍ ዕሴት 1 000 ይሁን እንበል ፤ በክፍል II የቀዋሚው ወረት ዕሴት 2,000 የተለዋዋጩ ወረት 500 ፤ እና ትርፍ ዕሴት 500 ይሁን ። ስለዚህ ጥቅል የሕብረተሰብ ምርት በሚከተሉት ክፍሎች ይታያል ።

ክፍል I = 4,000 ቀ + 1,000 ተ + 1,000 ትዕ = 6,000
ክፍል II = 2,000 ቀ + 500 ተ + 500 ትዕ = 3,000

በክፍል I የጠቅላላው ምርት ዕሴት ማለትም 6,000 የሆነው በመጨረሻው ዓመት ጊዜ በማሺን ፤ በጥሬ ሀብት ፤ ወዘተ . . . . መልክ ይኖራል ። ግን ከዚህ ክፍል ውስጥ ሠራተኞችና ካፒታሊስቶች የምርት መገልገያ ብቻ አይደለም የሚፈልጉት ፤ የምርት ሂደት የሚቀጥል ከሆነ የፍጆታ ዕቃዎችም ያስፈልጋሉ ። በክፍል I ያለተላቸው ምርቶች መጤን ይኖርባቸዋል ። እንዴት ነው የመገንዘብ (የመጤን) ሂደት የሚከናወነው ።




በክፍል I ከውጤቱ ከፊሉ 4,000ቀ የሚሆነው ፤ በዚያ ክፍል ውስጥ ላሉት ድርጅቶች በጥቅም ላይ የዋለውን ቀዋሚ ወረት ለመተካት ይሸጣል ። የክፍል I ውጤት ሌላው ክፍል (1,000 ተ + 1,000 ትዕ) በምርት መገልገያ መልክ የፍጆት ዕቃዎችን ለሚአመርቱ ድርጅቶች ይሸጣል ። እንኚህ የምርት መገልገያዎች ፤ የ2,000 ብር ምጥነት ያላቸው ፤ በክፍል II ያለውን ቀዋሚ ወረት ለመተካት ያገለግላል ።

በክፍል II ፤ በፍጆት ዕቃ መልክ ያለው (ልብስ ፤ ጫማ ፤ ምግብ ወዘተ . .) የጠቅላላ ምርቱ ዕሴት 3,000 ያህል ይሆናል ። 2,000 ምጥነት ያላቸው የፍጆት ዕቃዎች (በክፍል II የተመረቱት) ከምርት መገልገያዎች ይለዋወጣሉ (በክፍል 1 ከተመረቱት ጋር) ። የክፍል II ሌላው ውጤት የፍጆት ዕቃዎችን የያዙትና የተለዋዋጭ ወረት የተራባ ዕሴት በመሆን (500 ተ) ሲጨመር አዲስ የተመረተው ትርፍ (500ትዕ) ፤ ለዚህ ክፍል ሠራተኞችና ካፒታሊስቶች ይሸጣል ።

በዚህ መንገድ ጠቅላላው የሕብረተሰብ ምርት ይጤናል ። የመገንዘብ (የመጤን) ሁኔታ ፤ በቀላል ካፒታሊስት ዕርባታ እንደሚከተለው ነው ፤ ተለዋዋጭ ወረት ሲደመር የክፍል I ትርፍ ዕሴት ከክፍል II ቀዋሚ ወረት ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል።

በምርቱ ክፍሎች ዙሪያ በራሳቸው ክፍል ውስጥ የተጤኑ ባለሶስት ጉኖች (triangles) ቢሳሉና በሌላው ክፍል ውስጥ በተለዋወጡት ዙሪያ ደግሞ አራት ማዕዘኖች ቢቀመጡ ፤ እነሱን የሚአገናኝ መስመርም ቢሳል ፤ የሚቀጥለውን ስዕል እናገኛለን ።




ይህ ስዕል በቀላል ዕርባታ ውስጥ የመገንዘብን (የመጤን) ሁኔታ በግልጽ ያሳያል— I (ተ + ትዕ) = II ቀ ።

በተስፋፋ ካፒታሊስት ዕርባታ ውስጥ የመገንዘብ ሁኔታዎች

የተስፋፋ ዕርባታ ወይም ክምችት የካፒታሊዝም ጸባይ ነው ። ምርትን ለመጨመር በሕልውና ላይ ያለው ድርጅት የተስፋፋ ወይም አዲስ የተሠራ መሆን ይኖርበታል ። በማንኛውም በኩል አንዳንድ አዳዲስ የምርት መገልገያዎች በእንቅስቃሴ ላይ መዋል አለባቸው ። እናም በክፍል I የምርት መገልገያዎች ስለሚመረቱ ፤ አዲስ የተፈጠረውን ዕሴት ፤ የሚወክለው የክፍል I የምርት ክፍል (ተ + ትዕ) በክፍል II ካለው ቀዋሚ ወረት (II ቀ) የበለጠ መሆን አለበት ። በዚህ ሁኔታ ብቻ ነው በሁለቱም ክፍሎች ምርትን ለማስፋፋት በእንቅስቃሴ ላይ የሚውሉ ተረፍ የምርት መገልገያዎች ሊኖሩ የሚችሉት ።

ከዚህ በታች ያለው ምሳሌ ይህን ነው የሚአጤነው ።


ክፍል I : 4,000 ቀ + 1,000 ተ + 1,000 ትዕ = 6,000
ክፍል II : 1,500 ቀ + 750 ተ + 750 ትዕ = 3,000

በተስፋፋ ምርት ውስጥ ፤ በእያንዳንዱ ክፍል ያለው ትርፍ ዕሴት በሁለት ይከፈላል ። በካፒታሊስቶች ግላዊ ፍጆት የሚአልቀውና በሚከማቸው ማለት ነው ። የትርፍ ዕሴቱ የተከማቸው ክፍል የሚጠፋው ተጨማሪ የምርት መገልገያ በመግዛትና ተጨማሪ ጉልበት ኃይል በመከራየት ነው ።

የክፍል I ካፒታሊስቶች የትርፍ ዕሴታቸውን ግሚስ ማለትም ፤ 500 (አደለቡ) እንበል ። ይህም ማለት ለቀዋሚው 400 ለተለዋዋጩ 100 አከማቹ ርባቸዋል ፤ ማለትም የተጠራቀመውን የትርፍ ዕሴት ክፍል በመጀመሪያው ይኖ ጣው ወረት ጋር በማመጣጠን ያጠፉታል (ይሥሩበታል) ። ስለዚህ ፤ በክፍል I ያለው ዕሴት በሚቀጥለው ዓመት ወደ ምርት በሚሄድበት ጊዜ እንደሚታይ ሁሉ የሚቀ ጥለው ይዘት ይኖረዋል ፡— 4,4000 ቀ 1,100 ተ

ከክፍል I ጠቅላላ ውጤት ውስጥ (6,000) ፤ 4,4000 በዚያው ክፍል ውስጥ ይው ላል ። ቀሪው I,600 በክፍል II ከሚገኙ ውጤቶች ጋር ይለዋወጣል ። ግን በክፍል II ውስጥ ያሉት ካፒታሊስቶች 1,600 የሚአወጣ የምርት መገልገያ ለመግዛት ከቻሉ (በተከታዩ ዓመት በእነሱ ከሚጠፋው 1,500 ይልቅ ) ፤ ቀዋሚ ወረታቸውን ክፍል II ውስጥ ካላቸው ትርፍ ዕሴት በመውሰድ በ100 መጨመር አለባቸው ። እነኚህ 100 የትርፍ ዕሴት ክፍሎች በክፍል II ቀዋሚ ወረቱን ለማሳደግ የዋሉቱ ፤ ተለዋዋጭ ወረቱ በ50 መጨመር እንዳለበት ጥሪ ያሳያሉ ፤ በመጀመሪያ በክፍል II የዋለው ወረት የጠፋው 2 : 1 ምጥንነት ነውና ። ስለሆነ ፤ በተከታዩ ዓመት ምርት የሚሄደው የክፍል II ዕሴት የሚሆነው 1 600ቀ ተ 800 ተ ነው ፡—

የምርት መገልገያዎችንና የፍጆት ዕቃዎችን በክፍል I እና II የማከፋፈል ሂደት በሚቀጥለው ሥዕል ይታያል ።






የውጤትን መገንዘብ (በሥራ መዋል) የሚካሄደው በሚከተለው መንገድ ነው ። የምርት መገልገያዎችን በ4,400 ዕሴት በክፍል I ያሉት ካፒታሊስቶች እንዱ ካንደኛው የምርት መገልገያዎችን በ4,400 ዕሴት ለፍጆት ዕቃዎች በክፍል II (1,600) በክፍል II ለፍጆት ዕቃዎች ይገዛዛሉ ። የምርት መገልገያ ቀሪው ክፍል (1,600) በክፍል II ለፍጆት ዕቃዎች ይለዋወጣሉ ። በዚህ ልውውጥ ምክንያት የክፍል I ካፒታሊስቶች በ1,600 ዕሴት የፍጆት ዕቃዎችን ሲቀበሉ ፤ የክፍል II ካፒታሊስቶች ግን በ1,600 ዕሴት መጠን የምርት መገልገያ ያገኛሉ ። በክፍል II ቀሪው የፍጆት ዕቃ (1,400) አዋዋል የሚከናወነው በክፍል II ውስጥ በራሱ ነው ።

በክፍሎች መካከል ያለው የልውውጥ ሂደት እንደሚቀጥለው ሊታይ ይችላል፡—

I, 4,000 ቀ + | 1, 100 ተ ተ 500 ትዕ | = 6,000
II, | 1. 600 ቀ | + 800 ተ + 600 ትዕ = 3,000

በተስፋፋ ዕርባታ ውስጥ ያዋዋል (የመገንዘብ) ሁኔታ አኳያነት ነው — የተለዋዋጭ ወረት ዕሴት (1 000) ሲደመር በተለዋጩ ወረት ላይ የሚደመረው የተከማቸው ትርፍ ዕሴት (100) ሲደመር በካፒታሊስቶች የሚጨረሰው ትርፍ ዕሴት (500) ከቀዋሚው ወረት (1 500) ሲደመር በክፍል II ላለው ቀዋሚ ወረት የሚደመረው የተከማቸ ትርፍ ዕሴት (100) ጋር እኩል መሆን አለበት ።

በሁለተኛው ዓመት የምርት ሁለተኛውዑደት በከፍተኛ ወረት መስፋፋት ይጀምራል ፤ እናም የትርፍ ዕሴት ደረጃ 100 ፐርሰንት ከሆነ ፤ በሁለተኛው ዓመት ጥቅሉ የሕብረተሰብ ምርት እንደሚከተለው ይመጣል ፡—

ክፍል I — 4,400 ቀ + 1,100 ተ + 1,100 ትዕ = 6,000
ክፍል II — 1,600 ቀ + 800 ተ + 800 ትዕ = 3,200

እንዲህ ነው የተስፋፋ የካፒታሊስት ዕርባታ የሚከናወነው ፤ እናም እነኚህ የአዋዋል ሁኔታዎች ናቸው የተስፋፋውን ዕርባታ አዝማሚያ ቀደም አድርገው የሚወስኑት ።

በተስፋፋ ዕርባታ ውስጥ ፤ የምርት ኃይሎች ዕድገት የሚገለጸው የምርት መገልገያዎችን ለማምረት የሚጠፋው ሕብረተሰብ ጉልበት መጠን የፍጆት ዕቃዎችን ለማምረት ከሚወጣው በላይ በፍጥነት በመጨመሩ ላይ ነው ።

የተስፋፋ ዕርባታ ምጣኔ — ሀብታዊ ሕግ የምርት መገልገያዎች ምርት (መመረት) ከፍጆት ዕቃዎች መመረት ይልቅ ይበልጥ በፍጥነት ማደግ ነው ።

«የምርት መገልገያዎች ይበልጥ በፍጥነት የማደግ ትርጉምና ዓይነተኛነት ሕግ የሚንተራሰው የእጅ በማሺን ጉልበት የመተካት እውነቱ ላይ ነው ። — በአጠቃላይ የማሺን የብረት ኢንዱስትሪዎችን የአጀበው የቴክኒካዊ ዕድገቱ ነው ፡ — ይህም የከሰልና ምርት ከፍተኛ ዕድገትን ማለትም 'የምርት መገልገያ ለምርት መገልገያ' መዋልን ይጠራል ። » 1

የመገንዘብ (የአዋዋል) ንድፈ — ሀሳብ በቀላልና በተስፋፋ ካፒታሊስት ዕርባታ ውስጥ የሸቀጦችን አዋዋል አስፈላጊ ሁኔታዎች ግልጽ ያደርጋል ። ስለዚህ በምንም መንገድ በካፒታሊዝም ውስጥ እነኚህ ሁኔታዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል ። በተቃራኒው ሳያቋርጡም ይጣሳሉ ።

የምርት ሥርዓተ — አልባነት እና ውድድር «ሥርዓት» በሚሆኑበት ጊዜ ፤ ማንምሰው ገበያው የሚጠይቀውን የሚአውቅ የለም ። በዚህ ምክንያት በኢንዱስትሪ ቅርንጫፎችና በእያንዳንዱም ቅርንጫፍ መካከል የተወሰኑ ፤ አስፈላጊ ግንኙነቶች በማያቋርጥ ፤ ቁጥር ስፍር በሌለው የምጥንነት ግንኙነት መጣሶች ይመሰረታል ።

1. ቪ. አይ. ሌኒን ጠቅላላ ሥራዎች ቅጽ አንድ ገጽ 105

በካፒታሊዝም ውስጥ በምርትና በብሎት መካከል ተጻራሪ የሆነ ቅራኔ አለ ። የካፒታሊስት ምርት ዓላማ ከፍተኛ ምርት ለማምረት ነው ፣ የሚገኘው ምርትን በማ ስፋፋትና ወረት በማከማቸት ነው ። ወዲያውም ሁሉም ሂደቶች የሚከናወኑት የሠራ ተኛውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ዝቅ በማድረግ ነው ፣ ስለዚህም የመግዛት ኃይላቸውና የፍጆታቸው መጠንም ያነሰ ይሆናል ። ይህ የሸቀጦችን አዋዋል ችግር በመጣል የገበያን መጨማተር ያመጣል ።

ቡርዧዎች ይህን ቅራኔ ሊአስወግዱ የሚሞክሩት የውጭ ገበያን በማሸነፍ ነው ። ለውጭ ገበያ ትግል ፣ የመያዝ ፣ መከፋፈልና የእንደገና መከፋፈል የበለጠ ትብ ቅራኔ ዎችን ይፈጥሩና በካፒታሊስቶች መካከል ቁጥራቸው ይህ ነው ለማይባሉ ቅራኔዎች (ግጭቶች) መንስኤ ይሆናሉ ።

## 2 ብሔራዊ ገቢ

ብሔራዊ ገቢ ምንድነው ?

ጥቅል የሕብረተሰብ ምርት ማለት እንበልና በአንድ ዓመት ጊዜ ወይም በሌላ ጊዜ በሕብረተሰብ ውስጥ የሚመረተው የቁሳዊ ሀብት አካል እንደሆነ ቀደም አድርገን ገልጸናል ። ከሕብረተሰብ ምርት ቀዋሚ ወረት ይተካል ፣ ምክንያቱም ከምርት መገልገያ አዲስ ወደተሠራው ምርት የሚሸጋገር ዕሴት ነውና ። ቀሪው የሕብረተሰብ ምርት (ተለዋዋጭ ወረትና ትርፍ ዕሴት) በዓመት ውስጥ የሚፈጠረው አዲስ ዕሴት ነው ። ይህ የሕብረተሰብ ጥቅል የምርት ክፍል የካፒታሊስት ሕብረተሰብ ብሔራዊ ገቢ ነው ።

ለምሳሌ ፦— በአንድ አገር ውስጥ $ 90 ሺ ሚሊዮን ዕሴት ያለው ሸቀጥ በአንድ ዓመት ውስጥ የተመረተ ቢሆን ፣ ከዚሁ ደግሞ $ 60 ሺ ሚሊዮን በዓመት ውስጥ በጥቅል ላይ የዋለውን የምርት መገልገያ ለመተካት ቢውል ፣ በዚያ ዓመት ውስጥ የተገኘው ብሔራዊ ገቢ $ 30 ሺ ሚሊዮን ሆነ ማለት ነው ።

በቁሳዊ መልኩ ፣ የብሔራዊ ገቢው በውስጡ የግላዊ ፍጆት ዕቃዎችንና ምር ትን ለማስፋፋት የሚውለውን የምርት መገልገያ ክፍል ይይዛል ።

ብሔራዊ ገቢ የሚፈጠረው በቁሳዊ ምርት አድማስ ውስጥ በሚሠሩት ሰዎች ነው ። ይህ አድማስ ሁሉንም ቁሳዊ ሀብት የሚመረትባቸውን ቅርንጫፎች ይይዛል ፦— ኢንዱስትሪ ፣ እርሻ ፣ ሕንጻ ፣ ትራንስፖርት ወዘተ . . . . ። ብሔራዊ ገቢው የሚፈጠ ረው በሠራተኞች ፣ በገበሬዎች ፣ በእጅ ሙያተኞችና በምሁራን ማለትም በቀጥታ በቁሳዊ ምርት አድማስ ውስጥ በተቀጠሩት ነው ።

በኢ አምራች አካባቢ ፣ ምንም ብሔራዊ ገቢ አይፈጠርም ። ይህም የሚአጠቃል ለው ፦— መንግሥታዊ መዋቅሩን ፣ የዱቤ አሠራርን ፣ ንግድን (የምርት ሂደትን በማዟዟር አድማስ የሚካሄደውን ንግድ ሳይጨምር) ፣ ወታደሩን ፣ የሕክምና ተቋሞ ችን ፣ መዝናኛዎችን ፣ ወዘተ . . . . ይሆናል ። በእነዚህ ቅርንጫፎች ውስጥ የሚውለው ወጭ ሁሉ በምርት ክልል በሚፈጠረው ብሔራዊ ገቢ የተሸፈነ ነው ።


የብሔራዊ ገቢው በቁሳዊ ምርት አካባቢ እስከተፈጠረ ድረስ ፣ ለዕድገቱ የሚአ ስፈልጉት ሁኔታዎች የሚገኙት በምርት ላይ የሚሠማሩትን ሰዎች ቁጥር በመጨመር የጉልበት አምራችነታቸው ማየል ፣ እናም በኢ አምራችነት አካባቢ የተሠማሩት ሰዎች ቁጥር መቀነስ ያሻል ። ከካፒታሊዝም ዕድገት ጋር መንግሥታዊ መዋቅሩ ያድ ጋል ፣ የፖሊስና የወታደሩ ኃይል ብዛት ይጨምራል ፣ ብዙ ሕዝብ ቡርዧዎችን ለማገልገል ይውላል ፣ እናም ሥራ — አጥነት በሰፊው ይስፋፋል ። ይህ ሁሉ ተዳምሮ የብሔራዊ ገቢውን ዕድገት ይገታል ።



የብሔራዊ ገቢው አሰራጫጨት

በካፒታሊዝም ውስጥ የብሔራዊ ገቢው የሚሠራጨው መደብን ተንተርሶ ነው ፦— በበዝባዦች ፍላጎት እንጂ በሠራተኛው ሕዝብ ዝንባሌ አይደለም ። በብሔራዊ ገቢው ተቀዳሚና ሁለተኛው አሠረጫጨት ላይ ልዩነቶች መስመር ይኖርባቸዋል ።

ከሁሉም በፊት ብሔራዊ ገቢው በካፒታሊስቶች ዕጅ ነው የሚገባው ። የብሔ ራዊ ገቢ ው የተቀዳሚ አሠረጫጨት ሕልውና ያለው በካፒታሊስቶችና በሰራተኞች መካከል ነው ። ሠራተኞች ምንዳዕ ይቀበላሉ ፣ ካፒታሊስቶች — ትርፍ ዕሴት ፣ ይህም በኢንዱስትሪያሊስቶች ፣ ነጋዴዎች ፣ ባንከኞችና ትላልቅ የመሬት ከበርቴዎች መካ ከል ይከፋፈላል ። ይህ ሥርጭት በሚቀጥለው ስዕል የሚታየው ነው (እያንዳንዱ ዩኒት — ክፍል — $ 1,000 ሚሊዮን ነው) ።




ብሔራዊ ገቢው በካፒታሊስት ሕብረተሰብ መሠረታዊ መደቦች መካከል ከተ ሠራጨ በኋላ በወዝአደሩ ፣ በካፒታሊስቶችና በመሬት ከበርቴዎች — ሁለተኛ ሥር ጭት ወይም የእንደገና ሥርጭት ይካሄዳል ።

እንዴት ነው የብሔራዊ ገቢው የእንደገና ሥርጭት ሊመጣ የሚችለው ? በኢ— አምራች የኤኮኖሚ ቅርንጫፎች (በጤና ተቋሞች ፣ ሕዝባዊ አገልግሎቶችና በሕብረ ተሰብ ተሃድሶዎች ፣ በመዝናኛዎች ፣ ወዘተ . . .) ምንም ብሔራዊ ገቢ እንደማይፈጠር አይተናል ። ግን እነዚህን ድርጅቶች የሚቆጣጠሯቸው ካፒታሊስቶችና ተቋሞች ለተቀጣሪዎቻቸው ደመ—ወዝ ይከፍላሉ ፣ (ለዶክተሮች፣ ለኪነት ሙያተኞች ወዘተ. .) የመጠገኛ ወጭዎችን ይሸፍናሉ ፣ እና በተጨማሪ ትርፍ ያገኛሉ ። ካፒታሊስቶች እነኚህን ሁሉ የወጭ ዓይነቶች የሚሸፍኑት ከቁሳዊ ምርት በተገኘው ብሔራዊ ገቢ ለሰጡት አገልግሎት ዋጋ በመጠየቅ ነው ፣ ማለትም ፣ ለሕክምና አገልግሎት ፣ ለትም ህርት ፣ ለሕዝባዊ አገልግሎቶችና ተሃድሶዎች ፣ ወዘተ . . ክፍያ በመጠየቅ ። እነዚህ ለተሰጡት ግልጋሎቶች ክፍያዎች የድርጅቱን መጠገኛዎች (ሥራ ማስኪያጃዎች) ሸፍነው በኢ—አምራችነት ክልል ውስጥ ላሉት ካፒታሊስቶች አማካይ ትርፍ ያመ ጡላቸዋል ።

የሠራተኛው ሕዝብ ከፊል ገቢ በመንግሥቱ ባጀት ምደባ በኩል እንደገና ይሠ ራጭና በገዥ መደቦች ዝንባሌ መሠረት ጥቅም ላይ ይውላል ።

የቡርዧዋው መንግስት የራሱ ሠራዊት ፤ ፖሊስ ፤ የወህኒ ተቋሞችና ፍ/ቤቶች ፤ አስተዳደራዊ መዋቅሮችና ሌላም ይኖረዋል ። ሁሉም የሚተዳደሩት በመንግሥቱ ባጀት ነው ። ይህ ደግሞ የሚገኘው የገቢው ዋና ምንጭ በሆነው ሕዝብ ላይ ግብር በመጣል ይሆናል ። ይህም ማለት ሠራተኛ ሕዝቦች በብሔራዊ ገቢ ተቀዳሚ ሥርጭት አማካይነት ምንዳቸውን ከተቀበሉ በኋላ ከወሰዱት ውስጥ ለመንግስት ግብር መክፈል ይኖርባቸዋል ነው ። በዚህ መንገድ ፤ በሠራተኞች አካባቢ የቀለው ብሔራዊ ገቢ ክፍል ይቀንስለታል ።1

ካፒታሊዝም ሲዳብር የግብር ሸክም እየጨመረ ይሄዳል ። ለምሳሌ ፤ በእንግሊዝ በ1913 ታክሱ የብሔራዊ ገቢውን 11 በመቶ ፤ በ1924 ፤ 23 በመቶ ፤ በ1950—38 በመቶ ወስዷል ። በፈረንሣይ ደግሞ በ1913 — 13 በመቶ ፤ በ1924 — 21 በመቶ እና በ1950—28 በመቶ ነበር ።

የብሔራዊ ገቢው እንዴት በጥቅም ላይ እንደሚውል

ብሔራዊ ገቢው የሚጠፋው በብሎት (ፍጆት) እና በክምችት ላይ ነው ።እንደብሔራዊ ገቢው አሠራጫጩት ሁሉ በካፒታሊዝም ውስጥ አጠቃቀሙ መደባዊ ጸባይ አለው ። ለሠራተኞች ግላዊ ፍጆታ የሚውለው የብሔራዊ ገቢ ምጥንት ለብዙኃኑ የመነሻ የሕይወት መደጐሚያን አያረጋግጥም ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሠራተኛ ሰዎች በእጅግ አስከፊ የቤት ሁኔታ ፤ ከዕውነተኛ አስፈላጊዎቻቸው ነገሮች ራሳቸውን በማስወገድ ፤ እና ልጆቻቸውን ከትምህርት በማገድ ፤ ሌላ ሌላም ኑሮ ይገፋሉ ።

የብሔራዊ ገቢው ከፍተኛ ክፍል የሚወሰደው በበዝባዥ መደቦች ነው ፤ ካፒታሊስቶች ከፊሉን ለግላዊ ብሎት(መዝናኛን በመጨመር) እና እጅግ ብዙ አሽከሮች ለመቅጠሪያ ያውሉታል ። ካፒታሊስቶች ሌላውን ክፍል የሚጠቀሙበት ምርትን ለማስፋት ወይም ለክምችት ነው ።

ግን ይህ ክፍል ለሕብረተሰቡ ለሚአስፈልጉትና ሊደረጉ ከሚችሉት ነገሮች አንጻር ሲታይ አነስተኛ ነው ። የወረት ክምችት ከሌላው ሲነጻጸር በማነሱ ምክንያት የብሔራዊ ገቢው ብዙው የሚጠፋው ምርት በማይሰጥ ላይ ፤ በማስታወቂያ ፤ ምጣኔ ሀብቱን ወታደራዊ ይዘት በማስያዝ ፤ እጅግ መጠኑን የአስፋፋ መንግስታዊ መዋቅር በማካሄድ ፤ ወዘተ . . ነው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ የብሔራዊ ገቢው አሠረጫጨት መደባዊ ጸባይ የሠራተኛውን ሕዝብ የመግዛት ኃይል ከምርት የመስፋፋት ደረጃ በስተኋላ እንዲጐተት ያደርገዋል ። ከጊዜ በኋላ ይህ መጐተት እጅግ ብዛት ይኖረውና ከሚፈለገው በላይ በማምረት ወደ ምጣኔ ሃብታዊ ቀውስ ያመራል ።

## 3. ምጣኔ—ሀብታዊ ቀውሶች ፤

የቀውስ አፈጣጠርና መሠረታዊ ምክንያቱ

የፈረንሣዊ ተምኔታዊ ሶሻሊስት ፉሪዩ ፤ በምጣኔ —ሀብታዊ ቀውሶች ውስጥ የሚታዩትን ቅራኔዎች ሲገልጽ «መትረፍረፍ ለፍላጎትና ለዕርዛት ምንጭ ይሆናል» ይላል ።

ከተፈላጊው በላይ የማምረት ቀውስ የመጀመሪያው አሳሳቢ ምልክቶች የንግድ መዘጋት ፤ በገበያ ላይ የማይሸጡ ሸቀጦች መትረፍረፍ ፤ የፋብሪከሎች የሥራ ማቆም ፤ እና የብዙ ሠራተኞች ከሕይወት መደጐሚያዎች የመከልከል ሁኔታዎች ናቸው ።

---

1. ካፒታሊስቶችም ግብር ይከፍላሉ ። ግን ከራሱ በክፍያ መልክ ለነሱ ይመለሳል ፣ እና እጅግ ከፍተኛው ለአትራ [illegible] ። [illegible] ነው ። [illegible] ።



በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ «እጅግ ብዙ» ምግብ ፤ ልብስ ፤ ነዳጅ ፤ ወዘተ .. መመረቱ እርግጥ ነውን ? አይደለም ፤ ወደቀውስ የሚመራው ከመጠን በላይ ማምረት ፍጹማዊ አይደለም ፤ አንጻራዊ ነው ። የሸቀጦች መትረፍረፍ የሚኖረው ከአስፈላጊው ተጠያቂነት ሲነጻጸር እንጂ ለሕብረተሰብ ከሚአስፈልጉት ነገሮች አንጻር አይደለም ። የሕብረተሰብ አስፈላጊዎች ( requirements ) ቀውስ በሚኖር ጊዜ አነስተኛ አይሆኑም ፤ ግን በሠፊው ሠራተኛ ሕዝብ ዘንድ የመግዛት ኃይሉ ትብ ውድቀት ይኖራል እንጂ ። በቀውስ ጊዜ ሠራተኛ ሕዝቦች የዋና አስፈላጊዎች ከፍተኛ የሆነ ፍላጐት ይኖራቸዋል ፤ የፍላጐቶቻቸው ዕርካታ ከሌላው ጊዜ ሁሉ ያነሰ ነው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ዋናው ነባር የሆነው ከመጠን በላይ የማምረት የምጣኔ — ሀብታዊ ቀውስ ምክንያት የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ ነው ። በምርት ሕብረተሰብአዊነት ጸባይና የምርት ውጤት የካፒታሊስት ግላዊ የይዞት መልክ መካከል ያለው ቅራኔ መሆኑ ነው ።

የካፒታሊስት አመራረት የተመሠረተው በሕብረተሰብአዊ የሥራ ክፍፍል ነው። ካፒታሊዝም ሲዳብር መጠቅ ያለ የሥራ ክፍፍል ይፈጠራል ፤ ምርትም ከዚህ በፊት ባልታዩ ሁኔታ ጠበብት በሆኑ ቅርንጫፎች ይካሄዳል ። ትላልቅ ድርጅቶች በመቶና በሺ የሚቆጠሩ ሠራተኞችን ባንድነት ያሰልፋሉ ፤ እናም እነዚህ ድርጅቶች ሁሉ ተወሳሰበውና ተዛምደው ለብሔራዊና ለዓለም ገበያ ይሠራሉ ። በዚህ ሁኔታ ፤ ጉልበትን በሰፊው በማከት ፤ ካፒታሊዝም ምርትን ሕብረተሰባዊ ጸባይ ያስይዘውና እያንዳንዱ ሸቀጥም የብዙ ሺ ሠራተኞችን የሕብረተሰብ ጉልበት ይወክላል ።

ግን ካፒታል (ወረት) ምርትን ፍጹም ተጻራሪ ያለው ሕብረተሰባዊ ጸባይ ነው የሚሰጠው ። የምርት ሕብረተሰባዊ ሆኖ ማደግ የሚታየው የካፒታሊስቶችን ዝንባሌ በመጠቀም ነው ፤ የእነሱ ዓላማ ደግሞ ምርታቸውን ለመጨመር ነው ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሠራተኞች የሚሠሩባቸው የምርት መገልገያዎች የካፒታሊስቶች የግል ንብረት ናቸው ፤ ስለዚህ የብዙ ሚሊዮን ሠራተኞች ውጤት እፍኝ ለማይሞሉ ካፒታሊስቶች ንብረት ይሆናል ።

የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ በመጀመሪያ የሚታየው በተለያዩ ድርጅቶች የምርት ቅንጅትና በምርት ውስጥ በመላው ሕብረተሰብ ሠፍኖ በሚታየው ሥርዓት — አልባነት መካከል ባለው ቅራኔ ነው ። እያንዳንዱ ካፒታሊስት ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ነው የሚጥረው ። ከፍተኛ የምርት ደረጃ በመያዝ ፤ ካፒታሊስቶች የሕብረተሰቡን ፍላጐት በጠቅላላው ሳያጤኑ ምርትን ያስፋፋሉ (ወረታቸውን ይበልጥ ትርፍ ሊሰጡ ወደሚችሉ ኢንዱስትሪዎች ለማዞር ወይ ይቀንሳሉ) ። ስለዚህ በኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች መካከል ያለው ምጥኑታዊ ግንኙነት (ተመጣጣኝ ግንኙነት) ይጣሳል ፤ ስለሆነም የሕብረተሰቡን ምርት ለማመዛዘን አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ያደርገዋል።

የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ ሌላው ላቅ ብሎ የሚታይበት ለካፒታሊዝም የተፈጥሮ ጸባይ በሆነው ወሰን የሌለው የምርት መስፋፋት አዝማሚያና ካፒታሊዝም ራሱ የዋና ተጠቃሚዎችን የመግዛት ኃይል ስለሚወስን ነው ። የሠራተኛውን ሕዝብ።

ወሰን የሌለው የምርት ዕድገት አዝማሚያ ሂደት የሚከናወነው በካፒታሊዝም መሰረታዊ ምጣኔ — ሀብት ሕግ ነው ። በትርፍ ዕሴት ሕግ ። የትርፍ መሰብሰብ እያንዳንዱን ካፒታሊስት ወረት እንዲአደልብ ፤ ምርት እንዲአስፋፉ ፤ ቴክኖሎጂን እንዲአሻሽል ፤ አዲስ ማሺኖች እንዲአስተዋውቅ ፤ የበለጡ ሠራተኞቹን እንዲቀጥር ፤ እና የበለጠ ሸቀጥ እንዲአመርት ያደርገዋል ። ግን ይህ ወሰን ወደሌለው ለምርት መስፋፋት ጥማት ካፒታሊስቶችን ምንዳን ዝቅ እንዲአደርጉና የብዝበዛውን ደረጃ እንዲጨምሩ ያደርጋቸዋል ። ግን የብዝበዛ ማየልና የሠራተኛው ሕዝብ መራቆት ማለት በትክክለኛው ተጠያቂነት ላይ አንጻራዊ ማዘቅዘቅ ሸቀጦችን ለመሸጥም ዕድሉ የጠበበ

መሆንን ያመጣል ። ይህ ሁሉ ከመጠን በላይ የማምረት ምጣኔ — ሀብታዊ ቀውስን ነው የሚያመጣው ።

በተጨማሪም የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ የሚታየው በወዝአደሩና በቡርዧዋው መካከል ባለው የመደብ ተጻራሪነት ነው ። ካፒታሊዝም በካፒታሊስቶች እጅ የደለበውን የምርት መገልገያና ከጉልበታቸው በቀር ሌላ ተስፋ በሌላቸው ቀጥተኛ አምራቾች መካከል የመጨረሻ መለያየት አምጥቷል ። ይህ መለያየት ይበልጥ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ከመጠን በላይ በማምረት ቀውስ ፤ ባንድ በኩል በምርት መገልገያዎችና ሸቀጦች እጅግ መትረፍረፍ ፤ በሌላ በኩል ትርፍ የጉልበት ኃይል መኖር ፤ የኑሮ መደጐሚያ የሌላቸው የብዙ ሥራ — አጦች መብዛት ነው ።

*የካፒታሊስት ውደትና ደረጃዎቹ*

ከመጠን በላይ የማምረት ቀውስ በእያንዳንዱ ከ 8—12 ዓመታት ውስጥ ይደገማል ። የመጀመሪያው ኢንዱስትሪያዊ ቀውስ እንግላንድን በ1825 ዓ. ም. ነው የመታት ። ከ1847—48 ዓ. ም. በዩናይትድ ስቴትስና በብዙ አውሮፓውያን አገሮች የነበረው ቀውስ የመጀመሪያው የዓለም ምጣኔ ሀብታዊ ቀውስ ነው ። በ19ኛው ምዕተ ዓመት በተለይ እስከፊው ቅድመ — ሞኖፖሊን ወደ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መሸጋገር ያስመለከተበት ማለትም ኢምፔሪያሊዝም የተከሠተበት 1873 ነው ፡፡ የ20ኛ ምዕተ ዓመት አሰቃቂው ቀውስ ከ1929እስከ33 ያለው ነው ።

ካንድ ቀውስ ጀምሮ እስከሚቀጥለው ቀውስ መጀመሪያ ያለው ዑደት ተብሎ ሲጠራ ፤ በውስጡ አራት ደረጃዎች ይኖሩታል ፤ ቀውስ ፤ ዝቅጠት ፤ ማገገምና ንረት ።

ቀውስ — መሠረታዊ የዑደት ደረጃ — በተለይ የሚለየው በሸቀጦች ያለመጠን መመረት ፤ በተመን ማሽቆልቆል ፤ በመራቆት የተለያዩ ምክንያቶች ፤ በምርት ማቆም ፤ በሥራ አጥነት ማደግ ፤ በምንዳዕ መውረድ ፤ ሸቀጦችን ፣ ማሺኖችንና ድርጅቶችን ሆን ብሎ በማውደም ፤ እና በሀገር ውስጥና በውጭ የንግድ መቀነስ ነው ። በዚህ ደረጃ ጊዜ በምርት ማደግ አዝማሚያና በእንጻሩም በውጤታማው ተጠያቂነት መቀነስ መካከል ያለው ቅራኔ የሚገለጸው በኃይልና በአፍራሽ መልክ ነው ። በከፍተኛ ደረጃ ያደጉት የምርት ኃይሎች ጠባብ ቢጋር ካለው የምርት ግንኙነት ጋር — ለምርት ኃይሎች ዕድገት እንቅፋት ከሆነው — ይጋጫሉ ።

በቀውስ ጊዜ የምርት መስፋፋት በሕብረተሰቡ ውስጥ ካለው ውጤታማ ተጠያቂነት ደረጃ እኩል በኃይል የሚመጣው በመራቆት (ክስረት) ፤ በብዙ ድርጅቶች መፍረስና በምርት ኃይሎች ክፍል ሆን ተብሎ መውደም ብቻ ናቸው ዘዴዎቹ ። ከዚያም ከቀውስ ወደ ዝቅጠት ያለው መሸጋገር ይቀጥላል ።

የዑደቱ 2ኛ ደረጃ ዝቅጠት ሲሆን መለያው ደግሞ የቀውሱ እየቀጠለ መሄድ መቆሙ ነው ፤ ይሁንና አሁንም ቢሆን የኢንዱስትሪ ምርት እንደታከተ (የማይንቀሳቀስ) ፤ የሸቀጦች ተመን እንደወረደና ንግድ እንዳዘቀዘቀ የትርፍ ደረጃ አነስተኛ እንደሆነ ነው ያለው ። ሥራ—አጥነትና ምንዳዕ በቀውሱ ጊዜ እንደነበሩ ይቆማሉ ። የሸቀጦች የተጠራቀመ መድበል ( stock ) በከፊል ወድሟል ፤ በከፊል ደግሞ በዝቅተኛ ተመን ተሸጧል ። የካፒታሊስት ምርት ውድድርና ለገበያ ትግል ፣ እንዲሁም የጥሬ—ዕቃ ምንጮች ፤ ካፒታሊስቶችን ኢንዱስትሪን እንደገና እንዲያሟሉና ቀዋሚ ወረታቸውን እንዲያድሱ እስከገፋፋቸው ድረስ በዝቅጠት ደረጃ ጊዜ እንደነበር ይቆያል ። ካፒታሊስቶች ምርትን ለማርከስ ሲሉና በቀውስ ምክንያት በወረደው ተመን እንኳን ትርፋማ ለማድረግ ማንኛውንም የቴክኒካዊ መሻሻል መንገዶችን በጥቅም ላይ ያውላሉ ። የካፒታል ዕቃዎች ተጠያቂነት ምርትን ለማስፋፋት ካለው መገፋፋት ጋር አንድነት ይቀርባል ። ቀስበቀስ ወደሚቀጥለው የዑደት ደረጃ ሽግግር ቅድመ — ሁኔታዎች ይገነባሉ — ወደማገገም ።



የማገገም መለያው — ቀውሱ ነባር ወረታቸውን ማደሱን እንዲቀጥልና ቀ[illegible] በቀስ ምርትን ማስፋፋት እንዲጀምር የሚያገለግሉ ድርጅቶች መኖራቸው ላይ ነው ። የምርቱ ስፋት በቀውሱ ዋዜማ ደርሶበት የነበረውን ደረጃ ይቃረብና ፤ ኋላም ያን ደረጃ ዘሎ ይሄዳል ። ንግድ ይሻሻላል ፤ የሸቀጦች ተመን ይጨምራል ፤ ትርፍ ያድጋል ፤ ሥራ — አጥነትም ቀስ በቀስ ነው የሚመጣው ።

የካፒታሊስት ምርት ከቀውሱ በፊት ደርሶበት ከነበረው ነቁጥ በላይ ሲሄድ የንረት ደረጃ ይመጣል ።

በዑደቱ ውስጥ ንረት የመጨረሻው ደረጃ ነው ። በዚህ ደረጃ ጊዜ የምርት ወሰን — አልባ የሆነ እድገት አዝማሚያ ሙሉ በሙሉ ይንጸባረቃል ። እንደገና ካፒታሊስቶች አንዱ አንደኛውን ለማየል ፤ ምርትን ያስፋፋሉ ፤ የእንደገና ማደራጀትን ዘመቻ ያካሂዳሉ ፤ እናም ከዚህ በፊት ተደርጎ ያልታወቀ የሸቀጥ መጠን ወደገበያ ይላካል ። እጅግ ፍጥነት ያለው የምርት ዕድገት ከውጤታማው ተጠያቂነት ዘሎ ማምረት በፍጥነት ያድጋል ፤ የሸቀጦች መትረፍረፍም መድበሉ ይጨምራል ። በዚህ የንረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ገበያው ያለውጤታማ ተጠያቂነት በድንገት በሸቀጦች ተጥለቅልቆ ይታያል ፤ ተመን ይወርዳል ፤ ቀውስም ይጀምራል ። ስለሆነም እንደገና ሁሉም ዑደት በአዲስ መልክ ይጀምራል ።

ስለዚህ የካፒታሊስት ምርት የሚአድገው በለሆሣሥ ሳይሆን ፤ በተጠናከረ መዋለል ፤ ከፍና ዝቅ በማለት ነው ። የካፒታሊስት ምርት የሚአድግበት ዑደታዊ አካሄድ (ጸባይ) በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለው የትብ ቅራኔ ምክንያት እና ማረጋገጫ ነው ፤ ካፒታሊዝም እራሱ በእራሱ የዕድገት መንገድ ላይ እንቅፋት የሚያስቀምጥና ፤ ሊቋቋመው ወደማይችል የሕልውና ውድቀት የሚአመራ መሆኑን ያሳያል ።

በካፒታሊስት አገሮች ፤ ከኢንዱስትሪያዊ ቀውሶች ሌላ እርሻ ነክ ቀውስም አለ ፤ ይህም :— የእርሻ ውጤቶችን ከሚፈለገው በላይ የማምረት ቀውስ ነው ።

የእርሻ ነክ ቀውስ ዋናው ጫና የሚወድቀው በሠፊው ገበሬ ላይ ነው ፤ ይህም በእነርሱ ላይ ውድመታቸውን ያመጣል ።

*የካፒታሊዝም ቀውስና የቅራኔዎች መትባት*

እንደሚታወቀው ቀውስ የሚመጣው ካፒታሊዝም እራሱ ወደ ሕልውና እንዲመጣ ያደረገውን ኃይል ለመቆጣጠር ባለመቻሉ ምክንያት ነው ። እያንዳንዱ ምጣኔ — ሀብታዊ ቀውስ ወደትብ የምርት እና የሀገርና የውጭ ንግድ መቀዝቀዝ ያመራል ።

ለምሣሌ በእንግሊዝ ውስጥ የ1929—33ቱ ቀውስ የከሰል ምርትን ከ35 ዓመት በፊት ወደ ነበረው ደረጃ አውርዶታል ፤ የአረብ ብረትን ደግሞ ከ23ዓመት በፊት እንደነበረው ፤ የብረት ውጤትን 76 ዓመት በፊትና የውጭ ንግድን 36 ዓመት በፊት እንደነበረው ፤ አድርጎታል ።

በቀውስ ዘመን ከፍተኛ ሀብት ይበላሻል ፤ ወዲያውም የሠፊው ሠራተኛ ሕዝብ ክፍል እንገብጋቢ ፍላጎቶች ሳይሟሉ ይቀራሉ ። ስለሆነም ፤ 92 የአየርና የጋዝ ማሞቂያ (የማቅለጫም) ምድጃዎች በዩናይትድ ስቴትስ በ1929 እስከ 33 ባለው ቀውስ ጊዜ ፈራርሰዋል ፤ በእንግሊዝ 72 ፤ እና በጀርመን ደግሞ 28 ከአገልግሎት ውጭ ሆነዋል ። በ1933 ፤ 10.4 ኤከር መሬት ጥጥ እንደገና ታርሷል እና ሌላም ።

በቀውስ ጊዜ በሕብረተሰብ ውስጥ እጅግ አስፈላጊው የምርት ኃይል — የጉልበት ኃይል — ጠፍቷል (ተበላሽቷል) ። ቀውስ ፤ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሠራተኞችን መንገድ ዳር ጥሏል ። የሕብረተሰቡ ዋና ኃይሎች በዘንተኝነትና ዓላማ የለሺ ሕልውናን እንዲገፉ ተገደዋል ።

ቀውስ ፤ በቡርዧዋውና በወዛደሩ መደብ ፤ በመሠረታዊው ሠፊ ገበሬ እና በመሬት ከበርቴው መደብ ፤ በገንዘብ አበዳሪዎች ፤ ወዘተ . . . . በሚበዘብዟቸው መካከል የመደብ ቅራኔውን ያባብሳል ። በቀውስ ጊዜ ወዛደሩ ካፒታሊስቶችን በመዋጋት አግኝቶት ከነበረው መብቱ ከፊሉን (ብዙውን) ይነጠቃል ወይም ያጣል ።

የወዛደሩ ሠፊው ክፍል በቀውስ ምክንያት ከፍተኛ መራቆትን እንዲሠቃይ የመደብ ንቃት እንዲአገኝ እና አብዮታዊ ቆራጥነትን እንዲማር ይገደዳል ። ሠራተኛው ፤ ከድህነትና ከረሀብ የመላቀቂያው መንገድ ምጣኔ — ሀብታዊውንና የሕብረተሰብ ሥርዓቱን መለወጥ ብቻ መሆኑን እምናበታል ። ኋላ — ቀር የሆኑት የሠራተኛው ሕዝብ ክፍል እንኳን ይህን መገንዘብ ጀምረዋል ።

ስለዚህ ምጣኔ — ሀብታዊ ቀውሶች ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም የአብዮታዊ ለውጥን ፍላጐት ፤ የቡርዧዋን ሥርዓት ቅራኔ ክትመት የሚስጠውንና ለሕብረተሰብ የምርት ኃይሎች ዕድገት ወሰኑ ይህ ነው የማይባል የተስፋ በር የሚከፈት መሆኑን ያሳያሉ ።

## ለ- ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም—ኢምፔሪያሊዝም

በ19ኛው ምዕተ—ዓመት የመጨረሻው ሲሶ ላይ ካፒታሊዝም ወደ ከፍተኛውና የመጨረሻው ደረጃ ኢምፔሪያሊዝም — ደረሰ (ተሸጋገረ) ። ይህን ደረጃ ልዩ የሚአደርገው ጸባይ የነጻ ውድድር በሞኖፖሊዎች ግዛት (አስተዳደር) መተካት ነው ፡ በዚህ ዘመን የምርት ኃይሎች በታላቅ ፍጥነት ተራምደዋል ። አዲስ ዓይነት የብረት ማቅለጥ በብረትና በአረብ ብረት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በበሴመር ፣ በማርቴንና በቶማስ አማካኝነት ተለምደዋል ፡ ይህ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ ገዥ የነበሩት ትናንሽ ክፍል የእጅ ሥራ ሱቆች ወደ ትላልቅ የብረታ ብረት ሥራ እንዲሸጋገሩ ሁኔታዎች ጥሪ አደረጉ ፡ በዚህ ዘመን ብዙ ዓይነተኛ የሳይንስ ውጤቶች (ዲናሞ ፣ የእንፋሎት ሞተር የብስል ሞተር) በከፍተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪንና የትራንስፖርትን ዕድገት ያራመዱ ተሠርተዋል ፡ በእነኝህ አዲስ ዓይነት ደጋፊ ኃይሎች በመመሰረት በኤሌክትሪክ የሚሠራ መኪና ፣ አቶሞቢል ፣ የዲዝል ባቡሮችና አውሮፕላኖች መጡ ፡ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገትም ለምርትና ለዕለት ተዕለት የኤሌክትሪክ ጥቅም መንገድ ጠረገ ፡

በቀድሞ ዘመን ፣ ቀላል ኢንዱስትሪ የበላይነት ቦታ ይዞ ነበር ፣ ግን አሁን ከባድ ኢንዱስትሪ ፊት ለፊት ተደቀነ ፡ የከባድ ኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች በፍጥነት አደጉ ፣ ስለዚህ በ1900 ዓ.ም.የዓለም የአረብ ብረት ምርት በ1897 ዓ ም ከነበረው 56 ጊዜ ፣ ዘይት 25 ጊዜ እና የከሰል ውጤት 3 እጥፍ ጊዜ አደገ ። ከፍተኛ ደረጃ ምርት የማምረት በተለይም ከ1873 ዓ.ም.ምጣኔ—ሀብታዊ ቀውስ በኋላ ላይ ገው ፈጣን እንቅስቃሴ ነበር ፡

ከዚህ የምርት ኃይሎችና የምርት ዕድገቶች ጐን ለጐን የካፒታሊዝም ቅራኔዎች መባባስ አደገ ፡ ከመጠን በላይ የማምረት ምጣኔ ሀብታዊ ቀውሶች ይበልጥ ሳያቋርጡ ተደጋገሙ ፣ ይበልጥ አውዳሚ ሆኑ ሥራ አጥነትም ማደጉን ቀጠለ ። በካፒታሊስት መንግሥታት መካከል ለሠራተኛው ሕዝብ ከዚህ በፊት ታይቶ ያልታወቀ ስቃይ ያመጡ ጦርነቶች ተካሄዱ፡፡በመሆኑም የሠራተኛው ሕዝብ ሁኔታ በሠፊው አሽቆለቆለ ፣ የካፒታሊስቶች ሀብት ይህ ነው በማይባል ሰፋት አደገ ፣ ይህም የሠራተኛውን መደብ ምጣኔ—ሀብታዊና ፖለቲካዊ ትግል አጋጋለው ።

በሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ የቡርዧዎቹ ደጋፊዎች በካፒታሊስት ዓለም ውስጥ የሞኖፖሊዎች መመሥረት ማለት በካፒታሊዝም ዕድገት ውስጥ አዲስ



ታሪካዊ ዘመን መከፈት ነው ፣ ካፒታሊዝም ከእንግዲህ የሕዝቦችን ዝንባሌ አይቃወምም ፣ « በደንብ የተቀናጀ» ... ከቀውሶች ነጻ የሆነ « ሰላም የሠፈነበት » ነው ብለው ለመግለጽ (ለማወጅ) ተጣደፉ ። ለምሳሌ ፣ ካውትስኪና ሒልፈርዲንግ የምርትን ሥርዓተ አልባነትና ጦርነቶችን በተለያዩ አገሮች በሚኖሩ ካፒታሊስቶች መካከል ስምምነት በመድረስ (በመፍጠር) ማስወገድ እንደሚቻል ተሟግተዋል ። የእነዚህ ሁሉ ንድፍ ሀሳቦች ዓይነተኛ ዓላማ የካፒታሊዝምን ቅራኔዎች ለማለባበስና ሠራተኛውን መደብ ከአብዮታዊ ትግል ለማዘናጋት ነው ።

የሠራተኛው መደብ ርዕዮተ ዓለማውያን ለአዲሱ ክስተት (በ19ኛው ምዕተ ዓመት ለካፒታሊዝም የተለመደ ጠባይ — ኢምፔሪያሊዝም) ትክክለኛ ጥናት በማካሄድ ለኢምፔሪያሊዝም ቁርጥ ያለ ሳይንሣዊ ትንተና የማቅረብ ችግር ገጥሟቸዋል ። በመጀመሪያ ደረጃ ከካፒታሊዝም ቀንበር ሥር ነጻ ለመውጣት ለሠራተኛው መደብ ትግል ትክክለኛውን የንድፈ ሀሣብ መሣሪያ ለመስጠት ይህ አስፈላጊ ነው።

ይህ የተከናወነው በሌኒን ቀዋሚ በሆነ ሥራው ፣ ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም መጨረሻ ደረጃ(1916) እና በሌሎች ጽሑፎች ነው ። ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝምን መሠረታዊ መልኮች (ጸባዮች)ይዞ እንደሚቀጥል ተናግሮአል። በኢምፔሪያሊዝም ሥር የምርት መገልገያዎች በካፒታሊስቶች የግል ባለቤትነትና በምንዳዕ ሠራተኞችና በካፒታሊስቶች መካከል የብዝበዛ ግንኙነቶች ይኖራሉ ፣ ሥርጭት (አከፋፈል) የሐብትን መጨመር ማለትም የሀብት በጥቂት ሰዎች መድለብ ነው ፣ የሌሎች ኑሮ ግን ያሽቆለቁላል ፣ በቡርዧ እና በወዛደር መካከል የተጻራሪነት ግንኙነቶች ሕልውናዎች ይቀጥላሉ ። ኢምፔሪያሊዝም የቡርዧን መንግሥት ይጠብቃል ፣ ይረዳል ።

ስለሆነም ሁሉም የካፒታሊዝም ምጣኔ ሀብታዊ ሕጐች በኢምፔሪያሊዝም ውስጥ መሥራታቸውን ይቀጥላሉ ፣ የትርፍ ዕሴት ሕግ ፣ የካፒታሊስት ክምችት ጠቅላላ ሕግ የውድድር ሕግና የምርት ሥርዓት አልባነት ፣ ወዘተ . . . ይሆንና ፣ በኢምፔሪያሊዝም ሥር ፣ የእነዚህ ሕጐች አሠራር አንዳንድ ልዩ ባሕርዮችን ግልፅ ያደርጋል ።

የሌኒን የኢምፔሪያሊዝም ትንተና የካፒታሊዝም የሞኖፖሊ ደረጃ የሚለየው በሚቀጥሉት መሠረታዊ የምጣኔ—ሀብታዊ ገጽታዎች እንደሆኑ አሳይቷል ፦— «1/የምርት መድለብና ካፒታል ሞኖፖሊዎችን በመፍጠር በከፍተኛ ደረጃ አድጐ በምጣኔ ሀብታዊ ኑሮ ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወታል ፣ 2/ የባንክ ካፒታል ከኢንዱስትሪ ካፒታል ጋር መዋሃድና በዚህ መሠረት የፋይናንስ ካፒታል መፈጠርና የፋይናንስ ገዥነት 3/ የካፒታል ወደ ውጭ መውጣት ከሸቀጦች ወደውጭ መውጣት ሲነጻጸር የተለዩ ዓይነተኛነት መኖር 4/ ዓለምን በመካከላቸው የሚቃረጡ ዓለም አቀፍ ሞኖፖሊዎች መመሥረት እና 5/ የመላው ዓለም ግዛታዊ ክፍል በትላልቅ ካፒታሊስት ኃይሎች መካከል ቀድሞውኑ የተከፋፈለ መሆኑ» 1 ነው ።

2. ካ. ማርክስና ፍ. ኤንግልስ ፣ ስለብሪቴን «ሞስኮ» ገጽ 109
1. ቪ. አይ. ሌኒን ፣ ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ከፍተኛ ደረጃ ሞስኮ ገጽ 151

ምዕራፍ ፺ ።

# የኢምፔሪያሊዝም መሠረታዊ የምጣኔ ሀብት ገፅታዎች

## 1 የምርት መድለብና ሞኖፖሊዎች

የምርት መደለብ

ከኢምፔርያሊዝም ቀደም ብሎ ነጻ ውድድር ነበር ሕጉ ።በነጻ ውድድር ዘመን አንድና አንድ ዓይነት ሸቀጥ በተለያዩ ካፒታሊስቶች ፣ እያንዳቸው ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት በሚሠሩ ይመረታል ። ነጻ ውድድር ደካሞች እንዲጠፉ ጠንካሮች ግን ሀብታምነታቸው እንዲያድግና ምርት እንዲስፋፉ አደረጉ ኤንግልስ እንዳስቀመጠው፤— «ውድድር የዘመናዊ የሲቪል ሕብረተሰብ ገዥዎችን በሙሉ በመቃዎም የሁሉም ጦርነት አጠቃላይ መግለጫ ነው ።» 2 ነጻ ውድድር ፣ ጥቂቶችን በማበልጸግ ሌሎችን ለማጥፋት በመቶና በሺ የሚቆጠሩ ሠራተኞችን በሚቀጥሩ ትላልቅ ድርጅቶች ውስጥ የምርት መድለብን አመጣ ። በዕድገቱ የተወሰነ ደረጃ ላይ የምርት መድለብ ለሞኖፖሊ መምጣት መንገድ ጠረገ ፣ እናም የመጨረሻ ዕድገቱን የኢምፔሪያሊዝም ደረጃ ላይ ደረሰ ።

ለምሣሌ በጀርመን ፣ ከ50 በላይ ተቀጣሪዎች ያሏቸው ድርጅቶች በ1882 ዓ ም አጠቃላዩን የሠራተኞች ቁጥር 22 በመቶውን ያህል ሲይዙ፤በ1895—30 በመቶውን በ1907 — 37 በመቶ ፤ በ1925—47.2 በመቶ ፣ እና በ1939 — 49.9 በመቶ ይዘው ነበር ። በምዕራብ ጀርመን በ1955 ዓ ም ተቀጥረው ከነበሩት 87. 1 በመቶ ጠቅላላ ሠራተኞች ውስጥ ይሠሩ የነበሩት 50 እና ከዚያ በላይ ሠራተኞች ቀጥረው በሚአሠሩ ድርጅቶች ውስጥ ነበር ። በዩናይትድ ስቴትስ የዓመት ውጤታቸው ከሚሊዮንና ከዚያ በላይ ብር የሆኑ ትላልቅ ድርጅቶች በ1904 ዓ ም ካለው ጠቅላላ ቁጥር 0.9 በመቶ ነበር ያላቸው ። ስለዚህ ፣ ከጠቅላላ ሠራተኞች 25.6 በመቶውን ሲቀጥሩ ፣ የሚአመርቱት ደግሞ የአማሪካንን ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ውጤት 38 በመቶውን ነው ። በ1959 ዓ ም የዩናይትድ ስቴትስ ትላልቅ ድርጅቶች ከአጠቃላዩ 5.2 በመቶውን የያዙት ከጠቅላላው ሠራተኞች 55 በመቶ ሲቀጥሩ ከጠቅላላው የኢንዱስትሪ ውጤት 67.5 በመቶውን አምርተዋል ። በ1955 ዓ ም ዩናይትድ ስቴትስ 500 የኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽኖች የኢንዱስትሪን ጠቅላላ ውጤት አጋማሽ በማምረት ከጠቅላላው ትርፍ 68 በመቶውን አግኝተዋል ። ከዚህም ትላልቆቹ 50ዎቹ ፣ ከጠቅላላው ኮርፖሬሽኖች 0.5 በመቶዎቹ በኢንዱስትሪ ውስጥ የሚካሄደውን የዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላላ ምርት ውስጥ ሩቡን ያህል በራሳቸው ውስጥ አድልበዋል ።

ዛሬ ከዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያዎች 100 ቹና ከሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች 100 ዎቹ የዓለምን ካፒታሊስት ምርት አንድ ሶስተኛውን ያህል ይቆጣጠራሉ።

ከመድለብም ሌላ ፤ ወረት(ካፒታል) ማዕከላዊ ይሆናል ። «ማዕከላዊነት» (Centralization) የተለያዩ ካፒታሎች ( ወረቶች ) አንድነት በመፍጠር ወደ አንድ የተስፋፉ (የካፒታል) ወረት ይርሰው ወረትን የሚአሳድጉበት መጠሪያ ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው ስምምነት በመፍጠር ነው ፣ ለምሳሌ የተዋሀዱ ጥቅል ኩባንያዎች ሲመሠረቱ ወይም በኃይል ፣ ትብ በሆነ የመወዳደር ትግል ትላልቅ ካፒታል (ወረት) አነስተኞችን ሲአጠፉ ወይም ትናንሽ የካፒታሊስት ድርጅቶችን ሲወስድ ነው ።



ውድድር እያንዳንዱ ካፒታሊስት ሸቀጦቹን እንዲአረክስ ያስገድደዋል ፣ ይህንም የሚሠሩት ትላልቅ ካፒታሊስቶች ናቸው ። ትናንሽ ድርጅቶች ውድድር ፣ ለመቋቋም የማይችሉ፥ ይደመሰሳሉ ፤ ወይ በትላልቅ ካፒታሊስቶች እጅ ይወድቃሉ ። ይህ ሂደት ሁል ጊዜ ይካሄዳል ። ለምሳሌ ፣ የሚቀጥሉት ቁጥሮች በ1947 እና በ1966 መካከል በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ተራቁተው የወደቁትን የኩባንያ ቁጥሮች ይሰጡናል ፡- በ1947 — 3,474 ፣ በ1954 — 11,086 ፣ እና በ1958 14,964 ነበረ ፣ በ1960 የመራቆቱ ከፍተኛ ቁጥር በዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላላ ታሪክ ውስጥ ተመዝግቦ የነበረው ከ11,000 በላይ ነው ።

የምርትና የካፒታል (ወረት) መድለብና ማዕከላዊነት በትላልቅና ግዙፍ ድርጅቶች ውስጥ በብዛት የሚቆጠሩ ሠራተኞች አንድነት እንዲሠሩ አደረጋቸው ። ይህ ለሠራተኛው መደብ ከካፒታል (ወረት) አንጻር በመቆም እንዲተባበርና እንዲደራጅ ፣ ተደራጅቶም ውጤታማ ትግል ለማካሄድእንዲችል ወደ አብዮታዊ ኃይል እንዲለወጥ መንገዱን አቃለለት ።

የምርትና የወረት መድለብና ማዕከላዊነት በከፍተኛ ደረጃ ሥራን ሕብረተሰባዊ እንዲሆን ፣ በጉልበት ላይ የወረት (ካፒታል) ኃይል እንዲጨምርና በሠራተኞችና በካፒታሊስቶች መካከል ያለውን የመደብ ትግል እንዲጠናከር አደረገ ።

የሞኖፖሊ መልኮች

የምርት መድለብ በቀጥታ የሚአመራው ወደ ሞኖፖሊ ነው ። ከፍተኛ ወረት ከበስተኋላቸው ባስከተሉ ትላልቅ ድርጅቶች መካከል በውድድሩ ትግል አንዱ አንደኛውን ድል ለማድረግ አስቸጋሪ ነው ። ግን ከነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ያሉት ጥቂቶቹ ስለሆኑና የውድድሩ ትግል ከፍተኛ ኪሣራ ስለሚጠይቅ ፣ ለትላልቅ ድርጅቶች በመካከላቸው ገበያንና የጥሬ ሀብት ምንጮችን ፣ ለማከፋፈል ተመንን ለመወሰን (ለማውጣት) ወዘተ ሲባል ስምምነት ለመድረስ የሚቻልና አስፈላጊም ነው ።

ሞኖፖሊ ምርትን በሚቆጣጠሩ ወይም የአንዳንድ ሸቀጦችን ከፍተኛውን ሽያጭ በሚቆጣጠሩ ካፒታሊስቶች መካከል ያለ ስምምነት ወይም ማሕበር ነው ። እነዚህ ማህበሮች ምንም ዓይነት መልክ ይያዙ ፣ ሁሉም የሚአልሙት ለአንድ ዓይነት ግብ ነው - ከፍተኛ ምርት ለማምረት ።

ከሁሉም በፊት የሞኖፖሊ ማሕበሮች የሚመጡት በትላልቅ (ከባድ) ኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች በተለይም ምርት በፍጥንት በሚደልብባቸው ነው ። ግን እንዴ በከባድ ኢንዱስትሪ ላይ መቆጣጠር ከቻሉ፣ሞኖፖሊዎች ወደሌላ የኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች ይስፋፋሉ ።

የሞኖፖሊ ማሕበሮች ገጽታዎች ፍጹም የተለያዩ ናቸው፤በመጀመሪያ የመሸጫ ተመንን በሚመለከት ረገድ በግለሰብ ካፒታሊስቶች መካከል የሚደረጉ የአጭር ጊዜ ስምምነቶች ናቸው ። እነኝህ የረጅም ጊዜ ስምምነትን መሠረት ይጥላሉ ። የሞኖፖሊ መሠረታዊ መልኮች ካርቴል ፣ ሲንዲኬት ትረስት እና ኮንስርን ናቸው ።

ካርቴል ፣ ገበያን ለመከፋፈልና ተመንን ለመወሰን ስምምነት ላይ የደረሱና ሊመረት የሚገባውን የምርት መጠን የሚወስኑ ካፒታሊስቶች ሕብረት ነው ። ካርቴሉን የሚመሠርቱት ድርጅቶች ሸቀጦቻቸውን አንዱ ካንዱ ነጻ በመሆን ያመርቱና ይሸጣሉ ። ይህ የሞኖፖሊ መልክ በተለይ በሠፊው ተስፋፍቶ የነበረው ከጦርነት በፊት በጀርመን እና አሁንም ሠፍና የሚታየው በጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ ነው ።

ሲንዲኬት ፣ ከፍተኛ ደረጃ የሞኖፖሊ ሕብረት ነው ። ያንድ ሲንዲኬት አባል የሆኑ ድርጅቶች ነጻ በሆነ መንገድ ሸቀጦቻቸውን ያመርታሉ ግን የንግድ (የገበያ) ነጻነታቸውን ያጣሉ ። የሲንዲኬቱ አባላት በራሳቸው ውጤታቸውን አይሸጡም ፣ ጥሬ ሀብትም አይገዙም ፣ ግን ለዚህ ተግባር ጭምር የገበያ መዋቅር ያቋቁማሉ ። ይህ የሞኖፖሊ መልክ በሠፊው ተስፋፍቶ የነበረው ከአብዮት በፊት በሩሲያ ነው ።

ትረስት ፣ የሁሉንም አባል ድርጅቶች ጭምር ባለቤትነት የያዘ ሞኖፖሊ ነው ፣ የመጀመሪያ ባለቤቶች ባላቸው ድርሻ (Share) መሠረት ትርፍ የሚወስዱ ባለድርሻዎች ናቸው ።

ኮንሰርን ፣ የትላልቅ ትረስቶች ወይም የተለያዩ የኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች ፣ ባንኮች ፣ የንግድ ተቋሞች ፣ የትራንስፖርትና የመድን ኩባንያዎች ድርጅቶች ፣ በገንዘብ በኩል በተለይ ለአንድ ትልቅ የካፒታሊስት ቡድን ጥገኛ የሆኑበት ማሕበር ነው ።

ትረስትና ኮንሰርኖች በሠፊው የዳበሩት በዩናይትድ ስቴትስ ፣ እንግሊዝ ፣ ፈረንሣይ ፣ ጃፓንና ሌሎችም አገሮች ነው ።

**በቀንደኛ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሞኖ ፖሊ ማኅበሮች**

በኢምፔሪያሊዝም ውስጥ የሞኖፖሊ ማሕበራት በካፒታሊስት አገሮች ኤኮኖሚ ላይ የበላይነት አላቸው ። ሁሉንም የኢንዱስትሪ ፣ የመጓጓዣ ፣ የንግድ ፣ የመድንና የባንክ ቅርንጫፎችን በሠፊው ይሸፍናሉ ። ይህ የሚታየው ከሚከተሉት ምሳሌዎች በጣም አይነተኛ ካፒታሊስት አገሮች በሆኑት ነው ።

በዩናይትድ ስቴትስ ፦ እዚህ የብረትና የአረብ ብረት ኢንዱስትሪ የሚገዙት በ17 ሞኖፖሊዎች ነው ፣ ማለትም በ1959 የአረብ ብረትን ፣ የአምራችነት ችሎታ 94 በመቶውን በሚቆጣጠሩት ነው ። ከነኝህ ሞኖፖሊዎች ሁለቱ ፣ የዩናይትድ ስቴትስ የአረብ ብረት ኮርፖሬሽንና የቤተልሄም የአረብ ብረት ድርጅት—የሀገሪቱን ከፊል የዐረብ ብረት ምርት መጠን ይቆጣጠራሉ ። የዩናይትድ ስቴትስ የአረብ ብረት ኮርፖሬሽን የ140 የአረብ ብረት መሥሪያዎችና 180 ማቅለጫ ምድጃዎች አሉት ፣ የሀገሪቱን ያልተጣራ ብረት ምንጭ 70 በመቶውን ሲቆጣጠሩ ፣ የራሱ የባቡር ማጓጓዣ አለው ። በዘይት ኢንዱስትሪ ትልቁ መኖፖሊ በዩናይትድ ስቴትስና ሌሎች አገሮች የዘይት ኢንዱስትሪ ላይ የገዥነት ተፅዕኖ የሚአሳድሩ 20 ኩባንያዎችን የያዘው ስታንደርድ ነው ።

የአቶ ሞቢል ኢንዱስትሪ ሶስት ትላልቅ ሞኖፖሊዎች አሉት ። ጄኔራል ሞተር፣ ፎርድና ክሬይስለር፣ ማለትም በ1958 ዓ.ም. በዩናይትድ ስቴትስ 93 በመቶውን መኪና የሠሩት ናቸው ። እነኝህ ሶስት ሞኖፖሊዎች የጦር መሣሪያዎችና ጥይቶች አምራቾችም በመሆን ዓይነተኛ ናቸው ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሁሉንም የዩናይትድ ስቴትስን የሞተር ትራንስፖርት ፣ 75 በመቶውን የአውሮፕላን ሞተር ፣ 40 በመቶውን ታንክና 30 በመቶውን መድፍ ፣ አውቶማቲክ ጠብመንጃ ፣ አውቶማቲክ መሣሪያስ ፣ ወዘተ . . . አምርተዋል ።



በእንግሊዝ ታላላቅ ሞኖፖሊዎች እንደዩናይትድ ስቴትስ ሁሉ ምጣኔ ሀብቱን ይገዛሉ ። የእንግሊዝ የብረትና የዐረብ ብረት ፌዴሬሽን ፣ ለምሳሌ ፣ ሁሉንም የሀገሪቱን ዓይነተኛ የብረትና የዐረብ ብረት ኩባንያዎችን ያጣምራል ። ትልቁ መኖፖሊ ማለትም ከሌሎች ድርጅቶች ውስጥ የመሣሪያዎችን ወታደራዊ ትጥቆችን ፣ ወታደራዊና የሲቪል መሀንዲስነትና መርከብ ሥራን ፣ የበራራና የአየር መቆጣጠሪያን ፣ እንዲሁም የኤሌክትሪካዊ መሀንዲስነትን ፣ የሚቆጣጠረው አርምስትሮንግ - ቬከርስ የተባለው መሣሪያ ተቋም ነው ።

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ትልቁ ሞኖፖሊ የመሠረታዊ ኬሚካሎችን ምርት 95 በመቶውን ፣ የናይትሮጂን ውጤት 95 በመቶውን ፣ የማቅለሚያን (መንከሪያን) 40 በመቶውን የሚቆጣጠረውና ፣ ለወታደራዊ ተግባሮች ዋና የኬሚካል አምራች የሆነው ኢምፔሪያሊዝም የኬሚካል ኢንዱስትሪ ነው ። የኢምፔሪያል የኬሚካል ኢንዱስትሪ ከሌላ ዓይነተኛ የእንግሊዝ ኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች በተለይ ከመሣሪያ አምራች ተቋሞች ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው ።

በፈረንሣይ አንድ ሞኖፖሊ ጠቅላላውን የአሉሚኒየም ምርት በድርጅቶቹ ውስጥ አካብቷል ። አንድ ሞኖፖሊም 80 በመቶውን የቀለም መንከሪያ ውጤት ይቆጣጠራል ። 90 በመቶ የሚሆነው የመኪና ምርት የተካበተው በአራት የሞኖፖሊ ድርጅቶች ነው ።

በምዕራብ ጀርመን ፣ አንድ በጣም እጅግ ግዙፍ ሞኖፖሊ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ ላይ 370 ኩባንያዎች የተቆጣጠረና በጀርመንና በሌላም ቦታ 220 ቅርንጫፎች ያሉት የጀርመን የዓረብ ብረት ትረስት የሚባሉት ነበር ፤ ከጦርነቱ በኋላ በአሜሪካን ካፒታል (ወረት) ዶጋፊነት እንደገና የተቋቋመና አሁንም የአውሮጳውያን ማኅበረ-ሰብ የከሰልና የዐረብ ብረት ማሕበር ዓይነተኛ አባል ነው ። ሌሎች ግዙፍ ሞኖፖሊዎችም ፣ ክሩፖ ፣ ቴይሴን ፣ ወዘተ ... እንደገና የተጠናከሩት ከጦርነቱ በኋላ ሲሆን አሁን መሣሪያዎችና የዐረብ ብረት ያመርታሉ ። በኬሚካል ኢንዱስትሪ ገዥው ሞኖፖሊ አይ. ጂ. ፋርበን ኢንዲስትሪ ሲሆን ፣ ይህም በጦርነቱ መጨረሻ 380 ፋብሪካዎች በጀርመንና 500 ኩባንያዎች በሌሎች አገሮች ተቆጣጥሯል ። አይ ጂ. ፋርበን ኢንዱስትሪ አሁን እንደገና የቀድሞ ምጣኔ ሀብታዊ ቦታውን አኝቷል ።

ትላልቅ ሞኖፖሊዎችም የገዥነት ቦታ በኢጣልያ ፣ በጃፓን ፣ በቤልጂግና ሌሎች አገሮች ይዘዋል ።

**ሞኖፖሊዎችና ውድድር**

የቡርዧ ርዕዮተ— ዓለማውያን ሞኖፖሊ ውድድርን ያጠፋል የሚል አስተሳሰብ አላቸው ። እንደእውነቱ ከሆነ ግን ሞኖፖሊዎች ውድድርን አያስወግዱም ። አብረው ጎን ለጎን ይኖራሉ እንጂ ።

በመጀመሪያ ፣ ሞኖፖሊዎች የካፒታሊስት ምጣኔ ሀብቶችን ቢገዙም የጠቅላላው ኢንዱስትሪ መቶ በመቶ ሞኖፖሊአዊነት አልፎ አልፎ ነው ያለው ። ስለዚህ በሞኖፖሊዎችና የእነዚህ አባላት ባልሆኑት ካፒታሊስቶች መካከል (የውጮቹ ተብለው በሚታወቁት ) የውድድር ትግል አለ ። በዚህ ውድድር ሞኖፖሊዎች የውጮቹ ተብለው የሚጠሩት ከምኖፖሊዎቻቸው እንዲዋሃዱ በሚችሉት መንገድ ሁሉ ይጠቀማሉ ፣ ያለዚያ አማራጩ ፍጹም መጥፋት ይሆናል ።

ሁለተኛ ፣ ውድድር በሞኖፖሊዎች መካከል ይካሄዳል ። የካርቴልና የሲንዲኬት አባላት ለተሻለገበያ ፣ ለበለጠ የምርት ድርሻ እርስ በእርሣቸው ይታገላሉ ። በትረስቶችና ኮንሰርኖች ፣ ካፒታሊስቶች በቁልፍ ቦታዎች ላይ በመቆጣጠር ላይ እና በምርት ሥርጭት ላይ ይዋጋሉ ። በሞኖፖሊዎች ውስጥ ያለትግል ድብቅ ሆኖ ከመሔዱ ይልቅ ይፋ የተለመደ ነው ፤ እናም በአጋጣሚ ምክንያቶች ግልፅ

ሆኖ ይወጣና ወደ ሞኖፖሊው መበታተን ያመራል ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የቀድሞውን ለመተካት አዲስ ሞኖፖሊ ይመሠረት ይሆናል ።

ሶስተኛ ፣ በአንድ የኢንዱስትሪ ቅርንጫፍ ውስጥ ባሉ የተለያዩ መኖፖሊዎች መካከል ከአንድ በላይ ከሆኑ ውድድር አለ ።

አራተኛ ፣ በኢምፔሪያሊዝም ዘመን ውድድር፣ በተለይ በተለያዩ የኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች በሚገኙ ሞኖፖሊዎች መካከል ይባባሳል ፣ ለምሳሌ በከሰል ሞኖፖሊዎችና የብረትና የአረብ ብረት ሞኖፖሊዎች ማለትም እርስ በርሳቸው በሚደጋገፉት መካከል መሆኑ ነው ።

የቡርዧ ርዕዮተ ዓለማውያን «ሞኖፖሊ» ማለት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዕቅዳዊ ዕድገት ነው የሚለውአስተሳሰብ ፍጹም ሀሰት ነው። ምንም እንኳ ሞኖፖሊ ከነጻ ውድድር ውስጥ የመጣ ቢሆንም፣ ውድድርን አያጠፋም አብሮ ይኖራል እንጂ፤ በሞኖፖሊዎች ሕግ ውስጥ ውድድር ኋላ ቀርና ስግብግብነት ተወዳዳሪን ማንቅና ገንዘብን የሙጥኝ መያዝ፣ ጉቦ፣ ሕቡዕና ቀጥተኛ ኃይል በተግባር ይውላሉ ።

«ኢምፔሪያሊዝም ውድድርን አያስወግድም ። እንዲያውም ኢምፔሪያሊዝም የውድድርና የሞኖፖሊ ተቃራኒ መርሆዎች ውህደት (ጥምረት) ነው ። ስለሆነም ይህ ነው ለመውደም ለመጨማተሩና ለሶሻሊስት አብዮት መንገድ የሚጠርገው»[1]

## 2 ገንዘ ፊዊ ወረትና የገዘብ ገዥነት (Financial Oligaray)

በባንክ ውስጥ ሞኖ ፖሊዎችና የወረት መድለብ

የምርት መድለብና በኢንዱስትሪውስጥ የመኖፖሊዎች መመሥረት የወረት ባንክ ውስጥ መድለብና የባንክ ሞኖፖሊዎችን ወደ መፍጠሩ አመራ። በባንኮች መካከል ኃይለኛ ውድድር ያከተመው ትላልቆቹ ትንንሾቹን በመውሰድ ነው ። ትላልቅ ባንኮች ስምምነቶችን ይዋዋላሉ ፣ ስለዚህ የባንክ ሞኖፖሊዎች ብቅ አሉ ። ትናንሽ ባንኮችን የቁጠባ ባንኮችንና የብድር ማሕበራትን አፍነው ያዙ።እያንዳንዳቸው የባንክ ሞኖፖሊዎች በ20 ወይም በመቶ የሚቆጠሩ ትናንሽ ባንኮችን ይቆጣጠራሉ ። የባንክ ኮንሰርኖች በጣም ይዳብራሉ.የውጪት ድግግሞቻቸውም ይበዛሉ ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ በ1900 ዓ. ም. 10,382 ባንኮች በ$ 10785 ሚሊዮን መጠባበቂያ ጋር በ1940 ዓ. ም. 15,017 ባንኮች ከ$ 80,213 ሚሊዮን መጠባበቂያ (Assets) ጋር ነበሩ ። ስለዚህም በ40 ዓመት ጊዜ ውስጥ የባንኮች ቁጥር 50 በመቶውን ብቻ ነው የጨመረው፣ግን መጠባበቂያዎቹ 8 እጥፍ ነው ያደጉት ። በ1900 ዓ ም ከትላልቆቹ ባንኮች 20 ዎቹ በዩናይትድ ስቴትስ ከጠቅላላው የባንክ ተቀማጭ 15 በመቶውን ሲይዙ ፣ በ1956—31 በመቶውን ደርሰዋል ። በእንግሊዝ ፣ የአምስት ትላልቅ ባንኮች የአንድነት ሚዛን በ1900 ዓ ም ሁሉንም የባንክ ተቀማጭ ጠቅላላ ሚዛን 28 በመቶውን ይዞ ነበር ፣ በ1952 ዓ ም 70 በመቶውን ሆኖአል ።

በባንክ ውስጥ መድለብና የባንኮች ሞኖፖሊ መመሥረት በባንክና በኢንዱስትሪ መካከል የግንኙነት ለውጥ አመጣ ።

የባንኮች አዲሱ ሚና

በመሠረቱ ፣ ባንኮች ፣ ክፍያን ለማካሄድ ቀላል አማካይ አለዋዋጮች ነበሩ፣ ካፒታሊዝም እየዳበረ ሲሄድ የባንኮች የዱቤ አሠራር ይስፋፋል ፣ ባንኩ ወረት(ካፒታል) የሚወስደው ለተወሰነ ጊዜ ገንዘቡን ከማይጠቀምበትና ገንዘቡን ለሚፈልጉት ሰዎች ብድር ከሚሰጠው ካፒታሊስት ነው ። የባንክ ክምችትና ማዕከላዊነት ባንኮች ሠፊ ምጣኔ ሀብታዊ ሥልጣን በጠቅላላው ኢኮኖሚ ላይ እንዲይዙ የሚያስችል ሁኔታ ላይ ያደርሳል ።

1. ቪ. አይ ሌኒን ግቁል ሥራዎች ፣ ሩሲያ ፣ ንትሞ ፣ ትዝ 24 ፣ ገጽ 427



ትላልቅ ባንኮች የካፒታሊስቶችን ዕለታዊ (ጊዜአዊ) ተንቀሳቃሽ ሂግብ ሲአዙ ስለደንበኞቻቸው ሁኔታ ዕውቀት ይኖራቸዋል ፣ በእነሱ ላይ ቁጥጥርን ያካሄዳሉ ፣ እናም ዱቤን በቀላሉ ለማግኘት በማስቻል ወይም ለማግኘት አስቸጋሪ በማድረግ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶችን በጥገኝነት ደረጃ በማስቀመጥ ክንዋኔአቸውን ይመራሉ ።

ስለዚህ በክፍያ አደማሱ ውስጥ ጤናማ አለዋዋጭ በመሆን ባንኮች ሁሉ—ገብ ኃይል ያላቸው ገንዘባዊ ማዕከሎች ይሆናሉ ።

ይህ የባንኮች ወደ ሁሉ—ገብ ኃይል ወዳላቸው ሞኖፖሊዎች መሸጋገር በሠፊው የምርት መድለብን ያፋጥናል ። ይህ የሚሆነው ምክንያቱም ባንኮች በመጀመሪያና ከሁሉም በላይ በሞኖፖሊዎች ውስጥ ለተባበሩት ድርጅቶች ዱቤ ስለሚሰጡ ነው ። ይህን የሚአደርጉበት ምክንያት እነኛ ሞኖፖሊዎች አድገው ከባንኩ ዝንባሌ ጋር በመስማማት ድርሻ እንዲገዙ ይሆናል በሚል ነው ። በሞኖፖሊው ውስጥ ወሳኝ የሆነ ድምፅ እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ በቂ ድርሻ (ዕጣ) ይገዛሉ።

ገንዘባዊ ወረት Finance Capital

ስለገንዘባዊ ወረት አፈጣጠር ሌኒን ሲጽፍ « የምርት መድለብ ፣ ከርሱም የሞኖፖሊዎች መምጣት ፣ የባንክ ከኢንዱስትሪ ጋር መዋሃድ ነው ።እንዲህ ነው የገንዘባዊ ወረት የአነሳስ ታሪክ ፣ ይህነው የዚህም አጠራር ይዘት ።»[1] ይላል ።

ባንኮች ፣ የኢንዱስትሪ ፣ የንግድ ፣ የማመላለሻ ፣ የመድንና የሌሎች ሞኖፖሊዎች ዕጣዎች ይገዙና ተጨማሪ ባለቤቶች ይሆናሉ ። የኢንዱስትሪ ሞኖፖሊዎች በተራቸው ደግሞ ከተሳሰሩባቸው ባንኮች ዕጣዎች ይኖሯቸዋል ። ውጤቱ የሞኖፖሊ ባንክና የኢንዱስትሪ ወረት መዋሃድ ወይም መታታት ነው ። በዚህ መሠረት አዲስ ዓይነት ወረት ይመጣል — ገንዘባዊ ወረት የሚባል ።

የኢንዱስትሪና የባንክ ወረት መዋሃድ የተለያዩ መልክ አለው ። ከሁሉ ቀድሞ ይህ የሚንጸባረቀው በግላዊ ሕብረት ውስጥ ነው ። ማለትም ባንኩን የቀድሞ ባለቤቶች እንበልም የኢንዱስትሪ ፤ የንግድና ሌሎችም ሞኖፖሊዎች ሲመሩት መሆኑ ነው ። የባንክ መሪዎች በኢንዱስትሪ ሞኖፖሊዎች አመራር ቦታ ሲሰጣቸው የኢንዱስትሪ ሞኖፖሊ ፣ ተወካዮች በተራቸው በባንኩ ውስጥ የመግዛት ሥልጣን ይኖራቸዋል ።

ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ 400 የሚሆኑ ጥቂት ኢንዱስትሪያሊስት ቡድኖችና ባንከኞች በ250 ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች 1,200 የዲሬክተርነት ሥልጣን ቦታ አላቸው። የዚህ ዓይነት ቅንጅት ዓይነተኛ ምሳሌ ላውሬንስ ሮኪፌለር ማለትም ከ10 የተለያዩ ኩባንያዎች በላይ ዲሬክተር የሆነው ነው ።

በፈረንሣይ ፣ የትልቅ ባንክ ዲሬክተሮች የፓሪስ ባንክ ፣ በኩባንያዎች ቦርድ ውስጥ 190 የሥልጣን ቦታዎች ይዘዋል ፤ እነኚህም በተራቸው የቅርንጫፎችና የጥገኞች መረባዊ አሠራርን ይቆጣጠራሉ ።

በጀርመን ፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ፣ በጣም ትልቁ የጀርመን (ዶቼ) ባንክ 54 ተወካዮች በተለያዩ ብዙ ኩባንያዎች 707 የዲሬክተርነት ቦታ ሲይዙ ፣ በ1958 ደግሞ የዚሁ ባንክ 48 ተወካዮች በ126 ትላልቅ የምዕራብ ጀርመን ኩባንያዎች 662 ቁልፍ ቦታዎችን ይዘዋል ። የባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ሽርማን እስከ 40 የአማካሪ ኮሚቴዎችና የባንክ ቦርዶች ፣ የንግድና የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ይዟል(ይህ ሰው በሂትለር ውስጥ 42 ቦታዎች ይዞ ነበር ።)

1. ቪ. አይ ሌኒን ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ከፍተኛው ደረጃ ገጽ 76

የገንዘባዊ አገዛዝ የበላይነት ለገንዘባዊ ወረት ተጨባጭ መግለጫው ነው ።

የገንዘባዊ አገዛዝ

የሞኖፖሊዎችና የገንዘባዊ ወረት ዕድገት የሚታየው የሀገራቸውን ምጣኔ ሀብትና ፖለቲካ ጠቅላላ ሕይወት በእጃቸው በማድለብ የግለሰቦችን አነስተኛ ክበብ በፈጠሩ ትላልቅ ባንከኞችና ኢንዱስትሪያሊስቶች ነው ። ገንዘባዊ አገዛዝ ፤ማለትም፣የጥቂት ባለገንዘቦች የበላይነትና ሥልጣን ፣ አሁን መታየቱን ይጀምራል።ሁሉም የምጣኔ ሀብቱ ዓይነተኛ ቅርንጫፎች፣በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ሁሉም የፖለቲካዊ መዋቅሩ ቁልፍ ቦታዎችም በገንዘባዊ አገዛዝ ሥር ናቸው ።

ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ በኤኮኖሚው ውስጥ ወሳኙ ሚና የሚካሄደው በስምንት ገንዛባዊ ቡድኖች ነው፡- ሞርጋን ፣ ሮኪፌለር ፣ ዱፖንት ፣ ሚሎን ፤ የአሜሪካ ባንክ ፣ የቺካጎ ባንክ ፣ የክሊቭ ላንድ ባንክ ፣ እና የመጀመሪያው ብሔራዊ ከተማ ባንክ በሚባሉት ። በ1955 በእነዚህ ገንዘባዊ ቡድኖች ቁጥጥር ሥር የነበረው ጠቅላላ ወረት 218,500 ሚሊዮን ዶላር ነበር ። ከነዚህ ቡድኖች ትላልቆቹ የሞርጋንና የሮኪፌለር ናቸው ። በ1955 የሞርጋን የተዕዕኖ አድማስ (ክልል) ባንኮችና ኮርፖሬሽኖችን 65,300 ሚሊዮን ብር ከሆነ ወረት (ካፒታል) ጋር ወስዷል ። ከነኝህ መካከል 5ቱ ትላልቅ ባንኮች ፣ 14 የባቡር ሐዲድ ኩባንያዎች ፣ ብዙ የቴሌኮሙኒኬሽን ሞኖፖሌዎች ፣ የዩናይትድ ስቴትስ የአረብ ብረት ኮርፖሬሽን ፤ ጠቅላላ ኤሌክትሪክ ፣ ወዘተ . . . ናቸው ። በዚሁ ዓመት የሮኪፌለር የተፅዕኖ ክልል ወደ ባንኮችና ኮርፖሬሽኖች በመስፋፋት 61, 400 ሚሊዮን ዶላር ጋር አድጓል ፣ ይህም ሠፊውን የስታንድርድ ዘይት ሞኖፖሊን ፣ የባቡር ሐዲድ ፣ የዐረብ ብረትና ሌሎች ሞኖፖሊዎችን ይጨምራል ። በዩናይትድ ስቴትስ ባለቢሊዮንና ሚሊዮኖች ፣ የጠቅላላውን ሕዝብ 1 በመቶ የሚሆኑቱ ፣ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሀብት 60 በመቶውን ይቆጣጠራሉ።

በእንግሊዝ ፣ ስምንት ገንዘባዊ ቡድኖች በሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ላይ ወሳኞች ናቸው ። ዋና ኢንዱስትሪዎችን ይቆጣጠራሉ እናም የምጣኔ ሀብታቸውን ድርቅድሞ የእንግሊዝ ክፍል በነበሩት ግዛቶች ላይ ያስጠብቃሉ ።

የገንዘብ አገዛዝ ሕግ የሌሎችም ካፒታሊስት አገሮች ጸባይ ነው ።

የገንዘባዊ አገዛዝ ቁጥጥሩን የሚአውለው«የይዞታ ሥርዓት» በሚባል በምጣኔ ሀብት መልክ ነው ። ሥርዓቱ የሚሠራው እንደሚከተለው ነው ፣-አንድ ትልቅ ባለገንዘብ (ወይም ገንዘብ ያላቸው ቡድኖች) በራሱ የመቆጣጠር ዝባሌ ወይም በሌላ ዘዴ ፤

እንደ«ወላጅ(ተራቢ)ኩባንያ» (Parent Company) የሚሠራውን ዋና የተዋሀደ ጥቅል ኩባንያን ለመቆጣጠር ይበቃል ። ይህ ኩባንያ በሌሎች ኩባንያዎች ውስጥ ዕጣዎች ይወስዳል እናም፣በእነዚህ ውስጥ የዝንባሌውን ቁጥጥር ሲይዝ እንደበላይ ወይም የወላጅ ኩባንያ አዝማሚያን በመያዝ ቁጥጥሩን «እንደልጅ ኩባንያዎች (Daughter Companies) » በመመልከት ሲወስደው ፣ እነሱም በተራቸው « የልጅ ልጅ » ኩባንያን (Grand daughter Companies) »ወዘተ . . . እያሉ ይቆጣጠራሉ ። በዚህ የመቆጣጠር ሥርዓት ባለሺ ሚሊዮን ወረት ያለው ባለገንዘብ ተፅዕኖውን በ8ሺ ሚሊዮን ወረት ላይ ሊዘረጋ ይችላል ። በዚህ ዓይነት ዘዴ የቁጥጥሩ ስፋት ከንዋኔ በትላልቅ ወረት ካፒታሊስቶች በማከታተል እየጨመረ ነበር ። ዘዴውን ስንመለከተው ታላላቅ የገንዘብ « ንጉሶች » አንድነት በመሆን ብዙ ታሪካዊ ፒራሚዶችን የመገንባት ያህል ነው ።

የገንዘባዊ አገዛዝ በተጨማሪም በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ መንግሥታዊ መዋቅሩን በሥሩ በማድረግ ፖለቲካዊ ኑሮውንም ይገዛል ። ስለሆነም መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ማደግ ይጀምራል ።

## 3 የወረት ወደውጭ መውጣት—የዓለም ምጣኔ—ሀብታዊና ግዛታዊ ክፍፍል ።

የወረት ወደ ውጭ መውጣት

ከኢምፔሪያሊስት ዘመን በፊት ፣ በሀገሮች መካከል ዋናው የውጭ ምጣኔ ሀብታዊ ግንኙነት መልክ የውጭ ንግድ ማለትም የሸቀጦች ወደውጭ መላክ ነበር ። በኢምፔሪያሊዝም ደግሞ ፣ የዓለም ንግድ ይስፋፋል ፣ ግን የወረት (ካፒታል) ወደ ውጭ መውጣት ዓይነተኛነት ይኖረዋል ። የወረት ወደ ውጭ መውጣት ለሠፊው የካፒታሊስት ዓለም ክፍል በጥቂት ትላልቅ ኢምፔሪያሊስት አገሮች የመበዝበዝ መሠረት ነው ።

ነጥቡ ፣ ሞኖፖሊዎች በሚገዙበት ጊዜ እጅግ ከፍተኛ ዕድገት ያላቸው ካፒታሊስት አገሮች«ትርፍርፍ» ወረት ከማካበቱ ላይ ነው። እርግጥ ሞኖፖሊዎች ወረታቸውን የሠራተኛውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግና እርሻን ዘመናዊ ለማድረግ ከተጠቀሙበት « መትረፍረፍ » ሊኖር አይችልም ። ግን በዚያ መልክ ካፒታሊዝም «ካፒታሊዝም» ሊሆን አይችልም ። የካፒታሊስቶች ዓላማ ወረታቸውን ከፍተኛ ትርፍ ሊአገኙ በሚችሉበት ቦታ ማዋል ነው ።

ወረት ወደ ውጭ የሚወጣው በሁለት መልክ ነው ። የብድር ወረትና የምርት (አምራች) ወረት በሚባሉ ። የብድር ወረት ወደውጭ መውጣት የሚከናወነው ለአንድ መንግሥት ወይም ለሌላ አገር ካፒታሊስቶች ብድር ሊሰጥ ሲቻል ነው ። ብድሩን የሚቀበለው አገር ለተበደረው አራጣ መክፈል ይኖርበታል ። በዚህ ሁኔታ በዚያ በተበዳሪ አገር ሠራተኞች የተፈጠረው ትርፍ ዕሴት በአራጣ መልክ ወረቱን ወደውጭ ለላከው አገር ይላካል ።

የአምራች ወረት (ካፒታል) ወደ ውጭ መውጣት የሚከናወነው ካፒታሊስቶች በሌሎች አገሮች ውስጥ ኢንዱስትሪያዊ ድርጅቶችን ፣ የባቡር ሐዲዶችን ፣ ወዘተ ...ሲመሠርቱ ነው ። ይህ የሚካሄድው በሚከተለው ሁኔታ ነው ። ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የተዋሃደው ጥምር ኩባንያ የተመሠረተው በላቲን አሜሪካ አገሮች ውስጥ የዘይት ጉድጓዶችን ለመቆፈር ሲባል ነው ። የሚሸጡት ዕጣዎች የሚገዙት በአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ነው ። ከዕጣዎቹ ሺያጭ የሚገኘው ወረት በሚመለከተው ሀገር ሌላ ድርጅት ለማቋቋም ይውላል ። ግን ከዘይት ጉድጓዶች የሚገኘው ትርፍ ለባለ ድርሻዎቹ ይሄዳል ፣ እንበል ለአሜሪካን ካፒታሊስቶች ። በሁሉም መንገድ ወረት ወደውጭ የሚወጣው ከፍተኛ የሞኖፖሊ ትርፍ ለማስገኘት ነው ።

ወረት ወደውጭ የሚወጣው በይበልጥ በምጣኔ ሀብት ወደ ኋላ ለቀሩ አገሮች ይሆናል።እነዚህ አገሮች ያላቸው በጣም ትንሽ ወረት ነው፣መሬታቸው ርካሽነው፤በሠፊው ጥሬ ሀብት ሲኖራቸው የሠራተኛ ምንዳም ዝቅተኛ ነው ። ይህ ሁሉ ወረትን እዚያ በማዋል ይበልጥ ትርፋማ ያደርጋል ። በአሁኑ ወቅት በጣም የተጠናከረ የወረት ወደ ውጭ መውጣት ወደ አፍሪካ ፣ ላቲን አሜሪካ አገሮች ፣ መካከለኛው ምሥራቅ ነው የሚታየው፣ግን ወረት በተጨማሪም በኢንዱስትሪ ወደ በለጸጉ አገሮችም ይወጣል ። ስለዚህ የወረት ወደውጭ መውጣት ለተቀባዩም ሆነ ለላኪው አገር መጥፎ ውጤት አለው ።

ወረትን ወደሀገር ውስጥ በሚአስገቡ አገሮች ውስጥ በካፒታሊዝም ውስጣዊ ቅራኔዎች በሙሉ እየጨመረ የሚሄድ የካፒታሊስት ዕድገት አለ—የብዙሀን መራቆትና መጥፋት ፣ የመሬትንና ሌላ የብሔራዊ ሀብት መልኮችን በስስታምነት በሠፊው የማጋበስ የመሳሰሉ ሁኔታዎች ይታያሉ ። ኋላቀር የሆኑ አገሮች ምጣኔ ሀብት የሚአደገው የውጭን ወረት ፍላጎት ለማሟላት በተበለሸሸ ፤ በአንድ ዓይነት መንገድ ነው ። የማዕድን ኢንዱስትሪ በተለይ ለዕድገት ይመረጣል ።

ወረት ወደ ውጭ በሚልኩ ሀገሮች ውስጥ ፣ እንዲህ የማድረጉ ሁኔታ ሁለት መልክ አለው ። ባንድ በኩል ፣ እነዚህ አገሮች በሀብታቸው ላይ ይጨምሩበታል ፣ ማለትም ፣ በሌሎች አገሮች ውስጥ ካሏቸው ድርጅቶች ከውጭ ትርፍ ዕሴት በትርፍ መልክ ያገኛሉ ወይም ከብድር አራጣ ። በሌላ መንገድ ፣ የምርታቸው ዕድገት ይጐተታል ፣ ማለትም የወረት ወደውጭ መውጣት በእናት ሀገር ውስጥ ወረትን የማዋል (የማሠራጨት) መንገድ ያግዳል ።

የካፒታል ወደ ውጭ መውጣት በሀገሮች መካከል ወደ ሠፊ የምጣኔ ሀብት ግንኙነት ያመራል ። ግን እነኚህ ሠፊ ግንኙነቶች ኋላ ቀር የሆኑ አገሮች በምጣኔ ሀብት በገፉ አገሮች መበዝበዝን ነው የሚአመለክቱት ። ስለዚህ ፣ የወረት ወደ ውጭ መውጣት የኢምፔሪያሊስትን የጨቋኝነትና የገዥነት ዘዴንነው የሚፈጥረው።

የቡርዧ ርዕዮተ ዓለማውያን በኢምፔሪያሊዝም ዘመን የወረት ከሀገር ውጭ መውጣት « የዕርዳታ » መልክ ነው ፣ ኋላ ቀር ለሆኑ አገሮች « ዳረጐት » ነው ለማለት ይሞክራሉ ። በባሕሪው ኢምፔሪያሊዝም ምናልባት የቅኞችን የኢንዱስትሪ ዕድገት ሳያራምድ አልቀረም ፣ በገዥዎቻቸው ዘንድ የነበራቸውን ጥገኝነት ገዝቅ አድርጓል ፣ እንዲሁም ነጻ አውጥቷቸዋል የሚል የነጻነት ንድፈ-ሀሳብ ቀርቦ ነበር። የንድፈ ሀሳቡ ዓላማ የኢምፔሪያሊስት የወረት ወደ ውጭ ማስወጣት ካባ ለማልበስ ነው ። እንደእውነቱ ከሆነ የወረት ወደ ውጭ መውጣት የነጻ መውጣት መልክ ሳይሆን ግን ፣ አንዳንድ አገሮች ሌሎች አገሮችን የሚይዙበት « የተጨፈኑ ላሞኛችሁ » ተረት ነው ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በወረት ወደ ውጭ መውጣት ላይ አንዳንድ አዳዲስ ገጽታዎች ተከሠቱ። ነገሩ ፣ ብዙ አገሮች በአውሮጳና በእስያ ከካፒታሊዝም ቀንበር ሥር ሰብረው መውጣት ማለት ለካፒታሊስት መዋዕል ንዋይ ክፍት የነበሩት አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሱ መሄድ ነው ።

ያልተስተካከለው የወረት ወደ ውጭ መውጣት ይበልጥ ግልፅ እየሆነ መጣ። በአንፃሩም በእንግሊዝና በፈረንሣይ አዘቀዘቀ ። በዩናይትድ ስቴትስ በሌላ በኩል ፣ እጅግ አደገ።በ1949 ዓ.ም ከሀገር ውጭ የአሜሪካን ወረት መዋዕለ ንዋይ የሌሎች ካፒታሊስት አገሮች ሁሉ ተዳምሮ ከሚሆነው በላይ ነበር ። በ1939 እና በ1955 የዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላላ የውጭ መዋዕለ ንዋይ ወደ አራት ጊዜ ፣ እጥፍ አደገ ።

ዩናይትድ ስቴትስ በመንግሥታዊ ብድርና ዱቤ መልክ ወደ ኋላ ለቀሩ የላቲን አሜሪካ፣ እስያና አፍሪቃ እንዲሁም እጅግ በኢንዱስትሪ ለበለጸጉ አውሮጳ አገሮች ለእንግሊዝ ፣ ፈረንሣይ ፣ ምዕራብ ጀርመን ወዘተ . . . እጅግ ብዙ የሆነ ወረት (ካፒታል) ትልክ ነበር ። ዩናይትድ ስቴትስ የጠቅላላ ካፒታሊስት አገሮች የገንዘባዊ ብዝበዛ ማዕከል ነች ።

መንግሥታዊ ብድሮችና ዱቤዎች ፖለቲካዊና ወታደራዊ እንዲሁም ምጣኔ ሀብታዊ መልኮች አሏቸው ።

በወረት ወደውጭ መውጣት አማካኝነት እጅግ የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ገንዘባዊ ገዥዎች ወረቱን ወደሀገራቸው የሚአስገቡ አገሮችን ጠቅላላ ምጣኔ — ሀብታዊ ኑሮ በቁጥጥራቸው ሥር ለማምጣት ይመኛሉ ።

ሁሉም ኢምፔሪያሊስት አገሮች ወረታቸውን በሥራ ላይ በማውለት ከፍተኛ ትርፍ ሊአስገኙ ወደሚችልባቸው አገሮች ለመላክ ይሞክራሉ ። ይህ ደግሞ በካፒታሊስቶች መካከል ብቻ ሳይሆን ግን በኢምፔሪያሊስቶችም መካከል ጭምር ውድድርን ያመጣና በሞላ የካፒታሊስት ዓለም ውስጥ ቅራኔዎችን ያባብሳል ።



#### በካፒታሊስት ማኅበሮች መካከል የዓለም ምጣኔ ሀብታዊ ክፍፍል

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያሉ ሞኖፖሊዎች ለመጀመሪያና ከሁሉም በላይ የሚታገሉት በአገር ውስጥ ገበያ ተካፋይ የሌለው የበላይነት ለማግኘት ነው ። የአገር ውስጥን ገበያ ይከፋፈላሉ ፣ ከፍተኛ ተመን ያወጡና እጅግ ሰፊ ትርፍ ያካብታሉ ። ከፍተኛ ተመንን ለማቆየት ፣ ሞኖፖሊዎች የአገር ውስጥን ገበያ ከውጭ ውድድር ይከላከላሉ ። ለዚህ ተግባር መንግሥታት ( የሞኖፖሊዎች ) የገቢ ቀረጥን ከፍ አድርገው ይወስናሉ ፣ አንዳንዴም አንዳንድ ሸቀጦችን እንዳይገቡ ያግዳሉ ። ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦች ቀረጥ ሁልጊዜ ከራሳቸው ከሸቀጦች ዕሴት ያይላል ። በዚህ መንገድ የሞኖፖሊዎች የሀገር ውስጥ ገበያ የበላይነት ይረ ጋገጣል ።

ግን የአገር ውስጥ ገበያ ውሱን ነው ። ከትላልቅ ኮንሰርኖች በሰፊው ከሚወጡት ሸቀጦች ጋር የሚመጣጠን አይደለም ። ስለዚህ ሞኖፖሊዎች በውጭ ገበያ ላይ እንዲሸጡላቸው የበለጠ ጥረት ያደርጋሉ ። ግን እነኚህ ገበያዎች በገቢ ሸቀጦች ቀረጥ ከታጠሩ ይህን እንዴት ሊአደርጉ ይችላሉ ?

ከፍተኛ የገቢ ሸቀጥ ቀረጥን ለማስወገድ ወረትን ወደውጭ ያወጣሉ ። ካፒታሊስቶች በሌሎች አገሮች ፋብሪኮችን ያቋቋሙና ገበያዎቻቸውን በሸቀጦች ያጥለቀልቃሉ ። አገር ውስጥ የማይፈለጉ ዕቃዎችንም መላክ የገቢ ሸቀጦችን ቀረጥ ለመቋቋምና የውጭን ገበያ ለመያዝ ብዙ ይረዳል ። አገር ውስጥ የማይፈለጉ ዕቃዎች ( Dumping ) ማለት በፍጹም ዝቅተኛ ተመን ሽያጭን ፣ አንዳንዴም ከሸቀጦች ምርት ዋጋ በታች ለውጭ አገር የሚላኩትን የሚወክል ነው ። ወዲያውኑ ዝቅተኛ ተመን በተጠያቂነት ላይ ካለው ገበያ ተወዳዳሪዎችን በማስወጣት ፣ ሞኖፖሊዎች ተመኑን ከፍ ያደርጋሉ ።

ለውጭ ገበያ ፣ ለጥሬ ሀብት ምንጮችና ለማዋዕለ — ንዋይ ክልል የሚደረገው ትግል በተለያዩ ሞኖፖሊዎች የተዕዕኖ ክልል ውስጥ ወደ ዓለም ምጣኔ — ሀብታዊ ክፍፍል ያመራል ። የሞኖፖሊዎች ከራሳቸው የመንግሥት ድንበር አልፎ መሄድ የሚአመለክተው ፣ አሁንም አዲሱን ከፍተኛውን ደረጃ የምርትና የወረት መድለብን ፣ ሌኒን « የመጠቀ ሞኖፖሊ » ብሎ የጠራውን ነው ።

በአንድ ኢንዱስትሪ ውስጥ ጥቂት ትረስቶች ወይም ሲንዲኬቶች በመላው ካፒታሊስት ዓለም የወሳኝነት ሚና ለመያዝ ሲጀምሩ፤ የዓለም— አቀፋዊ ሞኖፖሊዎች የመመሥረት ሁኔታዎች ይፈጠራሉ ። ዓለም አቀፋዊ ሞኖፖሊዎች በተለያዩ አገሮች ትላልቅ ሞኖፖሊዎች መካከል በገበያ ክፍፍልና በጥሬ — ሀብት ምንጮች ላይ፣ በምርት መጠን (ኮታ)፤ በተመን ፖሊሲ ፣ ወዘተ . . የሚደረሱ ስምምነቶች ናቸው ።

የመጀመሪያው የዓለም አቀፍ ሞኖፖሊ መምጣት የታየው በ1860 እና 80 አካባቢ ላይ ነው ። በ19ኛው ምዕተ — ዓመት መጨረሻ ላይ ሞኖፖሊዎች 40 አካባቢ ደርሰዋል ፤ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ (1939) ከ300 በላይ ሆነዋል ። በአሁኑ ወቅት ከ350 በላይ ናቸው ። የካፒታሊስት አገሮች ታላላቅ ሞኖፖሊዎች የዓለምአቀፍ ሞኖፖሊ ጸባይ ይዘዋል ።

ሌኒን እንዴት ዩናይትድ ስቴትስና ጀርመን ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት በመላው የኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ሞኖፖሊ እንደነበራቸው አሳይቷል።በጀርመን ጠቅላላ የኤሌክትሪክ ኩባንያ (A.E.G.) የሚባለው በአሜሪካና በብዙ የአውሮፓ አገሮች ብዙ ድርጅቶችና ቅርንጫፎች ነበሩት ። በዩናይትድ ስቴትስ ደግሞ በመላው አሜሪካና በአውሮጳም ካሉ ድርጅቶች ጋር የኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ ሞኖፖሊ በጀኔራል ኤሌክትሪክ ኩባንያ ነበር የተያዘው ። በ1907 እነዚህ ሞኖፖሊዎች

ወረት ወደ ውጭ በሚልኩ ሀገሮች ውስጥ ፣ እንዲያ የሚያደርጉ ሁኔታ ሁለት መልክ አለው ። ባንድ በኩል ፣ እነዚህ አገሮች በሀብታቸው ላይ ይጨምሩበታል ፣ ማለትም ፣ በሌሎች አገሮች ውስጥ ካሏቸው ድርጅቶች ከውጭ ትርፍ ዕሴት በትርፍ መልክ ያገኛሉ ወይም ከብድር አራጣ ። በሌላ መንገድ ፣ የምርታቸው ዕድገት ይጐትታል ፣ ማለትም የወረት ወደውጭ መውጣት በእናት ሀገር ውስጥ ወረትን የማዋል (የማሠራጨት) መንገድ ያግዳል ።

የካፒታል ወደ ውጭ መውጣት በሀገሮች መካከል ወደ ሠፊ የምጣኔ ሀብት ግንኙነት ያመራል ። ግን እነኝህ ሠፊ ግንኙነቶች ኋላ ቀር የሆኑ አገሮች በምጣኔ ሀብት በገፉ አገሮች መበዝበዝን ነው የሚአመለክቱት ። ስለዚህ ፣ የወረት ወደ ውጭ መውጣት የኢምፔሪያሊስትን የጨቋኝነትና የገዥነት ዘዴንነው የሚፈጥረው።

የቡርዧ ርዕዮተ ዓለማውያን በኢምፔሪያሊዝም ዘመን የወረት ከሀገር ውጭ መውጣት « የዕርዳታ » መልክ ነው ፣ ኋላ ቀር ለሆኑ አገሮች « ዳረጎት » ነው ለማለት ይሞክራሉ ። በባሕሪው ኢምፔሪያሊዝም ምናልባት የቅኞችን የኢንዱስትሪ ዕድገት ሳያራምድ አልቀረም ፣ በገዥዎቻቸው ዘንድ የነበራቸውን ጥገኝነት ገዘት አድርጓል ፣ እንዲሁም ነጻ አውጥቷቸዋል የሚል የነጻነት ንድፈ-ሀሳብ ቀርቦ ነበር። የንድፈ ሀሳቡ ዓላማ የኢምፔሪያሊስት የወረት ወደ ውጭ ማስወጣት ካባ ለማልበስ ነው ። እንደእውነቱ ከሆነ የወረት ወደ ውጭ መውጣት የነጻ መውጣት መልክ ሳይሆን ግን ፣ አንዳንድ አገሮች ሌሎች አገሮችን የሚይዙበት « የተጨፈኑ ላሞኛችሁ » ተረት ነው ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በወረት ወደ ውጭ መውጣት ላይ አንዳንድ አዳዲስ ገጽታዎች ተከሠቱ። ነገሩ ፣ ብዙ አገሮች በአውሮጳና በእስያ ከካፒታሊዝም ቀንበር ሥር ሰብረው መውጣት ማለት ለካፒታሊስት መዋዕል ንዋይ ክፍት የነበሩት አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሱ መሄድ ነው ።

ያልተስተካከለው የወረት ወደ ውጭ መውጣት ይበልጥ ግልፅ እየሆነ መጣ። በአንፃሩም በእንግሊዝና በፈረንሣይ አዘቀዘቀ ። በዩናይትድ ስቴትስ በሌላ በኩል ፣ እጅግ አደገ።በ1949 ዓ.ም ከሀገር ውጭ የአሜሪካን ወረት መዋዕለ ንዋይ የሌሎች ካፒታሊስት አገሮች ሁሉ ተዳምሮ ከሚሆነው በላይ ነበር ። በ1939 እና በ1955 የዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላላ የውጭ መዋዕለ ንዋይ ወደ አራት ጊዜ ፣ እጥፍ አደገ ።

ዩናይትድ ስቴትስ በመንግሥታዊ ብድርና ዱቤ መልክ ወደ ኋላ ለቀሩ የላቲን አሜሪካ፣ እስያና አፍሪቃ እንዲሁም እጅግ በኢንዱስትሪ ለበለጸጉ አውሮጳ አገሮች ለእንግሊዝ ፣ ፈረንሣይ ፣ ምዕራብ ጀርመን ወዘተ . . . እጅግ ብዙ የሆነ ወረት (ካፒታል) ትልክ ነበር ። ዩናይትድ ስቴትስ የጠቅላላ ካፒታሊስት አገሮች የገንዘባዊ ብዝበዛ ማዕከል ነች ።

*መንግሥታዊ ብድሮችና ዱቤዎች ፖለቲካዊና ወታደራዊ እንዲሁም ምጣኔ ሀብታዊ መልኮች አሏቸው ።*

በወረት ወደውጭ መውጣት አማካኝነት እጅግ የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ገንዘባዊ ገዥዎች ወረቱን ወደሀገራቸው የሚአስገቡ አገሮችን ጠቅላላ ምጣኔ — ሀብታዊ ኑሮ በቁጥጥራቸው ሥር ለማምጣት ይመኛሉ ።

ሁሉም ኢምፔሪያሊስት አገሮች ወረታቸውን በሥራ ላይ ቢአውሉት ከፍተኛ ትርፍ ሊአስገኙ ወደሚቻልባቸው አገሮች ለመላክ ይሞክራሉ ። ይህ ደግሞ በካፒታሊስቶች መካከል ብቻ ሳይሆን ግን በኢምፔሪያሊስቶችም መካከል ጭምር ውድድርን ያመጣና በሞላ የካፒታሊስት ዓለም ውስጥ ቅራኔዎችን ያባብሳል ።



**በካፒታሊስት ማኅበሮች መካከል የዓለም ምጣኔ ሀብታዊ ክፍፍል**

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያሉ ሞኖፖሊዎች ለመጀመሪያና ከሁሉም በላይ የሚታገሉት በአገር ውስጥ ገበያ ተካፋይ የሌለው የበላይነት ለማግኘት ነው ። የአገር ውስጥን ገበያ ይከፋፈላሉ ፣ ከፍተኛ ተመን ያወጡና እጅግ ሰፊ ትርፍ ያካብታሉ ። ከፍተኛ ተመንን ለማቆየት ፣ ሞኖፖሊዎች የአገር ውስጥን ገበያ ከውጭ ውድድር ይከላከላሉ ። ለዚህ ተግባር መንግሥታት (የሞኖፖሊዎች) የገቢ ቀረጥን ከፍ አድርገው ይወስናሉ ፣ አንዳንዴም አንዳንድ ሸቀጦችን እንዳይገቡ ያግዳሉ ። ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦች ቀረጥ ሁልጊዜ ከራሳቸው ከሸቀጦች ዕሴት ያይላል ። በዚህ መንገድ የሞኖፖሊዎች የሀገር ውስጥ ገበያ የበላይነት ይረጋገጣል ።

ግን የአገር ውስጥ ገበያ ውሱን ነው ። ከትላልቅ ኮንሰርኖች በሰፊው ከሚወጡት ሸቀጦች ጋር የሚመጣጠን አይደለም ። ስለዚህ ሞኖፖሊዎች በውጭ ገበያ ላይ እንዲሸጡላቸው የበለጠ ጥረት ያደርጋሉ ። ግን እነኝህ ገበያዎች በገቢ ሸቀጦች ቀረጥ ከታጠሩ ይህን እንዴት ሊአደርጉ ይችላሉ ?

ከፍተኛ የገቢ ሸቀጥ ቀረጥን ለማስወገድ ወረትን ወደውጭ ያወጣሉ ። ካፒታሊስቶች በሌሎች አገሮች ፋብሪኮችን ያቋቁሙና ገበያዎቻቸውን በሸቀጦች ያጥለቀልቃሉ ። አገር ውስጥ የማይፈለጉ ዕቃዎችንም መላክ የገቢ ሸቀጦችን ቀረጥ ለመቋቋምና የውጭን ገበያ ለመያዝ ብዙ ይረዳል ። አገር ውስጥ የማይፈለጉ ዕቃዎች ( Dumping ) ማለት በፍጹም ዝቅተኛ ተመን ሽያጭን ፣ አንዳንዴም ከሸቀጦች ምርት ዋጋ በታች ለውጭ አገር የሚላኩትን የሚወክል ነው ። ወዲያውኑ ዝቅተኛ ተመን በተጠያቂነት ላይ ካለው ገበያ ተወዳዳሪዎችን በማስወጣት ፣ ሞኖፖሊዎች ተመኑን ከፍ ያደርጋሉ ።

ለውጭ ገበያ ፣ ለጥሬ ሀብት ምንጮችና ለማዋዕለ — ንዋይ ክልል የሚደረገው ትግል በተለያዩ ሞኖፖሊዎች የተፅዕኖ ክልል ውስጥ ወደ ዓለም ምጣኔ — ሀብታዊ ክፍፍል ያመራል ። የሞኖፖሊዎች ከራሳቸው የመንግሥት ድንበር አልፎ መሄድ የሚአመለክተው ፣ አሁንም አዲሱን ከፍተኛውን ደረጃ የምርትና የወረት መድለብን ፣ ሌኒን « የመጠቀ ሞኖፖሊ » ብሎ የጠራውን ነው ።

በአንድ ኢንዱስትሪ ውስጥ ጥቂት ትረስቶች ወይም ሲንዲኬቶች በመላው ካፒታሊስት ዓለም የወሳኝነት ሚና ለመያዝ ሲጀምሩ፤ የዓለም— አቀፋዊ ሞኖፖሊዎች የመመሥረት ሁኔታዎች ይፈጠራሉ ። ዓለም አቀፋዊ ሞኖፖሊዎች በተለያዩ አገሮች ትላልቅ ሞኖፖሊዎች መካከል በገበያ ክፍፍልና በጥሬ — ሀብት ምንጮች ላይ፣ በምርት መጠን (ኮታ)፤ በተመን ፖሊሲ ፣ ወዘተ . . የሚደረሱ ስምምነቶች ናቸው ።

የመጀመሪያው የዓለም አቀፍ ሞኖፖሊ መምጣት የታየው በ1860 እና 80 አካባቢ ላይ ነው ። በ19ኛው ምዕተ — ዓመት መጨረሻ ላይ ሞኖፖሊዎች 40 አካባቢ ደርሰዋል ፤ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ (1939) ከ300 በላይ ሆነዋል ። በአሁኑ ወቅት ከ350 በላይ ናቸው ። የካፒታሊስት አገሮች ታላላቅ ሞኖፖሊዎች የዓለምአቀፍ ሞኖፖሊ ጸባይ ይዘዋል ።

ሌኒን እንዴት ዩናይትድ ስቴትስና ጀርመን ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት በመላው የኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ ሞኖፖሊ እንደነበራቸው አሳይቷል።በጀርመን ጠቅላላ የኤሌክትሪክ ኩባንያ (A.E.G.) የሚባለው በአሜሪካና በብዙ የአውሮጳ አገሮች ብዙ ድርጅቶችና ቅርንጫፎች ነበሩት ። በዩናይትድ ስቴትስ ደግሞ በመላው አሜሪካና በአውሮጳም ካሉ ድርጅቶቹ ጋር የኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ ሞኖፖሊ በጀኔራል ኤሌክትሪክ ኩባንያ ነበር የተያዘው ። በ1907 እነዚህ ሞኖፖሊዎች

የቅኝ ገዥዎች ገንዘባዊ ወረት የጥገኛና የቅኝ ሀገር ሕዝቦችን ያለርህራሄ ይበዘብዛል ። እንደጠቅላላ ሕግ ሆኖ ፣ እነኝህ አገሮች የጉልበት ሕግ የላቸውም ፣ የሴቶችና የሕጻናት ጉልበት በሰፊው ሥራ ላይ ይውላል ፣ የሥራ ቀኑ ከ12—14 ሰዓት ወይም የበለጠ ይራዘማል ፣ ምንዳም በማስራብ ደረጃ ነው የሚቀረው ። የሠራተኛው ሕዝብ የጉስቁልና ኑሮ ለርሀብና ወረረሽኝ ምክንያት ይሆንና የሕዝቡን የቀስበቀስ መውደም ያስከትላል ።

የኢምፔሪያሊስት ብዝበዛና ጭቆና ወዲያውኑ በማይቀር ሁኔታ የቅኝና የጥገኛ ሀገሮች የመቋቋም ጦርነት—በብሔራዊ የአርነት ትግል የሚታየውን—ጥሪ ያደርግለታል ። የቅኝ ግዛት ሕዝቦች ብሔራዊ የአርነት እንቅስቃሴ በተለይ የተስፋፋው የኢምፔሪያሊስቶችን ቅኛዊ ሥርዓት የመሰባበር መልክ ካሳየው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው ።

## 4 የሞኖፖሊ ትርፍ-የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መገፋፊያ ኃይል

የሞኖፖሊ ትርፍ

በማንኛውም ደረጃ የካፒታሊዝም መሠረታዊ የምጣኔ—ሀብት ሕግ የትርፍ ዕሴት ሕግ ነው ። የጠቅላላውን የካፒታሊስት ምሥረታ ዕድገት ይወስናል ። ትርፍ ዕሴትን ለማካበት ሲባል ያልተከፈለበትን ጉልበት ለመበዝበዝ የሚታገሉትን የካፒታሊስቶች ትግል ይገልጻል ። ግን የካፒታሊዝም መሠረታዊ የምጣኔ — ሀብት ሕግ ራሱን ግልጽ የሚአደርግበት መልክ በተለያዩ የካፒታሊዝም ደረጃ ሁሉ አንድ አይደለም ።

ከኢምፔሪያሊዝም በፊት ፣ ነጻ ውድድር ገዥ በሆነበት ወቅት ከፍተኛ ትርፍ የመሰብሰብ ሁኔታ ይኑስም ይብዛ ከአንድ ኢንዱስትሪ ወደሌላው የወረት በነጻ መዘዋወር ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ይሄድ ነበር ። እርስ በእርሳቸው የሚወዳደሩ ድርጅቶች በብዛት ነበሩ ። የዚህ ውጤት የአማካይ ትርፍ ደረጃ መመሥረት ነው ።

በኢምፔሪያሊዝም ዘመን ፣ ነጻ ውድድር በሞኖፖሊዎች ግዛት ተተካ ። በኢንዱስትሪ ቅርንጫፎች ውስጥ ሞኖፖሊ በሰፈነባቸው ፣ ምጣኔ — ሀብታዊ ሁኔታዎች ሞኖፖሊዎችን ከፍተኛ ትርፍ እንዲአገኙ የሚአስችላቸው ፣ ወደ ሕልውና ይመጣል ። ከአማካይ ትርፍ በላይና ይበልጥ ፣ ከፍተኛ የሞኖፖሊ ትርፍ ሞኖፖሊዎች የሚአገኙትን ተጨማሪ ትርፍም ይጨምራል ፣ ምክንያቱም ያን የተወሰነ የምርት ክልል ወይም ልውውጥ ይገዛሉና ።

በኢምፔሪያሊዝም ዘመን ፣ በሞኖፖሊዎች የሚመረቱት ሸቀጦች እንደተቀዱሞው ሁሉ የሚሸጡት በምርት ተመን ሳይሆን በሞኖፖሊ ተመን ነው ። የሞኖፖሊ ተመን የምርት ዋጋንና ከፍተኛ የሞኖፖሊ ትርፍንም ይይዛል ።

የሞኖፖሊ ትርፍ ምንጩ

እንዴት ነው ካፒታሊስቶች ከፍተኛ የሞኖፖሊ ትርፍ የሚወስዱት? የከፍተኛ ሞኖፖሊ ትርፍ መሠረት ፣ እንደሌላው የካፒታሊስት ትርፍ ሁሉ ፣ በሰፊ የብዝበዛ ሂደት ውስጥ ከሠራተኞች ተጨምቆ የሚወጣው ትርፍ ዕሴት ነው ። በምርት ቅንጅት ውስጥ የተለያዩ የመጭመቅ (የብዝበዛ) ሥራ በሰፊው መዋል ምክንያት — አውቶማቲክ በማድረግ ፣ ማሺን በመለወጥና ጉልበትን በማፈግ — የትርፍ ዕሴት ደረጃና ብዛት ጭማሪ ይገኛል ።

የቡርዧዋው ሌላው ክፍል — የመሬት ከበርቴዎች ፣ ነጋዴዎች ፣ ወዘተ . . . ሠራተኞች ምንዳቸውን ከተቀበሉ በኋላ ደግሞ ይበልጥ ይበዘብዛሉ ።

የገበሬው መበዝበዝም ከፍተኛ የሞኖፖሊ ትርፍ ምንጭ ነው ። ሞኖፖሊዎች የተፈበረኩ ዕቃዎችን ለሰፊው ገበሬ በከፍተኛ ተመን ይሸጣሉ ፣ ወዲያውም የእ



ርሻ ውጤትን ከገበሬው በዝቅተኛ ተመን ይገዛሉ ። ገበሬዎች በብዛት በብድር ውስጥ ሲገቡና እርሻቸውም ሲጠፉ ፣ ሞኖፖሊዎች መሬታቸውንና ይዞታቸውን በጣም አነስተኛ በሆነ ክፍያ ይወስዱባቸዋል ።

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ወዛደሩ ፣ ሠራተኛው ገበሬና ዝቅተኛ ክፍያ (ደመወዝ) ያላቸው ክፍሎች በቡርዧው መንግሥትና እርሱን በሚደግፉት ትላልቅ ሞኖፖሊዎች የሚጣልባቸውን ተጨማሪ ብዝበዛ ይሸከማሉ ። ይህ ተጨማሪ ብዝበዛ የግብርን ፣ የመንግሥት ብድርን ፣ እና የወረቀት ገንዘብን ዋጋ ማውረድን መልክ ይይዛል ። የዚህ ኢሰብአዊ የሆነ ብዝበዛ ውጤት በአብዛኛው ሕዝብ ላይ ትብ የሆነ የኑሮ ማሽቆልቆልን ያመጣል ።

ሞኖፖሊዎች ከቅኝና ሌሎች ኋላ — ቀር ከሆኑ አገሮች ሕዝቦች ብዝበዛ እጅግ ሰፊ ሀብት ያግበሰብሳሉ ። የሚሰጡት ምንዳዕ ሠራተኞችን የመሠረታዊ ሕልውና መጠበቂያዎችን ፍላጎት ለማሟላት እንኳ በቂ አይደለም ። ሰፊው ሠራተኛ ውስብስብ የሆነ የግብር ሥርዓት ጫና ተጭኖበታል ። የግዴታ ሥራ በሁሉም በእርሻና በኢንዱስትሪ በግልፅ ውሏል ። ሞኖፖሊዎች በተጨማሪ ሸቀጦቻቸውን በከፍተኛ የሞኖፖሊ ተመኖች በመሸጥና ጥሬ — ሀብትንና የምግብ ዕቃዎችን በዝቅተኛ የሞኖፖሊ ተመኖች በመግዛት ያተርፋሉ ። በዚህ ባልተመጣጠነ ልውውጥ ኋላ — ቀር አገሮች በያመቱ 20,000 ሚሊዮን ብር ከአጠቃላዩ የብሔራዊ ውጤት ⅙ መሆኑ ነው — ያጣሉ (ይቀንሳሉ) ።

ጦርነቶችና ወታደራዊነት ጸባይ የያዘ ምጣኔ — ሀብትም ለከፍተኛ ሞኖፖሊ ትርፍ ዋስትና ነው ። በጦርነት ጊዜ የሠራተኞች የመበዝበዝ ደረጃ ፣ ግዴታ በሆነ የሥራ ዲስፕሊን በኢንዱስትሪ ድርጅቶች ውስጥ ስለሚውል ፣ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል ። በተጨማሪም ግብር ይጨምራል ፣ ተመን ይንራል ። ይህ ሁሉ ለካፒታሊስቶች ከፍተኛ ትርፍ ያስገኛል ። ለምሣሌ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የዩናይትድ ስቴትስ ሞኖፖሊዎች ትርፍ ከሰባት ዕጥፍ በላይ ንሯል ። በሰላም ጊዜ የምጣኔ — ሀብት ወታደራዊነት ፣ እንበልም ፣ ኢንዱስትሪን ከጦርነት ምርት ጋር ማሳሳምም ትርፍን እንዲአድግ ይረዳዋል ። ለምሣሌ ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ሞኖፖሊዎች የጦርነት ቁሳቁሶችን የማምረት ትርፍ ደረጃ ዛሬ ከ50— 100 በመቶ ድረስ ከሲቪል ኢንዱስትሪዎች ከፍ ያለ ነው ። ምርት ፣ ለጦርነት ፣ ለሞኖፖሊዎች ሰፊ ትርፍ የሚአስገኘው ፣ በሠራተኛው ሕዝብ ላይ የኑሮ ደረጃ ማሽቆልቆልን ያመጣል።

ሞኖፖሊ ወረት (ካፒታል) ከፍተኛ የሞኖፖሊ ትርፍ የሚአገኝበት ዐይነተኛ ዘዴዎች እነኝህ ናቸው ። በኢምፔሪያሊስት ዘመን ፣ የካፒታሊዝም ምጣኔ — ሀብታዊ መሠረታዊ ሕጐች የሕዝቡ ሰፊ ክፍል—ሠራተኛው ፣ ገበሬውና የቅኝ ግዛትና የጥገኛ አገሮች ሕዝቦች — የሞኖፖሊ ካፒታል (ወረትን) በመጻረር እንዲዋጋና የኢምፔሪያሊዝምን የመጨረሻ ዕለተ — ምፅዓት ለማቅረብ የሚአስችሉ ሁኔታዎችን ያዘጋጃል ።

ም ዕ ራ ፍ ፰

# ኢምፔሪያሊዝም በታሪክ ውስጥ ያለው ቦታ

# የዓለም ካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ

## 1. ኢምፔሪያሊዝም በታሪክ ውስጥ ያለው ቦታ

ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ከፍተኛውና የመጨረሻው ደረጃ ነው ። ኢምፔሪያሊዝም በታሪክ ውስጥ የሚይዘውን ቦታ ለመግለጽ ፤ የካፒታሊዝም ልዩ ደረጃ እንደሆነ ሌኒን ጠቁሟል ። ሶስት መሠረታዊ መልኮች አሉት ፤— ኢምፔሪያሊዝም 1/ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ፣ 2) የበሰበሰ ካፒታሊዝም ፣ 3/ የአረጀ ሊወድቅ የተቃረበ ካፒታሊዝም ነው ።

ኢምፔሪያሊዝም ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ነው

በምጣኔ ሀብታዊ ባሕሪው ፣ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ኢምፔሪያሊዝም ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ነው ። የሞኖፖሊዎች የበላይነትና ጸባይ ነው ፤ እናም ይህ ነው ኢምፔሪያሊዝም በታሪክ ውስጥ የሚይዘውን ቦታ የሚወስ ነው ።

ሌኒን ኢምፔሪያዝምና የሶሻሊዝም መከፋፈል በሚለው መጽሐፉ ፣ ሞኖፖሊ ካፒ ታሊዝም ራሱን የሚአንፀባርቅባቸውን አራት መንገዶች ገልጿል ።

በመጀመሪያ ፣ ሞኖፖሊዎች የዳበሩት የምርት መድለብ በጣም ከፍተኛ ደረጃ በደረስ ጊዜ ነው ። በዚህ የሚጠቃለሉት የካፒታሊስት ሞኖፖሊ ማሕበሮች ናቸው። ካርቴል፣ሲንዲኬት፣ትረስትና ኮንሠርን የሚባሉት ። በካፒታሊስት አገሮች የምጣኔ ሀብት ኑሮ ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ። የሞኖሊዎች ከምርት መድለብ የተነሣ መምጣትና የካፒታሊስት አገሮችን ፣ ምጣኔ — ሀብታዊና ፖለቲካዊ ኑሮ መግዛት የካፒታሊስትን ዕድገት አዲስ ደረጃ ጸባይ ነው የሚአሳየው—ኢምፔሪያሊዝምን ።

ሁለተኛ ፣ ሞኖፖሊዎች አማካይ አከፋፋይ በነበሩትና ኋላም ሁለገብ የገንዘብ ማዕከላዊ ኃይል ባላቸው ባንኮች አማካኝነት ነው ያአደጉት ። በእያንዳንዳቸው ከፍተኛ ዕድገት ባላቸው ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ከ5—10 የሚሆኑ ትላልቅ ባንኮች በኢንዱስትሪያዊና ባንክ ወረት መካከል (ከፍተኛ ገንዘብ በቁጥጥራቸው ሥር ባደረጉት ማለት ነው) « ግላዊ ሕብረት » ይገኛል ። ገንዘባዊ ወረትና ገንዘባዊ ሥልጣን የሀገሩን ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ኑሮ ይገዛሉ ። ጥቂት ባለቢሊዮንና ሚሊን ቡድኖች የሀገርን ጠቅላላ ሀብት ይወስዳሉ እናም ኃላፊነታቸው ለማንም አይደለም ከራሳቸው በቀር ።

ሶስተኛ ፤ ሞኖፖሊዎች እጅግ ዋና የሆኑ የጥሬ ሀብት ምንጮችን ፣ ገበያዎችችንና የወረትን መዋዕለ ንዋይ ክልል በተጠናከረ መልክ ወይመያዝ አመሩ ። ግዛታቸው በተወሰኑ አገሮች ወይም በጠቅላላ አህጉሮችም እንኳ ቢሆን ሊስፋፋ ይችላል ። ይህ ዓይነት የሞኖፖሊ ቁጥጥር በተለይ የጥቂት ቡድኖችን ገንዘባዊ ባለጸጎችንም ገዥነት አሳድጓል ፤ ስለዚህ በካፒታሊስት ሠፈር ውስጥ በሠፊው ቅራኔውን ያባብሳል ።

አራተኛ ፣ ሞኖፖሊዎች የመጡት ከኢምፔሪያሊስት ኃይሎች የቅኝ ፖሊሲ ነው ። የግዛቶች « ነጻ መያዝ»ዘመን በምጣኔ—ሀብታዊ ባርነት አማካኝነት በሞኖፖሊ የቅኞች ቁጥጥር ተተካ ። የወረትና የሸቀጦች ወደ ውጭ መላክ ፣ የምጣኔ ሃብትና የፖለቲካ እንደየሕዝቦች የባርነት ዘዴ በመሆን ፣ ወደዚህ መዳፊያ ነው የአሠራር ሂደቱ ።



ይህ ሁሉ አንድ ነጠላ ሞኖፖሊ ግዙፍ ድርጅቶችን በማስተባበር ባንድ የማምንጮችን በቅርብ የመከታተል ሁኔታ ሲአመጣ ፤ የገበያንና የጥሬ ሀብት ብቶችና ሳይንቲስቶች በቁጥጥራቸው ሥር አሉ።ሞኖፖሊዎች የምርትን ሕብረተሰባዊነት እስከተቻላቸው የመጨረሻ ደረጃ ድረስ በካፒታሊዝም ውስጥ ያካሂዳሉ።ግን ይህ ግዙፋዊ የምርት ሕብረተሰባዊነት የተመሠረተው በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ሆኖ የሚአገለግለውም ለእፍኝ ሙሉ ካፒታሊስቶች ዝንባሌ ነው ። ከምርት ኃይሎች ሠፊ ዕድገት ሠፊው ሕዝብ ምንም ጥቅም አያገኝም ፣ እንዲያውም ድህነቱና ብዝበዛው ነው እየጨመረ የሚሄደው ።

በመጨረሻም ፣ የሞኖፖሊዎች አገዛዝ የካፒታሊዝምን መሠረታዊ ቅራኔዎች በሠፊው ያባብሳል ፣ በምርት ሕብረተሰባዊ ጸባይና የምርት ውጤቶችን በግላዊ የካፒታሊስት መልክ በመውሰድ መካከል ያለውን ቅራኔ መሆኑ ነው ። ካፒታሊዝም በኢምፔሪያሊስት ደረጃው የሰብዓዊ ሕብረተሰብን ዕድገት ጉትቶ የሚይዝ አድሀሪ ኃይል ሆኗል ።

ሌኒን ሲጠቁም ፣ ሞኖፖሊዎች ወደ ታላቅ የምርት ዙሪያ ገባ ሕብረተሰባአዊነት ያመራል ብሏል።ለከፍተኛ ደረጃ ሕብረሰባዊነትና የምርት ዕድገት ማረጋገጫው ለሕብረተሰብ የሶሻሊስት ሽግግር ሁሉም ቁሳዊ ዝግጅቶች መኖራቸው ነው ።

በኢምፔሪያሊዝም ውስጥ የሕብረተሰብ የምርት ኃይሎች ፤ የጉልበትን ውጤት ከግላዊ ካፒታሊስት አበዛበዝ መልክ ጋር ከሚጋጩበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ። ስለ ሆነም ፣ የምርት ኃይሎች በቀስታ ያድጋሉ ወይም ወደምጣኔ — ሀብታዊ ቀውስ ይወረወራሉ ።

ወዲያውም (በዚያው ጊዜ) ሞኖፖሊዎች የሠራተኛውን ሕዝብ ጭቆና ወደ ዕንፋዊ ደረጃው ያደርሱታል ፤ ሠራተኛው መደብ በትግሉ ውስጥ ይገባል ፤ ይጠነክራል እናም በጦርነት በመንጠር የሥልጣንን ዙፋን የመንጠቅ ችሎታ ይኖረዋል ።

ሌኒን ፣ በካፒታሊዝም ውስጥ ፣ ከካፒታሊዝም ወደ ከፍተኛ የሕብረተሰብ ምጣኔ ሀብት መቅረፅ የመሸጋገር ዘመን ገዕታ በማንኛውም አቅጫጣ ዳብሮ ግልፅ ሆኗል ፣ ሲል ጠቁሟል ። ይህም ፣ ኢምፔሪያሊዝም በታሪክ መድረክ ላይ ያለውን ቦታ የሚወስነው የካፒታሊዝም ከፍተኛውና የመጨረሻው ደረጃ መሆኑን ነው ።

ኢምፔሪያሊዝም ጥባቴ ወይም የበሰበሰ ካፒታሊዝም ነው ።

ኢምፔሪያሊዝም ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ብቻ አይደለም ግን ጥባቴ (Parasitic) እና የበሰበሰ ካፒታሊዝምም ነው ። የኢምፔሪያሊዝም የጥባቴነት ጸባይ የሚታየው እጅግ ብዙዎች ካፒታሊስቶች በምንም መንገድ ከምርት ሂደት ጋር አለመዛመዳቸው ላይ ነው ። የቦዘኔነትና ጥባቴ ኑሮ ነው የሚገፉት ። በሞኖፖሊዎች ዘመን ካፒታሊስቶች ፣ ገንዘብ የሚአስገኙ ዕጣዎች ፣ የመንግሥታዊ ብድር ሠነዶችና ሌሎችም የገቢ ማስጠንቀቂያዎች ባለቤቶች ፣ ሆነዋል ። የኢንዱስትሪያዊ ድርጅቶች ቀጥተኛ አመራር የሚካሄደው በቅጥረኛ ቴክኒካዊ ሹሞች ነው ።

ከሁሉም በፊት የካፒታሊዝም መበስበስ የሚታየው በሕልውና ያሉትን የምርት ኃይሎች ሙሉ በሙሉ በጥቅም ላይ ለማዋል አለመቻል ፣ ለሥራ እጡ ሥራ አለመስጠትና ሙሉ በሙሉ የአምራችነት ችሎታን ለማሟላት አለመብቃት ላይ ነው ። እጅግ የበለጸገችዋ ካፒታሊስት አገር ዩናይትድ ስቴትስ አሁን እጅግ አሠቃቂ የሥራ አጥነት መታከቻና የአምራችነት ችሎታን ለማሟላት በማትችልበት ሁኔታ ላይ ናት ።

የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መበስበስና ጥባቴነት በሠፊው የሚብራራው የሠራተኛው ሕዝብ ምርት በማይሰጥ አድማስ ውስጥ በሚቀጠርበት ምጥነት ነው—በንግድ ፣ በገንዘባዊ አሠራር ፣ በመንግሥታዊ መዋቅር ። ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ በ1910 እና በ1955 ዓ. ም ምርት በማይሰጡ የምጣኔ ሀብት ቅርንጫፎች የተቀጠሩት ሰዎች ምጥነት (Proportion) ከ25 ወደ 51.4 በመቶ ከጠቅላላው ሠራተኛ ሕዝብ ጨምሯል (ይህ ቁጥር እርሻን አይጨምርም) ።

የካፒታሊዝም የጥባቴነት ጸባይ በተጨማሪ የሚገለጸው በወረት ወደውጭ መላክ ፣ በወታደራዊነት ማደግ ፣ እና ወደጦርነት በማዘንበል ላይ ነው ። እጅግ ብዙ ገንዘብ የሚጠፋው ቁሳዊ ሀብትን ለማምረት ሳይሆን ፣ ግን የምርት ኃይሎችን በማውደም ፣ ከሁሉም የሕብረተሰብን ዋና የምርት ኃይሎች ፣ የሰዓብዊ ሕብረተሰብን ነው ። ለምሳሌ በአንደኛው የዓለም ጦርነት 10 ሚሊዮን ሰዎች ተገድለው 20 ሚሊዮን ደግሞ ቆስለው ነበር ። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች በወረርሽኝና በርሃብ ሞተዋል ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወደ 50 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ተገለዋል። ይህ ነው የሰው ልጅ «ኢምፔሪያሊስቶች ቅራኔን ለማስወገድ ዘዴው ጦርነት ነው» ለሚሉት ጥረታቸው የከፈለው ዋጋ ።

በኢምፔሪያሊስት ደረጃ የካፒታሊዝም መበስበስ የሚወሰነው ሞኖፖሊዎች እራሳቸው (ሰው ሠራሽ ተመንን በማውጣት ከፍተኛ ትርፍን ለማግኘት እስከ አረጋገጡ ድረስ) የምርት ቴክኖሎጂና የማሻሻል መገፋፊያዎችን (Incentives) ከማዳከማቸው ላይ ነው ፤ ማለትም የባለሀበት ሂድ አዝማሚያን ይፈጥራሉ ። የሞኖፖሊ ድርጅቶች አዲስ የተገኙ መማሪያዎችን የሚገዙት ለመጠቀሚያ ሳይሆን ፣ ግን በጥቅም ላይ የዋለውን ሕልውናቸውን ለማገድ እንደሆነ ብዙ ብዙ የተለመዱ ሁኔታዎች አሉ ።

ግን ከፍተኛ የሞኖፖሊ ትርፍ መሰብሰብ ምንም ቢሆን ካፒታሊስቶችን አዲስ ቴክኖሎጂን እንዲአስተዋውቁ ማለትም ከድሮው ይበልጥ አምራች የሆኑትን ያነሳሳቸዋል ። ይሁንና በመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊስት ሁኔታ ሥር አዲስ ቴክኖሎጂን (አሠራርን) ማስተዋወቅ ፤ ሠራተኛውን መደብ ይጐዳዋል ። የካፒታሊስት አውቶ ማቲካዊነት (የመማሪያው) የሠራተኞችን ዳቦ ይነጥቃል ። ሥራ አጥነት የድጋል እናም የሠራተኛው መደብ የኑሮ ደረጃ ያዘቀዝቃል ።

ስለዚህ ለኢምፔሪያሊዝም ሁለት ተጻራሪ አዝማሚያዎች የተለመዱ ናቸው ፣ ባንድ በኩል ቴክኒካዊ እርምጃን የሚአጠናክር ፣ እና በሌላ በኩል ደግሞ ጐትቶ የመያዝ ።

የካፒታሊዝም መበስበስ በተጨማሪም የሚታየው የኢምፔሪያሊስት ቡርገዖዋዎች የተወሰነ ትርፍን ለሰለጠኑ (ልምድ ላላቸው) ሠራተኞች ጉርሻ ለመስጠት በሚጠቀሙበት ጊዜ ነው — የወዛደር መሰፍን ተብሎ ለሚጠራው ። በቡርዧዋው በመደገፍ ፣ የወዛደር መሰፍኑ በሙያ ማኅበር በሌላው የሠራተኛ መደብ ድርጅት የመሪነት ቦታን ለመያዝ ይታገላል ። ከነዑስ ከበርቴዎች ጋር በመሆን ለሠራተኛው እንቅስቃሴ ከፍተኛ አደጋን ያደርሳሉ ።

በወዛደር መሳፍንትነት ሰበብ ቡርዣዋዎች የሠራተኛውን አእምሮ ጥገናዊነትን በመስበክ ካፒታሊዝምን « ለማሻሻል » እና የመደብ ሰላምን « በማጠናከር ይመርዛሉ ። የወዛደር መሳፍንት የሠራተኛን መደብ ሁኔታ በመከፋፈል ሠራተኞች ኃይላቸውን አስተባብረው ኢምፔሪያሊዝምን እንዳይወረውሩ ችግር ይፈጥራሉ ።

የኢምፔሪያሊዝም ጸባይ ከቡርዧ ዲሞክራሲ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ፖሊሲው ወደ ፖለቲካዊ አድኃሪነት መመለስ ነው ።



ጸረ — ኮሚኒስትና ጸረ — ወዛደር ሕጐችን ፣ የኮሚኒስት ፓርቲዎችን ማገድ፤ ኮሚኒስቶችንና ሌሎች ተራማጅ ሠራተኞችን ከአገር ማባረር ፣ በፋብሪኮች ውስጥ በጥቁር መዝገብ ላይ መመዝገብ ፣ የቢሮ ተቀጣሪዎችን ታማኝነት መፈተን ፤ የዲሞክራሲያ ጽሑፎች በፖሊስ መታፈን ፣ አድማዎችን በጦር ኃይል መምታት ፤ የኢምፔሪያሊስት ቡርገዎች ገዥነታቸውን የሚአረጋግጡበት የተለመዱ ዘዴዎቹ ከፍሎች ናቸው ። እነዚህ ናቸው የሞኖፖሊ ጥባቴነትና መበስበስ መሠረታዊ ምክንያቶች ።

ኢምፔሪያሊዝም አርጅቶ ያፈጀ ካፒታሊዝም ነው ።

ሌኒን ሲጠቁም ኢምፔሪያሊዝም አርጅቶ ያፈጀ ካፒታሊዝም ነው ። ይህም ኢምፔሪያሊዝም በተፈጥሮው አላፊ ጠፊ ነው ማለት ይሆናል ። የካፒታሊዝምን ቅራኔዎች የወዛደር አብዮትን እስከሚአስነሳው የመጨረሻ ቅራኔ ድረስ ያተባል (ያባብሳል) ።

ዋናው ቅራኔ በወረትና በጉልበት መካከል ያለው ነው ። በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ዘመን ሠራተኛ ሕዝቦች ከዚያ በፊት ታይቶ ወደማይታወቅ ጥርሱን ወደ አገጠጠው ብዝበዛ ውስጥ ይገባል ።

አሮጌውን አዲሱ ዓይነት የብዝበዛ ሥልት ይጠግነዋል ። የትላልቅ ካፒታሊስቶች የሞኖፖሊ ደረጃ ከዚህ በፊት ያልተደረገ የጉልበት መታፈግ እንዲኖር ፣ እጅግ ሰፊ ሥራ አጥ በመኖሩ ምክንያት የጉልበት ኃይልን በዝቅተኛ የሞኖፖሊ ተመን እንዲገዙ ፤ ሠራተኛውን ሕዝብ እንደበላተኛ ከፍተኛ የሞኖፖሊ ተመን ለፍጆት ዕቃዎች ፣ ለግብር ፣ ወዘተ . . በማስከፈል እንዲጨቁኑ ፣ እድል ይሰጣቸዋል ። ተብቶ ያደገ ብዝበዛ ፣ የሠራተኞች ቁሳዊ ሁኔታ ማሽቆልቆል እና በኢምፔሪያሊዝም ዘመን የሠራተኛው መደብ የፖለቲካዊ ጭቆና እያደገ መሄድ በወዛደሩና በቡርገዖዋው መካከል ከዚህ በፊት ደርሶ ወደማያውቅ የተጠናከረ የመደብ ትግል ነው የሚአመራው ። በመጨረሻ አሮጌው የትግል ዘዴ ብቃት ያጣል ፤ እናም ወዛደሩ ትግሉን በምጣኔ — ሀብትና በንድፈ — ሀሳባዊ ግንባር እየቀጠለ እጅግ በከፍተኛ ቆራጥነት ወደ አብዮታዊ የፖለቲካ ትግል ያዞራል ።

ስለዚህ ኢምፔሪያሊዝም ሠራተኛውን መደብ ወደሶሻሊስት አብዮት መግቢያ ያመጣዋል ።

በኢምፔሪያሊስት ደረጃ የሌሎችን ሕዝቦችን ግዛት ለመያዝ በመሽቀዳደም ምክንያት በኢምፔሪያሊስት ኃይሎች መካከል የተባ ቅራኔ አለ ። እያንዳንዱ ልዩ የካፒታሊስት ቡድን በገበያዎች ፣ በጥሬ ሀብት ምንጮች ፣ በወረት መዋዕለ ንዋይ ክልል ያለውን ይዞታ ለማስጠበቅና ሌላም ለመያዝ ሙከራ ያደርጋል ። በካፒታሊስቶች መካከል ለተፅዕኖ ክልል በሚደረገው ምጣኔ ሀብታዊ ትግል የመንግሥቱ ሙሉ ድጋፍ ይኖረዋል ። በመጨረሻ ለተፅዕኖ ክልል ሲባል በኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል የሚካሄደው ኃይለኛ ትግል ኢምፔሪያሊዝምን የሚያዳክም ወታደራዊ ግጭት ይፈጥራል ፤ መሠረቱን እናግቶ የሶሻሊስት አብዮትን ያቀርባል ።

በኢምፔሪያሊዝም ዘመን በተለይም በአሁኑ ደረጃው ፣ ባንድ በኩል በቅኞችና በጥገኛ ሀገሮች በሌላ ወገን በኢምፔሪያሊስት ኃይላት መካከል እጅግ የተባ ቅራኔአለ ። የኢምፔሪያሊስት ኃይላት ባልበለጸጉ አገሮች ያሉ ሕዝቦችን ርኅራኄ የሌለው ብዝበዛና ጭቆና ያካሂዱባቸዋል ። በእነዚህ አገሮች ውስጥ የኢምፔሪያሊስት ጭቆናን ከካፒታሊዝም መዳበር ጋር በማሳደግ ሕዝቦቻቸውን ለአርነታቸው መራራ ትግል እንዲታገሉ ያነሳሳቸዋል ።

የሶሻሊዝም መምጣትና መጠናከር ለተጨቆኑ ሕዝቦች የነጻነት ዘመን መምጣቱን አሳዩ ። የብሔራዊ አርነት አብዮቶች ቅኝ ገዥዎችን የማያዳግም የጡጫ

ሰዋ አቅምቧቸዋል ። ከ50 በላይ የሚሆኑ መንግሥታት ከቅኝ ገዥዎች መቃብር ላይ ቆመዋል ። ከ1,500 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ከቅኝ ግዛት ነጻ ወጥቷል ።

እነዚህ ናቸው ኢምፔሪያሊዝምን ወደ አርጅቶ ያፈጀ ካፒታሊዝም የሚአሸጋግሩት ዐይነተኛ ቅራኔዎች ። ግን ኢምፔሪያሊዝምን እንደ አርጅቶ ያፈጀ ካፒታሊዝም አድርጐ መግለጽ ካፒታሊዝም እራሱ ይሞታል ፣ ወዲያውኑ ይጨማተራል ማለት አይደለም ። ኢምፔሪያሊዝም አርጅቶ ያፈጀ ካፒታሊዝም ነው ምክንያቱም የካፒታሊዝምን ቅራኔዎች በሙሉ ፊት ለፊት በማምጣት ፣ የሶሻሊስት አብዮትን በአጀንዳ በማስቀመጥ በተግባር የማይቀር ስለሚሆን ነው ።

የሶሻሊስት አብዮት ድል ማድረግ መጀመሪያ በሩሲያ ኋላም በብዙ አውሮጳ እና እስያ አገሮች ኢምፔሪያሊዝም አርጅቶ የፈጀ ካፒታሊዝም ነው ለሚለው ሌኒኒስታዊ መግለጫ ብሩኅዊ ማረጋገጫ ሆኗል ።

**መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ፦** የመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መለያዎች ፣ ከፍተኛ ደረጃ የምርት ሕብረተሰባዊነት ፣ የግላዊና መንግሥታዊ ሞኖፖሊዎች መወሳሰብና የመንግሥታዊ መዋቅሩ ለገንዘባዊ ሥልጣን ጥገኛ መሆን ናቸው ። የመንግሥታዊ መዋቅሩ ጥገኛ የሚሆነው በሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ውስጥ ለሞኖፖሊዎች ከፍተኛ ሀብት ለማስገኘት ጣልቃ ለመግባት ሲባል ነው ።

« መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ፣ » ይላል የሶቬየት ሕብረት የኮሚኒስት ፓርቲ ፕሮግራም ፣ « የሞኖፖሊዎችንና የመንግሥትን ኃይል (ጥንካሬ) በማዋሃድ አንድ ነጠላ አሠራር ፣ ተግባሩ ሞኖፖሊዎችን ማበልጸግ የሆነ ፣ የሠራተኛውን መደብ እንቅስቃሴ ለመጨቆንና የብሔራዊ አርነትን ትግል ለመርገጥ ፣ ለካፒታሊስት ሥርዓት የሚካላከል ፣ እና ጠብ አጫሪ ጦርነቶችን የሚአካሂድ ነው ። » 1

በኢምፔሪያሊዝም ዘመን በሁሉም የካፒታሊስት አገሮች ያሉ መንግሥታት ወይ የገዥ ሞኖፖሊዎች ታማኝ ተወካዮችን ወይም ሞኖፖሊዎች እራሳቸውን በውስጣቸው ይይዛሉ ። በሌላ በኩል ፣ ሚኒስትሮች ፣ ጄኔራሎችና ዲፕሎማቶች ብዙውን ጊዜ ዓይነተኛ ትርፋማ ቦታዎች በመሪ ሞኖፖሊዎች ውስጥ ይሰጣቸዋል ።

ለምሳሌ ፣ በ1955 አጋማሽ ላይ ከ272 እጅግ አይነተኛ ሥልጣኖች በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ 150ዎቹ የተያዙት በትላልቅ ካፒታሊስቶችና በ30 የኮርፖሬሽን ጠበቆች ነው ። የሮኪፌለር ቡድን በመንግሥቱ ውስጥ የተወከለው በመንግሥቱ ዋና ጸሐፊ ፎስተር ዱላስ ፣ ኋላም የሕጋዊ ተቋሞች መሪና በ15 ኢንዱስትሪዎችና ገንዘባዊ ተቋሞች ዳሬክተር በነበረው ነው ። ለረጅም ጊዜ በመንግሥቱ ውስጥ የዱፖንት ቡድን ተወካይ የመከላከያው ዋና ጸሐፊ የነበረው ቻርልስ ዊልሰን ፣ የጄኔራል ሞተር የቀድሞ ፕሬዚደንት ነው ። በ1961 መጀመሪያ ላይ በተመሠረተው በኬኔዲ አስተዳደር ፣ ብዙ ዋና ቦታዎች የተያዙት በትላልቅ ድርጅቶች ነው ። ስለዚህ ፣ ሮበርት ኤስ. ማክናማራ ፣ የፎርድ ሞተሮች ሊቀመንበር የመከላከያው ዋና ጸሐፊ ፣ ዶግላስ ዲሎን ፣ የዲሉን ፣ የሪድና ኩባንያው መሪ የጠቅላይ ግምጃ ቤቱ ጸሐፊ ወዘተ. . ሆነው ተሾመዋል ። የዩናይትድ ስቴትስ ሊቀ መንበር ኤፍ ኬኔዲ ራሱ ባለሚሊዮን ባለጸጋ ነው ፣ እናም የኬኔዲ ቤተሰብ ሀብት 400 ሚሊዮን ዶላር ነበር ። ከሃያአንዱ የካቢኔ ሚኒስቴሮች 14ቱ በእንግሊዝ መንግሥት ውስጥ ከሞኖፖሊዎች ጋር ተታተዋል ፣ ከ21ዱ 15ቱ ደግሞ በምዕራብ ጀርመን የኮንሰርኖች ወይም የተዋሃዱ ጥቅል ኩባንያዎች ተወካዮች ናቸው ። ሁኔታው በሌሎችም የካፒታሊስት አገሮች ተመሳሳይ ነው ። የመንግሥታዊ መዋቅሩ ከትላልቅ ሞኖፖሊዎች ሙሉ በሙሉ የጥገኝነት ማረጋገጫው ይህ ነው ። መንግሥት የሞኖፖሊ ቡርዡዋዎችን ተግባር (ሁኔታ) የሚአስተዳደር ኮሚቴ ሆኗል ።

---

1. ወደ ኮሚኒዝም ጉዞ (የሶቪየት ሕብረት ኮሚኒስት ፓርቲ 22ኛ ኮንግረስ መዝገብ) ፣ ሞስኮ ፣ ገጽ 471



በአሁኑ ጊዜ መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የሚከሰትባቸው ዋና መልኮች ምንድናቸው ? የሚታዩት በተለያዩ መልክ መንግሥታዊ ቁጥጥርና የአገሮችን ምጣኔ — ሀብታዊ ኑሮ እቅድ ለማስያዝ በሚወሰደው እርምጃ ፣ በሞኖፖሊዎች ዝንባሌ የመንግሥታዊ ንብረት አጠቃቀም ፣ መንግሥታዊ መዋቅሩን ለመቅረፅ መንግሥት ለሞኖፖሊዎች በሚሰጠው ዕርዳታ ፣ ከመንግሥት ሀብት ውስጥ በወረት መልክ ወደውጭ መውጣት ፣ ወዘተ . . . ነው ። መንግሥታዊ መኖፖሊ ካፒታሊዝም ራሱን የሚገልጽባቸው እነዚህ ሁሉ መልኮች አንድ ዓይነት ዓላማ አላቸው — የገንዘባዊ ሥልጣን መበልጸግ ።

የመበልጸጊያ ዋና ምንጭ መንግሥታዊ ድርጅቶችን ለመገንባት የሚውለው የባጀት ምንጭና በቡርዧው መንግሥት የግል ድርጅቶች መወረስ ነው ። የግል ሞኖፖሊዎች የመንግሥትን ፕሮጀክቶች ለመሥራት በሚአመች ሁኔታ ኮንትራት ይሰጣቸዋል ፣ ሥራው ሲጠናቀቅ እነዚህ ድርጅቶች ብዙውን ጊዜ ለትላልቅ ሞኖፖሊዎች ብዝበዛ በዝቅተኛ ኪራይ ይተላለፋሉ ወይም በዝቅተኛ ሽያጭ ይሸጣሉ ። አንድ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ድርጅቶችን ቢወርስ ፣ ውርሱን የሚአካሂደው በካፒታሊስቶች ዝንባሌ ነው ፣ ባጠቃላዩ ግለኛ ካፒታሊስቶች ለድርጅቱ መዋዕለ ንዋይ ማውጣት ምንም ጥቅም የሚአስገኝ አይደለም ብለው ሲሉ ነው የሚወርሰው ። ብዙውን ጊዜ የመጀመሪያ ባለቤቶች ከድርጅቶቻቸው ዕሴት በላይ ይከፈላቸዋል ፣ ከዚያም ጀምሮ ሥራው በትላልቅ ሞኖፖሊዎች ይካሄዳል ። ስለዚህ ፣ በማንኛውም መንገድ የመንግሥት ድርጅት ሥራ የሚከናወነው በካፒታሊስቶች ዝንባሌ መሠረት ነው ።

መንግሥታዊ — ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም በሠራተኛው መደብ ላይ ተጨማሪ ብዝበዛንና ለጠቅላላው ሕዝብም ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃን ያመጣል ። በመንግሥቱ መዋቅር በመደገፍ ሞኖፖሊዎች የሠራተኛውን መደብ የመበዝበዝ ደረጃ ከፍ ያደርጋሉ ፣ እናም ሁሉንም ሠራተኛ ሕዝብ በከፍተኛ ግብርና ተመን ይዘርፋሉ ። እነዚህ ሁሉ ለቅራኔዎች መትባትና በጉልበት እና በወረት መካከል ለተጠናከረ ትግል ምክንያት ይሆናሉ ።

ወዲያውም መንግሥታዊ — ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ፣ በካፒታሊዝም ውስጥ የምርት ሕብረተሰባዊነት ከፍተኛ ደረጃ ስለሆነ ፣ ለሶሻሊዝም ሙሉ ቁሳዊ ዝግጅትን ይይዛል ፤ ስለሆነም ወደሶሻሊዝም መዳፊያ ነው ። ግን ለሶሻሊዝም ሽግግር ሥልጣንን ወደ ሠርቶ አደሩ መደብ የሚአስተላልፍ አብዮት አስፈላጊ ይሆናል ።

መንግሥታዊ — ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም በተለያዩ ዘመንና በተለያዩ አገሮች የብሔራዊ ምጣኔ — ሀብት ዘርፎች ባልተስተካከለ ሁኔታ ያድጋል ። ስለዚህ የዓለም ጦርነቶችና የምጣኔ — ሀብት ቀውሶች ፣ የወታደራዊነትና የፖለቲካዊ መለዋወጦች የሞኖፖሊ ካፒታሊዝምን ዕድገት ወደ መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም እንዲሸጋገር አፋጠኑት ።

ቀኝ ክንፍ ሶሻሊስቶችና በራገሮች መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝምን እንደሶሻሊዝም እንዲቆጠር ለማሳመን ይሞክራሉ ። መንግሥት በካፒታሊስት አገሮች ምጣኔ — ሀብት ውስጥ ወሳኝ ኃይል እንደሚሆንና የምጣኔ — ሀብቱን ዕቅዳዊ አመራር በጠቅላላው ሕብረተሰብ ዝንባሌ መሠረት ዋስትና እንደሚሰጠው ፣ ወዘተ . . . . ያልማሉ ። ኑሮ ይህ በጠቅላላ እውነት እንዳልሆነ አሳይቷል ።

መንግሥታዊ — ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የኢምፔሪያሊዝምን አፈጣጠር ልዩ አያደርገውም ፤ በሕብረተሰብ ምርት ሥርዓት ውስጥ የመሠረታዊ መደቦችን ሁኔታ አይለውጠውም ፣ እንዲያውም በተቃራኒው በጉልበትና በወረት መካከል ያለውን ድንበር ጥልቀት ይሰጠዋል ፣ ማለትም በብዙኃኑ ብሔሮችና ሞኖፖሊዎች መካከል ያለውን ። የካፒታሊስትን ምጣኔ — ሀብት መንግሥት ሥርዓት ያስይዘዋል

የሚለው ሙከራ የምርት ሥርዓት — አልባነትና ውድድርን አያስወግድም ፣ በሕብረተሰብ ደረጃ ዕቅዳዊ የምጣኔ — ሀብት ዕድገትን ዋስትና አይሰጥም ፣ ምክንያቱም አሁንም የምርት መሠረት ካፒታሊስታዊ ባለቤትነትና የቅጥር ጉልበት ብዝበዛ ሆነው ይቀራሉና ።

« ከቀውስ — ነጻ የሆነ ዕቅዳዊ ካፒታሊዝም » ሁኔታ የቡርዧ ንድፈ ሀሳቦች ባሁኑ ወቅት ባለው የካፒታሊስት ምጣኔ — ሀብታዊ የዕድገት አዝማሚያ ቅጥሚገጥሟቸዋል ። የመንግሥታዊ — ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ዲያሌክቲክስ የካፒታሊስትን ሥርዓት ከማጠናከር ይልቅ ፣ ማለትም ቡርዧዎች እንደሚአጤኑት ፣ ይበልጥ የካፒታሊዝምን ቅራኔ ያባብስና መሠረቱን ያናጋዋል ።

አሁን የምጣኔ — ሀብት ነጻነትን መንገድ በተከተሉ በብዙ ኋላ — ቀር አገሮች (ሕንድ ፣ ኢንዶኔዥያ ፣ ጋና ፣ የተባበረው አረብ ሬፑብሊክ ፣ እና ሌሎችም) ውስጥ መንግሥት ለአንዳንድ የምጣኔ —ሀብት ሁኔታዎች ኃላፊ ነው ፣ እናም ከባድ ኢንዱስትሪ ፣ ያስፋፋል ። ግን እዚያ ፣ መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም አይደለም እያደገ የሚሄደው ፣ ግን መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ነው ። በምጣኔ — ሀብት ወደኋላ ለቀሩ አገሮች ይህ ተራማጅ ደረጃ ነው ፤ ምክንያቱም የእነዚህን አገሮች ምጣኔ — ሀብት ዕድገት በማስጠበቅ ከኢምፔሪያሊስቶች ምጣኔ — ሀብት ነጻ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል ።

ያልተስተካከለ የምጣኔ ሀብትና የፖለቲካ ዕድገት ሕግ

የእያንዳንዱ ድርጅት ፣ ኢንዱስትሪና አገር ያልተስተካከለ ዕድገት የጠቅላላው የካፒታሊስት ዘመን ጸባይ ነው ። ያልተስተካከለ ዕድገት የሚመጣው ከውድድርና ከካፒታሊስት ምርት ሥርዓት—አልባነት ነው ። ግን በቅድመ — ሞኖፖሊ ዘመን ፣ ካፒታሊዝም በአንጻራዊ መስተካከል ማደግ ይችል ነበር ። አንዳንድ አገሮች በሌሎች ከጊዜ ብዛት ተቀድመው ነበር ። ግን የካፒታሊዝም ያልተስተካከለ ዕድገት ጸባይ የተገታው ወደ ኢምፔሪያሊዝም ከተደረገው ሽግግር ጋር ነው ። ከዚያ የተለያዩ አገሮች እመርታዊ ዕድገት ጀመሩ ። የቴክኖሎጂ ያልተጠበቀ ምጥቀት አንዳንድ አገሮች ተወዳዳሪዎቻቸውን አልፈው እንዲሄዱ ዕድል ሰጣቸው ። መሪነቱን የያዙ አገሮች የተቻላቸውን ያህል ከፍተኛ መጠን ጥሬ — ሀብት ፣ አዲስ ገበያዎች የወረት መዋዕለ — ንዋይ ክልል ለመያዝ ተሯሯጡ ። ግን ምንም የሚያዝ ነጻ ግዛት አልነበረም ፣ ምክንያቱም የዓለም ክፍፍል ቀድሞውኑ አልቆ ነበርናነው ።

በኢምፔሪያሊስት ኃይላት መካከል የተለዋወጠው የምጣኔ — ሀብትና የወታደራዊ ኃይል ሕብረት ወደ ግጭት አመራ ። ቀድሞውኑ ተከፋፍሎ የነበረውን ዓለም እንደገና ለመከፋፈል ትግል ፈነዳ ። የኃይሎች ዝምድና መለዋወጥ የካፒታሊስቱን ዓለም በጠበኛ ቡድኖች መካከል ከፋፈለውና የዓለም ጦርነቶች ተቀጣጠሉ ። በኢምፔሪያሊስት ሰፈርና በዓለም ጦርነቶች ውስጥ የተባባሱት ቅራኔዎች በማንኛውም አቅጣጫ የኢምፔሪያሊስቶችን መዳከም አስገኘ ። በዚህ ምክንያት ፣ በኢምፔሪያሊስት ግንባር ውስጥ ሕብረቱ በተዳከመበት በኩል መግቢያ ቀዳዳ ተገኘ ፤ ይህም ለወዛደሩ ድል ማድረግ በጣም አመቺ ሁኔታን አስገኘ ።

በኢምፔሪያሊስት ዘመን የካፒታሊስት አገሮች ያልተስተካከለ ምጣኔ — ሀብታዊ ዕድገት ወደአልተስተካከለ ፖለቲካዊ ዕድገታቸው አመራቸው ። የመደብ የግ ቅራኔዎችም በሁሉም አገሮች በአንድ ዓይነት ደረጃ አልነበሩም ። የወዛደሩ የፖለቲካዊ ንቃትና አብዮታዊ ቆራጥነት እናም ሰፊውን ገበሬ ከራሱ ጋር በማስተባበር የመምራት ችሎታም እንዲሁ ያልተስተካከለ ነበር ። ይህም ማለት ለወዛደሩ አብዮት የፖለቲካዊ ሁኔታዎችም በተለያዩ አገሮች የበሰሉት በመዝረክረክ ነው ።

ሌኒን ፣ በኢምፔሪያሊዝም ዘመን የካፒታሊስት አገሮችን ያልተስተካከለ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ሕግ መነሻው በማድረግ ፣ ስለ ሶሻሊዝም በጥቂት አገሮችም ወይም በአንድ ካፒታሊስት አገር ብቻ ድል ማድረግ መቻልና ፣ በአንጻ



በመላው ዓለም የሶሻሊዝም ድል ለማድረግ አለመቻልን ታሪካዊ ማጠቃለያ አቀረቧል ። ከዚህም በላይ ፣ ይህን ለማድረግ አንድ ሀገር ከሁሉም ካፒታሊስት አገሮች ይበልጥ ማደጉ በፍጹም አስፈላጊ አልነበረም ።

የሶሻሊስት አብዮት በአንድ ሀገር ውስጥ ድል ማድረግ ለዓለም ሶሻሊስት አብዮት የመጀመሪያው ነበር ።

የሌኒን መደምደሚያ ዓይነተኛነት ለተለያዩ አገሮች ወዛደሮች አብዮታዊ አመለካከትን ማሳየቱ ፣ ስሜታቸውን አነሳስቶ የሶሻሊስት ሥርዓት ድል ማድረግ የማይቀር መሆኑን ማጠናከሩ ነው ። ለዓለም ምጣኔ — ሀብት የሶሻሊስት ሥርዓት የመመሥረት ፍላጎትና በሶሻሊስትና በካፒታሊስት አገሮች መካከል የሚራዘም በሰላም የመኖር ስምምነት መቻል የመጣው የሶሻሊዝም ድል ማድረግ በተለያዩ አገሮች በተለያዩ ጊዜ ከመምጣቱ ላይ ነው ።

የሶሻሊስት አብዮት ሌኒኒስታዊ ንድፈ — ሀሳብ ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠው በሌኒን በተመራው የኮሚኒስት ፓርቲ አቀነባባሪነት በታላቁ የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ድል ነው ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ብዙ የአውሮጳና የእስያ አገሮች ከኢምፔሪያሊስት ሥርዓት ውስጥ በድል አድራጊ አብዮቶች ምክንያት መንጠባጠባቸውና አሁን ሶሻሊዝምን በመገንባት ላይ መሆናቸው ለሶሻሊስት አብዮት ሌኒኒስታዊ ንድፈ—ሀሳብ ተጨማሪ ብሩኅዊ ማረጋገጫ ነው ።

## 2. የዓለም ካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ፤

የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ባሕርይና ደረጃዎች

« ዘመናችን ፣ ዋና ይዘቱ ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም መሸጋገር የሆነው ፣ በሁለት ተጻራሪ የሕብረተሰብ ሥርዓቶች መካከል ያለ የትግል ዘመን ነው ፣ የሶሻሊስትና የብሔራዊ — አርነት አብዮቶች ዘመን ፣ የኢምፔሪያሊዝም መሰባበርና የቅኝዊ ሥርዓት ተጠርጎ መጣያ ዘመን ፣ እጅግ ! እጅግ ! ብዙ ሕዝብ ወደሶሻሊስት ጐዳና የሚሸጋገርበት ዘመን ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሶሻሊዝምና የኮሚኒዝም የመስፋፊያ መንሠራፊያ ዘመን ፣ ነው ።» [1] ይህ በሶቪዬት ሕብረት የኮሚኒስት ፓርቲ ፕሮግራም የተቀመረው አባባል የካፒታሊዝምን አጠቃላይ የቀውስ ባሕሪ ያብራራል ።

የ1917 ዓም ታላቁ የሩስያ የጥቅምቱ የሶሻሊስት አብዮት ማለት የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ መጀመሪያ ነበር ። ካፒታሊዝም በዓለም ብቻውን የሆነ ሥርዓት መሆኑን አቆመ ። በ1/5ኛው ዓለም ላይ በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ፣ ግን ሕብረተሰባዊ በሆነ ሶሻሊስታዊ ባለቤትነት የተመሠረተ አንድ መንግሥት ወደ ሕልውና መጣ ። በሩሲያ የወዛደሩ አብዮት ድል ማድረግ ማለት የካፒታሊዝም ዘመን ማክተም መጀመርና የሶሻሊዝም ድል ሆነ። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ማለትም በኢምፔሪያሊስት ደረጃ በተለያዩ አገሮች ባንዴ ሳይሆን ግን በረጅም ጊዜ በተለያዩ ወቅት አንድ ካንዱ በመከተል ፣ ከካፒታሊስት ዓለማዊ ሥርዓት እየተንጠባጠቡ ሲወጡ ፣ ሶሻሊዝም ድል እያደረገ ይሄዳል ፣ የሚለው የሌኒን ንድፈ ሀሳብ እዚህ ላይ ነበር የተረጋገጠው ።

ቀደም ባለው ምዕራፍ ስለምጣኔ ሀብታዊ ቀውሶች አፈጣጠር ተመልክተናል። በካፒታሊስዝም ውስጥ የምጣኔ ሀብት ቀውስ ከሸቀጥ የመጠን በላይ መመረት ፀባይ አንዱ ነው ። የሚአድገው በምጣኔ ሀብት አድማስ ብቻ ነው ፣ ሆኖም በሕብረተሰብ ፖለቲካዊ ኑሮ ላይ የተወሰነ ውጤት አለው ። የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ በካፒታሊስት አገሮች ማንኛውንም የኑሮ አድማስ ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ

1. ወደ ኮሚኒዝም ጐዳና ፣ ገጽ 449

የሚለው ሙከራ የምርት ሥርዓት — አልባነትና ውድድርን አያስወግድም ፣ በሕብረተሰብ ደረጃ ዕቅዳዊ የምጣኔ — ሀብት ዕድገትን ዋስትና አይሰጥም ፣ ምክንያቱም አሁንም የምርት መሠረት ካፒታሊስታዊ ባለቤትነትና የቅጥር ጉልበት ብዝበዛ ሆነው ይቀራሉና ።

« ከቀውስ — ነጻ የሆነ ዕቅዳዊ ካፒታሊዝም » ሁኔታ የቡርዧ ንድፈ ሀሳቦች ባሁኑ ወቅት ባለው የካፒታሊስት ምጣኔ — ሀብታዊ የዕድገት አዝማሚያ ቅጥሚ ገጥሟቸዋል ። የመንግሥታዊ — ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ዲያሌክቲክስ የካፒታሊስትን ሥርዓት ከማጠናከር ይልቅ ፣ ማለትም ቡርዧዎች እንደሚአጤኑት ፣ ይበልጥ የካፒታሊዝምን ቅራኔ ያባብስና መሠረቱን ያናጋዋል ።

አሁን የምጣኔ — ሀብት ነጻነትን መንገድ በተከተሉ በብዙ ኋላ — ቀር አገሮች (ሕንድ ፣ ኢንዶኔዥያ ፣ ጋና ፣ የተባበረው አረብ ሪፑብሊክ ፣ እና ሌሎችም) ውስጥ መንግሥት ለአንዳንድ የምጣኔ —ሀብት ሁኔታዎች ኃላፊ ነው ፣ እናም ከባድ ኢንዱስትሪ ፣ ያስፋፋል ። ግን እዚያ ፣ መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም አይደለም እያደገ የሚሄደው ፣ ግን መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ነው ። በምጣኔ — ሀብት ወደኋላ ለቀሩ አገሮች ይህ ተራማጅ ደረጃ ነው ፤ ምክንያቱም የእነዚህን አገሮች ምጣኔ — ሀብት ዕድገት በማስጠበቅ ከኢምፔሪያሊስቶች ምጣኔ — ሀብት ነጻ እንዲሆን ይረዳቸዋል ።

ያልተስተካከለ የምጣኔ ሀብትና የፖለቲካዊ ዕድገት ሕግ

የእያንዳንዱ ድርጅት ፣ ኢንዱስትሪና አገር ያልተስተካከለ ዕድገት የጠቅላላው የካፒታሊስት ዘመን ጸባይ ነው ። ያልተስተካከለ ዕድገት የሚመጣው ከውድድርና ከካፒታሊስት ምርት ሥርዓተ—አልባነት ነው ። ግን በቅድመ — ሞኖፖሊ ዘመን ፣ ካፒታሊዝም በአንጻራዊ መስተካከል ማደግ ይችል ነበር ። አንዳንድ አገሮች በሌሎች ከጊዜ ብዛት ተቀድመው ነበር ። ግን የካፒታሊዝም ያልተስተካከለ ዕድገት ጸባይ የተገታው ወደ ኢምፔሪያሊዝም ከተደረገው ሽግግር ጋር ነው ። ከዚያ የተለያዩ አገሮች እመርታዊ ዕድገት ጀመሩ ። የቴክኖሎጂ ያልተጠበቀ ምጥቀት አንዳንድ አገሮች ተወዳዳሪዎቻቸውን አልፈው እንዲሄዱ ዕድል ሰጣቸው ። መሪነቱን የያዙ አገሮች የተቻላቸውን ያህል ከፍተኛ መጠን ጥሬ — ሀብት ፣ አዲስ ገበያዎች የወረት መዋዕለ — ንዋይ ክልል ለመያዝ ተሯሯጡ ። ግን ምንም የሚያዝ ነጻ ግዛት አልነበረም ፣ ምክንያቱም የዓለም ክፍፍል ቀድሞውኑ አልቆ ነበርናነው ።

በኢምፔሪያሊስት ኃይላት መካከል የተለዋወጠው የምጣኔ — ሀብትና የወታደራዊ ኃይል ሕብረት ወደ ግጭት አመራ ። ቀድሞውኑ ተከፋፍሎ የነበረውን ዓለም እንደገና ለመከፋፈል ትግል ፈነዳ ። የኃይሎች ዝምድና መለዋወጥ የካፒታሊስቱን ዓለም በጠበኛ ቡድኖች መካከል ከፋፈለውና የዓለም ጦርነቶች ተቀጣጠሉ ። በኢምፔሪያሊስት ሰፈርና በዓለም ጦርነቶች ውስጥ የተባባሱት ቅራኔዎች ፣ በማንኛውም አቅጣጫ የኢምፔሪያሊስቶችን መዳከም አስገኘ ። በዚህ ምክንያት ፣ በኢምፔሪያሊስት ግንባር ውስጥ ሕብረቱ በተዳከመበት በኩል መግቢያ ቀዳዳ ተገኘ ፤ ይህም ለወዛደሩ ድል ማድረግ በጣም አመቺ ሁኔታን አስገኘ ።

በኢምፔሪያሊስት ዘመን የካፒታሊስት አገሮች ያልተስተካከለ ምጣኔ — ሀብታዊ ዕድገት ወደአልተስተካከለ ፖለቲካዊ ዕድገታቸው አመራቸው ። የመደብ ቅራኔዎችም በሁሉም አገሮች በአንድ ዓይነት ደረጃ አልነበሩም ። የወዛደሩ የፖለቲካዊ ንቃትና አብዮታዊ ቆራጥነት እናም ሰፊውን ገበሬ ከራሱ ጋር በማስተባበር የመምራት ችሎታም እንዲሁ ያልተስተካከለ ነበር ። ይህም ማለት ለወዛደሩ አብዮት የፖለቲካዊ ሁኔታዎችም በተለያዩ አገሮች የበሰሉት በመዝረክረክ ነው ።

ሌኒን ፣ በኢምፔሪያሊዝም ዘመን የካፒታሊስት አገሮችን ያልተስተካከለ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ሕግ መነሻው በማድረግ ፣ ስለ ሶሻሊዝም በጥቂት አገሮችም ወይም በአንድ ካፒታሊስት አገር ብቻ ድል ማድረግ መቻልና ፣ በአንዶ



በመላው ዓለም የሶሻሊዝም ድል ለማድረግ አለመቻልን ታሪካዊ ማጠቃለያ አቅርቧል ። ከዚህም በላይ ፣ ይህን ለማድረግ አንድ ሀገር ከሁሉም ካፒታሊስት አገሮች ይበልጥ ማደጉ በፍጹም አስፈላጊ አልነበረም ።

የሶሻሊስት አብዮት በአንድ ሀገር ውስጥ ድል ማድረግ ለዓለም ሶሻሊስት አብዮት የመጀመሪያው ነበር ።

የሌኒን መደምደሚያ ዓይነተኛነት ለተለያዩ አገሮች ወዛደሮች አብዮታዊ አመለካከትን ማሳየቱ ፣ ስሜታቸውን አነሳስቶ የሶሻሊስት ሥርዓት ድል ማድረግ የማይቀር መሆኑን ማጠናከሩ ነው ። ለዓለም ምጣኔ — ሀብት የሶሻሊስት ሥርዓት የመመሥረት ፍላጎትና በሶሻሊስትና በካፒታሊስት አገሮች መካከል የሚራዘም በሰላም የመኖር ስምምነት መቻል የመጣው የሶሻሊዝም ድል ማድረግ በተለያዩ አገሮች በተለያዩ ጊዜ ከመምጣቱ ላይ ነው ።

የሶሻሊስት አብዮት ሌኒኒስታዊ ንድፈ — ሀሳብ ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠው በሌኒን በተመራው የኮሚኒስት ፓርቲ አቀነባባሪነት በታላቁ የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ድል ነው ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ብዙ የአውሮጳና የእስያ አገሮች ከኢምፔሪያሊስት ሥርዓት ውስጥ በድል አድራጊ አብዮቶች ምክንያት መንጠባጠባቸውና አሁን ሶሻሊዝምን በመገንባት ላይ መሆናቸው ለሶሻሊስት አብዮት ሌኒኒስታዊ ንድፈ—ሀሳብ ተጨማሪ ብሩኃዊ ማረጋገጫ ነው ።

## 2. የዓለም ካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ፤

የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ባሕርይና ደረጃዎች

« ዘመናችን ፣ ዋና ይዘቱ ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም መሸጋገር የሆነው ፣ በሁለት ተጻራሪ የሕብረተሰብ ሥርዓቶች መካከል ያለ የትግል ዘመን ነው ፣ የሶሻሊስትና የብሔራዊ — አርነት አብዮቶች ዘመን ፣ የኢምፔሪያሊዝም መሰባበርና የቅኝዊ ሥርዓት ተጠርጎ መጣያ ዘመን ፣ እጅግ ! እጅግ ! ብዙ ሕዝብ ወደሶሻሊስት ጎዳና የሚሸጋገርበት ዘመን ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሶሻሊዝምና የኮሚኒዝም የመስፋፊያ መንሠራፊያ ዘመን ፣ ነው ።» [1] ይህ በሶቪዬት ሕብረት የኮሚኒስት ፓርቲ ፕሮግራም የተቀመረው አባባል የካፒታሊዝምን አጠቃላይ የቀውስ ባሕሪ ያብራራል ።

የ1917 ዓም ታላቁ የሩስያ የጥቅምቱ የሶሻሊስት አብዮት ማለት የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ መጀመሪያ ነበር ። ካፒታሊዝም በዓለም ብቻውን የሆነ ሥርዓት መሆኑን አቆመ ። በ1/5ኛው ዓለም ላይ በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ፣ ግን ሕብረተሰባዊ በሆነ ሶሻሊስታዊ ባለቤትነት የተመሠረተ አንድ መንግሥት ወደ ሕልውና መጣ ። በሩሲያ የወዛደሩ አብዮት ድል ማድረግ ማለት የካፒታሊዝም ዘመን ማክተም መጀመርና የሶሻሊዝም ድል ሆነ። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ማለትም በኢምፔሪያሊስት ደረጃ በተለያዩ አገሮች ባንዴ ሳይሆን ግን በረጅም ጊዜ በተለያዩ ወቅት አንድ ካንዱ በመከተል ፣ ከካፒታሊስት ዓለማዊ ሥርዓት እየተንጠባጠቡ ሲወጡ ፣ ሶሻሊዝም ድል እያደረገ ይሄዳል ፣ የሚለው የሌኒን ንድፈ ሀሳብ እዚህ ላይ ነበር የተረጋገጠው ።

ቀደም ባለው ምዕራፍ ስለምጣኔ ሀብታዊ ቀውሶች አፈጣጠር ተመልክተናል። በካፒታሊስዝም ውስጥ የምጣኔ ሀብት ቀውስ ከሸቀጥ የመጠን በላይ መመረት ፀባይ አንዱ ነው ። የሚአድገው በምጣኔ ሀብት አድማስ ብቻ ነው ፣ ሆኖም በሕብረተሰብ ፖለቲካዊ ኑሮ ላይ የተወሰነ ውጤት አለው ። የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ በካፒታሊስት አገሮች ማንኛውንም የኑሮ አድማስ ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ

1. ወደ ኮሚኒዝም ጎዳና ፣ ገጽ 449

ውንም ጨምር ይገልጸል ፣ ባጠቃላይ የዓለም የካፒታሊስት ሥርዓት ሁለገብ የሆነ ቀውስ ነው ፣ ጸባዩም አርጅቶ ባፈጀው ካፒታሊዝምና በሶታው (ወጣቱ) ሶሻሊዝም መካከል የሚካሄድ ትግል ይሆናል። የካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ሽግግር የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ዋና ይዘት ነው ።

የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ያደገው በሁለት ደረጃዎች ሆኖ ስስተኛውን ተያይዞታል ። የመጀመሪያው የተጀመረው በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ሆኖ ይበልጥ ለይቶ ቁጭ ያለው ፣ በጥቅምቱ አብዮት ውጤት ነው ። ሁለተኛው ደረጃ ያደገው በሁለተኛ የዓለም ጦርነትና በአውሮጳና እስያ ብዙ አገሮች የሶሻሊስት አብዮት መካሄድ ላይ ነው ። በ1950 ዎቹ ሁለተኛው አጋማሽ የዓለም ካፒታሊዝም አዲሱን ስስተኛውን ደረጃ የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ገባ ። የዚህ አዲስ ደረጃ ይበልጥ ዓይነተኛ ገጽ (ጸባይ) ከዓለም ጦርነት ጋር በመዛመድ ሳይሆን ግን በሁለት ሥርዓቶች መካከል በሚደረገው የውድድርና የትግል ሁኔታ የኃይሎች ዝምድና ሶሻሊዝምን ተከትሎ በማዘንበሉ ምክንያት መሆኑ ነው ።

የካፒታሊዝም መሠረታዊአጠቃላይ የቀውስ ገፅታዎች ፤የብዙ አገሮች ከካፒታሊዝም እየተንጠባጠቡ መውጣት፣ኢምፔሪያሊዝም ከሶሻሊዝም ጋር ባለው የምጣኔ ሀብት ውድድር መዳከሙ፣ የኢምፔሪያሊዝም ቅኛዊ ሥርዓት ቀውስና መሰባበር፣ የኢምፔሪያሊዝም ቅራኔዎች በመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝምና እያደገ በሚሄደው ወታደራዊነት ሁኔታዎች መባባስ ፣ በተከታታይ እንደታየው ካፒታሊዝም የምርት ኃይሎችን በሙሉ በጥቅም ላይ ለማዋል ባለመቻል (ዝቅተኛ ደረጃ የምጣኔ ሀብት ዕድገት፤ ወቅታዊ ቀውስ ፣ ከማምረት ችሎታ በታች መሆን በአስቃቂ ሥራ አጥነት) ምክንያት እየጨመረ የሚሄደው ውስጣዊ ዕርጋታ ማጣትና የካፒታሊስት ምጣኔ ሀብት መበስበስ፤ በወረትና በጉልበት ቅራኔ መካከል ትግሉ እየ እየጠነከረ መሄድ ፤የዓለም ካፒታሊስት ምጣኔ ሀብት ቅራኔዎች በአስቃቂ ሁኔታ መባባስ ፣ በማንኛውም አቅጣጫ ታይቶ ያልታወቀ የፖለቲካ ብጥብጥ ማደግ ፣ የቡርዣ ነፃነቶች መከልከልና የፋሺስቶች ጨካኝ መንግሥት በብዙ አገሮች መቋቋም፣እና በቡርዧ ርዕዮተ ዓለምና ፖሊቲካ ጥልቀት ያለው ቀውስ መፈጠር ናቸው።

እነዚህ የካፒታሊዝም አጠቃላይ የቀውስ ገፅታዎች እንዴት እንደሚከሠቱ እንይ።

የዓለም በሁለት ሥርዓት መከፋፈል

ከ1914 — 18 የነበረው ያንደኛው ያለም ጦርነት የኢምፔሪያሊስት ኃይላት ዓለምን እንደገና ለመከፋፈል በተደረገው ትግል ጊዜ ተባብሶ የነበረ ቅራኔ ውጤት ነው ። ጦርነቱ ኢምፔሪያሊዝምን አዳክሞ ባለው የኢምፔሪያሊስት ግንባር መከፋፈል ፈጥሮ ነበር ። ቀዳዳው (ስብርብሩ) የተፈጠረው ማለትም ፣ በዓለም ኢምፔሪያሊዝም ሠንሠለታዊ መያያዝ ደካማ ጐን ለሁሉም ቅራኔዎች ዋና ነጥብ በነበረው ፣ በሩሲያ ነበር ። በሩሲያ የወዛደሩ አብዮት የድል ውጤት ዓለም በሁለት ሥርዓት ተከፋፈለች ፤ ካፒታሊስትና ሶሻሊስት በሚባሉ ።

በአጭር ጊዜ ውስጥ የሶሻሊስት ምጣኔ ሀብታዊ ሥርዓት በካፒታሊዝም ላይ ከፍተኛ ጥቅሙን አሳዩ (አከናወነ) ። በ1937 የሶቪየት ሕብረት በአውሮጳ የአንደኛነትን በመላው ዓለም የሁለተኛነት ደረጃን በኢንዱስትሪ ምርት ብዛት ወሰዳለች ።

በዓለም አቀፍ አደግራሪዎች የተዘጋጀው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተቀጣጠለው በፋሺስት መንግሥታት ክልል ነው — በጀርመን ፣ ኢጣሊያና ፣



ጃፓን ነው ። ጦርነቱ በፋሺስት ወራሪዎች ፍጹም ድልመሆን አከተመ ። ድሉን ለመቀዳጀት ሶቢየት ሕብረት ወሳኝ ሚና ተጫውታለች ። በጦርነቱ የሶቪየት ሕብረት ድል ማድረግ በመላው ዓለም ከዚያ በፊት ወደአልታዩ አብዮታዊና ብሔራዊ የአርነት እንቅስቃሴ አመራ ።

ብዙ አገሮች በአውሮጳና በእስያ ከካፒታሊስት ሥርዓት ተንጠባጠቡ ፣ ስለሆነም አሁን ከካፒታሊስት ቀንበር ነጻ የወጡና በትክክል ሶሻሊዝምን የሚገነቡ ከአንድ ሺ ሚሊዮን ሕዝቦች በላይ (ከ1/3ኛው የዓለም ጠቅላላ ሕዝብ) አሉ ። ይህም በሶሺያሊዝምና በካፒታሊዝም ኃይላት መካከል ከፍተኛ የሕብረት ለውጥ ፣ ማለትም ለሶሻሊዝም አመቺነትን ለካፒታሊዝም መደምሰስን ፣ አመጥቷል ።

ስለዚህ የጦርነቱ ንጥር ውጤት ፣ የካፒታሊዝምን አጠቃላይ ቀውስ የበለጠ ጥልቀት የሚሰጥ ነበር ። አሁን ሁለተኛው ደረጃ ተጀምሯል ። ሶሻሊዝም ከአንድ አገር ድንበር አልፎ ዓለማዊ ሥርዓት መሆኑ በመንፀባረቅ ላይ ነው ። ዛሬ ፣የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት አገሮች የዓለምን ግዛት 1/4ኛውን በላይ ይዘዋል ። ከዓለም የኢንዱስትሪ ምርት ለ37 በመቶውና ከዓለም የእርሻ ምርት ለ40 በመቶው ኃላፊ ናቸው ።

በአጭር ጊዜ ውስጥ የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት በካፒታሊዝም ላይ የበላይነቱን አሳይቷል ፣ የሶሻሊስት አገሮች ምጣኔ ሀብት ዕድገት ከካፒታሊስት ምጣኔ ሀብት እጅግ የፈጠነ ነው ። በ1961 ዓ ም የሶሻሊስት አገሮች የኢንዱስትሪ ምርትን ብዛት ከ1937 ሲነጻጸር ከሰባት ዕጥፍ በላይ ሲአድግ የካፒታሊስት አገሮች ግን በ2.5 እጥፍ ብቻ እንዳስደጉ ነው የሚአሳየው ።

አዲሱ ፣ ሶስተኛው የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ተጀምሯል ። የዚህ ደረጃ ዓይነተኛ መለያ ጸባይ ያለም ሶሻሊስት ሥርዓት በሰብአዊ ሕብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ወሳኝ ምክንያት ከመሆኑ ላይ ነው ። ስለሆነም መጀመሪያና ከሁሉም በላይ የቀውሱ አዲስ ደረጃ በሁለት ሥርዓቶች መካከል ውድድር ነው ። ማለትም የሶሻሊዝም ሁኔታ ጥንካሬው እየጨመረ ሲሄድ የኢምፔሪያሊዝም ሁኔታ ግን ድክመቱ ያይላል ።

የኢምፔሪሊዝም ቅኛዊ ሥርዓት ቀውስና መሰባበር

በጥቅምቱ አብዮት በመሳብ ፣ ለብሔራዊ አርነታቸው የሚአካሄዱት የቅኝ ግዛት ሕዝቦች ትግል በከፍተኛ ደረጃ ጥንካሬ አገኘ ፤ የኢምፔሪያሊዝም ቅኛዊ ሥርዓት ቀውስ ተጀመረ። ይህ ቀውስ በኢምፔሪያሊስት ኃይላትና በቅኝና ጥገኛ ሀገሮች መካከል ትብ የሆነ የቅራኔዎችን መባባስ ዓይነተኛ ያደርጋል ። የብሔራዊ አርነት ትግል ዕድገት የመጣው እራሳቸውን ከኢምፔሪያሊስት ቀንበር ነጻ ባወጡ የቅኝና ጥገኛ ሀገሮች ነው ። የብሔራዊ አርነት ኃይላት ወደ ሕልውና መጥተው ዕድገት ጀምረዋል ። የወዛደሩ ቁጥር — በዘመኑ ሕብረተሰብ ውስጥ ዋናው አብዮታዊ መደብ — ማደግ ጀምሯል ። ወዛደሩ ገበሬውን ፤ ሠፊውን የቅኝ ግዛት ሕዝብ የሚአጠቃልለውን ፣ ለጸረ — ኢምፔሪያሊስት ትግል አስልፎታል ። ብሔራዊ ከበርቴው ፣ ዝንባሌው ከውጭ ሞኖፖሊዎች አገዛዝ የሚጋጨውም ፣ እያደገ ነበር ።

በአንደኛው የዓለም ጦርነት መጨረሻ ላይ ይነስም ይብዛ ጠንካራ ጸረ—ኢምፔሪያሊስት ፍንዳታ ያልተካሄደባቸው ቅኝ ወይም ጥገኛ አገሮች አልፈው አልፈው ነበሩ ። በተለይ ስፋት ያለው የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ የታሰበው በቻይና ነበር። እዚያ ፣ በ1924 ፣ የሕዝብ ጸረ—ኢምፔሪያሊስት ጸረ—መልከኛ አብዮት ማለትም ያልተቋረጠ ፣ አብዮታዊ ጦርነት ፈነዳ ። ይህ አብዮት በቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ የሚመራውን ሕዝባዊ ነጻ አውጭ ሠራዊት ወደ ሕልውና አመጣ ፣ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎችም ሕዝባዊ መንግሥት ተቋቁሞ ነበር ። በሕንድ በኢንዶኔዥያና በሌሎች አገሮች ታላቅ የሆነ የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ ነበር ። ኢምፔሪያሊ

ዝምን በመቋቋም በዚህ የተጨቆኑ ሕዝቦች የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ መሪው ኃይል፣ብዙ ሚሊዮን ገበሬዎችን የቡርዣ ዲሞክራሲያዊ ተወካዮችን ሲላም … በዙሪያው አካቦ የያዘው የወዛደሩ መደብ ነው ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የብዙ ቅኝችና ጥገኛ ሀገር ሕዝቦች ከቅኝ ገዥዎች ነጻነትን አገኙና እንደነጻ ፣ ክብሩ የማይገሠሥ መንግሥት በመሆን ማደግ ጀመሩ ።የኢምፔሪያሊዝም ቅኛዊ ሥርዓት መሰባበር ጀመረ ።የቻይናው ያን ኮርያውያንና ቬየትናም ሕዝቦች የጀግንነት ትግል የውጭ ኢምፔሪያሊስቶችንና የበዝባዥ መደቦችን ገዥነት ወርውሮ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥታትን በማቋቋም ታዩ የቻይና ሕዝባዊ ሬፑብሊክ ፣የኮሪያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ እና የቬትናም ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ የሚባሉትን ።

በ1947 ዓ. ም. በብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ ተፅዕኖ ምክንያት የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም የሕንድን ነጻ መንግሥት እንዲያውቅ ተገደደ ። ከሕንድ ጋር ሌሎች አገሮች ፣ ኢንዶኔዢያና በርማ ፣ ሲሎን በነጻነት የዕድገት ጐዳና ላይ ወጡ። ብዙ የምሥራቅ አረብና አፍሪካ አገሮች ከጦርነት በኋላ ነጻ መንግሥት አቋቋሙ ፣ ለዘመናትም እስከጦርነቱ ማለቂያ ከ1,500 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የቅኝ ወይምየገማሽ ቅኝ ግዛትን ቀንበር ወዲያ ወረወሩ ። ኩባ፣ከዩናይትድ ስቴትስ በ90 ማይል የምትርቅ ትንሽ አገር በዩናይትድ ስቴትስ ሞኖፖሊዎች ተጨርንቃ ተከባና ተከድና የተያዘች የሶሻሊትን አብዮት ጐዳና ወሰደች ። በ1963 ዓ ም የቅኝ ግዛት ሕዝቦች፣በ1919 የዓለምን ሕዝብ 69.2 በመቶውን የነበሩት፣ ወደ 1.5 በመቶ ወረዱ ።ይህ በግልጽ የሚጠቁመው ወራዳዊው ቅኛዊ ሥርዓት መጨማተር መሰባበሩን ነው ።

አዲስ ነጻ የወጡትን ሕዝቦች ከገጠማቸው መሠረታዊ ችግር አንዱ የትኛውን ጐዳና እንደሚከተሉ ነው ፤- የካፒታሊስትን ጐዳና ወይስ ካፒታሊስታዊ ያልሆነ ዕድገት ።

እነዚህ ሕዝቦች ካፒታሊዝም ምንድነው የሚሰጣቸው ?

ለሕዝቦች መሠቃየት ካፒታሊዝም መንገድ ነው የሚመረጠው ። ወይ ፈጣን ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገትን ዋስትና አይሰጥም ፣ ወይም ድህነትን አያስወግድም ። የገጠሩ ካፒታሊስታዊ ዕድገት ገበሬውን የበለጠ ያጠፋዋል።የሠራተኞች ዕጣ ወይ ካፒታሊስቶችን ለማበልጸግ ከባድ ሥራ ፤ አለዚያም ሥራ አጥነት ነው ። ንዑስ ከበርቴዎች ከትላልቅ ካፒታል (ወረት) ጋር በሚካሄድ ውድድር ይደቆሳሉ ። ምሁራንችሎታቸውን መቸርቸር ይኖርባቸዋል ።

እነዚህ ሕዝቦች ለሶሻሊዝም ምን ይሰጣቸዋል ?

ሶሻሊዝም ለሕዝቦች የነጻነትና የደስታ መንገድ ነው ።የምጣኔ ሀብትና የባሕል ከፍተኛ ዕድገትን ያረጋግጣል ። ኋላ ቀሩን አገር ወደ ኢንዱስትሪላያዊ አገር ባንድ የትውልድ ዘመን ያሸጋግራል ። የሰው በሰው መበዝበዝ መወገድ የሕብረተሰብ የእኩልነት አለመመጣጠንን ከትመት ይሰጠዋል።ሥራ አጥነት ሙሉ በሙሉ ይጠፋል ። ሶሻሊዝም ለሁሉም ገበሬዎች መሬት ይለግሳል ። እርሻቸውን እንዲያሻሽሉ ይረዳቸዋል ፣ በውዴታ የሕብረት ሥራ ያስተባብራቸዋል ፣ ዘመናዊ የእርሻ ቴክኖሎጂንና አግሮኖሚን ያሟላላቸዋል ። ሶሻሊዝም ከፍተኛ ቁሳዊና ባሕላዊ የኑሮ ደረጃን ለሠራተኛው መደብና ሕዝብ ያረጋግጣል ።

ሕዝቦች እራሳቸው ሊወስዱ የሚፈልጉትን መንገድ ይመርጣሉ ። በዛሬው ዘመን በዓለም መድረክ ላይ የኃይሎችን ዝምድናና ከዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት እውነተኛው ጠንካራ ድጋፍ ማግኘት መቻል ፣ የቀድሞ ቅኝ ሕዝቦች የራሳቸውን



ዝንባሌ ለመያዝና ለመወሰን ነጻ ናቸው ። ምርጫቸው ጥገኛ የሚሆነው በራሳቸው የመደብ ኃይሎች ዝምድና ላይ ነው ። የሠራተኛ መደብ የሁሉም ሠራተኛ ሕዝብና ጠቅላላው የዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ካፒታሊስታዊ ያልሆነን የዕድገት ጐዳና ለመከተል ከሁሉም ይበልጥ ከብሔራዊ ዝንባሌ መጣጣሙን ያረጋግጣል ።

ምንም ቅኝ ገዥነት በተጨቋኝ ሕዝቦች ታላቅ የብሄራዊ አርነት እንቅስቃሴ ከባድ ጡጫ ቢሰቃይም እንኳን አሁንም አልሞተም ።

ዛሬ ቅኝ ገዥነት ግልጽ የመሣሪያ ጦርነት ብቻ አይደለም የሚአደርገው ፣

ግን አዲስ ነጻ ወደ ወጡ አገሮችም ድብቅ የሰርጎ ገብ ሴራ ያካሂዳል ፣ ዓለማው እነዚህን አገሮች በምጣኔ ሀብትና በፖለቲካ የኢምፔሪያሊስት ኃይላት ጥገኛ ለማድረግ ነው ።

የዛሬው የቅኝ ገዥነት ዋና ተጠሪ ዩናይትድ ስቴትስ ናት።በዩናይትድ ስቴትስ መሪነት ኢምፔሪያሊስቶች በሕገወጥነት የብዝበዛን አዲስ መልኮችና ዘዴዎችን በቀድሞ ቅኞች ላይ ያውላሉ ። ሞኖፖሊዎች የበላይ የተፅዕኖ ይዞታቸውን በኢኮኖሚና በፖለቲካ በላቲን አሜሪካ በእስያና በአፍሪቃ ለማቆየት ይታገላሉ ። የድሮ ይዞታቸውን አዲስ ነጻ በውጡት አገሮች ምጣኔ — ሀብት ላይ ለማስጠበቅና በምጣኔ ሀብታዊ « ዕርዳታ » ስም አዲስ ቦታን ለማግኘት፣እነዚህን አገሮች ወደ ወታደራዊ ክልል በመሳብ ፣ በነሱ ላይ ወታደራዊ አምባገነንነት በማስገባትና በግዛቶቻቸው ውስጥ የጦር ሠፈር ለማቋቋም ያነጣጥሩባቸዋል ።

የቅኛዊ ሥርዓት መሰባበር በማይቀር ሁኔታ የካፒታሊስት አገሮችን ምጣኔ ሀብትና የፖለቲካ ችግሮችን ያሳድግና በአጠቃላይ የኢምፔሪያሊዝምን መሠረት ያናጋዋል ።

የቅኝ ገዥነት ሙሉ በሙሉ መጨማተርና መሞት የማይቀር ነው ። የቅኛዊ ሥርዓት ባርነት በብሔራዊ — የአርነት እንቅስቃሴ ዕድገት ምክንያት መሰባበር ከዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት መመሥረት በኋላ ሁለተኛው ዓይነተኛ ታሪካዊ ክስት ነው ።

የገበያ ችግር መባባስ ፤ አለቆቂ ሥራ አጥነትና የምርት ማዘትዘቅ

ከካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውሶች አንዱ ገፅታ የገበያ ችግር መባባስና የወረት መዋዕለ ንዋይ ክልል ነው ። የዚህ መባባስ ምክንያት በሚአድገው ምርትና በሸቀጦች መሸጥ መቻል መካከል ሳያቋርጥ እየጨመረ የሚሄደው አለመመጣጠን ነው ። እንደሩሲያ ያለ አገር ከካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ከካፒታሊስት ሥርዓት መንጠባጠብ በካፒታሊስት አገሮች መካከል ለገበያና ለወረት መዋዕለ ንዋይ ክልል ያለውን ትግል ጨመረ ። ከካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ሁለተኛ ደረጃ ፣ ከዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት መመሥረት ጋር ፣ ካፒታሊዝም ሰፋፊ ገበያዎችንና የወረት መዋዕለ — ንዋይ ክልሎችን አጥቷል ።

የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት መቋቋም ወደ የዓለም ሶሻሊስት ገበያ መመሥረት አመራ ። አሁን ሁለት የዓለም ገበያዎች ተከሥተዋል —የሶሻሊስትና የካፒታሊስት አገሮች ገበያ የሚባሉ ።

የካፒታሊስት የብዝበዛ ክልል መጥበብ ፣ የዛሬው የኢምፔሪያሊዝም ቅኛዊ ሥርዓት መሰባበር ፣ የብዙኃኑ ሠራተኛ የኑሮ ደረጃ መባባስና የምጣኔ — ሀብት ወታደራዊ መሆን ፣ ሁሉም አንድነት ሆነው ፣ በዓለም ካፒታሊስት ገበያ ላይ ዛሬ ተባብሶ የምናየውን ቅራኔ ይሠራሉ ።

አዳጊ አገሮች ጋር ውድድርም ሌላው ለገበያ የተጠናከረ ትግል ከአዲስ — ምክንያት ነው ። እነዚህ አገሮች ለሸቀጦቻቸው ሸያጭ ሲሉ ከቀን ቀን ባለኢንዱ ስትሪ አገሮችን በመፃረር እየተወዳደሩ ናቸው ። ይህ በተለይ በቀላል ኢንዱስትሪ ሪዎች ምርት (ውጤት) እርግጠኛ ሆኗል ።

ለገበያና ለወረት መዋዕለ — ንዋይ ትግል በካፒታሊስት የሞኖፖሊ ማሕበ ራትና በአምፔሪያሊስት መንግሥታት መካከል ግጭቶችን ይፈጥራል ።

ከገበያና ከወረት መዋዕለ ንዋይ በተባበሰው ችግር ላይ በቅርብ የተያያዙት የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ከአቅማቸውበታች የመሥራትና ቀዋሚ የሆነ በሰፊው ሥራ — አጥነት መስፋፋት የመሰሉት ናቸው ።

በቅድመ — ሞኖፖሊ የካፒታሊስት ዕድገት ፣ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ከች ሎታ በታች ሥራ በሰፊው የዋለው በምጣኔ — ሀብታዊ ቀውስ ብቻ ነበር ። አሁን በካፒታሊዝም አጠቃላይ የቀውስ ዘመን ፣ የድርጅቶች ከችሎታ በታች መሥራት በ1925 — 29 የምጥቀ ንባር ጸባይ ሆኗል ፣ ማለትም — በገደል አፋፍ ላይ ነው ። ት ዘመን ፣ ለምሳሌ ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ኢንዱስትሪዎች (አምራች) ከማምረት ችሎታ 80 በመቶውን ነው የተጠቀሙት ፣ በ1930—34 ደግሞ 60 በመቶውን ነው። በ1957 መጨረሻ ላይ 78 እጅ ብቻ ነበር ። የዩናይትድ የዐረብ ብረት ኢንዱስትሪ በ1960 ከማምረት ችሎታው 54 እጁን ብቻ ነው የተጠቀመው ።

የዚህ አስቃቂ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ከችሎታቸው በታች አሠራር ፊት ለፊት የሚደቀነው በካፒታሊዝም አጠቃላይ የቀውስ ዘመን የሥራ — አጥነት ጸባ ይም በመለወጡ ነው ። ቀድሞ የሥራ — አጡ ሠራዊት የአደገው በምጣኔ—ሀብት ቀውስ ነበር ፣ ግን በማገገም ወይም በምጥቀት ዘመን ደግሞ ተመልሶ በሥራ መያዝ (መቀጠር) ላይ ሆነ ፣ በዛሬው ጊዜ ነባር ሰፊ ሠራዊት እየሆነ ነው ። በታወቀ ስታ ትስቲክስ መሠረት በ1959 የሥራ — አጡ ምጥነት ከጠቅላላው ሠራተኛ ሕዝብ ሲመዛዘን ፣ በካናዳና ኢጣሊያ — 8.9 በመቶ ፣ በቤልጅግ 7.2 በመቶ እና በዩናይ ትድ ስቴትስ ደግሞ 6.1 በመቶ ነበር ። በ1963 በዩናይትድ ስቴትስ የሥራ አጡ ብዛት ወደ 5 ሚሊዮን ሲጠጋ ፣ በእንግሊዝ ደግሞ ወደ 1 ሚሊዮን ሆኗል ።

በብዙ አገሮች ከፍተኛ ሥራ — አጥነት የብሔራዊ ጥፋት እየሆነ ነው ። እንደ 1961 ዓ.ምህረት አንዱ እውቅ ስታትስቲክስ ፣ ከሆነ በሰሜን አሜሪካ እና ምዕራብ አውሮጳ የዳበሩ አገሮች ውስጥ ፣ እንዲሁም በጃፓንና በአውስትራሊያ ዛሬ ባጠቃ ላይ 12 ሚሊዮን ሥራ — አጦች አሉ ። ይህም ከሠራተኛው 1/9ኛው ሥራ — አጥ መሆኑን ነው የሚአሳየው ።

ለውጦች በካፒታሊ ስት ዑደት ውስጥ

ዑደቱ ከአንድ የምጣኔ — ሀብት ቀውስ እስከ ሁለተኛው የመ ነሻ ዘመን ድረስ ነው ብለን እናስታውስ ። ዑደቱ አራት ደረጃ ዎች ይኖሩታል — ቀውስ ፣ ዝቅጠት ፣ ማገገም እና ምጥቀት የሚባሉ ።

በካፒታሊዝም አጠቃላይ የቀውስ ዘመን በካፒታሊስት ዑደት ውስጥ ለው ጥም ይፈጠራል ፣ የዑደቱ ጊዜ ያጥራል ፤ ስለዚህም ቀውሱ ይበልጥ ተከታታይ ይሆ ናል ። ካንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት የምጣኔ — ሀብት ቀውስ ከ8—12 ባሉት ዓመታት ተፈጥሯል ። በዓለም ጦርነቶች መካከል 1919 — 38/ሶስት የምጣኔ — ሀብት ቀውሶች ነበሩ ፤ ማለትም ፣ ቀውሱ ከ6 — 7 ባሉት ዓመታት ተካሂዷል ። ወዲያውም የቀውሶች ደረጃና ዝቅጠት እረጅም ነበሩ ፤ እና የምጥቀት ደረጃ አነ ስተኛ ቆይታ ነበር ያለው ። ቀደም ሲል ቀውስ ከ18 ወሮች እስከ ሁለት ዓመት ሲሆን ፣ ከ1929 — 33ቱ ግን ለአራት ዓመታት ቆይቷል ። በመጨረሻ ፣ የካፒ ታሊዝም አጠቃላይ የቀውስ ዘመን በምርት ትብ ውድቀትና በሥራ — አጥነት ከፍተኛ ዕድገት እንደተገለጸው የበለጠ እየጠለቀና አስቃቂ እየሆነ ሄደ ።



ለምሣሌ ዩናይትድ ስቴትስን ለ43 በመቶ የካፒታሊስት አገሮች የኢንዱስ ትሪ ምርት ኃላፊ የሆነችውን እንውሰድ ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የዩ ናይትድ ስቴትስ ኢንዱስትሪ በ1939 ቀድሞውኑ ለታከታተሉ ዓመታት በተከታ ታይ እየጨመረ በሄደው አስቃቂ የምጣኔ — ሀብት ቀውስ ተመቶ ነበር ። ከ1953 ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ አዲስ ምጣኔ — ሀብታዊ ቀውስ አደገና ወደ ኢንዱስትሪ የምርት ብዛት ቅነሳ ፣ እና የሥራ ትዕዛዝ የመቀበልን የመዘጋት ፣ የሥራ—አጥነት ማደግና በመጋዘኖች ውስጥ የሸቀጦች ድብር መከመር ፣ አመራ ። በ1954 ዓ ም ቀውሱ ቀጠለ ። በ1957 አጋማሽ ሌላ ከመጠን በላይ የማምረት ቀውስ በዩናይትድ ስቴስት ጀመረና በተለይ በ1958 ዓ.ም. ለመቃብር አፋፍ አዳረሰ ። የ1958 የመጀ መሪያ ስድስት ወራት ፣ ከ1957 ዓም ሲመዛዘን የርግ—ብረት ምርት በ38.3 በመቶ ፣ የዐረብ—ብረት ምርት—በ36.5 በመቶና የሞተር — ክር (መኪና) ምርት — በ33.6 በመቶ ወደቀ ። ይህ ልዩ ምጣኔ—ሀብታዊ ቀውስ በሌሎች የካፒታሊስት አገሮችም ተሠራጭቷል ።

የ1957 — 58ቱ ቀውስ በአሜሪካውያን ኢንዱስትሪ ውስጥ ለምጥቀት የሚ ያዘጋጅ መንገድ አልጠረገም ። ሁለት ዓመት ከማለፉ በፊት ዩናይትድ ስቴትስ ፣ በ1960 ፣ እንደገና በምጣኔ — ሀብት ቀውስ ውስጥ ተንኮታኩታለች ።

ስለዚህ ከጦርነት በኋላ ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ምጣኔ ሀብት አራት ጊዜ የም ጣኔ ሀብት ቀውስ ገጠመኝ ተለዋወጠበት ። ከዚህም በላይ ፣ በዑደቱ ደረጃ መሆን የሚገባው የቀውስ መከታተል ተበጠበጠ ። አንዳንድ ደረጃዎች ከነጭራሹ ጠፍ ተዋል ። ለምሣሌ ፣ ከቀውስ ወደማገጋም ሽግግር ከዝቅጠት ደረጃ ያለተከ ታታይ አይደለም የወጣው ፣ ማገገምም ወደ ምጥቀት (ንረት) በተከታታይ አይደለም የሄደው ፣ ግን በቀጥታ ወደ አዲስ ቀውስ እንጂ ። ከዚህም በላይ በተለያዩ ምክን ያቶች አሁን ወደ ቀውስ ሽግግር የሚፈጠረው በድንገት አይደለም ፣ ቀስ በቀስ ነው በረጅም የቅድመ — ቀውስ ዕርጋታ ነው ። ከእንግዲህ የድብር ሸቀጥ ልውውጥ እና የባንክ ጥፋት የለም ። ከጦርነት የቀውስ ዘመን በኋላ ቀውሱ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት ይቆይ እንደነበረው አልቆየም ።

ከጦርነት ጊዜ ጀምሮ በካፒታሊስት ደት ውስጥ የነዚህ ለውጦች መግለጫ ምክንያት ምንድነው ? ዋናው ምክንያት የካፒታሊስት ሥርዓት ባንዳንድ የኢንዱ ስትሪ ዘርፎች እና ጠቅላላ በአገሮች ውስጥ አስቃቂ የሆነ መታከትና (Stagnation) ማሽቆልቆል መግባቱን እንዲሁም በአጠቃላይ የዕድገት ደረጃ መገመት መኖሩን ለማመልከት ነው ።

ከጦርነት በኋላ ላሉት የካፒቲሊስት ዑደት ለውጦች ያመሩ ሌሎች ብዙ ምክንያቶች አሉ ።

1. በካፒታሊስት ዑደት የምጣኔ — ሀብት ወታደራዊነት ውጤት እጥፍና ተጻራሪም ነው ። ባንድ በኩል ፣ ከጦር መሣሪያ ምርት ጋር በተያያዙ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ተለዋዋጭ ንረት (ምጥቀትን) ያበረታታል ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ለካፒታ ሊስት ዕርባታ ቅራኔዎች መባባስ ምክንያት በመሆን ፣ እንደገና የበለጠ ጥልቀት ያለው ቀውስ እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል ።

2. መንግሥታዊ — ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም በመጠኑ የካፒታሊስት ዑደትን አዝማሚያ ተፅዕኖ ያሳድርበታል ። ይህም ማለት መንግሥት ሞኖፖሊዎችን በመ ወከል በምጣኔ—ሀብቱ ጣልቃ ይገባል ነው (የእርሻንና የኢንዱስትሪን ውጤቶች መንግሥት በመግዛትና በመሸጥ ፣ መንግሥት ለሞኖፖሊዎች ብድርና ዕርዳታ በመ ስጠት ፣ ወዘተ...) ። ስለሆነም እርግጥ ይህ ለአንዳንድ ምርቶች ዕድገትና ነባር ወረትን ለማጠናከር አስፈላጊ ነው ። በመንግሥት ሥርዓት አስጠባቂነት ፣ የሞኖፖሊ ቡር

ኀያዎች አፍራሹን የምጣኔ — ሀብት ቀውስ ኃይል ለመጠገን ይሞክራሉ ። ሆኖም መንግሥታዊ — ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የካፒታሊስቱን ዑደት ቢያደናቅፍም ፣ ከመጠን በላይ የማምረትን የምጣኔ — ሀብት ቀውስ አያስወግድም ።

3. ዘመናዊው ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ዕድገት የካፒታሊስት ዑደትን አዝማሚያ ይጫኑዋል ። ይህ የነባር ወረትን ፈጣን እርጅና ያመጣል ። ስለሆነም ፣ የወረት መዋዕለ ንዋይ በቀውስ ጊዜ ይዘጋ ይሆናል ፤ ሆኖም በዚያው ደረጃ ይቆያል ። ይህ ዑደት ቀድሞ ከነበረው ዕድገት ልዩ መልክ ይይዛል ።

4. በካፒታሊስት አገሮች የመደብ ትግል በዑደቱ ላይ ከፍተኛ ውጤት አለው ። ሠራተኞች በትግሉ ይበልጥ ግብ ሲመቱ ፣ ቡርዣዎች የበለጠ የምጣኔ — ሀብት ድርድር ለማድረግ ይገደዳሉ ። ይህ የውስጥን ገበያ እንዲስፋፋ ሲያስችል በአንዳድ እርምጃዎች (ሁኔታዎች) ከመጠን — በላይ የማምረትን ቀውስ ጥልቀት ለመጉተት ምክንያት ይሆናል ።

5. የቅኝ ገዥነት መሰባበርም የካፒታሊስት ዑደትን ያናቅፋል ። ይህ የፖለቲካ ነጻነትን ያገኙ አገሮች የምጣኔ — ሀብት ነጻነታቸውን ማጠናከር መጀመራቸው ላይ ነው የታየው ፡ የምጣኔ—ሀብት ነጻነታቸው ጉዳና በኢንዱስትሪያዊነት ነው ፡ ዛሬ ከካፒታሊስት አገሮች ወደ ውጭ ከሚላኩት መሣሪያዎች ግማሹን ያህል በተለይ ከምዕራብ አውሮጳ አገሮች ፣ የሚሄደው ኋላ — ቀር ወደሆኑ አገሮች ነው ፡ ይህ በምዕራብ አውሮጳ የኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ውጤት ላይ ጭማሪ እንዲኖር ሲአደርግ ከጦርነት በኋላ በካፒታሊስት ዑደት ውስጥ ለውጥ እንዲኖር ረድቷል ።

እነዚህ ናቸው በዛሬው ጊዜ ለካፒታሊስት ዑደት አዝማሚያ መለወጥ ምክንያት ከሚሆኑት አንዳንዶቹ ። እነዚህ ምክንያቶች ናቸው የካፒታሊስት አገሮች ከጦርነት በኋላ ያላቸውን የምጣኔ — ሀብት ደረጃ ምንም ከ1929— 33 ቀውስ መለስ ያለ መቃብር አፋፍ ቢሆንም ተከታታይ እንዲሆን ያስገደዱት ።

የኢንዱስትሪ ዘርፎች ከችሎታቸው በታች የማምረት ጸባይ ፣ ነባር የሆነ ሥራ አጥነት ፣ ከቀን ቀን ተከታታይ የሆነ የምጣኔ — ሀብት ቀውስ ፣ ካፒታሊዝም በእሱው ውስጥ ያደጉትን በዛሬው ጊዜ የምርት ኃይሎችን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም እንደማይችል ማረጋገጫዎች ናቸው ። ካፒታሊዝም በሰው ልጅ ዕድገት ላይ እጅግ ሰፊ እንቅፋት ሆኗል ። የመሣሪያ ውድድርንና የምጣኔ — ሀብትን ወታደራዊነት የፖለቲካና የምጣኔ — ሀብት ቅራኔዎቹን ማስወገጃ ለማድረግ እየሞከረ ነው ።

[illegible]

የምጣኔ — ሀብት ወታደራዊነት የሚአመለክተው እጅግ ሰፊ የኢንዱስትሪ ክፍል ከሲቪላዊ ምርት ውጤት ወደ መሣሪያ ውጤትእና የቁሳዊ ዕሴቶች በስትራ ቲጂያዊ መጠባበቂያ መልክ መከመርን ነው ። ለምሣሌ በዩናይትድ ስቴትስ ፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ ላይ የፌድራል አስተዳደሩ ቀጥታ ወታደራዊ ወጭ ከጠቅላላው ወጭ14 በመቶ ነበር ፣ ግን በ1953 እና በ1960 መካከል ቀጥተኛ የወታደራዊ ወጭ ወደ 45,000 — 46,000 ሚሊዮን ዶላር በዓመት ወይም የፌደራሉን የዓመት ባጀት 2/3ኛውን ደርሷል ። በ1962 ፣ ይህ ወጭ 52,000 ሚሊዮን ነበር ። በእንግሊዝና በፈረንሳይ ከጦርነት በኋላ የወታደራዊ ወጭ ከጠቅላላው ባጀት 1/3ኛውን ወስዶታል ።

የምጣኔ — ሀብት ወታደራዊነትና የመሣሪያ ውድድር የጦርነት አደጋን ይፈጥራል ። በዚህ ምክንያት የሶቪዬት ሕብረት ፣ ሌሎች የሶሻሊስት አገሮች እና ሁሉም ሰላም — ወዳድ ሕዝብ ለጠቅላላና ለሙሉ በሙሉ ትጥቅ መፍታት ጠንካራ የሆነ ትግል እያካሄዱ ናቸው ። « ሁልጊዜም በቀራጥነት የመሣሪያ ውድድርን ተቃ



ውመናል » ብሏል ክሩቼቭ በ22ኛው የሶቪዬት ሕብረት የኮሚኒስት ፓርቲ ኮንግሬስ ላይ ፣ « ባለፈው ጊዜ ፣ በዚህ መስክ ያለው ውድድር በሕዝቦች ላይ ከባድ ሸክም ብቻ አይደለም ያደረሰው ፤ ግን በማይቀር ሁኔታ ወደ ዓለም ጦርነት አምርቷል ። አሁንም በጠነከረ መልክ የመሣሪያ ውድድርን ተቃውመናል ምክንያቱም ትልቅ ቴክኒካዊአብዮት በጦርነቱ አሠራር ተከናውኗል ፣ እናም የዘመናዊ የጦር መሣሪያ በጥቅም መዋል በማይቀር ሁኔታ በብዙ መቶ ሚሊዮን ለሚቆጠር ሕዝብ ሕይወት መጥፊያ ሆኗል ። » 1

እና አሁንም የኢምፔሪያሊስት ኃይላት አጠቃላይ ሙሉ በሙሉ ትጥቅ የመፍታትን ሁኔታ ለመቀበል ፈቃደኛ አይደሉም ። ለምን ? ምክንያቱም የመሣሪያዎች ውድድር ከዚህ በፊት ታይቶ ወይማይታወቅ የሞኖፖሊዎች ትርፍ ዕድገት የመራልና ነው ። ለምሣሌ — የአሜሪካውያን ሞኖፖሊዎች ትርፍ በ1938 እና በ1959 መካከል ከ 3,300 ሚሊዮንዶላር ወደ 48,000 ሚሊዮን ዶላር ጨምሯል ፣ ይህም—ከ 14,5 ጊዜ በላይ እጥፍ ነው ። የ250 ኮርፖሬሽኖች ጠቅላላ ትርፍ ከ7,500 ሚሊዮን ዶላር በ1961 ወደ 8,800 ሚሊዮን በ1962 አድጓል ፣ ይህም 16.4 በመቶ ነው ።

ከዚህም በላይ ፣ የካፒታሊዝም ርዕዮተ — ዓለማውያን የብሔራዊ ኤኮኖሚን ወታደራዊ ማድረግና ፣ የመሣሪያ ውድድር የካፒታሊስትን ምጣኔ — ሀብት ከመጣኔ — ሀብት ቀውሶችና ከሥራ አጥነት ነጻ ያደርጋውል ብለው ያስባሉ ። እንደ እውነቱ ከሆነ የምጣኔ — ሀብት ወታደራዊነት ፣ በአምራች ችሎታዎችና በሕዝቡ ውጤታማ ጠያቂነት መጨማተር መካከል ያለውን ልዩነት ስለሚአባብስ ፣ በማይቀር ሁኔታ ወደ አዲስ ፣ ይበልጥ ጥልቀትና ስፋት ወዳለው ምጣኔ — ሀብታዊ ቀውስ ያመራል ። « የመሣሪያ ውድድር » ብሏል ክሩቼብ በሶቪዬት ሕብረት የኮሚኒስት ፓርቲ 20ኛ ኮንግሬስ ላይ « በሽታውን አያድንም ፤ ይበልጥ ያባብሰዋል እንጂ ፣ እናም የምጣኔ ሀብቱ ወታደራዊነት ይበልጥ በተስፋፋ መጠን ፣ ውጤቱ ለካፒታሊዝም የዚያኑ ያህል መቃብር መቆፈር ነው ። »2

የመሣሪያ ውድድር ለሠራተኛው መደብና ለሁሉም ሠራተኞች ሕዝቦች ከባድ ሸክም ነው ። ለምሣሌ ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በእያንዳንዱ ሰው የወታደራዊ ወጭ ከ1913—14 በነበረው የሕዝብ ቀረጥ ዓመት 3.5 ብር ፣ በ1929—30 7 ብር ፣ እና በ1954—55 250 ብር ነበር ይህም በዘመኑ ከ70 ጊዜ በላይ እጥፍ አድጓል ማለት ነው ። በእንግሊዝ ፣ በእያንዳንዱሰው ላይ የነበረው ወታደራዊ ወጭ በ1913 — ከ1£—14 ሺልንግ በ1954—55 ወደ 29£ (ፓውንድ) 6 ሺልንግ አድጓል ። ይህ ሰፊ ውጭ የሚገኘው በማከታተል በቀጥታና በኢርቱዕ በሚሰበሰበው ግብር ነው ። በዩናይትድ ስቴትስ በቀጥታ ግብር በ1956—57 ከነበረው ሕዝባዊ የግብር ዓመት ከ1937—38 ከነበረው ሲወዳደር የገንዘብ ዕሴትን ዝቅጠት እንኳ ጨምሮ ወደ 13 ጊዜ እጥፍ አድጓል ። በእንግሊሊዝና ጣሊያን ቀጥታ ግብር እጥፍ ሆኗል ፤ በፈረንሣይም በዚሁ ዘመን ሶስት ጊዜ እጥፍ ነበር ።

ከጦርነት በኋላ የመሣሪያ ውድድር በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ፣ የወረቀት ገንዘብን የመግዛት ኃይል እንጦርጦስ በማውረድ ወደ መጠቀ ንረት አምርቷል ። በዩናይትድ ስቴትስ የተዘዋወረው የወረቀት ገንዘብ መጠን በ1958 ዓ. ም. መጀመሪያ ላይ ከ1937ቱ 5,600 ሚሊዮን ዶላር ሲወዳደር ወደ 27,400 ሚሊዮን ከፍ ብሏል ። በእንግሊዝ በመዘዋወር ላይ የነበረው የወረቀት ገንዘብ በ1958 መጀመሪያ ላይ ፣ ከ1937ቱ £460 ሚሊዮን ሲወዳደር ፣ ወደ £1,850 ሚሊዮን ሆኗል ።

1. ወደ ኮሚኒዝም ጉዳና ፣ ገጽ 47
• ኒኪታ ክሩሽብ ፣ የኮሚኒስት ፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ 20ኛው የፓርቲው—ኮንግሬስ ሪፖርት ፣ ሞስኮ 1956 ፣ ገጽ 17

በጣሊያን ፣ በ1958 የወረቀት ገንዘብ መዟዟር ከ1937ቱ 18,000 ሚሊዮን ሊሬ
ሲነጻጸር ወደ 1,852,000 ሚሊዮን ሊሬ ደርሷል ።

በግብር ሸክም መጨመርና በንረት ማደግ ምክንያት ሞኖፖሊዎች ስማዊ

በግብር ሸክም መጨመርና በንረት ማደግ ምክንያት ሞኖፖሊዎች ስማዊ ምንዳዕን « ለማደንዘዝ » ማለትም በተወሰነ ደረጃ ለማቆየት ይታገላሉ ። ይህም ከእውነተኛ ምንዳዕ ቅነሳ ፣ የሰፊው ሠራተኛ የኑሮ ሁኔታ ማሽቆልቆል ፣ ሠራተኛው መደብ የካፒታሊስትን ጭቆና በመቃወም እንዲታገል ማድረግ ማለት ነው ። ለዚህ ግልጽ ማረጋገጫው የሚታየው መጠን — ርዕዩ በጨመረው የአድማ እንቅስቃሴ ነው ። ሆን ተብሎ የተቀነሰውን የ11 አገሮች የታወቀውን ስንጠረዥ በመውሰድ ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ፣የእንግሊዝ ፣የፈረንሣይ ፣ የጀርመን ፌዶራል ሬፑብሊክ ፣ የጃፓን ፣ የካናዳ ፣ የአውስትሪያ ፣ የስዊድን ፣ የቤልጅግ ፣ የሆላንድ ፣ እና የአርጀንቲና — እና ከጦርነት በፊት ያሉትን ዓመታት (1930—39) ከጦርነት በኋላ ካሉት (194554) በማወዳደር የአድማዎች ቁጥር ከ67,000 ወደ 101,000 በውስጣቸው የተሳተፉት ሠራተኞች ከ2 ሚሊዮን ወደ 73 ሚሊዮን ፣ እና የጠፋው የሥራ ቀን ከ240 ሚሊዮን ወደ 672 ሚሊዮን ጨምሯል ።

የወዛደሩ የመደብ ትግል ፣ ብልጭ ድርግም ከማለት አልፎ የማያቋርጥ ነበል ባል ሆን ።

ከጦርነት በኋላ ባሉት ዘመናት የካፒታሊስት አገሮች ሠራተኛ መደቦች ከምጣኔ — ሀብት ትግል ጋር ራሳቸውን አሳሳሳሙም፤ግን ከጦርነቱ በፊት ካለው ይበልጥ በታላቅ ቆራጥነት በሀገር ውስጥ መሠረታዊ ጥያቄዎችና በውጭ ፖሊሲ በተግባር በመሳተፍ ፣ እንዲሁም ለሰላምና ለዲሞክራሲያዊ ነጻነቶች የሕዝብ ትግል ግንባር ቀደም በመሆን መርተዋል ።

የወዛደሩ የመደብ ትግል የሚመራው በኮሚኒስቶችና ሠራተኞች ፓርቲዎች በማርክሲስት — ሌኒኒስት ንድፈ — ሀሳብ መሠረት ፣ በዛሬው ዘመን ጥንካሬውና አስተማማኝ ዕድገቱ በጠቅላላው ገጠመኝ በተረጋገጠው ነው ።

ሞኖፖሊዎች የብሔሩን ፍላጎት ይጻረራሉ

በዛሬው ጊዜ በሰፈነው ሁኔታ ፣ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ ያሉ የሞኖፖሊ ቡርዧዎች ፍላጐቶች ከወዛደሩና ባጠቃላይ ከብሔሩ ፍላጐት ጋር ሊታረቅ ወደማይችል ቅራኔ ይደርሳሉ ።

ሞኖፖሊ ወረት የሠራተኛውን መደብና የሌሎች ሠራተኛ ሕዝቦችን ክፍል መበዝበዝ ያጠናክራል — የገበሬዎችንና የእጅ ባለሙያዎችን ። በዛሬው ጊዜ የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ደረጃ የሠራተኞችና የገበሬዎች የኑሮ ሁኔታ በአስቃቂ መልክ አሽቆልቁሏል ። በዩናይትድ ስቴትስ ሞኖፖሊዎች የአሜሪካን ገበሬዎች በ1950 ዓ.ም.ለሚገዙት ዕቃ ይከፍሉት ከነበረው በ1959 ዓ. ም. 12 በመቶ ተመኖችን አንረዋቸዋል ። በዚሁ ዘመን ግን የ7 በመቶ የተመን ማሽቆልቆል ገበሬዎች በማሽጧቸው ምርቶች ላይ ታይቷል ። በሞኖፖሊያዊው መንግሥት የተፈጠረው በኢንዱስትሪዎችና የእርሻ ሸቀጦች ተመን መካከል ያለው ልዩነት የብድር ሸክምና የግብር ጫና በገበሬዎች መካከል ወደ ብዙዎች መውደም ያመራል ። በ1952 እና በ1959 መካከል 776,000 ገበሬዎች በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከስረዋል (ተራቁተዋል) ።

የሞኖፖሊ ዝንባሌ የሚጋጨው ከሠራተኛው ሕዝብ ዝንባሌ ጋር ብቻ ሳይሆን ግን ከአነስተኛና መካከለኛ ቡርዧዎችም ጋር ነው ። ከመንግሥቱ ጋር ሞኖፖሊ ካፒታሊስቶች የግብር ፣ የዱቤ (የብድር) ፣ የታሪፍና የተመን ፖሊሲ በዝንባሌአቸው መሠረት የትርፍ ዕሴት የእንደገና መሠራጨትን የሚያረጋግጥ ያወጣሉ ፣ አነስተኛና መካከለኛ ቡርዧዎች ከትርፉ ምንም ዓይነት ድርሻ ይከለከሉና ይደመሰሳሉ ።



የመካከለኛ ቡርዧዎችና የመካከለኛ — መደብ ክፍሎች ዝንባሌ እንደሠራተኛው መደብ ሁሉ ከሞኖፖሊ ቡርዧዎች ፣ ከቡርዧዎች የፖለቲካ ፓርቲና መንግሥት ፣ ከሞኖፖሊዎች ዘብ ጠባቂ ጋር ግጭቱ እየጨመረ ይሄዳል ። ለዚህ ነው የሠራተኛው መደብ ፣ ገበሬው ፣ ምሁሩና የከተማ አነስተኛ መካከለኛ ቡርዧዎች በተለይ የሞኖፖሊዎችን ገዥነት ጠርጎ ለመጣል ፍላጐት የሚኖራቸው ።

በዛሬው ሁኔታ የብሔሩ ሁሉ ኃይሎች ለሰላም ፣ ለብሔራዊ ነጻነት ፣ ዲሞክራሲን ለመጠበቅ ፣ እጅግ ዋና እንዱስትሪዎችንና ዲሞክራሲያዊ አመራራቸውን ለመውረስ ፣ እና ጠቅላላውን የምጣኔ—ሀብት የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎት መጠቀምን ለማርካት በመሳሰለው ትግል ጸረ — ኢምፔሪያሊስት ሆነው ሊቆሙ ይችላሉ ።

የኮሚኒስትና ሠራተኞች ፓርቲዎች ለጸረ — ሞኖፖሊ ግዛት ትግል ግንባር ቀደሞች በመሆን ሰፊውን ሕዝብ በዚህ ትግል ውስጥ ለመምራትና ለማሰለፍ ይጥራሉ ።

በካፒታሊስት ፡ አገሮች መካከል የትራኢዎች ማደግ

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የካፒታሊስት አገሮችን ያልተስተካከለ ዕድገት አባባሰው ። ጀርመን ፣ጃፓንና ጣሊያን በወታደራዊ ድል መመታት ተሰቃዩ ፣ ምጣኔ — ሀብታቸው በአስቃቂ ሁኔታ ከእግር ሥር ዋለ ። ፈረንሣይ በወረራው ጊዜ ከፍተኛ ጥፋት ደርሶባታል ። እንግሊዝ በጣም ተዳከማለች ። የዩናይትድ ስቴትስ ብቻ ናት ከጦርነቱ ትርፍ ያገኘችበት ። በ1948 ዩናይትድ ስቴትስ ለ56.6 በመቶ ከካፒታሊስቱ ዓለም ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ምርት ባለቤት ስትሆን ፣ እንግሊዝ — 11.5 በመቶ ፣ ምዕራብ ጀርመን — 4 በመቶ ፣ ፈረንሣይ—4 በመቶ ካናዳ 3.5 በመቶ ጣሊያን — 2 በመቶ ፣ ጃፓን 1.5 በመቶ ነበር ኃላፊነታቸው ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ፣ በካፒታሊስት ዓለም በኃይሎች ዝምድና ሕብረት) ጠበቅ(ከበድ) ያሉ ለውጦች ተካሂደዋል ። እነሱ ምንድናቸው ?

በመጀመሪያ ፣ ዩናይትድ ስቴትስ በካፒታሊስት ዓለም ምርትና ንግድ ላይ የፍጹም የበላይነቷን አጣች ። ከ1948 ጀምሮ በዓለም የካፒታሊስት ኢንዱስትሪ ምርት ድርሻም 10 በመቶ፣በ1960—4 በመቶ ወድቋል፣የውጭ ንግዷ ከ23.4 በመቶ ወደ 18.1 በመቶ በመቶ እና መጠባበቂያ ወርቅ ከ74.5 በመቶ ወደ 43.9 በመቶ አሽቆልቁሏል ። ከሌሎች የካፒታሊስት ኃይላት መካከል ፣ ዩናይትድ ስቴትስ አሁን በማቀራረብ (በግምት) ከሁለተኛው ያለም ጦርነት በፊት የነበረችበትን ቦታ ነው የያዘችው ።

ሁለተኛ ፣ በፈረንሳይና በእንግሊዝ ቃዋቂ የሆነ ድክመት ነበር ። እነዚህ መንግሥታት ቅኝ ግዛቶቻቸውን ሁለተኛ ላያገኟቸው እያጧቸው ነበር ። ከጦርነት በፊት በኢንዱስትሪ ምርት የነበራቸውን ቦታ ለማግኘት አልቻሉም ። እንግሊዝ በ1937 ከካፒታሊስቱ ዓለም የኢንዱስትሪ ምርት 12.5 በመቶውን ስትይዝ ፣ ግን በ1961 ይህ ቁጥር ወደ 9 በመቶ ወርዷል ። የፈረንሣይ ደግሞ 6 እና 5 በመቶ ነበር ።

ሶስተኛ — ድል የሆኑት አገሮች ፣ በተለይም ምዕራብ ጀርመንና ጃፓን ፣ ፈጣን ዕድገትን ወስደው ነበር ። ምዕራብ ጀርመን ፣ ጃፓንና ጣሊያን ባንድነት የካፒታሊስት አገሮችን የኢንዱስትሪ ምርት ከ17 በመቶ በላይ ፣ ከጦርነቱ ዋዜማ በፊት ከነበረው ይበልጡት አምርተዋል ።

በምጣኔ — ሀብት ግንኙነት ያለው የኃይል ለውጥ በኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል ወደ ገበያ ትግል አምርቷል ።

ዩናይትድ ስቴትስ ምጣኔ — ሀብታዊ ጥቅሟን በከፍተኛ ጥረት የምትጠቀም በት ሌሎች አገሮችን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ጥገኛ ለማድረግ ነው ። ከጦርነት በኋላ ባሉት የመጀመሪያ ዓመታት በጣም ስፊ በሆነ የካፒታሊስት ዓለም ገበያ ላይ የበላይነቷን በማቋቋም ግቧን መታለች ። ግን ምዕራብ ጀርመን ፣ እንግሊዝ ፤ ፈረንሣይና ጣሊያን ዩናይትድ ስቴትስ በዓለም ገበያ ላይ በውድድር የወሰደችባቸውን እንደገና በቦታው መልሰውታል ። ይህ በዩናይትድ ስቴትስ ፣ በእንግሊዝ ፣ በምዕራብ ጀርመንና ሌሎች አገሮች ሞኖፖሊዎች ማኅበር መካከል የገበያ ትግልን አጠናከረ። የዩናይትድ ስቴትስ የገበያ ፣ የጥሬ ሀብትና የተፅዕኖ ክልል ትግል ፣ የምዕራብ አውሮጳ ኢምፔሪያሊስቶችን የመቋቋም ዕድገት ችግር ላይ ጣለው ። የምዕራብ አውሮጳ ሞኖፖሊዎች ከፍተኛ ትርፋቸው እንዲበለሻሽባቸው አልፈለጉም ።

በሞኖፖሊዎች መካከልም ያለው ትግል በካፒታሊስት አገሮች መካከል የበለጠ ቅራኔውን እያሰፋው ሄደ ።

በተለይ ዋናው በኢምፔሪያሊስቶች መካከል የነበረው ቅራኔ በዩናይትድ ስቴትስና በእንግሊዝ ያለው ነበር ። የዩናይትድ ስቴትስ ሞኖፖሊ ወረት በእንግሊዝ የውርስ ገበያዎችና የተፅዕኖ ክልሎች ላይ የጥቃት ድንበር ሠራ ። ዩናይትድ ስቴትስ እንግሊዝ በበላይነቷና በቅኛቿዋ ሥር የነበሩትን የብዙ ምጣኔ — ሀብታዊ ዝምድናዎችን ለማጥፋት አንዳንድ ግቦችን መታለች ። በእንግሊዝና በዩናይትድ ስቴትስ መካከል ያለው ትግል ይበልጥ እየተጠናከረ የሄደው በውጭ ንግድ ክልልና የጥሬ ሀብትን ምንጭ በሚመለከት ረገድ ነው ።

በፈረንሣይና በዩናይትድ ስቴትስም እየጨመሩ የሚሄዱ ቅራኔዎች አሉ ። የአሜሪካ ሞኖፖሊዎች ከቀን ቀን ወደ ፈረንሣይ ምጣኔ — ሀብት ውስጥ ሰርገው እየገቡ ናቸው ። ብዙ የአሜሪካ ተቋሞች በፈረንሣይ ውስጥ የኢንዱስትሪ ድርጅቶችን ከፍተዋል ። የውድድር ትግሉም በውጭ ንግድ ክልል በኩል እያደገ ነው ። ዩናይትድ ስትቴስ በፈረንሳይ የቀድሞ ገበያዎች ላይ በሞሮኮ ፤ ቱኒዚያና አልጀሪያ የጥቃት ድንበር እየሠራች ናት ። ፈረንሣይን ከአፍሪካ ገበያዎች በማውጣት ወደ መቃብር አፋፍ የማድረስ ምልክቶች በአሜሪካ አዝማሚያ ላይ እየታዩ ነው ። የዩናይትድ ስቴትስ ግራኪ ክልሎች ፣ የብሔራዊ — አርነት እንቅስቃሴ ውስጥ « በአማካሪነት » ስም በማከታተል ጭራ መቁላት ፣ በአፍሪካ አገሮች የፈረንሣይን ግዛት በአሜሪካ ሞኖፖሊዎች ለመተካት ነው ፣ በደቡብ ቪየትናም እንደተካላቸው ሁሉ ። ይህ የዩናይትድ ስቴትስ ዝንባሌ በፈረንሣይ የገዥ ክበቦች ዘንድ ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል ።

በኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል ቅራኔዎች ይበልጥ የተባባሱት በምዕራብ ጀርመንና ጃፓን በዓለም ገበያ ላይ መከሰት ነው ። ከጦርነት በኋላ ባለው ጊዜ ዩናይትድ ስቴትስ በምዕራብ ጀርመን ምጣኔ — ሀብት እጅግ ዋና በነበሩት ቅርንጫፎች ውስጥ ጠንካራ ያሸናፊነት ቦታ ለመያዝ ፣ የምዕራብ ጀርመንን ሞኖፖሊዎች በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ትሞክር ነበር ። እንግሊዝም እንዲሁ ። ግን ዩናይትድ ስቴትስ ወይም እንግሊዝ የበላይነት ተፅዕኖ ለማቋቋም አልቻሉም ። እያደገ በሚሄደው የኢንዱስትሪ የማምረት ችሎታ በመደገፍ ፣ የምዕራብ ጀርመን ሞኖፖሊዎች መጀመሪያ የሰፈው የመስፋፋት የዕቅድ ጉዳና ተጓዙ ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ ዓመታት ላይ ፣ ምዕራብ ጀርመን ከካፒታሊስት አገሮች መካከል የመጨረሻ ከነበሩት ቦታዎች አንዱን ይዛ ነበር ። ግን ዛሬ በዓለም ሁለተኛውን ቦታ ከዩናይትድ ስቴትስ ቀጥሎ ይዛለች ።

በኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል ያሉት ቅራኔዎች የመጡት ፣ ከምርት ሕብረተሰብባዊ ጸባይና በካፒታሊስቶች ግላዊ አወሳሰድ መልክ መካከል ካለው መሠረታዊ ቅራኔ ነው ። በኢምፔሪያሊስቶች መካከል ያለውን ቅራኔ የሚያስወግድ ምንም ስምምነት ፣ ድርድር ፣ ሕብረት ወይም እርቅ የለም ።



የዛሬው ጊዜ ዋና ቅራኔ — በሚያድገው ሶሻሊዝምና በሚሞተው ካፒታሊዝም መካከል — በካፒታሊስት ቡድኖች ውስጥ ያለውን ውስጣዊ ቅራኔ አያስወግድም ። የዘመናችን ዓይነተኛ ቅራኔ በኢምፔሪያሊስቶች ግንኙነቶች መካከል ሁለት ዓይነት ውጤት ነው ያለው ። ባንድ በኩል የካፒታሊስት አገሮችን ሕብረት ያጠናክራል ፣ ወታደራዊ ክልሎችን እንደ (NATO, SEATO, CENTO) ያሉትን ባንድነት ለማቋቋም ምክንያት በመሆን ፣ በኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል ጦርነት እንዳይፈነዳ ያደርጋል ። በሌላ በኩል ፣ በካፒታሊስት አገሮች መካከል በዛሬው ዘመን የዓለም ዕድገት መሠረታዊ ችግሮች አካባቢ አዲስ የቅራኔ ምንጮችና ግጭቶች ይፈጥራል ።

« በትክክል ፣ በኢምፔሪያሊስት ሰፈር ውስጥ የሚከናወንና የሚውጠነጠን ሁለት ዓይነት አዝማሚያ አሉ ፣ » ብሎ ክሩቼቭ ጠቁሟል ። « አንዱ ኃይሉን ጸረ ሶሻሊስት አድርጎ ባንድ ማሰለፍ ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ በኢምፔሪያሊስት ኃይላትና እንዲሁም በኢምፔሪያሊስት ኃይላትና በሌሎች የካፒታሊስት አገሮች መካከል ቅራኔዎችን የማባባስ ነው ። 1

በኢምፔሪያሊስቶች መካከል ያሉት ቅራኔዎች በማይቀር ሁኔታ ወደ ዓለም ጦርነት የሚአመሩ ብቻ አይደሉም ። ካፒታሊዝም ዓለምን የሚገዛ ኃይል በነበረበት ጊዜ ፣ የኢምፔሪያሊስት ቅራኔዎችና በአገሮች መካከል የኃይል ሚዛን መበጥበጥ (መለዋወጥ) በመጨረሻ ወደ ዓለም ጦርነቶች አምርቷል ። ዛሬ ፣ ካፒታሊዝም እንደ ብቸኛ የዓለም መንግሥታት ሥርዓት ሞኖፖሊ መሆኑን አጥቷል ። ዛሬ ለሰው ልጅ ዕድገት ዋና ምክንያት የሆነ የሶሻሊስት ሥርዓት አለ ። ዛሬ የወራሪ ኃይላትን የሚለጉምና የዓለም ጦርነትን በሕብረተሰብ ኑሮ ውስጥ ለዘላለም ሊያስወግድ የሚችል በዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት የሚመራ የተዋሃዱ የዓለም ኃይላት ፣ ያሉበት አዲስ ታሪካዊ ሁኔታ ተፈጥሯል ።

* * *

አሁን በቅጥር ጉልበት ብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን የካፒታሊስት ሥልተ — ምርት መርምረናል ። በካፒታሊዝም ጊዜ ፣ በተለይም በዕድገት ደረጃው ላይ በጉልበትና በወረት ፣ እንዲሁም በኢምፔሪያሊስቶች በራሳቸው መካከል የነበሩ ቅራኔዎች እስከ መጨረሻው ድረስ ተብተዋል ። የእነዚህ ቅራኔዎች ጥልቀት ማግኘት የካፒታሊስቱን ዓለም ወደ አዲስ ምጣኔ — ሀብታዊና የሕብረተሰብ እመርታ እንዲሁም ፣ በመጨረሻ ትንታኔ ፣ የካፒታሊዝም አብዮት በሶሻሊዝም አብዮት መተካትን አምጥቷል ።

በዛሬው ጊዜ ያሉት እውነቶች ማርክስ ከ100 ዓመት በፊት ደርሶባቸው ለነበሩት መደምደሚያዎች ፣ በታሪክ ሂደት የካፒታሊስት ሥልተ — ምርት ይወድማል ላለው የበለጠ ማረጋገጫዎች ናቸው ።

1. ወደ ኮሚኒዝም ጎዳና ፣ ገጽ 186

Proudly Brought to You
By
www.binyamhk.wordpress.Com



ዋጋው ብር 2.25